3ኛ ዕትም

# የመኝታ ቤት
# ምስጢሮች

እንዳለጌታ ከበደ



ሀዐ.ቁ 185

ትረካዎች

# የመኝታ ቤት ምስጢሮች

እንዳለጌታ ከበደ

# የመኝታ ቤት ምስጢሮች

ሦስተኛ ዕትም፡-2011 ዓ.ም
ሁለተኛ ዕትም፡-2003 ዓ.ም
የመጀመርያ ዕትም፡-2000 ዓ.ም

የሽፋን ሥዕል፡-ሄኖክ ጌታቸው

ባ/ካህ/ተ 1972-7 ጠ ቁ 185



የዚህች መጽሐፍ መታሰቢያነት
በኢትዮጵያ ዘመናዊ አጨጭር ልቦለድ ታሪክ
እንደፊር ቀዳጅ ከሚቆጠሩት
ከ'ጉለሌው ሰካራም' (1941 ዓ.ም) ደራሲ
ከተመስገን ገብሬ እና ከ'መስከረም' (1949 ዓ.ም) እና
ከ'ሌላው መንገድ' (1951) ደራሲ ከታደሰ ሊበን ይሁንልኝ፡ ፡

ከብዙ አክብሮት ጋር!

## ማውጫ


. ከቀብር በፊት.....5
. በልደት ቀን.....13
. አቤሴሎም.....19
. የእኛ ክፍል ልጆች.....33
. የወርቅ በርጩማውን ፍለጋ.....50
. ? .....63
. እኔ ፣ አባቴና አንዲት ጊደር.....66
. የመኝታ ቤት ምስጢሮች (ዱላው) .....78
. ወደ ታች.....84
. ያልተኖረው ሕልም.....87
. ማደርያ.....109
. የሚቹ ጥላ.....117
. የመኝታ ቤት ምስጢሮች (እናትና ሚስት).....131
. የእንጀራ እናት ነገር.....150
. ተራኪው.....158
. ብርሃን ፍለጋ.....166
. አዲስ ስም.....171
. ከዘመን ጀርባ.....189
. የተቆለፈበት.....193

# ከቀብር በፊት

ከመሞቴ በፊት እንደምሞት አውቅ ነበር:: አውቅ ነበረ፤ ካንሰር ነው የገደለኝ::

ሞት እንዲህ ነው እንዴ? ህመም የለውም:: በፍጹም! ሶኬት የመንቀል ያህል ነው:: ሲኳትን በኖረ አካሌ ውስጥ ጎያው ነፍሴ ስትነቅል ይሰማኛል:: ፀጥ! በቃ ህመም አልነበረውም:: ምንም ያልተደረገ ያህል ነበር የቆጠርኩት:: የተሰማኝ መርፌ ጥጥ ላይ ሲወድቅ ለመስማት እንደመሞከር ያለ ስሜት ነው::

ከሞትኩ በኋላ የማያዩኝን ዐይኖች ማየት ጀመርኩ:: የማይሰሙኝን ጆሮዎችና የማያወሩኝን አፎች መከታተል ቀጠልኩ:: እያንዳንዱን እንቅስቃሴ መከታተል የሚያስችል መንፈስ ነው የተገለጠልኝ:: አዲስ ሰው ሆኛለሁ:: የማያዩኝን ማየት...የማይሰሙኝን መስማት...

ከመሞቴ በፊት ለሞት እየተቃረብኩ መሆኑን ባውቅም፣ ትላንትና ማታ ነፍሴ ከሥጋዬ እየተለየች እንደሆነ ሲሰማኝ ግን ደነገጥኩ:: አዘንኩ::

አሁን ነፍስ ብቻ ነኝ:: ነፍስ ሆኜ ነው ማወራው:: ነፍስ ብቻ ሆኜ ነው፣ እየሆነ ያለውን ነገር የምከታተለው::

ሥጋዬ አጠገብ መሆን ይሰለቸኝ ጀምሯል:: ሥጋዬ ቤቴ ነበር:: ሃያ ዘጠኝ ዓመት ኖሬበታለሁ:: አየሁት፤አሁን ባዶ ሆኗል:: ለሃያ ዘጠኝ ዓመት ተከራይቼ ከኖርኩበት ቤት ኮተት ቅራቅንቦዬን ይዤ እንድወጣ በአከራዬ

የተገደድኩ መሰለኝ:: አዘንኩ:: አልቅስ አልቅስ አለኝ:: ለካስ ይሄ ቤት የእኔ አይደለም:: የኪራይ ነው:: እኔ ስለቀው ይፈርሳል:: ምስኪን::

ምስኪን ቤቴና ፈራሽ ገላዬ አጠገብ እናቴ አለች:: የብዙ ነገሮቼ እናት:: የመጀመሪያዋ መምህሬ! መልሳ መላልሳ የሰራችኝ የኔዋ አናጺ:: በመሪር ሀዘን ተውጣለች፤ በመሪር ልቅሶ ተጐድታለች:: የእሷ የመሰላት ቤት ፈርሷል::

- ወዮ እናቴ! ወዮ እናቴ! ወዮ እናቴ! ወዮ ወየው!!!

ለስንት ሰው የሚበቃ ዕንባና ለስንቱ የሚተርፍ ልቅሶ ለአፅናኝ እስከታስቸግር ድረስ በእኔ እየጨረሰችው ነው:: ታላቅ ወንድሜ በእኔ ቀብር ሰበብ የሚወደውን የእግር ኳስ ጨዋታ እንዳያመልጠው በሚጨነቅበት ሰዓት፣ ታላቅ እህቴ ማን መጣ ማን ቀረ እያለች ሂያጅ መጪውን ልቅሶ ደራሽ በምትቆጣጠርበት ሰዓት፣ታናሽ ወንድሜ እኔ በሞት ተለይቸዋለሁና የግል ኮሌጅ ትምሕርቱን የሚያስጨርሰው የገንዘብ አቅም ከየት እንደሚያመጣ በሚያሰላስልበት ሰዓት... እናቴ ግን ከልቧ ታለቅስልኝ ነበር::

"አድባሬ...አድባሬ... አድባሬ ... ዛሬ ተገረሰስክ፤ ዛሬ ለሞት ተሸነፍክ!" ትላለች፣ እናቴ::

አለቃቀሷ ግን አድባሯ የተገረሰሰ ሳይሆን ከአምላኳ ጋር ያቆራረጧት፣ ወይም የምትንበረከከለትና የምትብረከረከለት ጣኦት ያፈረሱባት ነበር የሚመስለው::

ሀዘኗን መቋቋም አቃተኝ:: አጠገቧ መቆምም ራስን ለስቃይ መጋበዝ መስሎ ተሰማኝ:: እናም ወጣሁ:: ከመኝታ ከፍሌ ወጣሁ:: ወጣሁና ደጅ ላይ ቆምኩ:: ድንኳን ተተክሏል:: ድንኳኑ ሰው ጠግቧል:: ነፍሴ - *ሥጋ* ያልለበሰችው ነፍሴ - ሳያይዋት ታያለች::

የእኔ መሞት ግድ የሰጣቸው ጥቂቶች ብቻ ነበሩ:: አንዳንዶቹ ጭራሽ አያውቁኝም:: ቤተሰቦቼን ብለው ነው የመጡት:: የእድር፣ የዕቁብ፣ የማኀበር አባላት:: እናም አንዳንድ ወግ መተረክና መስማት የራባቸው የአካባቢው የዕድሜ ቱጃሮች...

በሞት መገረም ጀምሬያለሁ:: ሞት እንዲህ ነው እንዴ? ሞት ዝም ማለት ይመስለኝ ነበር:: ምንም አለማወቅ፤ ምንም ወደ መሆን መሸጋገር ይመስለኝ ነበር:: አንድም ቀን ሞት ይህን ይመስላል ብዬ አስቤ አላውቅም ነበር:: ፈጽሞ!

ቅድም የራሴ ሞት ነበር ያስለቀሰኝ:: ከሚያሰቃየኝ ካንሰር የመላቀቅ ስሜት ሳይሆን ከምወደው ማኅበረሰብ የመነጠልና የመገንጠል ስሜት ነበር የተሰማኝ:: ጥቅጥቅ ያለ ዛፍ የበዛበት ጫካ የሆንኩ ነበር የመሰለኝ:: አሁን አንድም ዛፍ በውስጤ የለም:: ምድረ በዳ ሆኛለሁ:: ሰው የለኝም:: ወደ ማላውቀው መንገድ ልጓዝ ነው:: ወደ አላነበብኩት ምዕራፍ ልሸጋገር ነው::

ተናድጃለሁ፤ አዝኛለሁ፤ አብዝቼም አልቅሻለሁ...

አዎን! ቅድም የራሴ ሞት ነበር ያስለቀሰኝ:: ስለእኔ በሚነገረው ነገር ሆዴ ባብቶ ነበር:: ረብ ያለው ህይወት በዘመኔ ያሳለፍኩ አልመሰለኝም ነበር:: በሰዎች አንደበት ስለ እኔ ስሰማ ግን አለቀስኩ:: በህይወት መቆየት ነበረብኝ አልኩ:: ከጐጆ ቤት አናት አንዱን ሳር መዝዞ የማውጣትን ያህል የእኔ መሞት ብዙ የማያጐድል ይመስለኝ ነበር:: ለካስ ለአንዳንድ ዘመዶቼ የህይወታቸው ምሰሶ ነበርኩኝ:: ለካስ ትቢያ አልነበርኩም...እና ለዚህ ነበር ለገዛ ሞቴ ያለቀስኩት::

አሁን ግን ሰለቸኝ:: ለፈረሰው ገላዬና ለተውኩት ሥጋ ቤቴ የሚለቀሰው ልቅሶ ከመጠን እያለፈ ነውና ቋቅ አለኝ:: ሊያስመልሰኝ ያሰበ መሰለኝ:: በእውነቱ አታካች የሆነ ነገር ነው:: በዚህ አለም ለገዛ ሞታችን የሚለቀሰውን ልቅሶ የመስማትን ያህል አሰልቺ ነገር ይኖር ይሆን? የመጀመሪያዎቹ ጥቂት ደቂቃዎች ድንቅ ሕብረ ዝማሬ ሲመስል የቆየው ልቅሶ ቀስ በቀስ እንደ ጩረባ ተዝካር ይሆናል:: እናም አለመወለድ ይሻል ነበር ይሆን የሚል ጥያቄ ያስነሳል...

- ምን አባቴ ልሁን?

ወደ ጓሮ አመራሁ:: ጓደኞቼና የሥራ ባልደረቦቼ የተጣመመ ክብ ሰርተው ተቀምጠዋል:: የህይወት ታሪኬን እየጻፉት ነው:: ጐንበስ አልኩና የጻፉትን ማንበብ ጀመርኩ:: እየጻፉት ያሉትን ነገር እያነበብኩ እንደሆነ ቢያውቁ ምን

ይሰማቸው ይሆን? የሚል ሀሳብ መጣብኝ፡፡ የህይወት ታሪኬን ማንበብ ጀመርኩ፡፡

እንዴት ያስቃል? በህይወት ዘመኔ የሠራኋቸው ስንትና ስንት ስንፈቶችና ጉብዝናዎች ያልተፈፀሙ ያህል ተረስተዋል፡፡ ወይም አልተፈለጉም፡፡ እነዚያ ስንፈቶችና ጉብዝናዎች ግን በትክክል እኔን የመግለፅ አቅም ነበራቸው፡፡ ግን አልተጻፉልኝም፤ አልተጻፉብኝም፡፡ አውቀው በድፍረት ሊሆን ይችላል፤ ወይም ሳያውቁ በስህተት፡፡ የሆነው ሆነና ቀብሬ ላይ እንዲነበብ የተዘጋጀው የህይወት ታሪኬ ለመበሳጨት ምክንያት ሆነኝ፡፡

ይገርማል! የሞተ ሰው መበሳጨት ይችላል እንዴ? መቻል ይችላል፤ብስጭቱን የሚያይለት የለም እንጂ! እሱ መንፈስ ነው፡፡ ቅዱስ ሊሆን ይችላል ወይም ርኩስ፤ግን መንፈስ ነው፡፡

የት አባቴ ልሂድ? የት አባቴ! የእናቴ ድምጽ ይሰማኛል፡፡ ልቅሶዋ፡፡ እማዬን ምን ነካት? ረበሸችኝ፡፡ በጣም ረበሸችኝ፡፡ ራሷን በመርሳቷና የምታደርገውን ነገር ባለማወቋ ረበሸችኝ፡፡

ቸኮልኩ፡፡ ምናለ ቶሎ ተቀብሬ ባረፍኩት የሚል ሀሳብ መጣብኝ፡፡ ያለ ሾፒ የማይንቀሳቀስ መንገደኛ ሆንኩ፡፡ እኔ እንደዚህ 'የተካበደ' ነገር አልወድም፡፡ በህይወት እያለሁም ከበብ ከበብ ሲያደርጉኝ የምወድ ዓይነት ሰው አልነበርኩም፡፡ ደግሞ ይሉኝታ የሚያጠቃቸው ሰዎች ናቸው አስከሬኔን የከበቡት፡፡

እያስመዘገቡ ነው - በእናቴና በሌሎችም የቤተሰብ አባላት ዘንድ ውለታ ለማስቀመጥ፡፡

- የእኔ መሞት ስንቱን ሥራ አስፈታ? ስንቱን...

ሰለቸኝ፡፡ ሰዓቱ በሄደ ቁጥር መሰልቸቴ በዛ፡፡ ደግሞ የእናቴ ሀዘን፡፡ ምን ነካት? ለምንድነው የምትፈራው አጉቴን የማትሰማው? ምነው ልቧ ለአጉቴ ተግሳጽ ደነደነ፡፡

ወዮ እናቴ!

ኖሬ ምን ጨመርኩላት? ሞቴስ ምን አጉድልባታለሁ? ለምን እንደ እህል ብጣሪ ቆጥራ አትተወኝም? ለምን ያልነበርኩና ያልተፈጠርኩ ያህል አትረሳኝም? ለምንድነው፣ ፀፀት ሰቅዞ የሚይዛት? እንክብካቤ ያጉደለችብኝ ይመስል፤ ለማይድን ደዌ አሳልፋ የሰጠችኝ ይመስል፤ከደዌዬ እንዳልድን በመንገዴ ላይ እሾህ ያልነቀለች ይመስል፤ለምንድነው የጥፋተኝነት ስሜት የሚሰማት? ለምንድነው?

- ምናለ ተቀብሬ ባረፍኩት!

ከእሷ ተለየሁ፤እንደተለየሁ አንድ ድምጽ ሰማሁ:: የማውቀው ዓይነት የልቅሶ ድምጽ:: ወደ አዲሷ አልቃሽ አመራሁ:: ልከ ነኝ:: የጠረጠርኩት ነገር ልከ ነው:: እሷ ናት:: የድሮ ፍቅረኛዬ:: ለሁለት ዓመት ያህል በፍቅረኝነት ቆይተን፣ ሥፍራና ጊዜ ከለያየን አምስት ዓመት ሆኖት ነበር:: በቅርቡ ግን ተገናኘንና መንፈሳችንን አደስነውና እንደገና የተበጠሰውን የፍቅር ከር ቋጠርነው:: ማን ነግሯት ነው የመጣችው?

ማንም አላወቃትም:: ማንም አያውቃትም:: ቆማ እዬዬዋን አስነካችው:: ጨርቋን ጥላ የምታብድ መሰለች:: ቤቱ በእሷ ልቅሶ ተነቃነቀ:: እኔ ግን ጨነቀኝ:: ማነሽ ቢሏት ማን ነኝ ልትል ነው? የእሷ ብቻ አልነበርኩም:: ማነሽ ቢሏት ጉድ ይወለዳል:: ማነሽ ባላሏት!

የአሁኗ ፍቅረኛዬ ከጓዳ ብቅ ብላ የድሮ ፍቅረኛዬን አየቻት:: ሁኔታዋን ልብ ስትል እንደ ቅርብ ዘመድ ሳይሆን አይቀርም የቆጠረቻት:: ይህች ፍቅረኛዬ የፊተኛዋን ፍቅርኛዬን ስም ሳነሳበት ፊቷ አመድ ነበር የሚለብሰው:: አሁን ግን ይኸው ተቃቅፈው ይላቀሳሉ:: ጨነቀኝ:: በቀብሬ ዕለት በእኔ ሰበብ ፀብ ተፈጥሮ የሚያዋርድ ሥራ እንዳይሠራ መፀለይ ፈለግኩ:: አደጋ ሸተተኝ:: የጥፋተኝነት ስሜት ተሰማኝ:: ከሞት በኋላ አለ የተባለው ህይወት እውነት ከሆነ፣ ጻድቃንን ወደገነት፣ ሃጥአንን ወደ ሲኦል መስደድ የሚባለው ነገር ካለ፤እኔ ከየትኛው እንደምመደብ ከወዲሁ ገመትኩ:: ዘገነነኝ:: እኔ ለሁለት እመቤት ያደርኩ የፍቅር አሽከር ነበርኩ፤ ሁለቱም የሚዘፍኑልኝ 'የብቻዬ' ብለው ነበር::የሁለቱም ‹ባል› ስለነበርኩ አሁን የአመንዝራነት ስሜት ተሰማኝ::

አንዷ አንዷን በመልከ አታውቃትም:: በድምጽ አትለያትም:: ዛሬ የእኔ መሞት አተያያቸው:: በቀብሬ ቀን ተቃቀፉ:: ተቃቅፈው ተላቀሱ::

ጠላኋቸው:: በጣም ጠላኋቸው:: ይህንን ጥላቻ ይዤ ወደ መቃብር ባልወርድ ደስ ይለኝ ነበር:: ለምን አባታቸው ነው፣ ይህንን ያህል ተቃቅፈው የሚላቀሱት? ለምንድነው፣ ይህን ያህል የጥፋተኝነት ስሜት እንዲሰማኝ የሚያደርጉት?

አንድ ሀሳብ ወደጭንቅላቴ ጓዳ ብቅ አለ::

ሐረር ያለው፣ ያ የምስጢሬ ተካፋይ፣ መሞቴን አልሰማም ኖሯል? ከተሰማኝ የጥፋተኝነት ስሜት መላቀቅ ነበረብኝ::

ከነፍኩ:: ወደ ጓደኛዬ አድራሻ ከነፍኩ:: ውበትና ጥበብ በማያቀዘቅዘው እሳት ውስጥ ነበርኩ:: ሀዘን ለብልቦኛል:: የሚለቀስልኝ ልቅሶ የሰለቸኝን ያህል የጓደኛዬ ቀልድ ናፍቆኛል::

ሄድኩ፤ ሄጄም አገኘሁት:: አየዋለሁ፤ አያየኝም:: ይሄ ነው፤ የመፅናናቴ ጌታ:: ገና እንዳየሁት ነው ሞቴን የረሳሁት:: የእናቴንም ልቅሶ:: የዘማዊነት ስሜቴንም ጭምር!

ይኼ የልብ ጓደኛዬ ጐስቆል ብሏል ልበል? ከገላው የሆነ ነገር ጐድሏል:: የሆነ ነገር ተቆርሶ ወድቋል:: ሥጋ ያነሰው መስሏል:: ደግሞ አይስቅም፤ አያስቅም:: ድምጹን፣ ቀልዱንና ፈገግታውን ምን ገደለው?

የጓደኞቹም ጥያቄ ነው:: ምን ሆኗል? ይላሉ:: ከቢሮው ይወጣል:: ይገባል:: ይወጣል:: ይገባል:: ይመላለሰዋል:: ያዛጋል:: ቡና ያዛል:: ፉት! ጭልጥ!! በሲጋራ ላይ ሲጋራ:: ደግሞ እንደገና ማዛጋት...

"ምን ሆነሃል? አሞሃል?" ብለው የሥራ ባልደረቦቹ ጠየቁት:: "አላመመኝም!" ብሎ ሲመልስላቸው ሰማሁ:: ታዲያ ምን ሆኖ ነው፣ ዛሬ ቀልድ የጐደለበት? ምን ሆኖ? የሣቅ ግቱ የነጠፈ፤ አንደበቱም ያልተፈታ?

ደብቶታል::

የቢሮው ስልክ ጮኸ:: ጮኸና ከቁዘማው ያነጠበው መሰለ:: ለደዋዩ፣ "ዛሬ የሆነ ነገር ሆኛለሁ!" አለው:: የደዋዩ ድምጽ አይሰማኝም:: ጓደኛዬ ጥቂት

ቃላት ከሰማ በኋላ ደነገጠ:: ደርቆ ቀረ:: ጮኸ:: ስልኩን ሳይዘጋ ጮኸ:: ቢሮ ውስጥ መኖሩን እስኪረሳ ድረስ ጮኸ::

"ሞተ!...ሞተ ነው የምትሉት? ወዮ ጓደኛዬ! ወዮ! ወዮ!" ስሜን ጠርቶ አለቀሰ::

ባልደረቦቹ፣ "ትክሻው ነግሮት ነበር!" አሉ፣ ትከሻው ላይ ሆኜ ሰማኋቸው:: ሴቶቹም፣ "እንደ ዛሬ ደብሮት አያውቅም!" አሉ:: ስለእኔ የነገራቸውን አንዳንድ ገጠመኞች እየገጣጠሙ፣ በነበረውና በሰሙት ላይ እየቀጣጠሉ ማውጋት ቀጠሉ:: የጨጓራ ካንሰር እንደያዘኝ ጭምር ነግሯቸው ነበር::

ከመሃላቸው ተለየ:: ወዳጄ ልቤን ተከተልኩት:: ዓየሁት - ዓየሁት - ዓየሁት:: መሞቴን ከሰማበት ደቂቃ ጀምሮ ይሄ ጓደኛዬ ማርጀት ጀምሯል::

ምናለ ለእናቴ እንደ ልጅ ሳይሆንላት ባይሸመግል? ምናለ ቶሎ እናቴ ዘንድ በደረሰ!

ደረሰ:: አስከሬኔ ላይ ሲንከባለል ሳይ ዕንባዬ መጣ:: እንደ አዲስ ተለቀሰ:: ደረት ተደቃልኝ:: ፀጉር ተነጨልኝ:: ፎቶዎቼና ልብሶቼ ማላቀሻ ሆኑ:: ወይኔ ጓደኛዬ! ዕንባ በዕንባ ሆኑ:: ትንሽ ቆይቶ እናቴን አባብሎ ወደ ጐረቤት ወሰዳት:: ለእሱ ተሸነፈችለት::

ተከተልኩት:: ምን ሊነግራት ነው እልኩ:: አንድ ጥግ አስይዞ አፅናናት - የመፅናናቴ ጌታ! 'ልጄ አፈር ሳይቀምስ እህል በአፌ አይዞርም!' ያለች እናቴን - ጨጓራዋ እንደ ፍም እየፈጃት የምትንበለበለዋን እናቴን - ለምኖ ወተት አስጐነጫት:: ዳቦም አጐረሳት:: እየተናነቃትም ቢሆን መዋጥ ጀመረች::

እፎይ! አሁን ነው ፈገግ ያልኩት:: የገዛ ፈገግታዬ ያጽናናኝ ጀመረ:: ከሞትኩ ስንትና ስንት ሰዓት አልፏል? ደስታ ርቆኝ ነበር:: አሁን ነው ደስ ያለኝ:: እሰይ!

አሁን ባዶ አይደለሁም:: አሁን ምድረ በዳ አይደለሁም:: አዲስ ነገር በቅሎብኛል:: የእናቴን ሀዘን በሆዴ፣ የጓደኛዬን ፍቅር በልቤ ይዣለሁ::

ገርሞኛል፤ከመገረምም በላይ ተገርሜያለሁ:: ሞት እንዲህ ነው እንዴ? ከተቀበርኩ በኋላ እየሆነ ያለውን ነገር የመከታተል ችሎታዬ የምነጠቅ መስሎኛል::

እስከቀበር ድረስ እስከ መጨረሻዋ ሰከንድ ከእናቴና ከጓደኛዬ አልተለየሁም...

አሁን ወደተቆፈረልኝ ጉድጓድ ልገባ ጥቂት ሰከንድ ነው የሚቀረኝ:: ከአሁን በኋላ የሚሆነውን አላውቅም:: ግዳጄን ፈፅሜያለሁ፤ 'ሩጫዬን ጨርሻለሁ!!!!!!!!!!!!!!!!!!!!!!!!!!!!!!!!!!!!!!!!!!'

ለካስ ሞት ማለት ይኸ ነው፤ ምድር ላሉ ሰዎች ይህን ማን በነገራቸው!

..........

# በልደት ቀን

እሰይ! ይኸው ቅዳሜ መጣ:: ቅዳሜ ዛሬ ሆነ:: ተናፋቂው ቀን ደረሰ:: የአበራሽ ልብ ነጋለት:: የዘጠኝ ዓመት ፊቷ ፈገግታ በርቶበት ዋለ! የቅዳሜ የከሰዓት በኋላ ውሎዋን በጣም ነበር የጓጓችለት:: የእኔ ቢጤ ያደረበትን ቁርበት ሳይጠቀልል ነው፣ እናትዋን ከእንቅልፍ ያነቃቻት:: ገላዋን አጥባ፣ ፀጉሯን ሰርታ፣ ቀባብታ እንድታስውባት...

ትንሽ ቆየት ብላ ደግሞ ፍቅርተ ጋ ትሄዳለች:: ቀጠሮዋ ከእሷ ጋር ነው:: ፍቅርተ ጓደኛዋ ናት፣ የከፍል ጓደኛዋ! ዛሬ ስምንት ዓመት ይሞላታል፤ ስምንተኛ ዓመቷን አሙቃ ለማክበር ከሰዓት በኋላ ጓደኞቿ ይከቧታል:: የዘመድ ልጆች ይከቧታል፤ የጎረቤት ህጻናት ያነግሷታል::

ዛሬ ቅዳሜ ነው:: ትንሽ ቆይቶ ቅዳሜ ከሰዓት በኋላ ይመጣል:: ከመምሸቱ በፊት ብዙ ሣቅ አለ:: ብዙ ጨዋታ አለ:: ብዙ ዘፈን አለ:: ብዙ ዳንስ አለ:: ብዙ ብዙ ነገር አለ::

አበራሽ የዛሬውን ቅዳሜ ወዳዋለች፣ናፍቃው ነበርም-በተለይ የከሰዓት በኋላውን::

"እማ! ጓደኛዬ የልደት ቀኗን ስታከብር፣ ቤታቸው ውስጥ ማን ባይኖር ደስ ይለኛል መሰለሽ?" ብላ ትጠይቃታለች::

አጎዛ ገበያ የዋለ እናቷን አያጣትም:: ሰዉ ከእሷ አይደል ሽንኩርት የሚገዛው?

"ማን ባይኖር ደስ ይልሻል?" ትላለች እናት::

"ወንድሟ ነዋ፤ትንሱ መኪናቸውን የሚነዳው:: እኔን በደንብ የማይወደኝ:: ያ! ፀጉሩ እንደ ሴት ሲያድግበት እሱ ደግሞ ሹሩባ ተሰርቶ የሚሄደው..."

"አንቺን የማይወድሽ ለምንድነው?"

"እኔንጃለታ!"

"ለምን ግን..."

"ፍቅርተን በመኪና ሊወስዳት ሲመጣ፣ እኔን ግን ዝም ይለኛል:: እሷ ደግሞ እኔን እቅፍ እቅፍቅፍ አርጋ አስጨንቃ ካቀፈችኝ በኋላ ወንድሟን ትለምንልኛለች:: አንድ ቀን 'የሚያደከም ብዙ መንገድ ብቻዋን በእግሯ ከምትሄድ በእኛ መኪና ሩቅ ቦታ አድርሳት:: ስሞትልህ! ስቀበርልህ!' ብላ እየሳመች አሳዝና ስትለምነው እሱ ግን አሳፈራት:: እያሳፈረ ሰደባት:: 'ሂጂ ወደዛ! የማነሽ ሞልቃቃ! ይሄ የማንም ልቅምቃሚ ማመላለሻ አይደለም' ብሎ ተቆጣት:: ብዙ ከተበሳጨባት በኋላ መኪናውን እያስፈተ...ለከ እንግሊዝኛ እያስዘፈነ አቡዋራ አከናንቦኝ ሄደ"

ድምጽዋ ሻከረ:: ድምጽዋ መከፋት ጎበኘው:: "ጥዋት እኔና አንቺ በሽቀን አልነበር፤ ጫማ የሚሰፋልኝ ሰውዬ ስናጣው፣ ልክ እንደዚያ ነው ሚያበሽቀኝ"

"አይዞሽ በቃ! አይዞሽ እሺ..." አለቻት፣ እናት:: ራሷን ነበር እያፅናናች የነበረችው:: ልጇ ስለፍቅርተ ወንድም ስትተርከላት ፊቷ ጭው ብሎ ነበር የምትሰማት:: ፊቷ ጭው ብሎ! በፀጥተኛ ሌሊት ውስጥ እንደሚደመጥ የባይተዋር ዋሸንት::

"አይዞሽ እሺ!"

አበራሽ ምንም ያልሰማችና የእናቷን ስሜት ያልተረዳች መስላ፣ "ደግሞ የሚያሳስት ምክር ይመከራታል:: ‹ለምን ጓደኛ አትቀይሪም› ብሎ እንደተቆጣት - አሳዝና በ - ጣ - ም አሳዝና ነገረችኝ::... ድንገት እሱ ሲመጣብን እንደነጋገራለን:: እንደነጋገጥና - እንደማይተዋወቅ ሰው እንራራቅና - በሩቅ በሩቅ ሆነን ተያይተን - ቻዎ እንባባላለን!"

በዚህን ጊዜ እናቷ የመከፋቷን ድባብ የምትሸፍንበት አቅም አጣች፡፡ “ከፉ፤ የሰው ከፉ ...”

ከአበራሽ ውጪ ሌላ ልጅ የላትም፡፡ ባለቤቷ ጦር ሜዳ ሄዶ እንደወጣ ከቀረ ዓመታትን አስቆጥሯል፡፡ ለስድስት ጊዜ ያህል የጥምቀትን በዓል ያለ አባወራ አክብረዋል፡፡ አሁን ጦርነት የለም፡፡ ጦረኞች ፀብ አብርደው ሰይፋቸውን ወደ ሰገባቸው መልሰዋል፡፡ ወደ ወጡበት ጎጆ ገብተዋል፡፡ የአበራሽ አባት ግን...

አሁን እናትና ልጅ የቤታቸውን ምሰሶ ረስተውታል፡፡ ምሰሶ አልባ ጎጆ...

አበራሽ፣ “ፍቅርተ ከተጣላችኝ እስከሞት ድረስ - ሙትትት እስከል ድረስ - ሌላ ጓደኛ አይኖረኝም!” ማለት ታዘወትራለች፡፡

የቀጠሮው ሰዓት እየደረሰ ነው፤ ቅዳሜ፣ ከሰዓት በኋላን እየጠራው ነው፡፡ አበራሽ ሽር ጉድ አብዝታለች፡፡

እናቷ፣ “ሂጂ! ፊትሽን በመስታወት እዩው ሂጂ!” ብላ ወደ ሳሎን ላከቻት፡፡

አበራሽ ከጥቂት ደቂቃ በኋላ ፊቷን ፈገግታ ሞልቶት ተመለሰች፡፡ “ቆንጆ ልጅ እንዳደረግሺኝ አየሁ!” አለች፣ ቀስ በቀስ እየፋፋ የሚሄድ ፈገግታ ፊቷ እምብርት ላይ እየተወለደ፡፡

የለበሰችው በበዓላት ቀናት ብቻ የምትለብሰውን ቀሚስ ነው፡፡ ቀሚሱን ትወደዋለች፡፡ “ይሄን ስትገዥልኝ ብዙ ሽንኩርት የሸጥሽበትን ገንዘብ ነው አይደል ያሳለቅሁብሽ...አይደል?” - ሁል ጊዜ የምታነሳው ጥያቄ፡፡

“አንቺ ጉብዥልኝ፤ ፈተና አለፊልኝ እንጂ ገና ምን አይተሽ፣ ወርቅ አለብስሻለሁ”

አበራሽ የእናቷን ምኞት ስትሰማ ግር ይላትና፣ “ወርቅ ሲለበስ ግን ደስ ይላል፣ እማ? ትልቅ ስንሆን - ፍቅርተ፣ የለበስኩትን ወርቅ ልታይልኝ ስትመጣ ፀሃይ ከሆነ ያብረቀርቅባትና ዐይኗን ቢያሳምማትስ?” ታመጣዋለች ጥያቄዋን!

እናቷም ፈገግ ብላ፣ "እንቀባርሬ አሳድግሻለሁ፣ አስጌጥሻለሁ ማለቴኮ ነው!" ትላታለች::

"ታዲያ እንደሱ አትይኝም፤ የሚያሳስት ነገር ከምትናገሪ?"

ለስምንት ሩብ ጉዳይ...

"አንቺ እማ፣ኧረ ቶሎ በይ...ከሰዓት በኋላ ካለፈ እኮ ቶሎ ነው ሰማዩ ጥቁር ሆኖብኝ የሚያስፈራራኝ?"

አበራሽ ወጣች፤ የቤቷን ደጅ ለቀቀችው:: ወደ ግቢ የሚያመራውን መንገድ ተያይዛዋለች:: ባጌጠ ብረት የተበጀውን በር በጥንቃቄ ገፋ አድርጋ እግሯን ወደ ውስጥ ሰደደችው::

ጥቂት የክፍል ተማሪዎች፣ አብሮ አደጎችና የዘመድ የወዳጅ ልጆች ሳሎኑን አጥብበውታል:: ሁሉም አምሮባቸዋል:: ትናንሽ ከንፍ አልባ መልዓኮች!

የሚበላ የሚጠጣው ነገር የጠረጴዛውን ሆድ ሚጢጢ ተራራ አሳክሎታል:: ብርቱካን፣ ኬክ፣ ሙዝ፣ ከረሜላ፣ ለስላሳ...በመጠን የማይተናነሱ ስምንት ሻማዎች ብርሃን መርጨት ጀምረዋል:: ሙዚቃው ላንቃው እስኪሰነጠቅ ያቅራራል:: ግድግዳው በመልካም ምኞት መግለጫ ጽሑፎች፣ ካርዶችና ጌጣጌጦች አሸብርቋል:: የህጻናቱ ሣቅና ልፊያ ደርቷል::

ፍቅርተ እጅዋን አበራሽ አንገት ላይ አሳርፋ፣ "አሁን ትንሽ እንቆይና ፎቶ እንነሳለን:: ተቃቅፈን ነው የምንነሳው እሺ? ብዙ የሚያስቁ ፎቶዎች እንነሳለን:: አልበሜ እስኪሞላ:: ቪዲዮም እንቀረፃለን!!"

"እሺ" ትላለች፣ አበራሽ እንግድነት ልቧን እየገዛው::

"አከስቶቼ ደግሞ ብዙ ስጦታ አሁንም አሁንም እያመጡልኝ አላልቅም አለ:: ሲጠራቀምልኝ ላንቺ አካፍልሻለሁ:: ላንቺ ብቻ ነው ማንም ሰው ሳያውቅብኝ የምሰጥሽ:: እሺ አበራሽዬ፤ እሺ?"

ኬክ አቀረበችላት::

አበራሽም ከቀረበላት ኬክ ቆረስ አድርጋ መብላት ልትጀምር ስትል፣ "ቆይ! ነይ መጀመሪያ ከማሚ ጋር ላስተዋውቃችሁ" አለችና እየመራች እናቷ አፍንጫ ስር አቀረበቻት:: "ማሚ ይህችኮ ናት፣ አበራሽ ትባላለች ያልኩሽ አንደኛ ጓደኛዬ ..."

እናቷንና ጓደኛዋን አስተዋውቃ እንደ ጨረሰች፣ ከሁለቱ ተነጥላ፣ ብርርር ብላ፣ ልደትዋን በማስመልከት ከሚጨፍሩት እድምተኞች ጋር ተቀላቀለች::

እናትየው አበራሽን እቅፍ አድርጋ ከሳመቻት በኋላ፣ ዐይኖቿን ወደታች ስትልክ፣ አንድ ነገር አይታ ደንገጥ አለች:: "ውይ ምነው?" አለች:: "ጫማሽን አውልቀሽ ደጅ ላይ ትተሽ የገባሽው ማን ሲያወልቅ አይተሽ ነው? ምንጣፉ በጫማ ቢረገጥ ምን የሚሆን መስሎሻል? ሌሎቹን እዩአቸው እስኪ፣ አንድም ሕጻን ሳያወልቅ እኮ ነው የገባው?" አለች የፍቅርተ እናት፣ ሀዘኔታም ተግሳፅም በተቀላቀለበት ድምጽ::

የአበራሽ ፊት ሀፍረት ተመላለሰበት:: በርግጥ ለጓደኛዋ እናት ጥያቄ ምላሽ ይሆን ዘንድ አንዲት ቃል ጣል ማድረግ ፈልጋ ነበር:: ነገር ግን አልሆነላትም:: ደግሞም ፊቷ ፍም ለብሷል:: ብርክ ይዟታል...ወደ አፍዋ ያደረሰችውን ኬክ የመጉረስ አቅም እስኪያንሳት ድረስ!

"የኔ እናት... በይ ... ደጅ ያኖርሺውን ጫማ አድርገሽ ግቢና እኩዮችሽን ተቀላቅለሻቸው ደንሺ:: ሌሎቹን አታያቸውም እንዴ?" አለቻት:: ወደ ጐረቤቶቿ ዘወር ብላም፣ "ነገረ ሥራዋ ሁሉ እንደ ትልቅ ሰው ነው! አሁን በዚህ ዕድሜ ጫማ አውልቆ ሰው ቤት መግባት አይገርምም?" ብላ፣ የዘመኑ ልጆች አርቆ አስተዋይ የመሆናቸውን ነገር አንስታ በመገረም ታወራ ጀመር::

የፍቅርተ እናት አበራሽን ወደ መውጫው በር፣ ማለትም ጫማዋ ተቀምጧል ብላ ወደ ገመተችበት ደጅ ገፋ አደረገቻት:: አበራሽ ግን ቀጥ!

ፀጥ!! ተሳቀቀች፣ ዕንባ እየተናነቃት ለሦስት አራት ደቂቃ ያህል ደጅ ላይ ቆመች:: ቆመች!! ልክ የሌለው ሀዘን ጫንቃዋን ወደታች ተጭኗታል:: ከብዷታል:: "ሊያመኝ ነው!" አለች ለራሷ::

እግሮቿን አየቻቸው:: አቧራ ቦንኖበት፣ አቧራው የባዝሊኑ የማብለጭለጭ ሃይል እንዳይቀንስባት በጥንቃቄ ተራምዳ ነው እዚህ ቤት የደረሰችው::

የፍቅርተ እናት ይህን አታውቅም:: የአበራሽ እግሮች ጫማ የሚባል ነገር ከረገጡ ምን ያህል ጊዜ እንደሆናቸው አታውቅም:: ከሦስት ቀናት በፊት የተገዛላት አዲስ ጫማ፣ እናቷ፣'ጫማ በአዲስነቱ ዙሪያው ካልተሰፋ ይቀደዳል' ብላ ለጫማ ሰፊ መስጠቷን አታውቅም:: ጫማ ሰፊው ደግሞ፣ ‹አደርሳለሁ!› ያለው ለዛሬ ቢሆንም ልቅሶ ገጥሞት ወደ ገጠር መግባቱን አታውቅም::

የፍቅርተ እናት ይህን ሁሉ አታውቅም:: እናም፣ "ሂጂ!" አለቻት:: ወደ ደጅ ላከቻት:: "ጫማሽን ተጫምተሽ ግቢ!" አለቻት::

አበራሽ ቀና ስትል ፍቅርተን ከቤት ወደ ትምህርት ቤት አድርሶ የሚመልሳት ሹርቤ ወንድሟን አየችው::

እየመጣ ነው፣ እየቀረበ ነው፣ ወደ ፊቷ::

ግቢውን ለቅቃ ወደቤቷ ስታዘግም አደገኛ ውሻ የሚያሳድዳት ነበር የሚመስለው....

......

# አቤሴሎም

አባትና ልጅ...

“አቢ!”

“እ?”

“አትሂድብኝ!”

“ካልሄድኩ ከሥራ እባረራለኋ! ከተባረርኩ ደግሞ ገንዘብ ስለማይኖረን ይርበናል”

ዝምታ!

“አቢ?”

“እ?”

“ሌላ ዓመት በዐል እስኪመጣ ስንት ቀን ይቀረዋል?”

“ለምን ጠየቅከኝ?”

“እንደገና መጥተህ እንድታጫውተኝ”

ከባድ ዝምታ!

መሽቷል፡፡ የተቀመጡት ሳሎን ነው፡፡ ከተጐዘጐዘ ሁለት ቀን የሆነው ቄጠማ ወለሉ ላይ ይታያል፡፡ ቄጠማው ወደ መድረቁ ነው፡፡ ፊት ለፊት በሚታየው

የምግብ ጠረጴዛ በሕጻናት የተሳሉ፣'እንቁጣጣሽ እንኳን ደህና መጣሽ' የሚል ጽሑፍ ያለባቸው ሁለት ሥዕሎች ይታያሉ:: አንዱ ሥዕል ተጨማድዷል:: የሠዐሊው ስም ከሥዕሉ በላይ ገዝፎ ይታያል:: *ቴዎድሮስ አቤሴሎም::*

የቴዲ አባት፣ በስርዐት ተተኩሰው ሶፋ ላይ የተቀመጡትን ልብሶቹን እያነሳ ሻንጣ ውስጥ እየከተተ ነው:: ሻንጣው አጠገብ የታሸጉ ዳቦ ቆሎዎች፣ በሶና የመሳሰሉት ነገሮች:: ሶፋው ፊት ለፊት ባለው ጠረጴዛ በብርጭቆ ጠላ ይታያል:: ጠላው ተጋምሷል::

የአስር ዓመቱ ቴዲ አባቱን ብቻውን በማግኘቱ እየቦረቀ ነበር የገባው:: የአባቱን ሻንጣ ሲያይ ፊቱ ሀዘን ይለብስና በዝግታ ወደ ጠረጴዛው ቀረበ:: የተጨማደደ ሥዕሉን አየ:: ብስጭት እየታየበት፣ ሳሎን ውስጥ ወደተሰቀለው የእናቱ ፎቶ ዐይኑን ላከ:: ፎቶው፣ 'ሠራሁልህ አይደል' የሚለው መሰለው::

የተጨማደደ ሥዕሉን፣ እንደታናሽ ወንድሙ ሥዕል ቀጥ ለማድረግ ሙከራውን ተያያዘው::

ታናሽ ወንድሙ አቤል ተኝቷል::

“አቢ!”

“አቤት የእኔ ልጅ!”

የቴዲ ፊት ደነገጠ:: ዐይኑ ፈጦ እጁን አፉ ላይ አኖረ::

“ምን ሆንክ?”

ቴዲ በሹክሹክታ፣“እንደሱ አትበል! ማሚ ደስ አይላትም” አለው::

“ምን አልኩ ቴዲ?”

ወደ አባቱ ጆሮ ቀርቦ፣ “አቤት!”አለና፣መልሶ ደግሞ፣ “የእኔ ልጅ አትበለኝ!” ብሎ ማስጠንቀቅ ጀመረ::

አባት የልጁን ፀጉር እየደባበሰ፣“ብልህስ?” አለ::

"ማሚ ብትኖር ኖሮ፣ 'አቤት የእኔ ልጅ ማለት ምን ማለት ነው ፤ያንተን ያልሆነ ልጅ ወልጄ አውቅ ይመስል' ትልህ ነበር"

አባቱ የመጣው ከሩቅ ነው:: ለአዲስ ዓመት በዓል፣ የሰባት ቀን ፍቃድ ተቀብሎ:: ከሰባቱ ቀናት አራቱ ቀናት በመንገድ ጉዞ ያልቃል...

ነገ መንገደኛ ነው::

"አቢ"

"እ?"

"ማሚን ተጣላት:: አኩርፏትና፣ ለብዙ ቀን ዝም በላትና፣'ለምንድነው ሳናግርህ የማታነጋግረኝ ስትልህ፣ ቴዎድሮስን ለምን ታበሳጪዋለሽ! አንቺ ያልወለድሽው ይመስል...' በላት:: እሺ?"

ዝም::

"ትላታለህ አይደል?"

"ቴዲ!"

"እ?"

አባትየው ምን መመለስ እንዳለበት ሲያሳላስል ቆየና፣ "ሂድ! ከልጆች ጋር ተጫወት" አለው::

"ካንተ ጋር ይሻለኛል:: አንተ የሌለህ ቀን ከእነሱ ጋር እጫወታለሁ"

"አቢ!"

"እ?"

"እንደቅድሙ ፀጉሬን አሻሽልኝ፤ ሳታሳምም ቀስ ብለህ ጭንቅላቴን እከከልኝ"

ዝቅ ብሎ ፀጉሩን ሳመለት:: በፍቅር ፀጉሩን ዳበሰለት:: ቴዲ ፈገግ ከማለት ይልቅ ለንብጩን ጥኋል::

"ምን ሆነሃል?"

ቴዎድሮስ፣ የአባቱን ጭልም ያለ ፂም እየደባበሰ፣ "እናቴ አትወደኝም፤ ተጣላት:: እኔ በጣም እየወደድኳት እሷ ግን አቤልን ብቻ ትወደዋለች፣ 'እምወድህ ናልኝ እስኪ' ትለውና አጠገቧ ታስቀምጠዋለች:: እንቅልፍ መጥቶበት እስኪወስደው ድረስ..."

አባት ስለ አቤል መስማት አይወድም:: አቤል አባቱን የማይመስለው ህጻን! እናቱንም የማይመስለው! የአባቱን ጓደኛ መስሎ ቁጭ ያለው!!

የቴዎድሮስ እናት የአንድ ድርጅት ጸሐፊ ናት:: ታሪኩ በሚሰራበት ድርጅት ተቀጥራ የምትሠራ::

*ከብዙ ቀናት በፊት፣ባልና ሚስቱ - ቡና ቤት ውስጥ - እንዲህ ተባብለው ነበር::*

***ባል፡-*** *ከዚህ ሰውዬ ጋር ያለሽን ጓደኝነት አልወደውም::*

***ሚስት፡-*** *እንደማልወደው እያወቅህ ለምን እንደዚህ ትለኛለህ?*

***ባል፡-*** *እኛ ስንጣላ ያስታረቅሽን እንቺ ነሽ፤ 'አለሌ ነው፤ ካንተ ጋር የሚሄድ ባህርይ የለውም' ያልሺኝ አንቺ ነሽ፤ 'እሱ ቢሮ ለጉዳይዋ ገብታ ለመኝታ ያልተጠየቀች ሴት የለችም' ያልሺኝ አንቺ ነሽ!*

***ሚስት፡-*** *ነኝ::*

***ባል፡-*** *ያልነበረብኝን አመል ያበቀልኩት ላንቺ ብዬ ነው:: ላንቺ ብዬ ያልሆንኩት ነገር የለም:: ከበፊት ጀምሮ:: ከአስር ዓመት ጀምሮ:: ሁሉም ነገር ላወራሽ አልፈልግም:: ግን እንድታውቂው እፈልጋለሁ...*

**ሚስት፡-** *ይገባኛል፤ የምትለው ሁሉ ይገባኛል:: ባትነግረኝም ይገባኛል፤ አልገባህ ብሎ እንጂ በፊትም ነግሬህ ነበር:: አንተ ማድረግ የማትፈልገው እሱ ግን የሚችለው አንድ ነገር አለ::*

**ባል፡-** *ምንድነው እኔ ሳልችለው እሱ የሚችለው ነገር?*

**ሚስት፡-** *ማጨስ!*

**ባል፡-** *ሲጋራ?*

**ሚስት፡-** *አንተ ቆይተሃል፣ 'ሃይማኖቴ የሚቃወመውን ነገር እንዳደርግ የምትገፋፊኝ ከሆነ አንጋባም' ካልከኝ:: ደግሜ ያልጠየቅኩህ ከውሳኔህ ፈቀቅ የማትል እንደሆንክ ስለማውቅ ነው:: ይገባሃል አይደል? ማጨስ ፈልጌ ከልከለኸኛል!*

**ባል፡-** *ልታጨሺው የፈለግሽውን የሲጋራ ዓይነት ጥሩ አልነበረም:: ላንቺ ደህንነት ብዬ ነው:: ለምንወልዳቸው ልጆች ጤንነት ብዬ!*

*[ቢራውን አንስቶ ጠጣ]*

**ሚስት፡-** *ለእሱ ብለህ ብቻ አይደለም:: ሲጋራውን እንዳላጨስ የፈለግህበትን ምክንያት ታውቀዋለህ:: የበፊት ፍቅረኛዬ - ነፍሱን ይማረውና - ከእሱ ውጭ ወንድ አላውቅም ነበር:: ፍቅረኛሞች ከሆን ከአምስት ዓመት በኋላ ነው አብረን የተኛነው:: ከነድንግልናዬ ነው ያለሁት - አልኩት:: እውነቴን ነበር:: በምንም ተዐምር ቢሆን ልዋሸው አልችልም:: ለመጀመሪያ ጊዜ የተኛሁት ከእሱ ጋር ነው:: ድንግልናዬ ግን አልነበረም:: ተወኝ:: አማላጅ ላከሁበት:: እምቢ አለ:: ለውሸታም የሚፈታ ፊት የለኝም አለ:: በቃ! በቃ! ተለያየን! በቃ ሳንጋባ ተፋታን:: ትዝታውና የሚያጨሰው የሲጋራ ጭስ ብቻ ተረፈኝ:: ሱሰኛ ሆኜ ነበር:: ባጨስ ቁጥር ከአጠገቡ የማልጠፋ...*

**ባል፡-** *አንቺን ተሟግቼ መርታት አልችልም::*

**ሚስት፡-** *[ቦርሳዋን አንስታ ብድግ አለች] ቅናት ዓይነት አለው:: ሰው እንዴት በሙዋች ይቀናል? በሙዋች አይቀናም:: ለሰሚም ደስ አይል:: ያንተ ጥል ከጓደኛህ ጋር አይደለም:: ጓደኛህ አለሌ ሆነና እኔ እወሰልታለሁ ማለት ነው? በአንተ ላይ? ቢያርዱኝም አላደርገው!*

እንዲህ በተመላለሱ በሰባተኛው ወር ወለደች::

አቤልን ወለደችው:: ቴዎድሮስ ወንድም አገኘ:: ወንድሙን ግን አልተቀበለውም::

"አቢ ተጣላት:: አቤልን እግሯ መሃል አስገብታ ፀጉሩን ታሻሽዋለች:: 'አንቺ ካልወሰድሽኝ ትምሕርት ቤት አልሄድም' ሲል ግንባሩን እየሳመች ታባብለዋለች:: ሲያምመው ታለቅስለታለች:: እንቅልፏን ሳትተኛ ብዙ ቀን ትቆያለች:: ምግብ ሲያቀርቡላት አቤልዬ ሳይሻለው አልበላም! ትላለች:: ጐረቤቶች ሲለምኗት ሁሉ እሺ አትልም"

ዕንባ ዕንባ ይለዋል::

"እኔ ዩኒፎርሜ ስለቆሸሸ ትምሕርት ቤት አልሄድም ስላት፣ 'ድሮስ እንድትቀና ነው እንጂ እንድትማር መች ተፈጠርከና?' ትለኛለች:: ሲያመኝ፣'ኸረ ሐኪም ቤት ውሰጂው' ሲሏት፣'የትም ሲልከሰከስ ቀይቶ...'ትለኝና፣ እጄን አሳምማ አስነስታ ትወስደኛለች:: *ክሊኒክ* ከሄድን በኋላ ሐኪሙ ስቆ የሆነ ነገር ጻፈና፣ 'ያመጣሽው ምን ሆኖ ነው?' ሲላት፣ እሷ ደግሞ፣'ምንም አልሆነም:: ማቃሰት የጀመረው ታናሽ ወንድሙ ሲታመም አይቶ ነው፤ ጐረቤት ሐኪም ቤት ውሰጂው ብሎ ጨቅጭቆ ሊገድለኝ ሲል ነው፣ ወደ አንተ ያመጣሁት:: አፉ ላይ ውሃ ጠብ አርግበት፤ መድኃኒት መስሎት፣ ይድናል' አለችው:: 'በወንድሙ በአቤል ቀንቶ ነው' አለችው:: 'ስንት የሚቀናበት ነገር እያለ በሕመም ይቀናል' አለች እንጂ፣ ‹ልጄ ያተኩሳል!› ብላ በደንብ አሳዝና አልነገረችውም፤ምግብ አይበላለትም፤እንቅልፍ አይወስደውም አላለችውም፤ አልተንከባከበችኝም:: በሐኪሙ አስሳቀችብኝ:: ከዚያ ሐኪሙ የሚቀዘቅዝ ብረት ልቤ ላይ አድርጐ የምውጠው መረመረኝና ኪኒን ሰጠኝ:: 'እይዞህ! ጐበዝ!' ካለኝ በኋላ ወደ ቤት ልንሄድ ስንል አስታወከኝ:: ማሚ ተቆጣችና፣ 'ተዋረድ! የሚያዋርድ ይዘዝብህ! አውቀህ ነው ያስመለስከው:: ጣትህን ወደ አፍህ ውስጥ አስገብተህ!' አለቺኝ:: ውሸቷን'ኮ ነው አቢ:: ከዚያም፣ 'የምታዝለው ይዘዝብህ ሸክም:: ሂድ በእግርህ፤ ወለም ዘለም ሳትል በቀጥታ ወደ ቤትህ....' ብላኝ፣ እሷ ወደ ሌላ ቦታ ሄደች!"

ዕንባውን መጠራረግ ጀመረ:: አባትየው ሃሣብ ጠምዶ ይዞታል:: በግማሽ ልቡ ነው፣ ቴዎድሮስን የሚያዳምጠው::

አቤል ሰባት ወር ሲሞላው ከሚስቱ ጋር የተመላለሰውን እያሰበ ነበር::

***ባል፡-*** *ይሄ ልጅ የማነው?*

***ሚስት፡-*** *የማን እንዲሆንልህ ትፈልጋለህ? አሁንስ አበዛኸው!*

**ባል፡-** የእኔ አይደለም! አታለሺኛል፣ ትሄጅለት እንደነበር ይሄው ማረጋገጫ፣ አባቱን መሳይ ልጅ ወልደሻል...

**ሚስት፡-** ተራ ሴት አታድርገኝ፣ የማደርገውን አውቃለሁ:: ለማተቤ የምታመን ባለትዳር ነኝ...

**ባል፡-** አቤል የኔ አይደለም!

**ሚስት፡-** ያንተ ካልሆነ በመንፈስ ቅዱስ ነው ማለት ነዋ ያረገዝኩት!

**ባል፡-** አቤል በምንም ተዓምር ቢሆን ካንተ አብራክ ነው የተከፈለው አትበይኝ፣ ደሜ ደሙ ውስጥ የለም:: ጉድተሸኛል!

**ሚስት፡-** ካላመንከኝ አላስገድድህም:: ከጠላኸኝ ጠላኸኝ ነው፣ ሰበብ አታብዛ:: ቤትህን እተውልሃለሁ:: ሆሆይ! ‹ፍቅር ብር አምባር ነው መውለቅ ነው ያለብኝ› አለች ዘፋኟ:: የግድ ልጅ እናቱን ወይም አባቱን መምሰል አለበት?

**ባል፡-** ኧይ! የአባቱን ጓደኛ ነው መምሰል ያለበት....

**ሚስት፡-** እኔ ዕውቀት የለኝም:: የፈጣሪ ተፈጥሮም ብዙ ነው:: ከአንተ ይልቅ ከጓደኛህ ጋር ብዙ ሰዓት እውላለሁ:: ከሚያጫሰው ሲጋራ ፍቅር ይዞኛል::

**ባል፡-** ከሙዋቹ ፍቅረኛሽ ጋር የነበረሽን ፍቅር መርሳት ስለማትፈልጊ ነው እንጂ ...

**ሚስት፡-**መርሳትማ አልፈልግም!! [በቁጣና በመንገብገብ] በጭራሽ! ምን የሚያስረሳ ነገር ተገኝቶ? በተዓምርማ አምናለሁ:: ነፍሰጡር ሴት አዘውትራ የምታየውን ሰው የመውለድ ዕድል እንዳላት ሳይንስ ያረጋግጥ እንደሆነስ?

**ባል፡-** እንዲህ የሚባል ነገር የለም!

**ሚስት፡-** ሟቹ ጓደኛዬ ያታለልኩት መስሎት ነበር:: ማንም ካልወሰደው ድንግልናሽ የት ሄደ? አለኝ:: እውነቱን ነው የት ወሰድኩት? ግራ የገባ ነገር! ታማኝ ሆኜ ሳለ እንደ ከሃዲ እንደ ሂያጅ ያስቆጠረኝ!

አቤል አደገ::

አባት ግን ለአቤል ስስታም ሆነ:: ጨዋታ አይሰጠውም:: ሳቅ አይሰጠውም:: ፍቅር ነፈገው:: በአባቱ የተረሳ ልጅ ሆነ::

ይህን ጊዜ እናትየው ቴዎድሮስን ጣል ጣል በማድረግ፣ 'እኛም ገብቶናል፤ ጉድጓድ ምሰናል' ብላ መዘየድ ጀመረች:: ባል ባበሳጫት ቁጥር ቦርሳዋን ከፍታ ለአቤል ቸኮሌት ታጐርሰዋለች:: ከአፏ ነጥቆ ወደ አፉ እንዲያስገባ ታበረታታዋለች:: ቴዎድሮስ በመቁለጭለጭ ብዛት ምራቁን አስር ጊዜ ይውጥና፣ ቀስ ብሎ፣ ቸኮሌቱ የታሰረበትን ወረቀት አንስቶ፣ተደብቆ ይልሳል:: ተደብቆ:: ሽንት ቤት ገብቶ::

እሷ ደግሞ ባለቤቷን ለማስቆጣት የጓደኛውን አመል መተረክ አይጠበቅባትም፤ ለሚች ፍቅረኛዋ የነበራትን ስሜት መዘርዘር አይጠበቅባትም::

"አቤል ና!" ማለት ብቻ፤ "ና!" ብላ ፀጉሩን መደባበስ፤ "ና!" ብላ ጭኗ ስር አስገብታ ደረቷ ላይ እንቅልፍ እንዲወስደው ማድረግ ብቻ! ሕጻኑን በፍቅር ዐይን ስታየውና ደረቷ ላይ ስታስተኛው አባወራው በንዴት ይበግናል::

የሚተሻሸው ገላ አድጐበት የጓደኛውን የሰውነት ቅርፅ ይይዝባታል:: 'በለው...በለው!!!!!!!!!!!!!!!!!!!!!!!!!!!!!!!!!!!!!!!!' ይለዋል::

ይንቆራጠጣል:: የሚያደርገውን ያጣል:: የተሰማውን የቅናት ስሜት ለእሷ ላለማሳየት ብሎ፣ የፎቶ አልበሙን አንስቶ ይገልጣል:: አልበሙ ውስጥ ያሉ ፎቶዎችን እያየ ሲሄድ፣ እያንዳንዱ ፎቶ ያንን ዘመን፣ ያንን ጊዜ እና ፎቶውን የተነሱበትን ዘመን እንዲያስታውስ ያደርገዋል:: ይገልጣል አልበሙን:: የጓደኛውን የታሪኩን ፎቶ ሲያይ ይደነግጣል:: ብድግ ይላል:: ፎቶው ሦስት ምስሎችን ይዟል:: አንድ - እራሱ፣ ሁለት - ሚስት፣ ሦስት - ጓደኛው:: ጓደኛው ታሪኩ ጥቅሻ በሚመስል ሁኔታ ሚስቱን ሲያይበት በፎቶው ውስጥ አየ:: ተበሳጨ:: ፎቶውን ሸረካከተው:: ሚስቱ ቀና ብላ አየችው:: እያያት ነበር:: ፎቶውን ቀዳዶ ካደቀቀው በኋላ እሳት ውስጥ ጨመረው::

የሚጨቃጨቁበት ጉዳይ በእሷ ድል አድራጊነት እስካልተጠናቀቀ ድረስ ተውኔቱ እንደሚቀጥል ሁለቱም ያውቃሉ::

ተሸንፋ አታውቅም::

ቴዎድሮስ ምሬቱን ቀጥሏል::

"‹ቴዎድሮስንም ውደጂው!› በላት:: ሰው ሲወደኝ ደስ አይላትም:: 'የአባቱ ልጅ ነው› ብላ ለሰው ትናገራለች፤'ላስቅሽ ነው ተዘጋጂ!' ብዬ ጓደኞቼ የነገሩኝን ቀልድ ልነግራት ስል፣ 'ሞዛዛ!' ብላ ሌላ ሌላ ቦታ ታያለች:: አትስቅልኝም:: ለሌላ ሰው ያሳቀው ነገር ስነግራት፣ 'ቀልደህ ሞተሃል! ሂድ ሱቅ ሂድና ስኳር ግዛ' ትለኛለች:: ‹ውደጂኝ!› ብዬ አልቅሼ፣ እግሯ ስር ወድቄ ስለምናት፣ 'አመለኛ ነህ፤ቀናተኛ ነህ' ትለኛለች:: ከአቤል ጋር እየተሳሰቅን ስንጫወት፣ 'ያንተ ከፋት ይበቃናል፤ ተንኮል አታስተምረው!' ትለኛለች:: አቢ ተጣላት፤ 'ቴዎድሮስዬን ለምን ታበሳጭዋለሽ? አንቺ ያልወለድሽው ይመስል' በላት::አንተ ግን ለምን ከእኛ ጋር አትኖርም፤ ሩቅ አገር መሄድ ምን ያደርግልሃል? እኛ ቤት ኑር...እ? ስታመም ሐኪም ቤት ትወስደኛለህ"

አባትየው አሁንም ሃሣብ ላይ ነው:: የልጁና የሚስቱን ነገር መለስ ብሎ እያስታወሰ::

የቴዎድሮስ ስም በአባቱ ድምጽ ተሰማ ማለት የእናትየው ጆሮ ይነቃል::

'አቤት!' ይላል፣ ባለበት ሆኖ:: ወዲያው ቀልጠፍ ፈጠን ብሎ፣ አባቱ ፊት ቆሞ፣ 'መጥቻለሁ አቢ! ይኸው...' ይላል፣ አቋቋሙን እያሳመረ::

እናቱ፣ 'ጅል! የሰው ጅል! መጥቻለሁ ይላል እንጂ መምጣትህን እያየ አይደለ? ለዐይነ ስውር እንኳ የማይባለውን!'

አባት፣'ተይ እንጂ ልጅ እኮ ነው' ይላል፣ ከኪሱ ብርቱካን አውጥቶ ልጦ እያጐረሰው::

'ልጅን ስርዓት ማስያዝ በልጅነቱ ነው! ተጣምሞ ያደገ ችግኝ ከመሆኑ በፊት...' ትላለች፣ የአቤልን ፀጉር እየደባበሰች::

አባት ይህን የአደጋ ጥሪ ደወል እንደሰማ፣ 'ሂድ ወደ ጓዳ!' ይለዋል - ቴዎድሮስን፣ 'ከወንድምህ ጋር ተጫወት:: ወደ ጓዳ ይዘኸው ሂድ...'

ቃላት አያስፈልጉም:: ተግባብተዋል:: 'ጥሩ አይደለም፤ የምታደርጊው ነገር!' አላት አንድ ቀን፣ 'ልጅን መጨቆን ደግ አይደለም፤ አንቺ ነሽ ያልፈጠረበትን ስሜት በውስጡ የምታሳድሪበት!'

'ይመስልሃል? ሳያመው ይተኛልኮ! ሳይታመም እናቴጋ ውሰዱኝ ይላልኮ! ተመልከት እንግዲህ፣ የሚጥል በሽታ ስላለብኝ ትምህርት ቤት አልሄድም የሚል ህጻን ነው! አውቆ እየተፈጠፈጠ...መሃል አስፋልት ላይ እየተዘረረ?'

'ሆን ብሎ የሚወድቅ ሰው የለም:: በዚያ ላይ የአስር ዓመት ሕጻን!'

'የነገረኝ ሐኪሙ ነው እኮ:: እኔማ ደንግጬ ነበር:: ወንድሜ የሚጥል በሽታ አለበት አይደል? እናም ቴዲም በዘር የተላለፈበት መስሎኝ...እሱ ግን የወንድሜን ሁኔታ አይቶ ሲነሳበት እንዴት እንደሚዝለፈለፍ አይቶ፣ ኧረ ምኑ ይነገራል የዚህ ልጅ ጉድ! ሰው በገዛ እጁ ሳይታመም ታማሚ ይመስላል?'

'እያስመሰለ ነው ያለሽ ማን ነው?'

'ሐኪሙ ነዋ! ፍቅር አትንሱት:: እንዲህ ዓይነት ፀባይ ያመጣው እንክብካቤ ለማግኘት ፈልጎ ነው አለኝ!'

'ውነቱን ነው፤ ልጄን መንከባከብ ትተሻል...'

'ጡት አላጠባው ከዚህ በላይ! ወንድሜ ሲነግረኝኮ አላመንኩትም ነበር:: ወንድሜ የሚጥል በሽታ በተነሳበት ጊዜ እንዴት እንደምንከባከበው ዓይቶ ቀና! ክፉ! የሰው ክፉ! ከዚያ ብቻውን ይለማመድ ጀመረ! አወዳደቅ አሳየኝ ይለው ነበር አሉ ወንድሜን - አንተ እንደወደቅህ በሰዎች መሐል ስወድቅ ዐይኔ ይገለባበጥብኛል፤ምላሴም ተጐልጉሎ ይወጣልኛል፤ ግን አረፋ መድፈቅ አልቻልበትም፤አረፋ የሚደፈቅልህ እንዴት ነው? ይለዋል አሉ'

'በቃ አትንገሪኝ...'

'አሁን ይሄ ምኑ ነው ቴዎድሮስ? ርጉም! የተረገመ ዘር! ቃኤል ነው ይሄ! ቤቴ ውስጥ ጦርነት የከፈተ...'

አባት ይህንና ይህንን የመሳሰሉ ምልልሶቹን አስታውሶ ትካዜ ተጫጫነውና መጠጥ ቤት መሄድ አስፈለገው!

ሕጻኑ ቴዎድሮስ አሁንም የደረሰበትን ከመተረክ ወደኋላ አላለም:: "የሚያስቅ ነገር ስነግራት አትስቅም:: ሲያመኝ አታለቅስልኝም:: ሐኪም ቤት አትወስደኝም:: ውሃ ታስጠጣኛለች ፀበል ነው ብላ:: ደግሞ አንተ ስትመጣ ስትመጣ ሽርሽር አትውሰደኝ:: እኔን ለብቻዬ አታንሸራሽረኝ፤ ብቻዬን ካንሸራሸርከኝ አንተ የሌለህ ቀን አቤልን ኬክ ቤት እየወሰደች ብዙ የሚጣፍጥ ነገር ታበላዋለች:: ብቻዬን አትውሰደኝ:: ማሚ አቤልን ብቻውን ኬክ ቤት እንዳትወስደው!"

ቀና አለ ልጁ:: ቡና ቤት ደጅ ደርሰዋል! አባት ልጁ እየተከተለው መሆኑን ረስቷል:: ቴዎድሮስ ወደ ቡና ቤቱ ለመግባት አመነታ! ለእናቴ ሰው ቢነግራትስ፣ ሰው ቢነግርብኝስ? አለ::

አባትየው ብቻውን ገባ:: ብቻውን የመጣ መስሎታል::

ልጅ ደጅ ላይ...

አባት ቢራ ጠጥቶ ጠጥቶ... ከቡና ቤት ሲወጣ...

ልጁን ደጅ ላይ አገኘው::

"ቴድሮስ!"

"አቤት አባቴ... "

"ምን ትሠራለህ?" አለው፣ 'አቢ' የሚለውን የቁልምጫ ስሙን ለምን ወደ 'አባቴ' መቀየር እንደፈለገ ግራ ገብቶት፣ "ምን ትሠራለህ?"

"ምንም"

"ከማን ጋር መጣህ?"

"ካንተ ጋር..."

አባት ትዝ አለው::

ቴዎድሮስ ያሳሰበው ሌላ ነገር ነበር:: "ለማሚ ቡና ቤት ወሰድኩት ብለህ እንዳትነግራት!"

"ምንም አላደረግሁልህምኮ ልጄ!"

"በእሷ ፊት ልጄ አትበለኝ:: ‹ምን ማለት ነው፤ያንተ ያልሆነ ልጅ ወልጄ አውቅ ይመስል!› ትልሃለች..."

አባት ኪሱ ውስጥ ያኖረውን ሲጋራ አወጣ:: አጭሶ የማያውቀውን ሲጋራ:: ሊያጨሰው ነበር የገዛው:: ይህ ሲጋራ የሚስቱን አመል ቀይሮበታል:: ሚስቱ የቀድሞ ፍቅረኛዋን የምታስታውስበት ነው:: ቤቱ ውስጥ ጦርነት የቀሰቀሰ ነው:: ሚስቱ 'ልጅ' ይዛ የመጣችው በሲጋራ ሱስ አሳብባ ነው::

'ደስ የሚላት ከሆነ አጨሳለሁ!' ብሎ ነበር የገዛው:: አጭሼው ልጭስ ብሎ! አሁን ግን ...

ይህ ሲጋራ...የሚስቱን ጡት ቢያቃጥልበት...ወይም የአቤልን ግንባር ቢያተኩስበት ተመኘ:: ብቻ አንድ ጠባሳ ፈልጓል:: በአንድ ሰው አካል ላይ...በታየ ቁጥር የሚታወስ!

ወደ ቤት እየተጠጉ ነው...

"ተጣላት! አኩርፋት:: ለምንድነው ሳናግርህ የማታነጋግረኝ ስትልህ 'ቴዎድሮስን ለምን ታበሳጭዋለሽ? አንቺ ያልወለድሽው ይመስል!' በላት:: እናንተ ከተጣላችሁ በኋላ፣ የሚያጨሰው ጓደኛህ ሲመጣ ‹ሁለቱን አስታርቃቸው፤ እናትና አባቴን አስታርቃቸው !› ብዬ አልቅሼ እለምነዋለሁ:: ከአባቴ ጋር ስትጣሉ እናቴ አስታርቃችሁ አልነበረም ወይ አንተ ተራህን አስታርቃቸው እለዋለሁ...አንተም ከእንግዲህ እኛ ጋር ኑር:: ስታመም ታዝንልኛለህ...በወላጆች ቀን አብረኸኝ ትሄዳለህ:: ስሸለም ታጨበጭብልኛለህ!"

አባቱ ሲጋራውን እንደያዘ ነው:: እሳት ያልላሰ ሲጋራ:: አፍ ያልጐረሰው ሲጋራ...

ከብሪቱ ኪሱ ውስጥ ነው...

የቤቱን ደጅ ማንኳኳት ጀመረ:: ዘወር ሲል ቴዎድሮስ የለም:: ዘወርወር....

የለም:: የት ሄደ?

"ቴዎድሮስ!"

"አቤት አቢ!" አለ፣ በሹክሹክታ:: አጥር ጥግ ተቀምጧል:: አጥፍጥፍ ብሎ::

"እሱ ውስጥ ምን ትሠራለህ?"

አሁንም በሹክሹክታ፣ "አንተ ከገባህ በኋላ እገባለሁ:: አንድ ላይ ከገባን፣‹ምን ስታቶሶቱሱለት ነበር?› ትለኛለች፤ ‹መቅናት ብቻ ነው የምታውቀው› ትለኛለች:: ያንሸራሸርከኝ መስሏት፣ አንተ ሩቅ አገር ለሥራ ስትሄድ አቤልን ኬክ ቤት ታመላልሰዋለች፤ አውቃ ታስርበኛለች...አሁን አንተ ወደ ቤት ግባና አንተ ከገባህ በኋላ እኔ እገባለሁ!"

"እ?"

"አውቃ ታስርበኛለች፣ ለብዙ ሰዓት ታስርበኛለች"

የተዘጋው በር ተከፈተ:: በሩን የከፈተችላቸው ሠራተኛዋ ናት::

ሶፋ ላይ ባለቤቱ ከአቤል ጋር እየተላፋች ነው::

አባት ወደ ቤት እንደገባ፣ፍም የተከመረበትን ምድጃ አየ::ምድጃውን በርግጫ መታው:: ሚስት በድንጋጤ ብድግ ብላ ስታየው በጥፊ አጮላት:: ሕጻኑንም በርግጫ:: ከጥቂት ደቂቃ በኋላ...

የአምቡላንስ ድምጽ ሰፈሩን በፍርሃት ያርደው ጀመር::

የቴዲ አባት...የአቤል እናት....ታሪኩ...ባልና ሚስት!

*'ጨዋታው ፈረሰ፤ ዳቦ ተቆረሰ!*

.....

# የእኛ ክፍል ልጆች

## (የአማርኛ አስተማሪያችን ስለ ስርአተነጥብ ያስተማረን ለታ)

ይኼኛውን ተርም የመዝለል ሃሳብ ነበረኝ፡፡ ሰሞኑን ለመማር በማያነሳሱ ምክንያቶች ተውጫለሁ፡፡ የመነጠልና የመሰደድ ፈረስ ሲጋልብብኝ ሰንብቷል፡፡ የእኔ በምላቸው ሰዎች ያዳመጥኳቸው ቃላት ያሣምሙኝ ይዘዋል፡፡ እና የትላንትናውን ዓይነት ሰው መሆን አቅቶኛል፡፡ የኛ ክፍል ልጆች ሻይ ቡና ለመባባል ሲጠራሩና፣ 'ትንፋሽ እንለዋወጥ' ብለው ድራፍት ሲገባበዙ እኔን ርዕሰ ጉዳይ ማድረግ አብዝተዋል፡፡

ዛሬ ክፍል የመጣሁት ደመና ያጠላበት ስሜን ለማደስና ፀሀይ እንዲወጣበት ለማድረግ አይደለም፡፡ መግደላዊትን አይቼ፣ በፈገግታዋ ፀሀይ ለመሞቅ ነው፡፡ ሲገርም! ሰው እንዴት የሚነቅፈውን ሰው በመናፈቅ ይሰቃያል? በትክክል እንደማፈቅራት የሚገባኝ እንዲህ ባለ ጊዜ ነው፡፡ እንደምትወደኝ ትነግረኛለች፤ እንደምትጠላኝ እርግጠኛ እንድሆን የሚያስችሉ ነገሮች ደግሞ ታደርግብኛለች፡፡ እንደምታከብረኝ ትነግረኝ ነበር፡፡ ግን በእሷ ልክ የሚያብጠለጥለኝ እስከዛሬ ድረስ አልተወለደም፡፡ ቢሆንም እወዳታለሁ፡፡

እኔና እሷ የምንተዋወቀው እዚህ አይደለም፡፡

እኛ ልኳንዳ ቤት ሥጋ ልትገዛ ትመጣ ነበር፡፡ ያኔ በትርፍ ጊዜዬ፣ ገንዘብ በመቀበልና ደንበኞቼን በማግባባት አባቴን አግዘው ነበር፡፡

የተግባባነው እዚያ ነው፡፡

ብዙ ነገር ከራሴ ጋር እያወራሁ ሳለ መምህሩ ገባ፡፡ የአማርኛ መምህር፡፡ ይኼ መምህር የሚሞቀኝም የሚበርደኝም ዓይነት አይደለም፡፡ ዛሬ የመጣሁት

መግደላዊትን ለማግኘት ነው:: የኔይቱን ማርያም:: አንድ የክፍል ጓደኛዬ፣ መግደላዊት አውርታቸዋለች የተባሉ እልፍ አእላፍ አሉባልታዎችን እየዘረዘረ ነገረኝ:: ዝም ብዬ ሰማሁት:: የሰማሁት ለእኔ ለማውራት ያነሳሳው ምክንያት ምን እንደሆነ 'አርቆ ለማሰብ' ነበረ:: አርቆ አሳቢ ቅርብ አዳሪ:: የመግደላዊትን ስም አነሳልኝና፣ 'ባታውቅ ባይገባት እንጂ፣ በእጅ ያለ ወርቅ መዳብ ሆኖ ነው እንጂ አንተ እኮ ክርስቶሷ ነህ!' አለኝ:: ደነገጥኩ:: ምን ለማለት ፈልገህ ነው? እስከለው አልጠበቀም:: 'ሰው ሁሉ ሲንቃት፣ ሰው ሁሉ ሲርቃት፣አዳሜ ሲጥላትና ሲያብጠለጥላት አንተ ግን አቀረብካት!' አለኝ::

እንዲህ በማለቱ ደስ አላለኝም:: ከአጠገቡ ለመራቅ ብዙ ጊዜ አልፈጀብኝም:: ሲያሳንሷት መስማት ደስ አይለኝም::

ያውና! የተቀመጠው አጠገቧ ነው:: በወዳጅነት መንፈስ ሲያወጋት ይታየኛል:: አሳዘነችኝ:: ልኳንዳ ቤት የተሰቀለ ሥጋ መስላ ታየችኝ:: እኔ ምንም የሌለኝ፣ እሷን በመጕምጀት የምሰቃይ ሥጋ አፍቃሪ ነኝ:: የጐመጀለትን ሥጋ በእጁ ማስገባት የሚችለው ባለገንዘብ ብቻ ነው::

መግደላዊቴ! በአራጆቿ ተከብባለች:: ሥጋዋን በመቁረጥ ይረካሉ:: የቆረጡትን ሥጋ አጉርሰውኝ ያውቃሉ:: የመቆሸሽ ስሜት እንዲሰማኝ ካደረጉኝ ነገሮች መካከል አንዱ ይሄ ነው::

ይኸው! አሁን እንኳን ሳስበው ያቅለሸልሸኛል::

መምህሩን አየሁት:: 'የአማርኛ ስርዓተ ነጥቦች አጠቃቀም' ብሎ ጻፈ:: ስርአተ ነጥቦችን በመደዳ ደረደራቸው:: ምልክቶቹን ማየት ብቻ አደከመኝ::

. ፡ ። ፣ ? ! ፤ ¡ ፦ ...

መግደላዊት ደብተሯን ገልፃ መጻፍ ጀምራለች:: ወደ እኔ አታይም:: ወደ እኔ ማየት ያልፈለገችበት ምክንያት ሂሩት አጠገቤ ስለተቀመጠች አይደለም:: ሂሩትና እኔ በተለየ ዐይን መተያየት እንደጀመርን መወራት ከተጀመረ ብዙ ወራት አልፎታል:: እኔ ግድ የለኝም:: እሷም ስሜት አልሰጣትም:: ሂሩትን ጠንቅቄ አውቃታለሁ::

በእኔና በሂሩት መካከል ተፈጥሮ ስለነበረው ፍቅር ተኮር እንቅስቃሴ ለመግደላዊት የነገረቻት ኤልዛቤል ናት። ኤልዛቤልን አለማመን እንዴት አስቸጋሪ ነው? ፈገግታዋ ይቆሰቁሳል። ሣቋ ነገር ያስፈለፍላል። ኤልዛቤል ዐይኗ ውስጥ ጥልቅ ጉድጓድ አለ። ትላንት የአርቆ አስተዋይነት ምልክት ይመስለኝ ነበረ። አሁን አሁን ግን ዐይኗ ውስጥ ያየሁት ጥልቅ ጉድጓድ ኩሬ እንደሆነ ይገባኝ ጀመረ። ኩሬው ወሬ ነው። ወሬያችንን እያነሳን ዐይኖቿ ውስጥ እየደፋን ጉድጓዱንም ያሰፋነው፤ጉድጓዱን የሞላነው እኔና ሂሩት ነን።

ከብዙ ወራት በፊት፣ ኤልዛቤል ከሂሩት ጋር የመሳሳሜን ዜና ነገረቻት። ያኔ፣ እንዲያ ያደረግሁት በሴት ላይ ሴት የመደረብ ሱስ ተፀናውቶኝ አልነበረም- በእኔና በመግደላዊት መካከል የነበረው ፍቅር የሞተ መስሎኝ ስለነበር እንጂ! እኔን የማትፈልግበት ምክንያት ከእኔ በፊት ለሌሎች ማውራቷ እጅጉን አበሳጭቶኝ ስለነበርም ጭምር። እንዳደርጋቸው ከማትፈልጋቸው ነገሮች መካከል አንዱ ከሂሩት ጋር የነበረኝን ጓደኝነት ማቋረጥ ነበርና ይለይላት ብዬ ያወጣችብኝን ህግ አስገድጄ ደፈርኩት። በእኔ ውስጥ ያደረ መንፈሷን አስቆጣሁት።

ሂሩትን ሊፍት ውስጥ አገኘኋት።

ሳምኳት፤ ሂሩትን ሳምኳት። እናም በሁለታችን መካከል አዲስ ክብሪት ተጫረ። ሙቀት ተረካከብን። አንድም ልጅ እንዳልወለደ፣ ክረምት እንደሚጫወትበት አረጋዊ ሆኜ ነበር ...

- ትሻልን ፈትቶ ትብስን አገባ አሉ አንዳንዶች።

ገና የጣድነው የፍቅር ድስት በወሲብ ፍም ለብ ማለት ሳይጀምር ሂሩት ለኤልዛቤል እንዲህ አለቻት።

'ማዘጋጃ ሄደን ተፈራረምን። ከአባቴ ገንዘብ ወስጄ ሉኳንዳ ቤታቸው አጠገብ ከትፎ ቤት ልንከፍት ነው!' የመሳሰሉት ጭራም ቀንድም የሌላቸው በሬ ወለደ አሉባልታዎች።

ሂሩት ስሜን ከስሟ ጋር ሰፋችው። ሥራዋ ያልኖርነውን ህይወት መተረክ ሆነ።

“አንዴ ዝም በሉ!” የሚል ድምጽ ከሄድኩበት የቁጭት ዓለም መለሰኝ:: የኛ ክፍል ልጆች መንጫጫት ጀምረው ነበረ:: ተማሪዎቹ ወደ እኔ ያያሉ:: የአንዱን ዐይን ስሸሽ የሌላው ይቀበለኛል:: ከሌላው ስሸሽ ለሌላ ዐይን አሳልፎ ይሰጠኛል:: ለመንጫጫትና ለመጪጪህ ያነሳሳቸው ምክንያት ምንድነው? ለምን ወደ እኔ ያያሉ?

“ዮናስ!” አለኝ፣ መምህሩ::

አቤት አይደል የሚባል? ግን ጠፋብኝ::

“ስምህ ዮናስ ነው አይደል?”

“ነው” አልኩት::

የእኛ ክፍል ልጆች እኔን ያዩኛል:: ሳስበው በነነዌ ዘመን ያለሁ መሰለኝ:: ትምህርት ቤቱ ባህር መስሎ ታየኝ:: ክፍላችን ደግሞ ማዕበል የሚያንገላታው መርከብ:: ከተማሪዎቹ አንዱ ማዕበሉ የተነሳው በእኔ ሰበብ እንደሆነ ሊነግረኝ ተዘጋጅቷል:: የአብዛኛው ተማሪ ዐይን እየከሰሰኝ ያለ ይመስለኛል:: የፍቅርን ህግ የጣሰ፣ የአምላኩን መንፈስ ያስቀየመ አንድ ሰው እነሆ በእዚህ ክፍል አለ! እየተባባሉ እንደሆነ እገምታለሁ:: ለአንዳንዶቹ እኔ እንደ ነብዩ ነኝ:: ነብዩ ዮናስ:: ያለፈውን ሴሚስተር እንደጨረስን ጸሎት ላይ ነበር የሰነበቱት:: ዛሬ ክፍል ውስጥ መግባት ብጀምር፣ዕጣ ተጣጥለው፣ወደ ባህሩ ሊወረውሩኝ ተሽቀዳደሙ::

አዎን፤ ወደባህር ሊወረውሩኝ ነው፤ ባህሩ ከመናወጽ ፀጥ እንዲል:: ዓሣ ነባሪ እንደሚውጠኝ አውቃለሁ፣ ቢሆንም ሞትን አልፈራም::

ሦስት ቀንና ሦስት ሌሊት ምን አላት? ከአሣ ነባሪ ሆድ እንደወጣሁ ለውዴ እገለጣለሁ:: ያኔ ቀድሜ የማየው መግደላዊትን ነው::

ሞት አያስፈራኝም...

"ዮናስ!" አለኝ መምህሩ:: ከመቸው ወደኔ መጣ? እነዚህ ተማሪዎች ለምንድነው ተራራ ስወጣ የሚከተሉኝ? ወይስ ስቀለው ለማለት ነው? ሊተፉብኝና ሊዘባበቱብኝ?!

"ዮናስ!"

"አቤት..."

"እስኪ አንድ ምሳሌ ስጠኝ?"

"ለምኑ?"

"ስለ አራት ነጥብ አጠቃቀም እያስረዳኋችሁ ነው:: እና እስኪ አንድ ምሳሌ..."

ዐይኔ መግደላዊት ላይ ተወረወረ::

"እስኪ አንድ ምሳሌ..." አለኝ::

ድምጼን አጥርቼ፣ "ከትናንት ይበልጥ ዛሬ እወድሻለሁ፤ የነገውን ያህል ግን በጭራሽ ሊሆን አይችልም::" አልኩት:: ዐረፍተ ነገሩ እንደረዘመ አውቃለሁ፤ ቢሆንም...

ሌሎች ተማሪዎች የሚያቀርቧቸው ምሳሌዎች - ከአበበ በሶ በላ - ከጫላ ጩቤ ጨበጠ ዓይነት ዐረፍተ ነገሮች ብዙ የዘለሉ አልነበሩምና በአመላለሴ ተማሪውም ሆነ መምህሩ ተገርመዋል:: እኔም ዐረፍተ ነገሩን የሠራሁት እግረ መንገዴን ለመግዲ መልዕክት ለማስተላለፍ ነበር!

"ሌላ ምሳሌ..." አለ፣ መምህሩ::

አንድ እጅ ከፍ አለ::

መግደላዊት ናት:: "ዶሮን ሲያታልሏት በመጫኛ ጣሏት" አለች::

በፍጥነት መልስ ስለሰጠችኝ ደስ ብሎኛል። ግን ደግሞ እንደ አታላይ መቆጠሬ አስከፋኝ። እንደማላወቃት ሆኖ ነው የሚሰማት። እኔ ደግሞ እንደማታውቀኝ አውቃለሁ። እንድንፈላለግ ያደረገን ምን እንደሆነ ግራ እስኪገባኝ ድረስ።

ከአንድ ወር በፊት...

ኤልዛቤል ባለችበት - አንድ ካፌ ውስጥ - እኔና መግደላዊት ተወያየን። አስቸኳይና አጣዳፊ ስብሰባ እንደማለት። ያ ቀን ኤልዛቤልን አወቅኋት። መግዱ፣ 'እኔ እና አንተ በአንድ ቋንቋ እያወራን ጭራሽ መግባባት ስላልቻልን ዛሬ በሦስተኛ ሰው ፊት ነው የምናወራው' አለች። 'እኔ እና አንተ ስናወራ ኤልዛቤል ብትኖር ይከፋሃል?' አለችኝ፣ ተረጋግታ።

'ችግር የለም' አልኳት፣ ምን ዓይነት ድራማ እየተቀነባበረ እንደሆነ እያሰብኩ። ጀመረች። ያነሳችው ነጥብ ባጭሩ ማጠቃለል ይከብዳል ግን...

ባጭሩ በእኔ እና በሂሩት መሀከል በአንድ ወቅት ስለተፈጠረው ግንኙት አወጋን። በተጨማሪም፣ 'ከተለያየን በኋላ፣ እኔ አንተን አትተወኝ እያልኩ አላስቆም አላስቀምጥ ብዬህ አውቃለሁ ወይ?' አለችኝ። (አዎን አልኩ ለራሴ አዎን። ቻው ብላ ካሰናበተችኝ ከብዙ ቀናት በኋላ አልቅሳ እንደለመነችኝ አስታውሳለሁ። 'አንተም የኔ ሁን፣ እኔም የአንተ ብቻ፤ በፍቅር እንኑር ፀንተን በጋብቻ፤ እከተልሀለሁ እስከ አለም ዳርቻ!' የሚሉ ስንኞች ያሉበት ግጥም ቋጥራልኛለች። ሆኖም ይህንን በኤልዛቤል ፊት መናገር መግደላዊትን ማሳነስ መስሎኝ ዝም!) አንተ አይደለህ ወይ እየተከተልከ፣ በቀን አስር ጊዜ እየደወልከ የምትጨቀጭቀኝ፣ የምትረብሸኝ፣ሰላም የምትነሳኝ?› አለችኝ። እውነቷን ነው። ከቅርብ ጊዜ ወዲህ ግን እሷን የማይበት ዐይን ለውጬ ተራ ጓደኛዋ ለመሆን መሞከሬን እንደምን ዘነጋችው?

ይህ ከሆነ በኋላ አንድ የሚያናድድ ነገር ሠራችብኝ።

ስለተፈጠረው ስህተት ማሰብ እራስን ለንዴት አሳልፎ መስጠት እንደሆነ ስለሚሰማኝ ለሀሳቡ ጭንቅላቴን መዝጋት ይሻለኛል። ይህን ታሪክ የተሟላ ለማድረግ ግን፣ ማንም አፍቃሪ ፍቅረኛው ባታደርግበት የሚመርጠው ነገር ከዚህ በታች ባሉት ክፍት ቦታዎች ቢያስፍር ቅር አይለኝም።

መምህሩ ስሌዳውን በብዙ ምሳሌዎች አዥጎርጉሮታል፡፡

"እሺ ሌላ ምሳሌ..."

አንድ ሰው እጅ አወጣ፡፡

መልሱን ግን አልሰማሁትም፡፡ ልክ እንደ ጥያቄው፡፡

መግደላዊት አወጣች፡፡

"አስቀድሜ ከወደድኩህ ውድ ይልቅ አሁን የጠላሁህ ጥል በለጠ" አለች፡፡

እጄን አወጣሁ፡፡

"ቂም በቀልን ለእኔ ተዉ ይላል የሰራዊት ጌታ እግዚአብሔር"
ኤልዛቤል ፈቃድ ሳትጠይቅ ምሳሌ አዋጣች፡፡

"ሃጥያተኛ ማንም ሳያሳድደው የገዛ ጥፋቱ ያሳድደዋል"

እኔም እጄን አወጣሁ፡፡

"የጥበብ ተሰጥኦ ያላቸውን ሴቶች መርዳት ደስ ይለኛል"

ከጐኔ የተቀመጠው ተማሪ ያልኩትን ዐረፍተ ነገር ከጻፈው በኋላ፣ 'መርዳት' በሚለው ቃል ላይ አሰመረበት፡፡ 'ር' የምትለዋን ፊደል በ'ብ' ቀየራትና፣ "ለማለት የፈለግከው እንደዚህ መሰለኝ" አለኝ፣ ሣቁ ተፈትልኮ ሄዶ መምህሩ ጆሮ እንዳይደርስ እየተጠነቀቀ፡፡

መምህሩ ለአራት ነጥብ በተሰጡ ምሳሌዎች የጠገበ ይመስላል:: የትምህርተ ስላቅ ምልክት ጻፈ:: አንገቱን ወደ እኔ ላከ:: ዛሬ ኮከብ ተሳታፊ ወጥቶኛል::

"አንቺን አግብቶ ከመኖር በየዕለቱ ሺህ ሽንፍላዎችን እንዳጥብ ቢፈረድብኝ ይሻለኛል¡"

ተማሪዎች ሣቁ::

መቸም በልባቸው ሂሩትን ሳይሆን አይቀርም ብለው እንደሚያስቡ ጥርጥር የለውም::

መግደላዊት ፊቷን አቆምጭጫ ስታየኝ አየኋት::

መምህሩ ያያት ይመስል፣ "ልብ በሉ፤ በትምህርተ ስላቅና በቃለ አጋኖ መሃከል ብዙ ልዩነት አለው" አለን::

ሂሩት፣ አጠገቧ ከተቀመጠችውና ዝናብ የዘነበባት ዝንብ ከምትመስል ጓደኛዋ ጋር የሆነ ነገር እየተጻጻፈች ነው:: ከዚህች ጓደኛዋ ጋር ሰሞኑን እንዲህ ተባባሉ አሉ::

'አንቺ የጓደኛሽ ፍቅረኛ የነበረውን ሰው ፍቅረኛ ማድረግ ነውር አይደለም ወይ?' አለቻት::

'አልፈልገውም፤ አይመጥነኝም፤ ትቼዋለሁ ብላ የነገረችኝ እሷ እኮ ናት'

'ተይ እንጂ?'

'ውነት! እንደፈለኩት አውቃ አይደለም ወይ በነፃነት እንዳፈቅረው የሚጐድልበትን ነገር አከፋፍታ የነገረችኝ'

'ቢሆንም የሰውን ባል...'

'እኔ የራሴን ፍቅረኛ ነው ያፈቀርኩት' አለች ሂሩት፣ የሰው ባል ወስደሻል ተብላ ስትጠየቅ የራሴን ባል ነው ያገባሁት ያለችውን ሴት አስታውሳ::

እኔና መግደላዊት በዚሁ ርእሰ ጉዳይ ጥያቄና መልስ ተለዋወጥን።

የእሷ ጥያቄ:-

'ከዚህች ልጅ ጋር መቅበጥ ፈልገሃል ልበል?'

የእኔ መልስ:-

'አንቺ አሻሮ ነው ብለሽ አጣጥለሽ የጣልሽኝ እኔን፣ እሷ ቆሎ ነው ብላ አንስታ ብትቆረጥመኝ ምን አለበት?'

.....

አንድ ቀን ለመግደላዊት ደወልኩላት፡፡

'ለምን ደወልክ?'

'ልጠይቅሽ ብዬ...' አልኳት፣ በቁጣ መሞላቷ ገርሞኝ፡፡ በዚህ አለም ላይ ሦስት ነገሮችን እፈራለሁ፡፡ በዕብድ እጅ ያለ ድንጋይ፣ ቀንዳም በሬና በሷ በኩል የሚደርሱኝ ቁጡ ቃላት፡፡

'ምንድነው የምትጠይቀኝ?'

'ዛሬ ክላስ አለ?...'

'አላውቅልህም፤ ደግሞ አትደውል፤ ጠልቼሃለሁ ከልቤ ጠልቼሃለሁ፤ አስጠልተኸኛል፤ ጥልትልት ነው ያደረግኩህ ...' አለችኝ፡፡

እውነትም፣ አንድን ሰው እንዴት እንደምንጠላው ለመግለፅ የምንጠቀምበት ድምጸት ነበር የተጠቀመችው፡፡

እንዴት እንዳልመጣልኝ አላውቅም እንጂ እንዲህ ብላት ኖሮ ብዬ አሰብኩ፡፡ 'ወድደሽኝ ታውቂ ይመስል ምንድነው ጠልቼሃለሁ ማለት?'

ሌላ ቀን ደወልኩላት:: ስልኳን ማንሳት አቆመች:: ዘጋችኝ:: ልቧንም፣ ዐይኗንም፣ እጇንም ቆለፈችብኝ::

ሂሩት ደግሞ ያለምንም ቁጠባ ያላትን ሁሉ ልትሰጠኝ ስትተጋ መግደላዊትን የማይባት መስታወት ሆነች:: መናፈቅ - መወደድ - መፈቀር ናፍቆኝ ነበር:: በአንድ እጅ ለማጨበጨብ መሞከር ሰልችቶኝ ነበር::

መግደላዊት ከእኔ ጋር ከተለያየን በኋላ፣ "ጓደኝነት መጀመር ያለብህ በዕውቀት ከኔ ከምትበልጥ ሴት ጋር ነው!" ያለችው ነገር አስቆኝ ነበር:: የኔ ልብ ከፍት የሥራ ቦታ የተለጠፈበት የማስታወቂያ ሰሌዳ ይመስላል እንዴ? ፍቅርን ፍቅር ያደረገው ሲቪ አይደለም፤ ፍቅርን ፍቅር ያደረገው ዲቪ አይደለም፤ ፍቅርን ፍቅር ያደረገው...

ቀና አልኩ:: መምህሩ ቀጥሏል::

መግደላዊት ለተጠየቀችው ጥያቄ እየመለሰች ነበር::

"ይሉህን በሰማህ፤ገበያም ባልወጣህ! አለችው ልጅቱ"

ሳስበው የቆየሁትን ነገር ያወቀችብኝና በልቧም፣ 'ድንቄም መወደድ' ብላ ሳታሽሟጥጠኝ አልቀረችም::

መምህሩ ምሣሌ እየጠየቁ ያሉት ስለትእምርተ ጥቅስ ምልክት አጠቃቀምን ነበር::

እጄን አወጣሁ:: ዕድሉ ተሰጠኝ::

"አንቺኮ አለመፈቀርን የተማርኩብሽ ሰሌዳዬ ነሽ' አላት፣ ቅስሙ ተሰብሮ" አልኩ::

መምህሩ ፈገግ አለ:: ትክ ብሎ ሲያየኝ ቆየና፣ "ዐረፍተ ነገሮችህን ከየት ነው የተማርካቸው? እንዴት ነው የምትቀምራቸው?" አለኝ::

"ምነው፣ ለምሳሌነት አይበቁም?" አልኩ፣ ለድንገተኛ ጥያቄ ያለኝ አማራጭ ርዕስ ማስቀየር ስለነበር...

"ይበቃል እንጂ - ይበቃል - እንዲያው ለነገሩ ያህል ነው:: እሺ ሌላ ...."

አንድ ሁለት ልጆች እጅ አወጡ:: መልሶቻቸውን አሰሙ:: እኔ ግን አልሰማኋቸውም:: እኔ አሁን መስማት የምፈልገው ራሴን ነው:: ራሴን እየሰማሁ ካልሆነ መግደላዊትን እየሰማሁ ነው ማለት ነው::

ሌላ ጥያቄ...

ለኤልዛቤል ዕድሉ ተሰጣት::

"በገባ በወጣ ቁጥር የአብነት አጎናፍር አትሂጂብኝ የሚለውን ዘፈን ይዘፍንላታል"

መምህሩ የኤልዛቤልን ምላሽ እንደሰማ ቀበል አድርጎ፣ "በዚህ ዐረፍተ ነገር ውስጥ የነጠላ ትምርተ ጥቅስ ምልክት የሚያስፈልገው ቃል የቱ ነው?" አለ::

ብዙ እጆች እንደ አንቴና ተመዘዙ:: ሁሉም በአንድነት መለሰ:: "'አትሂጅብኝ' የሚለው ቃል" አሉት::

ገብቶኛል:: እውነት ነው፤ ‹አትሂጅብኝ› የሚለው ዘፈን የእኔን ሕይወት የሚመስል ነገር አለው:: ነቀራ መሆኑ ነው:: ስታስጠላ!

የሴት አያቷ ልጅ ናት፤ቁልጭ እርሳቸውን:: እርግጥ በሁለት ነገር ይበላለጣሉ:: ሴት አያቷ ኤልዛቤልን በሃምሳ ዓመት ይበልጧታል:: ኤልዛቤል ሴት አያቷን፣ ስለ ስርዐተ ነጥብ ጥቅምና አገባብ በመማር ትበልጣቸዋለች:: ከዚህ ውጭ በሌላ ነገር አይበላለጡም::

ሁላችንም፣ ስለሷ ስናወራ ጭንቅላት ያላት ልጅ እንላለን:: ልክ ነው ጭንቅላት አላት:: ሂትለርም ጭንቅላት አለው:: ኢያጎም! የእሷ ጭንቅላት ግን የጭንቅና የላት ውጤት ነው:: ተንኮሎቿን በጭንቅ ትወልዳቸዋለች:: አሳዳጊ የበደላቸው ሆነው እንዳያድጉ ተንከባክባ ታሳድጋቸዋለች:: ከጭንቅ

በኋላ የሚመጣውን ላት ነው የምትወደው፡፡ ላት አይቶ የማይጐመጅ ደግሞ ጥቂት ነው፡፡

ኧይ ኤልዛቤል! ዳሌዋ...በእርግጥም ኤልዛቤል፣ጭንቅና ላት ያላት ልጅ ናት፡፡

ሰውን 'በልኳንዳ አራጅ ዐይን ነው የምታየው!' (ይህን አገላለፅ የማውቀው በማን ግጥም ውስጥ ነበር?)

እዩአት እንግዲህ - ምሳሌዋ ተቀባይነት ስላገኘ ስትፍነከነክ፡፡

እሷን ማየት አቆምኩና ወደ መምህሩ...

ካንቺ ጋር በተጣላሁ ጊዜ፣ 'ሲጋራ ማቡነን ጀምሯል፤ማተቡንም በጥሷል' ብለሽ አስወርተሻል አሉ -

ልበል ይሆን ብዬ አሰብኩ፤ አሰብኩና እጄን ሳወጣ -

"የምፈልገው አዲስ እጅ ነው!" አለ መምህሩ፡፡ ያወጣሁትን እጅ አወረድኩት፡፡ አዲስ እጅ ሲጠፉ ዐይኑን ወደኔ ወረወረ፡፡

"'ድንጋይ ነው ትራሱ፣ አሮጌ ነው ልብሱ፣ የኪራይ ነው ቤቱ ብለሽ አውርተሻል፤ እኔን በበረደኝ ምን አባሽ ቆርጦሻል?' አለ ድምጻዊው" በነጠላ ትምርተ ጥቅስ ውስጥ መግባት ያለበት የቱ እንደሆነ ጠየቅሁ፡፡

ሌሎች መለሱለት፡፡

መግደላዊት ሙሉ ልቧን ሰጥታኝ እየተከታተለችኝ እንደሆነ ተሰምቶኛል፡፡ ቀና አልኩ፡፡ እንዳጋጣሚ ሆኖ መምህሩ እያየኝ ነበር፡፡

"ጥያቄ አለህ?" አለኝ፡፡

"የለኝም!"

"ገብቶሃል?"

እንኳንስ ሊገባኝ ያለውንም አልሰማሁ::

"ገብቶሃል?" አለኝ፣ መልሶ::

"አዎ!" አልኩት፣ አፌ እንዳመጣልኝ::

መግደላዊት እጅ አወጣች:: እንድትናገር ተፈቀደላት:: "ጉረኛ!" የሚለውን ቃል ስንጠቀም ከቃሉ በኋላ ቃለ አጋኖ ብናስገባ ስህተት ይሆናል?"

እንዲህ ከማለቷ በፊት ልትል የምትችለውን ጠርጥሬ ነበር::

"በጭራሽ!" አለ መምህሩ፣ ሳያስበው ለቃለ አጋኖ የሚመች ቃል እየተጠቀመ::

መምህሩ በሥርዐተ ነጥብ ምንነትና አጠቃቀም ዙርያ መስጠት የሚጠበቅበትን ዕውቀት ሰጥቶ ጨርሷል:: "ጥያቄ ያላችሁ?" ማለት ጀመረ::
እጅ አወጣች::

"ቤተሰቦቼ አፍረውብሃል፤ ጓደኞቼ ታዝበውሃል፤ ልቤም ተቀይሞሃል - እነዚህን ሦስት ዐርፍተ ነገሮች የምናያይዛቸው በምን ዓይነት ስርዓተ ነጥብ ነው?" ብላ ጠየቀች::
የመለሰላትን አልሰማሁም:: ዐረፍተ ነገሮቿን እያብሰለሰልኳቸው ነበር::

እንደገና ሌላ ጥያቄ...ዛሬ አልተቻለችም::

"ያንተን ባህርይ በሦስት ልከፍለው እችላለሁ:: አንዳንድ ጊዜ ዕብድ ትመስለኛለህ፤አንዳንድ ጊዜ ደግሞ ሕጻን ትሆንብኛለህ፤ አንዳንድ ጊዜ ደግሞ የደብተራ ዓይነት ባህርይ አይብሃለሁ - እነዚህን ዐረፍተ ነገሮችንስ በምንድነው የምናያይዛቸው?"

ቁርጥ ያለ መልስ ሰጣት::

"በድርብ ሰረዝ"

መግደላዊትና ኤልዛቤል ሲያንሾካሹኩ ይታየኛል፡፡

ከእኔ ውጭ ሌላ ርዕስ ሊኖራቸው አይችልም፡፡ ሁለቱን አንድ ላይ ሆነው ሳያቸው ሁለት ነገር ይታየኛል፤ሁለት ነገር፡፡ ቢላዋ እና ሥጋ፡፡ የቢላዋ ተልዕኮ ሥጋን ቆርሶ ማሣነስ ነው፡፡ ኤልዛቤል ቢላዋ - መግደላዊት ሥጋን እየቆረሰች - እያሳነሰች - ሲያሻት ለቋንጣ ዘልዝላ - - ሲያሻት ጐረድ ጐረድ አድርጋ - ሲያሻት ለቅቅል- ሲያሻት ለጐመን በሥጋ ለሁላችንም ምላስ በሚስማማ መልኩ ስትከሽን ቆይታ ዘወር ብላ ደግሞ፣ 'እንዲህ ብለው ሲቦጭቁሽ ሰማሁ!' ትላታለች፡፡

"አንድ ሁለት ምሳሌዎች አምጡና የዛሬውን ትምህርታችንን እንቋጫለን" አለ መምህሩ፣ ወደ እኔ እያየ፡፡

-ይኸ መምህር ያለኛ በቀር ሌላ ተማሪ ያለ አልመሰለውም ልበል?

እጄን አወጣሁ፤ በአገጩና በዐይኑ የቀጥል ምልክት አሳየኝ፡፡

"እመኝኝ፤ የዋህነቴ በዝቶ አንቺን ስላሳነስኩ በጣም ተፀፅቻለሁ!"

ያልኩትን ሰሌዳ ላይ ጻፈው፡፡ ሁለቱን ዐረፍተ ነገሮች በድርብ ሰረዝ ሰፋቸው፡፡

ስለጥያቄ ምልክት ጠየቀን፡፡
ፈቃደኝነቱን ሳልጠይቅ ድምጼን አስገባሁ፡፡ "ለአምስት ደቂቃ ያህል አግኝቼ ሁሉንም ነገር ዘርዝሬ ባስረዳሽስ?"

- አጫጭር ዐረፍተ ነገሮችን የመጠቀም ልምድ ይኑርህ ዓይነት አተያይ አየኝ፡፡

ደብተሮቼን ማስተካከል ስጀምር፣አንድ ከጓደኛዬ የተዋስኩትን መጽሐፍ አገኘሁ፡፡ እዚህ መድበል ውስጥ አንድ፣ እኔ የጻፍኩት እስኪመስለኝ ድረስ ስሜቴን የነካኝ ግጥም አለ፡፡

*የተለየሽኝ - ለት፣*
*ጣሪያ አፈሰሰ*
*የተለየሽኝ - ለት፣*
*ምርጊቱ ፈረሰ*
*ሸንቁር ሆኜ ቀረሁ፣*
*ተሸንቆርኩልሽ*
*ገላዬ ተቀዶ፣*
*ብርዱን ለበስኩልሽ ...*

እያንዳንዱ መስመር፣ እያንዳንዱ ቃላት፣ የኖርኩት እስኪመስለኝ ድረስ ልቤን ስለነካው ገልብጬ ለምን አልሰጣትም የሚል ሀሳብ መጣብኝ፡፡

ግጥሙን ገልብጬ ስጨርስ ወረቀቱን አጥፌ፣አጣጥፌ፣ ፊት ለፊቴ ለተቀመጠው ሰው ሰጠሁት፡፡

'ለመግደላዊት' የሚል አለው፣ ወረቀቱ ፊት ላይ፡፡ የሰጠሁት ተማሪ ለሌላ ተማሪ ሰጠው፡፡ ሌላ ተማሪ፣ ለሌላ ተማሪ...እሷጋ ሊደርስ ሰባት ስምንት ሰዎች እጅ መሽከርከር ይጠበቅበታል፡፡

ሊደርሳት ጥቂት ደቂቃ ሲቀረው መምህሩ አየ፡፡ "እኔ እያስተማርኩ ወረቀት እየተጻጻፉ መቀባበል ምንድነው?" አለ፣ ከብዙ መነጫነጭ ጋር፡፡

ዝም፡፡

ተቀብሎ አነበበው፡፡

"መግደላዊት?"

"አቤት!"

አቤት ፍርሃቷ!

"ጉበዝና ጨዋ አልነበርሽ እንዴ?"

ዝም፡፡

"ቲቸር እኔ ነኝ" አልኩ፣ "እኔ ነኝ፣ ወረቀቱን ጽፌ የላክሁላት፡፡"

ቀምበር ከትከሻዋ አውርጄ እንደተሸከምኩላት ቆጥራ፣ ደስ ሲላት አየሁ፡፡

"ለምን?" ጠየቀ፣ መምህሩ፡፡

"ግጥም ውስጥ ስርአተ ነጥብ እንዴት እንደምንጠቀም ላሳያት ብዬ"

ወረቀቱን ገለጠው፡፡ በዝምታ ሲያነበው ቆይቶ ድምጹን ጨምሮ ማንበብ ጀመረ፡፡

*አገር እንቅልፍ ለብሶ፣*
*አገር እንቅልፍ ለብሶ*
*በፀጥታ ባህር በእንቅልፍ እየዋኘ፣*
*እኔ ግን ብቻዬን፣*
*ብቻዬን ሆንኩና፣*
*እንቅልፍ ባይኔ ሞተ፡፡*
*አኩለ ሌሊት ላይ ነፋሱን ጠራሁት*
*ዋሽንቱን ነፍቶልኝ*
*በፉጨቱ አባብሎ፣*
*እንቅልፌን ሊያመጣ*
*ከብቻነት ድባብ፣*
*ከናፍቆት በረሀ እኔን እንዲያወጣ*
*ተጣራሁ፣ ተጣራሁ፣ ተጣራሁ፣*
*ልቤን ማስተኛበት*
*መውሰጃ ጥግ አጣሁ፡፡*

"አንተ ነህ የጻፍከው?"

"አይደለሁም"

"ከየት ነው ያመጣኸው?"

ምንጩን ወረቀቱ ላይ ማስፈሬን ነገርኩት፡፡

“ምንጮ እንዲህ አይጠቀስም” አለኝ::

አጠቃቀሱን አስተካከሎ እንደገና ሰሌዳ ላይ ጻፈው::

እንዳለጌታ ከበደ፣**ልብ ሲበርደው**፣ፋር ኢስት ትሬዲንግ፣ 2001 ዓ.ም::

የመግደላዊትን ሣቅ ሰምቼ ነቃሁ:: ስትስቅ ፊቷ ቢጫ ይሆናል፤ መሬት ላይ እንዳፈረጡት እንቁላል:: ሣቋ በጭረቅ ይላል:: ይገርመኛል፤ ስትስቅ ደግሞ ጭኖቿን ግጥም አድርጋ ትይዛቸዋለች:: ግጥም በተለይ የሣቋ ምንጭ እኔ ሆኜ የተገኘሁ እንደሆነ:: ጭኖቿን ግጥም አድርጋ የመዝጋቷ ምስጢር ምን እንደሆነ አልጠየቅኳትም::

ብቻ፣ያ ቀን ማታ፣ ከክፍል እንደወጣን ብዙ ሣቆችና ብዙ ደጋግ ቃላት ተለዋወጥን:: ቅሬታዋን በፍቅር አባብዬ ገደልኩት:: የታባቱንና!

ራት በላን:: ወይን ጠጣን:: ወይን የጠጣች ቀን ደግሞ እኔ አሰኛታለሁ:: እና....

ኧይ ከዚያ በኋላ የሆነው ነገር ለሌላው ሲተርኩት አይደለም፤ለብቻ ሲያስቡት ነው ደስ የሚል!

—

# የወርቅ በርጩማውን ፍለጋ

የቋንቋ መምህርት ነኝ...

አንዳንድ ሰው፣ጥዋት ከእንቅልፉ ሲነቃ፣ ምላሱ ላይ የገባውን ዘፈን ቀኑን ሙሉ ሲያንጎራጉረው እንደሚውል፣እኔ ደግሞ ጥዋት በአእምሮዬ የሰረገ አንዳች ብሂል ወይም አገላለጽ አብሮኝ ውሎ ያመሻል:: ዛሬ ዳኛቸው ወርቁ ከጻፈው፣ ‹አደፍርስ› ልቦለድ መጽሐፍ ላይ ያገኘሁት አንድ አገላለጽ በውስጤ ታትሞ ቀርቷል::

*"...ያቺ በሌላዋ ሀገር የምትጣደፈው፣ የምትፍለቀለቀው፣ የምትንቦለቦለው ሕይወት እዚህ እፎይ ብላለች:: በእርጋታ፣ በዝግታ ታምማለች፣ በተገማሸረ መስክ ውስጥ እንደሚብሰከሰክ ውሃ..."*

ሰሞኑን ከምንጊዜውም በላይ ስለሀገር ጉዳይ ያሳስበኝ ጀምሯል:: ሆድም ይብሰኛል:: ሆኖም የብሶቴ ምንጭ ምን እንደሆነ አላውቅም:: ሠራተኛዬ ዘሪቱ ወደ ወላጆቿ ልትሄድብኝ ነው ብዬ ስለሰጋሁ ሳይሆን አይቀርም:: ወይም ደግሞ የታናሽ እህቴ ማለትም የአስቴር እጮኛ 'አሜሪካ ሄጃለሁ!' ይበል እንጂ ደቡብ አፍሪካ ገብቶ ቀበቶ በመሸጥ እንደሚተዳደር ስለሰማሁም ይሆን ይሆናል ... ወይም ደግሞ ባለቤቴ - ነፍሱን ይማረውና - ይሠራበት የነበረበት ድርጅት 'ለሟቹ ቤተሰቦች' ብሎ የሠጠኝ የገንዘብ ካሣ ምናባቴ አድርጌ የረባ ነገር እንደምፈይድበት ግራ ስለገባኝም ይሆናል:: ብቻ የሆነ ነገር ሆኛለሁ፤ ወይም ልሆን ነው::

ዘሪቱ ከሄደችብኝ ቤቴን ማን ቀጥ አድርጎ ይይዝልኛል?

ዘሪቱ እኔ ቤት በሠራተኛነት ተቀጥራ መሥራት ከጀመረች አራት ዓመት ሆኗታል:: ያኔ፣ አስቴር ወደ ቤይሩት ለመሄድ ጓዝ ጉዝጓዟን መጠቅለል በጀመረችበት ሰሞን ነው፣ ዘሪቱን ያገኘኋት፤ ያለተያዥም የቀጠርኳት:: አመንኳት፤ ታመነችልኝም!

‹ይህቺን መልከ ጥፉ፣ ይቺን ከጨለማ በባሰ ሁኔታ የጠቆረች ሴት ለሠራተኝነት የቀጠረችው ባለቤቷን ስለማታምነው ነው!› ተብሎ ተወራ፡፡

ባለቤቴ ሾፌር ነበር፡፡ በአንድ የግል ድርጅት ውስጥ ተቀጥሮ የሥራ አስኪያጁን መኪና ነበር የሚነዳው፡፡ ቆይቶ ግን ሁለቱም የመኪና አደጋ ይዟቸው ሄደ፡፡ ስለ አደጋውም ሆነ ሊሞት ሲል አይቼበት የነበረውን ስቃይ ላለማስታወስ ለራሴ ቃል ከገባሁ ሁለት ዓመት አልፎኛል፡፡

ጠመዝማዛውና 'እንኳንስ ሰው ዝንጀሮ አይወጣውም' የተባለለት የአላማጣ መንገድ ለስንቶች ሕይወት ማለፍ ተጠያቂ ሆኖ ይሆን? አለማሰብ ነው የሚሻለው!

ከወራት በፊት፣ የባለቤቴን የካሣ ጥያቄ ጉዳይ ዳር ለማድረስ ስሯሯጥ...መላ ሰውነቴ ውሃ ውስጥ እንደከረመ ሳሙና በተልፈሰፈሰበት ዕለት...

"እቴትዬ ..." አለችኝ፣ ዘሪቱ፡፡

"አቤት!"

"አንድ ነገር ባስቸግርዎት አይታዘቡኝም?"

"ምን ሆነሻል?"

"ለእኔ የእርስዎን ያህል ክብር ሰጥቶ የሚያነጋግረኝ የለም! ከዚህ ቤት ወጥቼ ሌላ ሥራ ባልጀምር ደስ ይለኛል፡፡ ግን የኑሮ ጉዳይ ሆኖ..."

"ይህ ሁሉ ዳርዳርታ ደሞዝ አነሰኝ ለማለት ነው?"

ደንገጥ ብላ፣ "ኧረ እቴትዬ ከፍያማ አያንሰኝም! ያሳሰበኝ ደሞዜ አይደለም፤ ታናሽ ወንድሜ ገጠር ከሚሆን እዚህ ሆኖ ቢሠራ ይሻለዋል የሚል ሃሣብ እየመጣብኝ ነው፡፡ እኔስ እስከመቼ ድረስ የሠራሁበትን ሁሉ - ጥቂት ብር ብቻ አስቀርቼ - ወደቤተሰቦቼ ልላክ?"

"የወንድምሽ ሥራ ምንድነው?"

"ምንም!"

"እንዴት ምንም?"

"ጊዜውን የሚያሳልፈው በአምልኮ ነው!"

"በአምልኮ?"

ምን ለማለት እንደፈለገች ታብራራልኝ ጀመር::

"አዎ! በተወለድኩበት አካባቢ መድረሻውን የማላውቀው አንድ የታወቀ ወንዝ አለ:: በወንዙ ውስጥ የአካባቢው ነዋሪ 'የዌራ አንደት' ብሎ የሚጠራት የተለየች ፍጥረት - ከአምላክ በታች ከሰው በላይ የሆነች ፍጥረት - ትኖርበታለች ይባላል:: አንዳንዶች የአካባቢው ነዋሪዎች ጊዜያቸውንና ገንዘባቸውን ወደ ወንዙ በመወርወር ይሰጧታል:: ከክፉ ነገር እንድትታደጋቸው፣ ከብቶቻቸውንም በውሃ ሙላት ከመወሰድ እንድትጠብቅላቸው አጥብቀው ይማፀኗታል፤ ከዓመት እስከ ዓመት ይገብሩላታል:: በየዓመቱ 'ለዌራ አንደት' ክብር ተብሎ በግ ይታረዳል:: በአዝመራ ጊዜ ነጭ ገብስ በስሟ ይዘራል:: ሰብሉ በደረሰ ጊዜ ከሌላ ጥሬ ጋር ሳይደባለቅ በጥንቃቄ ይቀመጣል:: የግብር ወቅት ሲደርስ 'ለዌራ አንደት' ይወሰድላታል:: ኧረ ብዙ ነገር ነው የሚደረግላት..."

"እና ወንድምሽ ይህችን ጣኦት የሚያመልካት ምን ለማግኘት ነው?" አልኳት፣ ራሷን ከእምነቱ ተከታዮች ለማራቅ የምታደርገውን ጥረት ከንግግሯ እየተረዳሁ::

"የወርቅ በርጩማ ለማግኘት..."

"አልገባኝም"

"ወንዙ ውስጥ ግዙፍ የሆነ የወርቅ በርጩማ አለ ብለው ነዋሪዎቹ ያምናሉ:: የቆየ ወሬ ነው:: ወንዙ እምብርት ላይ ሁልጊዜ የሚሽከረከር ነገር አለ:: የወርቅ በርጩማው እዚያጋ ነው ያለው ይላሉ:: በፊት ዋኝተው ገብተው በርጩማውን ለማውጣት የሞከሩ ነበሩ አሉ፤ምን ዋጋ አለው ሳይሳካላቸው ቀርቶ ሕይወታቸው አልፏል:: የታወቁ ዋናተኞችም ቢሆኑ አልሆነላቸውም! ከልቡ ያቺን ፍጥረት ያመለከ የወርቅ በርጩማውን ለግሉ ያደርገዋል ተብሎ ይታመናል!"

"ይሄማ ከኋለኞች ሁሉ ኋላ የሚያስቀር አመለካከት አይደል?"

"እንግዲህ፣ እንደዚያ ነው የሚያምኑት:: ወንድሜ ደግሞ የሁላችንም ሕይወት ሊለወጥ የሚችለው፣ በርጩማው በእጄ ሲገባ ነው ብሎ ያምናል:: የወገኖቹን የእጅ ሙያ ወርሶ ልክ እንደናቴ ወንድሞች መንቀሳቀስና ራሱን መለወጥ ሲገባው፣ በምኞትና በመጎምጀት ብቻ ጊዜውን ያቃጥላል! በዚያ ላይ በቅርቡ ማግባት ይፈልጋል"

"እና አሁን ምን አስበሻል?"

"እዚህ ይምጣ፡፡ እዚህ ይኑርና የከተማ ሰው ይሁን፡፡ እንደኔ የማታ ትምህርት ጀምሮ ቢያንስ ቁጥርና ፊደል ይለይ! የሥራ ሰው ይሁን...የቀን ሥራ እየሠራ ለራሱ ይወቅበት! እስኪደራጅ ድረስ ብዙ ጊዜ ስለሚፈጅበት ልረዳው እፈልጋለሁ፡፡ እና፣የአንድ ወር ደሞዝ ቅድሚያ እንዲሰጡኝ ነው የምለምንዎት..."

ደስ አለችኝ!

"ብርቱ ነሽ እኮ ዘሪቱ! እኔ ደግሞ አንቺን አግዝሻለሁ፤አይዞሽ!" አልኳት፡፡

አቤት! ያን ሰሞን ይሄ የወርቅ በርጩማው ነገር እንዴት መዝናኛ እንደሆነን? አስቴር ስልክ ስትደውልልኝ ይህንኑ ነገር ስነግራት፣ "አትቀልጅ! እውነታቸውን ቢሆንስ? ይልቁንስ መጥቼ ዕድሌን ልሞክር!" ስትል ቀለደች፡፡ ለእጮኛዋም ይህንኑ ጉዳይ ነግሬው ነበር፤ ግን ምንም ስሜት አልሰጠውም፡፡

እጮኛዋ ከወር በፊት፣ እኔ ወደማስተምርበት መለስተኛ ሁለተኛ ደረጃ ትምህርት ቤት መጥቶ፣ ‹ውጭ አገር ልሄድ ነው!› ነበር ያለኝ፤ ‹አሜሪካ....›

እንደዚህ ሲለኝ፣ መጀመርያ በብርቱ ደንግጬ ነበር፡፡ ‹እናንተ ልጆች ምን እየሆናችሁ ነው? አብዳችኋል? አስቴር ቤይሩት ሄደች፡፡ የተሻለ መኖር የሚያስችላችሁን አቅም ብናገኝ ብላ፡፡ አሁን አንተ ያለን ይበቃናል፤ ቀስ በቀስ እናድጋለን ማለት ሲገባህ አንተም ልብህ እንደ ጠበል ዕቃ ውጭ ማደር ይጀምር?› ብዬ ተቆጣሁት፡፡

አልሰማኝም፡፡

አስቴርና እጮኛዋ ከተማሪነት ዘመናቸው ጀምሮ አብረው ነበሩ፡፡ መለያየት የሚባል ዕጣ፣ አለመስማማት የሚባል ጣጣ በሁለታቸው መሃል መንገድ አልዘረጋም ነበር፡፡ አንድ ቀን ግን አስቴር፣ 'እቴት፣ ወደ ቤይሩት ልበር ነው፡፡ የምነግርሽ እንድታውቂው ነው፡፡ እና አሁን አንቺን እያማከርኩሽ ሳይሆን ውሳኔዬን እያሳወቅሁሽ ነው፡፡ ስለዚህ አለመሄድ እንደሚሻልና እዚህ ሀገር ሠርቶ መለወጥ እንደሚቻል በማሳመን እንዳታደክሚኝ' አለችኝ፡፡

'ቤይሩት? እሺ፤ መሄዱንስ እሺ ተሳክቶልሽ ትሄጂያለሽ እንበል፤መሄጃ ገንዘቡ ከየት ይመጣል አስቴር?'

'ለመሄጃ?'

'አዎ!'

'ጓደኛዬ ከወላጆቹ የወረሰውን ቤት አከራይቶታል:: ከእሱ እወስዳለሁ:: የምሄደው ደግሞ ለአንድ ለሁለት ዓመት ያህል ብቻ ነው:: ቶሎ ሠራርቼ እመለሳለሁ' አለች፤አለችና ብዙም አልቆየች ሄደች::

አፍታ ሳትቆይ የምትመለስ የምትመስለዋ ሴት ይኸው አራት ዓመት ሆናት::

አሁን ደግሞ እሱ...

በርግጥ የሚያናግረኝ ፈገግ ብሎ ነበር:: ያ ፈገግታ የእሱ እንዳልሆነ አውቃለሁ:: የእሱ አይደለም:: የእህቴ ነው:: ፊቱ ላይ እየተነበበ ያለው የራሱ ፈገግታ አይደለም! ከአስቴር የኮረጀው ፈገግታ ነው:: ኣ! ኣ! የአስቴርም አይደለም:: ያየሁበት የተሸነፈ ሰው - ማለት አሸንፋለሁ ብሎ በደጋፊዎቹ ፊት ሲፎከር የቆየ ሰው - ከፍተኛ በሆነ የነጥብ ብልጫ ሲሸነፍ ፊቱ ላይ የሚታይበት ዓይነት ፈገግታ ነው:: አስቴር ወደ ቤይሩት ልትሄድ ስትል ስለ ኢትዮጵያ ስታወራኝ የነበራት ዓይነት ፈገግታ...ተስፋ የቆረጠ - ሀፍረት የበዛበት ፈገግታ...እንደ ልቡ ለመሆን አቅም ያነሰው ፈገግታ!

‹እና ልትሄድ ነው፣ ወሰንክ?› አልኩት፣ የሚያወራውን በፅሞና ሰሰማ ቆይቼ::

‹አዎ! እስኪ ልሂድና ይገኘ ልምጣ!›

‹ምን?›

‹ያንን፣ የዘሪቱ ወንድም ከልብ የሚያመልከውን የወርቅ በርጩማ!›

ሀዘን የሞላው ፈገግታ ተለዋወጥን::

ወደ አሜሪካ ሳይሆን ወደ ደቡብ አፍሪካ መሄዱን ከሚያውቁት ሰዎች መረጃ ያገኘሁት ዛሬ ነው:: አስቴርንም እንደኔ ዋሽቷት ይሆን?

የተመላለስነውን ማሰላሰል ቀጠልኩ::

'የምሄደውኮ የአስቴርን ስቃይ ልቀንስላት ብዬ ነው:: አስቴር ትንሽ ሠራርታ እስከትመጣ ድረስ ምን ያህል ጊዜ ይፈጅባታል? አይታወቅም:: ለሁለት ዓመት በቻ ብዬ አስምዬ ሸኘኋት! ምላ ተገዘታ፣ ሆነልኝም አልሆነልኝም ባልከኝ ጊዜ እመለሳለሁ አለችኝና ሄደች:: ሄደችብኝ:: የት አለች ታዲያ?› አለኝ፣ በመነጫነጭ::

‹ወላጆቼ ናቸው:: እሷ ስትሄድ የችግር ቀዳዳዎቻቸው በእጥፍ በዙ...› አልኩት::

‹ታዲያ አስቴር ጫንቃዋ መሸከም ከሚችለው በላይ ጭነት እያረፈባት እንደሆነ እያወቅሁ ዝም ማለት እንዴት ያስችለኛል? ፍቅር ማለት ምንድነው? ለምን ዞር ዞር ብዬ እንጀራዬን የምጋግርበት ምጣድ ገዝቼ አልመለስም? የእኔ እጆች የተፈጠሩት ሌሎች ድል ሲያደርጉ፣ ሌሎች የአሸናፊዎች አሸናፊ ሲሆኑ፣ ሌሎች የሜዳሊያ ባለቤት ሲሆኑ እያጨበጨቡ እንዲኖሩ ብቻ ነው? እና መሄድ አለብኝ:: የመጣሁትም ልሰናበትሽ ነው› አለኝ፣ ሩጫውን እንደጨረሰ ሰው መታከት እየታየበት::

ይሂድ! እስኪ ይሂድና፣ ‹የወርቅ በርጩማውን› ይፈልግ::

ዛሬ ምን እንደነካኝ አላውቅም:: ቀንድና ጭራው የማይታይ፣ መያዣ መጨበጫ የሌለው ሀሳብ ሲፈታተነኝ አምሽቷል::

የዘሪቱ ነገር ...

ገጠር፣ እተወለደችበት አካባቢ ሄዳ በመጣች ቁጥር በቀርከሃ የተሠሩ ጌጣጌጦች ታመጣልኛለች:: ለቢላዋ ማስቀመጫ ... ለመመገቢያ ዕቃ ... ለልብስ ማስቀመጫ የሚሆኑ ዕቃዎች ... የወለል ምንጣፎች! የማታመጣልኝ የዕደ ጥበብ ውጤት የለም:: ‹እነዚህ ነገሮች ገጠር እናንተጋ ይሸጣሉ ማለት ነው?› ስላት፣ ‹አባቴ ነው የሚሠራቸው! ውሰጂላት ብሎኝ ነው› ትለኛለች::

አንጨቃጨቅም:: አንጨካከንም:: ወር ጠብቃ፣ ‹እትዬ ደሞዝ› አትለኝም:: ዓመት ሲሞላ እኔ ዘንድ የተጠራቀመላትን ብር ትቀበልና፣ አንዳንድ ነገሮች ገዛዝታ፣ ለቤተሰቦቿ ትወስድላቸዋለች::

‹የተረፈሽን ገንዘብ ምን አደረግሽበት?› ብዬ እጠይቃታለሁ::

‹የወላጆቼን ቤት አሳደስኩበታ....›

‹አራት መቶ በማይሞላ ብር?›

‹አዎ! በትናንሽ ጎጆ ቤቶች እኮ ነው የምንኖረው፤የተገለልን ነን፤ከሰውም አንቆጠር!›

ይገርመኝና ሌላ ጥያቄ አስከትላለሁ::

‹የመጀመሪያ ልጅ ነሽ?›

‹ለእናቴ አዎ! ለአባቴ ግን አይደለሁም:: አባቴ ብዙ ሚስቶች አሉት:: እምና በአንድ ወር ውስጥ ሁለቱ ሚስቶች በአንድ ጊዜ ወልደውለት የሚያበላቸው

አጥቶ ሲበሳጭ የወር ደሞዜን ላከሁለትና በጣም ተደሰተ፡፡ ባለብዙ ሚስት መሆን በኛ ጎሳ ነውር የለውም,

‹የት ነበር አልሺኝ፣ ያንቺ የትውልድ ቦታ…›

‹ሩቅ ነው! ከአዲስ አበባ ወደ ሆሳዕና በሚወስደው መንገድ ….›

ከዘሪቱ ጋር ባወራሁ ቁጥር ትዝ የምትለኝ አስቴር ናት፡፡

ባለፈው በጻፈችልኝ ደብዳቤ ላይ እንዲህ ብላኝ ነበር፡፡

*‘ሰሞኑን ወደ ቀጣሪዎቼ የትውልድ ሀገር ወደ ግብፅ ሄደን ነበር፡፡ አሠሪዎቼ ልጆቻቸውን ይዘው የትውልድ ሀገራቸውን ለማስጎብኘት ፐሮግራም ነድፈው ነበር፡፡ ሞግዚት ነኝና ከልጆቹ ጎን አልጠፋሁም ነበር፡፡ ብዙ ብዙ ነገር አየሁ፡፡ ታዲያ ለልጆቻቸው እነሱ ኔል ብለው የሚጠሩትን የዓባይን ወንዝ ሲያሳዩአቸው ሳይ በደስታ ተቅበጠበጥኩ፡፡ የምሆነውን አሳጣኝ፡፡ አሠሪዎቼ መቅበጥበጤን፣ በደስታ መስከሬን አስተውለው፣ ምን ሆነሻል አሉኝ፡፡ እኔም ዓባይ እኮ የኛ ነው አልኳቸው፡፡ በዚህ ጊዜ ሣቁ፡፡ ከት ብለው ሣቁ፡፡ እንዲህ ተስቆብኝ አያውቅም፡፡ ምነው? ስላቸው፣ ምናሉኝ መሰለሽ? የኛ ነው አልሽኮ! ዓባይ ልትሠሪበት ወይ ልትለውጪው፣ ወይ ሊለውጥሽ ይገባል፤ አንድ ነገር ካልሠራሽበት ያንቺ አይደለም፡፡ እስኪ እስካሁን አንቺና ወገኖችሽ በዓባይ ላይ ምን ሠራችሁበት? ምን ሠራችሁለት? ዓባይን ሥሪበት፤ ያኔ ያንቺም ሀብት ይሆናል፡፡ እኛ ብዙ ሆኖልናል፤ብዙም ሆኖንለታል፡፡ ከዓባይ ውጪ መኖር አንችልም! ብለው ሥቀው ተሳለቁብኝ …*

*‘ሌላ ጊዜ ደግሞ፣ ዛሬም ወደ ዓባይ ልንሄድ ነው፤ ተዘጋጂ ሲሉኝ፣ አልሄድም አልኳቸው፡፡ አልሄድም ያልኳቸው አንደኛ፣ ባለፈው ዓባይ የኛ ነው በማለቴ ለሷ እኮ ናት እንዲህ ያለችው ብለው በብዙ ሰው መሃል ስላሣቁብኝና ስላሣቁብኝ ሲሆን፣ ሁለተኛ፣ ላንቺ ደብዳቤ ለመጻፍ ጊዜ እንዲኖረኝ ብዬ ነበር፡፡ ከዚያ፣ እንግዲያውስ ከእኛ ጋር የማትሄጂ ከሆነ…ብላ እመቤቲቱ የሥራ መዓት ቆለለችብኝ፡፡ ከጉብኝቷ ስትመለስ፣ ይሠራ ካለችው የተወሰነውን ብቻ ነበርና የሠራሁት ጮኸችብኝ፡፡ ተንጨረጨረች፤ አብጠለጠለችኝ፤ድሮስ የናንተ ነገር! ዓባይን የሚያህል ታላቅ ወንዝ ከደጃችሁ ሲያልፍ ተዓምር ልትሠሩበትና ስልጣኔን ልታውጁበት ቀርቶ ረሃባችሁንም አላሸነፋችሁበት፡፡ ከዚያ ከሰነፍ ሀገር መጥተሽ ቤት ለማፅዳት መጥረጊያ ለማንሳት አለመስነፍሽም ይገርመኛል አለችኝ፡፡ እኔ ደግሞ ኢትዮጵያ ውስጥ ውስጥ ያልነበረኝን ሀገር የመውደድ ስሜት ከየት እንዳመጣሁት እንጃ ሀገሬ ስትሰደብ ያመኛል፤ እራስ ምታት፣ ጨጓራው ኧረ ምኑ ቅጡ?’*

አስቴር የልጅ አዋቂ ናት፡፡ ያለእሷ ድጋፍ ይኸን ጊዜ እንዴት ባለ የችግር ሕይወት ኑሯችንን እንገፋ እንደነበር ሲታወሰኝ ይዘገንነኛል፡፡ እሷ ውጭ ስትወጣ ቤተሰቦቼ ደግሞ የተዘረጋ መዳፍ ሆነው ጠበቋት፡፡

ከቅርብ ጊዜ ወዲህ ግን፣ 'እቴትዬ ጡር መፍራት ደግ ነው' ዓይነት ሀሳቦች በየደብዳቤዎቿ መነሻና መቋጫ ብቅ ብቅ ማለት ጀምረዋል፡፡

*ትዝ ይልሻል? እንዷት ሠራተኛችን፣*

*ሠራተኛ ቀጥረው ሲሞላው አንድ ዓመት*

*ሌባ ነው ይሉታል ደሞዝ ለማስቀረት!*

*የሚል ግጥም ያለበት ዘፈን ዘፍና ምን ለማለት ፈልገሽ ነው ብዬ ከወር ደሞዟ አስር ብር ያስቆረጥኩባት ቀን? አቤት ያ ቀን ያነባችው ዕንባ! ያቺ አስር ብር ከደሞዟ ስለጐደለች ፕሮግራሟን እንዴት አመሳቅሎባት ይሆን? ይኸው! አንጋጥጠው የተፉት ምራቅ ሆኗል የኔ እጣ! ያንን ግጥም ዛሬ እንዴት እንደምወደው እቴትዬ! ያቺን ባለሁለት መስመር ስንኝ ስንት ዓይነት አንጀት የሚበላ የሀዘን እንጉርጉሮ አውጥቼላታለሁ መሰለሽ? ባለፈው በማይረባ ሰበብ የስድስት ወር ደሞዜን እንደከለከሉኝ ነግሬሻለሁ አይደል?›*

ደብዳቤዋ እኔን አንቅቶኛል፡፡ ሠራተኞቼን ከወላጆቼ በተሻለ ሁኔታ ነው የምንከባከባቸው፡፡ የማሳድራቸው በፈራረሰ ማዕድ ቤት ውስጥ - ለዚያውም - ምድጃ ስር - የተበጣጠሰ ሰሌን አንጥፌ - አይደለም፡፡ የምጣድ ማሰሻ የመሰለ ብርድ ልብስ - ያውም እግር ወይ እናት ብቻ የመሸፈን አቅም ያለውን ብርድ ልብስ ሰጥቼ አይደለም የማኖራቸው፡፡ የሚበሉት ትርፍራፊ አይደለም፡፡

ከቡና ቤት ሴቶች ይልቅ ለቤት ሠራተኞች በቀላሉ የሚሰበር ልብ አለኝ፡፡ በተለይ ለመልከ ጥፉዎቹ... ወንድን እንደተራቡ ወጣትነታቸው ሲያልፍ ማየት አቤት ማሳዘናቸው፡፡ ፍቅርን... መታቀፍን... መወደድን... እንደሰው መቆጠርን እንደተቸገሩት ያርጣሉ፡፡ ‹እማ› የሚል የእምቦቃቅላ ድምጽ እንደናፈቃቸው፡፡ አንዳንዷ ደግሞ ከችግር እሸሽ ብላ ዘላ በገባችበት ቤት ትደፈራለች፡፡ ሻሽ እየተወረወረላት፣ቅባት እየተገዛላት፣ርካሽ ሸበጥ እየተቸራት፣ካረገዘች በኋላ ዕጣ ፈንታዋ በእመቤቷ ወይም በጌታዋ መባረር ይሆናል፡፡ ቀጣሪ ታጣለች፡፡ ‹የምንፈልግሽ ያለ ልጅሽ ነው› የሚል ፈታኝ ጥያቄ ይመጣል፡፡ ቀስ በቀስ ለልመና እጇን ትሰጣለች፡፡ ልጇም በረንዳ አድሮ በጎዳና መተዳደር ይጀምራል፡፡ ካልሆነለት፣ የእለት ጉርሱን ሊሞላ ማጅራት መቺ ሊሆን!

እኔ እንደዚህ እንዲሆኑብኝ አልሻም:: ግና ምን ዋጋ አለው? ይኸው ለቁም ነገር አበቃታለሁ፤ ከጎኔ አልለያትም ያልኳት ዘሪቱ ልትሄድብኝ ሳይሆን አይቀርም:: ከጥዋት ጀምሮ ሲቀፈኝ የዋለው ያላንዳች ምክንያት አይደለም:: እናቷ የመጡት ሊወስዷት ከሆነ፣ እኔ ከምከፍላት የተሻለ የሚከፍላት ሰው ቢያገኙ ነው::

ደሞዝ ልጨምርላት ይሆን? ዘሪቱ እናቷን ካገኘች ጊዜ ጀምሮ፣ "እማ! የመጣሽው ለምንድነው?" ብላ መልሳ መላልሳ ስትጠይቃቸው፣ እናትየው ግን ስለጤንነቷና ስለ ሥራዋ ነበር የሚያነሱባት:: ዘሪቱ መወትወቷን ስትቀጥል፣ "ማታ ስንተኛ እነግርሻለሁ" ሲሏት ሰምቻለሁ- ምንም እንኳን ያወሩት በሹክሹክታ ቢሆን!

ዘሪቱ ከልብ ተስማምታኝ ነበር:: ባለቤቴ ያረፈ ጊዜ እንዴት ትንከባከበኝ እንደነበር መርሳት አልችልም:: አፅናንታኛለች:: አኩርታኝ ነበር:: ምን ዋጋ አለው፣ አሁን ደግሞ ልትሄድብኝ ነው መሰለኝ::

እስኪመሽ ጨነቀኝ:: ሁለቱን፣ የአምስትና የስምንት ዓመት ሴት ልጆቼን አጣጥቤ፣ አጫውቼና አስጠንቼ አስተኛኋቸው::

እነዘሪቱ መኝታቸውን ያነጠፉት ሳሎን ነበር:: ሳሎኑ ከመኝታዬ ጎን ነው::

ሁላችንም የተኛን ሲመስላቸው እናቷ መጀመሪያ በሹክሹክታ፣ ቀጥሎ ደግሞ እየጋለ በመጣ ድምጽ፣ "ልጄ የቸገረ ነገር ገጥሞኛል:: ዘንድሮም እንደ ድሮ ወንድምሽ ሥራ ጠል ሆኗል:: አይሠራም:: አያርስም:: ሥራውም እርሻውም 'የዌራ አንደትን' ብቻ ማምለክ ሆኗል:: ትንሽ ዘርቶ፣ ወቅቱን ጠብቆ ካጨደ በኋላ ወስዶ ለሷ ነው:: ምንም ሀብት ንብረት ሳይኖረው፣ 'ባርኪልኝ!' ብሎ ይለምናታል:: ያ! የወርቅ በርጩማ ልቡን ወስዶታል...አባትሽም ችላ ይለኛል:: እኔ በወለድኩ፣ እናንተን ባደረስኩ እንዲህ መረሳት አለብኝ ወይ?"

"እማማ! ድምጽሽን ቀንሺ፤እቴትዬን ከእንቅልፍ ትቀሰቅሻታለሽ! እሺ በይ አሁን ንገሪኝ:: አሁን ደግሞ ምን ሆናችሁ? ማለቂያ የለው የናንተ ጣጣ!"

እናቷ ድምጻቸውን በመጠኑ ቀንሰው ቀጠሉ:: "የጎደለብን ገንዘብ አይደለም ልጄ! ዕድሜ ላንቺ፤ የምታጎርሺን ከአፍሽ ነጥቀሽ አይደል? ዕድሜሽን ያርዝመው እንጂ ሥራ ከጀመርሽ በኋላ ሰፈርተኛ የሚቀናብን ሆነናል ...ተንቀባርረን፣ ከሰው ጋር እንቀላቀላለን:: በፊት የአፈር ገንፎ ይመስላሉ እያሉ ይሳለቁብን የነበሩ ሁሉ አሁን አፋቸውን ይዘዋል፣ ዕድሜ ላንቺ!"

ጀሮዬን ቀስሬ ማዳመጤን ቀጥያለሁ:: ከየጣሪያው ስር ስንት ዓይነት አቤቱታ አለ? ስንት ዓይነት የተከፋ ልብ? ስንት ዓይነት አፅናኝ ያጣ ልቅሶ? ልብን የሚያጨልም...

የዘሪቱ ድምጽ ይሰማኛል:: "አጥሩን አሳጠርኩላችሁ፤ቤቱን አሳደስኩላችሁ:: አሁን ደግሞ ታናሽሽ ሊያገባ ነው፤ በወጪ አግዢው አላችሁኝ:: ስንቱን ቀዳዳ ልሸፍን? እኔስ እማ? እኔስ! ለእኔስ?"

በዕንባ ሳትታጠብ አልቀረችም:: ድምጽዋ ነገረኝ::

"ያንቺ ጉዳይ መቼ ሳያሳስበኝ ቀርቶ ሆነና? ከወንድምሽ ጋር ተጣልተናል፤ ተኮራርፈናል፤ ባንቺ ጉዳይም ተቀያይመናል"

"በእኔ ጉዳይ? ለምን?"

"እህትህን ለምን ታስቸግራታለህ? ሁልጊዜ ለእኛ በመጨነቅ ዕድሜዋን ልትገፋ ነው? ስለው፣ እንደዚህ ዓይነት፣ እንድታመነታና እንዳትረዳኝ የሚያደርጋትን ሃሳብ የምታመነጪው እኔ ትዳር ልመሰርት ስል ነው እንዴ? ብሎ ተቆጥቶ አኮረፈኝ..."

ዘሪቱ፣ "እሺ አሁን እኔ ምን እንዳደርግ ነው የምትፈልጊው?" አለች::

"የሰርግህን ወጪ በትንሹም ቢሆን እሸፍንልሃለሁ ብለሽ ደብዳቤ ጻፊለት::"

"እንዴ? የወንድሜን የሰርግ ወጪ ለመሸፈንኮ ቢያንስ ሁለት ሦስት ዓመት መሥራት አለብኝ:: ያውም የደሞዝ ጭማሪ ካገኘሁ! ከየት አመጣለሁ እማ? በእርግጥ ታሳዝኚኛለሽ ግን..."

አሳዘነችኝ:: ይህቺ ከተወለደች ሃያ አምስት ዓመት ያስቆጠረች የማትመስል ሴት ስንቱን መከራ፣ ስንቱን ሃላፊነት ተሸከማለች? ቆይ ደሞዟን...

"ለሱ አታስቢ!" አሉ እናቷ::

"ለምኑ?"

"ለወንድምሽ የሰርግ ወጪ ነዋ..."

"ምን አዲስ ነገር ተገኝቶ ነው የማላስበው? እናንተ ሃሳባችሁን ሁሉ እኔ ጫንቃ ላይ ጥላችሁ አይደል፣ በሰላም ዕንቅልፋችሁን የምትለጥጡት? መሥራት የሚገባችሁን ያህል ለመሥራት ስንፋችሁ በኔ ገንዘብ የከርሞ እቅድ ትነድፋላችሁ"

"ይኸውልሽ ዘሪቱ፣ ጅማ ያሉት የቀርከሃ ሰፋ ሠርተው በመሸጥ የሚተዳደሩ ወንድሞቼ ተደራጅበት፤ ነግጂበት ብለው የላኩልኝ ትንሽ ብር አለ:: 'ለአንዳንድ ጉዳይ ማሚያ ይሆንሃል ብለሽ ለወንድምሽ ትልኪለታሽ:: 'ከማግባትህ በፊት ሥራ መያዝ አለብህ፤ በላኩሁልህ ገንዘብ ተሳፈርበት፤ ወደ እኔ ወደ ከተማ ናበት' ትይዋለሽ:: ግን አደራ! ገንዘቡን ከኪስሽ እንዳወጣሽው እንጂ እኔ እንደሰጠሁሽ ወፍ እንዳይሰማ!"

"ኧይ እማዬ ...አንዳንዴ የምታመነጪው ሃሳብኮ!"

"ምን ላድርግ? ብቻሽን ስትለፊ እያየሁ እጄን አጣጥፌ አልቀመጥ! የምሰጥሽን ብር ከላከሽለት ከተማ ገብቶ መሥራት ብዙ ገንዘብ የሚያስገኝ ይመስለውና ወደዚህ ይመጣል፤ቀልቡንም ከዌራ አንደት አንስቶ ለራሱም ሆነ ለቤተሰቡ ቀለቡን መስፈር ይጀምራል"

የተስማሙ መሰለኝ:: እኔም እፎይ ብዬ...ዘሪቱ እንደማትሄድብኝ እርግጠኛ ሆኜ...በባለቤቴ ሞት ምክንያት ያገኘሁትን ብር ምን እንደምሠራበት እያውጠነጠንኩ...የለውጥ ቀን ቅርብ እንደሚሆን ተስፋ እያደረግሁ...ወደ መኝታ ቤቴ ልሄድ ስል ስልኩ ጮኸ::

ደነገጥኩ:: በዚህ ሰዓት የሚደወልልኝ ከአስቴር ብቻ ነው:: አስቴር ምን ሆና ይሆን? ስፈራ ስቸር ስልኩን አነሳሁት:: ልክ ነኝ:: እሷ ናት:: ረዥም የሆነ ሰላምታ ከተለዋወጥን በኋላ፣ "እቴትዬ!" አለች:: አቤት ድምጽዋ ውስጥ ያለው ፍቅር! በናፍቆት የተሞላ ዜማ! እንደዚህች ያለች እህቴን በባዕድ ሀገር እንድትንሳቀል መፍቀዴ ምን ሆኜ ነው?

"ወዬ!"

"ደወለልኝኮ!"

"ጓደኛሽ?"

"አዎ! ከደቡብ አፍሪካ! አሳዘነኝ:: ተላቀስን:: እንዳያሳስበኝ ብሎ አጽናናኝ:: የተባባልነውን እጽፍልሻለሁ...እሺ እቴትዬ!"

"አይዟችሁ ይነጋል..."

"እንዴት ነው እቴት፣ ቤተሰብ አቤቱታ ማሰማት አልጀመረም? ባለፈው የሠራሁበትን ብር ሁሉ ለጓደኛዬ ላክሁለት:: ከወላጆቹ የወረሰውን ቤት አሳድሶ፣ለሆቴል በኮንትራት አከራይቶት እኮ ነው፣ በደቡብ አፍሪካ አድርጎ አሜሪካ ለመግባት ስንቁን የቋጠረው! ስንደራጅ ቤቱን እኛ እንሠራበታለን!"

“ይሁን እስኪ እንግዲህ...”

“እቴትዬ! ሁልጊዜ እጠይቅሻለሁ ብዬ እየረሳሁ!”

“ምን?”

“ሠራተኛሽ ዘሪቱ አጫውታሽ ያዝናናችኝ ያ የወርቅ በርጩማ ነገር የት ደረሰ? ለወንድሟ ተበረከተለት? እምልኮው ዋጋ አገኘ?”

ተሳሳቅን፡፡

“ለምን ጠየቅሽኝ?”

“ወደ ሀገር ቤት ስገባ የራሴን የወርቅ በርጩማ ለመሥራት ላቤን ማፍሰስ እንዳለብኝ ይሰማኛል፡፡ በከንቱ ምኞት የሚገኝ በረከት ሳይሆን ጠንክሮ የመሥራት ውጤት ምልክት ነው ያ የወርቅ በርጩማ! ...እቴትዬ! እኔ እዚህ መርሮኛል! ትንሽ ሠራርቼ እመጣለሁ...ላብድ ጥቂት ነው የቀረኝ...በየጊዜው የጓደኞቼ ቁጥር ሲቀንስ፣ በሙቅ ውሃ ሲነፍሩ፣ ከፎቅ ሲወረወሩ፣ እሟሟታቸው ሲከፋ እያየሁ እንዴት እንዴት ሆኜ ነው እዚህ በሰው ሀገር ተደላድዬ የምኖረው?” አለችኝ፡፡

“ለምን አትመጪም? ነይ እዚህ! ዛሬ ነገ አትበይ! እኛም በስጋት አለቅንኮ! የግድ ቤተሰቦችሽ እንዲያልፍላቸው ያንቺ ሕይወት ማለፍ አለበት?”

“ኧይ እቴትዬ! ዛሬ ነገ ሳትይ ነይ አልሺኝ? ምን ይዤ? መጥቼስ ምን ሰርቼ ልበላ?”

“አንድ የመጣልኝን ሃሳብ ልንገርሽ?” አልኳት፣ ለጥቂት ደቂቃ ሳሰላስል ቆይቼ፡፡

“ምንድነው?”

“ላበድርሽ ነው! መለስተኛ ንግድ ሊያስጀምርሽ የሚችል ብር! ጓደኛሽ በውርስ ያገኘውን ቤት ወደ ንግድ ተቋም የመለወጥ ዕቅድ አላችሁ አይደል? እረዳችኋለሁ!”

“ከየት አምጥተሽ?” እንደተገረመች ያስታውቃል፡፡

“ለማንም እንዳትነግሪ! ቤተሰብም ቢሆን እንዳያውቀው! የባለቤቴ ኢንሹራንስ ተከፍሎኛል፡፡ ስለዚህ እሰጥሽና፣ ገንዘቡን ትሠሪበትና ዕቁብ ገብተሽ ትከፍይኛለሽ ...”

"ኧይ አቴትዬ!" ሃሳቤን እንደወደደችው ተረድቼያለሁ::

መፍትሄውን የኮረጅኩት ከዘሪቱና ከእናቷ እንደሆነ የታወሰኝ ስልኩን ከዘጋሁት በኋላ ነው!

*'በተገማሸረ መስከ ውስጥ እንደሚብሰከሰከ ውሃ...'*

ሕይወታችን መንቀሳቀስ የምትጀምርበት ቀን ሩቅ እንደማይሆን ተሰማኝ::

የዛሬዋን ማታ ወደድኳት::

----

## ?

ለብዙ ሰዓት ጠበቅሁ:: ጥበቃዬን ደግሞ አልሰለቸሁትም:: በጥበቃ ያባከንኩት ጊዜ በዕንባና በላብ የተሞላ ነበር:: ብዙ ዕንባ ወረደኝ:: ብዙ ላብ ፈሰሰኝ:: ከመጠበቅ ግን ወደኋላ አላልኩም:: ከዐይኔ የሚዘንበው ዕንባ ሰውነቴን አጐደለው:: ከገላዬ የሚወርደው ላብ የቆምኩበትን መሬት አረጠበው:: የቆምኩበት ጭቃ ሆነ::

የቆምኩበትን ቦታ ሳልለቅ ብዙ ነገሮች ተለዋውጠዋል:: ብዙ የፀሃይ ስርቀቶችና የጀምበር ጥልቀቶች ተከናውነዋል:: እኔ ግን እንደነበርኩ አለሁ:: የወጣትነት ዘመኔን በጥበቃና በፍለጋ ከማባከኔ በቀር...

ለብዙ ሰዓት ከመቆሜ የተነሣ፣ ለማዛጋት የከፈትኩት አፌን መልሼ መዝጋት ረስቼ፣ ይኸው ሸረሪት ሁሉ አፌ ላይ ድር ማድራት ጀምሮ ነበር:: ትላንት ገላጣ የነበረው የቆምኩበት ቦታ ዛሬ ሙጃ ውጦት ግማሽ ሰውነቴን ደብቆታል::

የሰው ልጅ አደብ ገዝቶ ከእንቅልፍ ጋር በተወዳጀበት ሰዓት፣ እኔ ግን የከዋክብትን ሹክሹክታ ለማዳመጥ ጆሮዬን አስግጌ ነበር:: ዕድሜ ለመስንበት! እፅዋት ሁሉ ተላምደውኛል:: ነፍሳትም በትንፋሼ መደናገጥ አቁመዋል:: የራሳቸው ሆኛለሁ::

መንገዴ ከመንገዳቸው ተለያይቷል::

ጠበቅሁ:: ብዙ ቀናት አለፈ:: መንግሥት መጣ:: ተመልሶ ሄደ:: ሌላ መንግሥት መጣ:: ተመልሶ ሄደ:: ብዙ ነገር መጣ:: ብዙ ነገር ሄደ:: እኔ ግን ቆምኩ:: በተስፋ እና በምኞት፣ በህልምና በቅዥት እግር ብረት ታሰርኩ:: በመጠበቅ ልክፍት ተይዤ መቆም ሥራዬ ሆነ:: እንደቆምኩ ተረግዞ የነበረ ልጅ ድክድክ ብሎ መሄድ ጀመረ:: ዓለም በማላውቃቸው ጉዶች መሞላቷን ልብ እያልኩ አይቶ እንዳላየ ሰው ዝምታ ዋጠኝ::

መጠበቄን ግን አልሰለቸሁትም::

ብዙ ላብ ወረደኝ፤ ብዙ ዕንባ ፈሰሰኝ::

ቆይቶ፣ ልመናዬ ዕረፍት ነሳው መሰል፣ እግዚአብሔር በራዕይ ተገለጠልኝና፣ "የምትጠብቀውን ነገር ንገረኝ:: አሟላልሃለሁ፤ እመነኝ! አለኝ:: ለመፅናትና ለመፅናናት ብዬ የከፈልኩትን ዕንባና ላብ እያስታወሰ፣ ውዳሴውንም እያጐረፈ፣ "ጥያቄህን ለመስማትና ምላሹንም ለመስጠት ሰባት ደቂቃ ሰጥቸሃለሁ" አለኝ::

አመንኩት:: ደስታዬ ወደር አጣ:: ከደስታ ብዛት እንዳላብድ ሰጋሁ::

"ንገረኝ!" አለኝ::

ምን ልንገረው? ጉዴ ፈላ:: እስከዛሬ ስጠብቅ የቆየሁት ነገር ምንድን ነበር? 'የውርደት ቀን አይነጋም' አልኩ በልቤ:: ምንድን ነበር? ብዙ የቆምኩለት ጉጉቴን የረሣሁት በመቆየት ብዛት ይሆን እንዴ? ማስታወስ አቃተኝ:: ተስፋዬን ማን ሰረቀው?

"የምትጠብቀውን ነገር ንገረኝ፤ አሟላልሃለሁ..." አለኝ ጌታ፣ ጥያቄውን ደግሞ::

ሰባት...ስድስት...አምስት...አራት ደቂቃ ብቻ ይመስለኛል- የቀረኝ ጊዜ:: ምን ልበለው? እስከ ዛሬ የቆየሁት ምን ስጠብቅ ነበር? ስጠብቅ የቆየሁትን ነገር ሊያስታውሰኝ የሚችል ሰው ማን ነው? ስጓጓ የቆየሁት ምን እንዲሆንልኝ ነበር?

ያ ሁሉ መቆም፣ ያ ሁሉ መቆዘም፣ ያ ሁሉ በአልበገር ባይነት መሞላት፣ ያ ሁሉ ራስን ለመርሳት መሞከር ምን ለመሆንና የት ለመድረስ ነበር?

ምን ሆኜ ነው፣ ስፈልግ የቆየሁትን፣ ዕንባዬንና ላቤን የዘራሁበትን ጊዜዬን ያላንዳች ስስት የገበርኩለትን ነገር፣ ለመርሳት የበቃሁት? እንዴት እየፈለግሁ ያለሁትን ነገር ልዘነጋው ቻልኩ? ሰው እንዴት መስዋዕት የከፈለበትን ጉዳይ ይረሳል?

አራት...ሦስት...ሁለት...አንድ ደቂቃ ይመስለኛል - የቀረኝ ጊዜ...

"ፍቃደኛ ነኝ..." አለኝ ጌታዬ፣ ለሦስተኛ ጊዜ::

ዛሬ ምን ነክቶኛል፤ እንዴት ስፈልገው የቆየሁትን ነገር እዘነጋለሁ? ሁሉንም ነገር ማድረግ የሚችለው የሃያላን ሃያል፣ እፊቴ ቆሞ ፍቃዴን ለመሙላት ዝግጁ ሲሆን እኔ እንዴት ዝም እላለሁ?

አንገቴን ደፍቼ ማሰብ ጀመርኩ:: አንድ ሃሣብ መጣልኝ::

እውነቱን መናገር!

ወይስ፣ 'የምጠብቀውን ታውቃለህና አድርግልኝ' ልበለው?

ይህችኛዋን መረጥኩ፡፡ ቀና ስል የለም። ብቻዬን ነኝ፡፡ ያ መንፈስ ጥያቄውን አቀብሎኝ መልሴን ሳይሰማ ሄዷል ለካ!

ዜሮ ደቂቃ ብቻ ነበር የቀረኝ...

.....

# "እኔ፣ አባቴና አንዲት ጊደር!"

—1—

"ግባ!" አለችው ጸሐፊዋ፣ አባቱ ብቸኛ ጊደራቸውን በሚያዩበት ደጋግ ዐይን ነበር በዐይኖቿ የዳሰሰችው::

ገርበብ ያለውን በር ከፍቶ ወደ ውስጥ ገባ::

የድርጅቱ ሥራ አስኪያጅም በምቹ ወንበር ላይ እየተሽከረከሩ ከምጥን ፈገግታ ጋር ተቀበሉት::

"ስምህ ሞገስ ነው?"

ሞገስ በአዎንታ ራሱን ነቀነቀ::

"የትምህርት ማስረጃህን አይተነዋል:: ድርጅቱ ባወጣው ክፍት የሥራ ቦታ ላይ ከተወዳደሩት ሰባ ሁለት ሰዎች መሃከል አንተ ተሽለህ ተገኝተሃል፤ማለትም አንደኛ ሆነሃል:: ስለሆነም መስፈርቱን የምታሟላ በመሆንህ ልናሳልፍህ ተገደናል!" አሉት::

ልቡ በደስታ ተሞላ:: በሥራ አስኪያጁ ፊት ግን የምስራች አይሯሯጥበትም:: ዝምተኛ ፊት ነው ያላቸው:: የታሸገ ፖስታ መስለው ታዩት:: የታሸገ ፖስታ ሲያይ ፍርሃትና ናፍቆት ይመላለስበታል:: የሥራ አስኪያጁ ፊትም እንደዚሁ ነው፤ የመሞቅም ሆነ የመቀዝቀዝም ምልክት የማይታይበት:: አባቱ እንደሚጽፉለት የታሸገ ደብዳቤ...

ትላንት የደስታ ማታ ነበር የሆነለት:: ሥራ ፍለጋ ያልረገጠው ደጅ የለም:: ሁሉም የሚጠይቁት ተመሳሳይ ነገር ነው - የረዥም ጊዜ የሥራ ልምድ:: እሱ ደግሞ ልምድ የለውም::የተመረቀው በቅርብ ነው::

የምርቃት ዕለቱን በማስመልከት፣ በተመራቂ ተማሪዎች አስተባባሪነትና ተሳታፊነት ልዩ የዳንስና የጭፈራ ማታ ተዘጋጅቶ ነበር:: እሱ ግን የመቀላቀል ሃሳብ አልነበረውም:: ሆኖም በዝግጅቱ አስተባባሪዎች ቅን ፍላጎትና ጉትጎታ ለመሳተፍ ተገደደ:: እንዲህ ባለቦታ መገኘት 'ክብሩ' አይፈቅድለትም:: ከሰዎች ተነጥሎ የመኖር ልምድ ኖሮት አይደለም:: ግን ወጪ በሚያስወጡ ጉዳዮች ሰበብ ራሱን ከጓደኞቹ የመገንጠል ልማድ አዳብሯል - በአራት ዓመት ውስጥ::

እና በዝግጅቱ ታድሞ ለመጀመርያ ጊዜ ሰከረ:: ከጠላ በቀር ሌላ ነገር ቀምሶ የማያውቀው ሞገስ በስድስት ቢራ ሰከረ:: ለመጀመርያ ጊዜ ከማያውቀው አለም ጋር ተቀላቅሎ ቀና ብሎ ከመሄድ አልፎ ሚዛኑን መሳት ጀመረ:: ብዙ ነገርም ቀባጠረ:: ሰከረ::

'ስለ እግዚአብሔር ብላችሁ እኔ መለፍለፍ ማቆም አቅቶኛል:: ስለዚህ እናንተ የምናገረውን ባለመስማት የዜግነት ግዴታችሁን ተወጡ:: ለእኔ ያላችሁንም ፍቅር የምለውን ባለመስማት ግለፁ!' አላቸው፣ በአዋጅ ለፋፊ ድምጽ:: ማሳሰቢያውን እንደማስታወቂያ እየደጋገመ - እየደጋገመ - እየደጋገመ::

ነጋ:: ከእንቅልፉ ሲነቃ በማያውቀው ቦታ፣ ከብዙ ሰዎች ጋር ሆኖ ራሱን አገኘው::

ከእንቅልፉ ያነቃው ሣቃቸው ነበር::

ዐይኑን ገልጦ ሲያያቸው የሳቃቸው መጠን ጨመረ:: 'እንዳች የሚያስቅ ተንኮል ተፈፅሞብኝ ይሆን?' ብሎ አሰበ:: ምናልባት ጥላሸት ቀብተውኝ እንደሆነ ብሎ ፊቱን ዳበሰ:: ግን ፊቱ ንፁህ ነበር::

"ምንድነው የሚያስቃችሁ?"

ከሣቂዎች አንዱ የትናንት ማታ ማሳሰቢያውን ደገመለት::

ገባው:: ልቡ በብዙ ድንጋጤዎች ተሞላ:: ለመሄድ ተነሳ:: ዙርያው ካሉት ሰዎች መሀል አብዝቶ ወደሚወዳጀው ኤልያስ ፊት ቀረበ:: "ና!" ብሎት ወደ ውጭ ይዞት ወጣ:: "ስለ እግዚአብሔር ብለህ ንገረኝ፤ ትላንት ሰክሬ እንደ ነበር አስታውሳለሁ፤ ብዙ ነገር መለፍለፌንም አስታውሳለሁ:: ምን እንዳልኩ ግን ትዝ አይለኝም፤ ልትነግረኝ ትችላለህ?" ብሎ በጥያቄ ወተወተው::

"ያን ያህል የሚታወስና የሚያሳስብ ነገር አልተናገርክም!" አለ ኤልያስ::

"የሚታወስና የሚያሳስብ ነገር ካልተናገርኩ ታዲያ ምንድን ነበር እንዲያ የሚያስቃችሁ?"

"ያው የተማሪ ነገር ታውቀው የለ!" አለ፣ ጥያቄውን ቀለል አድርጎ፤ "በዚያ ላይ የመጀመሪያ ጊዜህ ይመስለኛል - ቢራ ስትጠጣና ስትሰክር!"

"እና ጠጥቼ ከሰከርኩ በኋላ ምን አልኩ? ኤልያስ ስሞትልህ ንገረኝ! ከኔ ጋር ያለህ ወዳጅነት እንዲቋረጥ ካልፈቀድክ በስተቀር አትደብቀኝ!" አለው፣ ከብዙ መለማመጥ ጋር::

"ሞገስ! ለምንድነው የምታስጨንቀኝ?"

"አንተ መናገር ያልፈለግከው ለምንድነው?" ወተወተው::

"ነግርኸናልኮ! አስረግጠህ ነግረኸናል:: ምስጢሬን ከነገርኳችሁ እጠላችኋለሁ ብለሃል:: ስለዚህ አንተን ማጣት አልፈልግም፤ ምንም እንዳልተናገርክ በመቁጠር ኑሮህን ቀጥል"

ሞገስ ዕንባ ተናነቀው:: "ጥፋተኛው አንተ አይደለህም፤እኔ ነኝ:: ወዳጅነታችንን ስመዝነው አክብጄ ማየት አልነበረብኝም"

ኤልያስ ንጭንጩን ችላ ብሎ ቀጠለ:: "ባለፈው ያልከኝን ታስታውሳለህ? ወደ ሳይኮሎጂ ዲፓርትመንት ሃላፊ ቢሮ የሄድክ ቀን እንኳን? እዚያ ሄደህ ማበድ አለማበዴን በምን ላረጋግጥ እችላለሁ፤ የአዕምሮ ጤናማነት መስፈርቱ ምንድነው? ብለህ በጥያቄ ያጣደፍካቸው ጊዜ? እሳቸው ደግሞ በአጠያየቅህ ተገርመው ማንነትህን በማውጣጣት ብዙ ጥያቄዎች በመጠየቅ ሊያከሙህ ፈለጉ:: አንተ ግን ምንድነው ለበጐነታቸውና ለአካሚነታቸው የሰጠኸው ምላሽ! ታውቀዋለህ፤ አልነግርህም!" አለ ኤልያስ::

እውነትም ሞገስ፣ የስነ ልቦና አማካሪውን አግኝቶ ምስጢሩን ከዘከዘከላቸው በኋላ ከፍተኛ የሆነ የመዋረድ ስሜት ተሰምቶት ነበር:: ዶክተሩን ጠልቷቸው ነበር:: እሳቸው በሚያዘወትሯቸው ካፌዎች ደጅ ርቆ ነበር:: በማይመላለሱበት መንገድ መምጣትና መሄድ ሥራው አድርጎት ነበር::

"አባቴ አንዲት ጊደር ናት ያለችው:: ነግሬህ የለ! የኛ ቤት ሁነኛ የቤተሰብ አባላት ሦስት ነን:: አባቴ፣ እኔና ጊደራችን:: እና- አባቴ ጊደራችን ላይ የተጣበቀባትን መኻገር ሊነቅል ሲል አታስጠጋውም:: ዶክተሩ ምስጢሬን ከሰሙ በኋላ መራገጥ መንፈራገጥ ብቻ ነበር የቀረኝ:: ልቤ ላይ የተጣበቀው

መኽገር ደሜን መጥጦ በአጥንት ያስኬደኝ እንደሆነ አያለሁ እንጂ ከህመሜ ሊፈውሰኝ ከሚሞክር ዶክተር ጋር አልደራደርም!" አለ፣ ፍርጥም ብሎ::

ሞገስ እንዲህ ነው:: ኤልያስም ይህንን ፀባዩን ያውቅበታል:: የአባቴ ጊደር ወደ ግጦሽ የሚያሰማራት ሰው ስታጣ እንዲህ ብላ ነው የምትጮኸው፣ ብሎ ራሱን ወደ ከብት ባህርይ ለውጦ፣ አካሄዱን ቀይሮ፣ እንደ ጊደርዋ መጮኹን ቢነግረው ...

- ዕብደትን የሚያህል ሸከም በሸማግሌው አባቴ ጫንቃ ላይ ላኖረው እግዜር ጥቂት የምሬትና የወቀሳ መዝሙር ላሰማ ብሎ አንጀት በሚበላ ዜማ በፈጣሪው ላይ መማረሩን ቢነግረው...

- እዚህ ተሰብስባችሁ በምርቃታችሁ ዋዜማ ላይ በሀሴት በመመስከር ላይ የምትገኙ ተማሪዎች ሆይ! በብዙ ነገር ትበልጡኝ ይሆናል፣ አብዝቶ በመደህየት ግን ጫፌም አትደርሱም ማለቱን ቢነግረው...

- መዝሙረኛውን ዳዊት ሆኜ ዳግም ተወልጃለሁ፤ ዩኒቨርስቲው በአራት ዓመት ቆይታ ውስጥ የወንጭፍን አወነጫጨፍ ጥበብ አስተምሮኛል:: ከእንግዲህ ጠጠር ፍለጋ፣ በየክፍት የሥራ ቦታ ማስታወቂያ ስሌዳው አፈጥጣለሁ:: ጠጠሩ በእጄ ሲገባ እኔ ዳዊት ድህነት ጎልያድን እገድለዋለሁ ብሎ መዛቱን ቢነግረው...

ይህንን ሁሉ ቢነግረው ይደብተው ይሆናል:: በስፍራው የተገኙትን ተማሪዎች ማነጋገር ያቆም ይሆናል::

"ቴንኪዩ!" አለ ሞገስ፣ ቃላት ሊገልፀው የማይችል ስሜት ዐይኑን እየሞላው::

"ለምኑ?"

"ለእምቢታህ!"

"አልገባኝም!"

"ማታ የሆንኩትንና ያልኩትን ንገረኝ ስልህ አለመናገርህ በጣም አስደስቶኛል:: መናገር የማይገባኝን ነገር ተናግሬ ብገኝ ልጠላህ እችል ነበር ይሆናል"

"ታዲያ ካልነገርከኝ ብለህ የምታስጨንቀኝ ለምንድን ነበር?"

"እኔንጃ! አንዳንዴ ለራሴ የማይገቡኝን ነገሮች አደርጋለሁ:: ያደረግሁትን እረሳለሁ:: አባቴን እሆናለሁ:: ጤነኛ በመሆንና ዕብድ በመሆን መሃከል ያለው የልዩነት ድልድይ ይፈርስብኛል:: በጭራሽ እኔ 'እኔ' አልሆንም::

እውነቴን ነው የምልህ! ከጥቂት ወራት በኋላ ብዙ ነገር ተቀባኝሮብኛል:: ድልድዩ ፈርሶብኛል:: የአባቴ ህመም ተጋብቶብኛል:: ጐህ ቀድዶ ጀምበር እስኪሰርቅ ድረስ ስለ አባቴ ዕብደት አስባለሁ:: አባቴን አሳክሜ ወደ ጤናማዎች ዓለም የማስመልስበትን ቀን ስለሚናፍቀኝ ነው መሰለኝ:: ዕብደቱ ሳይጋባብኝ አልቀረም!" አለ ድምጹ እየሻከረ፤ዕንባ እየተናነቀው::

"ኧይ ሞገስ..." አለ ኤልያስ፣ ከጥልቅ ሀዘን ጋር:: "ስለራስህ ያለህ ግምት በፍፁም ልክ አይደለም!"

"እሱን ተወው:: በእኔ ልክ ማንም እኔን ሊያውቀኝ አይችልም:: ብሎኔ ላልቷል:: የጠበቀ የሚመስለው በአንተ ብርታት ነው"

ፀጥታ ሆነ::

"የምትሠራው ሥራ ከሌለህ አብረኸኝ ቆይ..." አለ ሞገስ፣ እባክህን እምቢ አትበለኝ በሚል ድምጸት::

"እሺ"

"ቤተክርስቲያን እንሂድ?"

"እንሂድ"

ከብዙ ፀጥታ በኋላ፣ "ኤልያስ የተዋወቅን ቀን የነገርኩህን ታስታውሳለህ?" አለው፣ ቆም ብሎ::

"ትዝ አይለኝም"

"እንዴት ትዝ አይልህም? ትዝ ይልሃል፤ ትዝ የማይለው ሰው ለመምሰል የምትሞክረው አውቀህ ነው"

"ምን ነበር የነገርከኝ?"

"ድባብ መናፈሻ ቁጭ ብለህ ጋዜጣ እያነበብክ ነበር:: አንዲት መጣጥፍ አንብበህ ስትስቅ አየሁህና ሣቅህን እንድታጋባብኝ ቀረብኩህ:: መጣጥፉ በድህነትና በጉስቁልና ስለሚኖሩ የአንድ መንደር ነዋሪዎች የሚተርክ ነበር:: በዚያች መንደር ውስጥ አንዲት ሻይ ቤት ተከፈተች:: ሻይ ቤቷ የምትከፈተው በሳምንት አንድ ቀን ነው:: በመንደሯ ውስጥ ከቤተክርስትያኗ ቀጥሎ ስመ ገናና ናት:: መዝናኛም ጭምር:: ለመፅናናትም ለመዝናናትም ብዙዎቹ ደጇን ይረግጣሉ፤ ሃምሳ ሳንቲማቸውን መኸርረጥ አድርገው አውጥተው 'ሻይ!' ብለው ያዝዛሉ - ስሙን አስተካክዬ ጠርቼዋለሁ ወይስ አበላሽቼው ይሆን?

በሚል ፍርሃት ተይዘው፡፡ ከዕለታት አንድ ቀን አንድ አረጋዊ ከልጅ ልጃቸው ጋር ሆነው ወደ ገበያ ሄዱ፡፡ ወደ ገበያ ሄዱት የሚሸጥም የሚገዛም ዕቃ ኖሯቸው አልነበረም፡፡ ሻይ ቤቱን ለማየትና ሻይ የመጣጣታቸውን ዜና ለአካባቢው ሰው ተናግረው ከብራቸውን ለማሳደግ እንጂ፡፡ ግና ምን ሆነ? ወደ ሻይ ቤቱ ገቡ፡፡ እንደገቡ የሻይ ቤቱ አስተናጋጅ አፊታቸው ቀረበ፡፡ 'ምን ልታዘዝ?' አለ፡፡ 'እስኪ ሻይ አምጣልኝ!' አሉ፣ ለሦስት ሰዓት ከሀያ ደቂቃ የተጓዘ እግራቸውን እያፍታቱ፡፡ 'ለልጁስ?' አለ አስተናጋጁ፣ የሚቁለጨለጨውን ህጻን እያየ፡፡ 'ተወው! ለእኔ ብቻ አምጣልኝ፤ እሱ የዛሬ ሳምንት ከእናቱ ጋር ጠጥቶ ተመልሷል!' አሉ፡፡ አይገርምህም? አንተ ያነበብከውን ስትተርክልኝ በሣቅ ብዛት ዕንባህ እየፈሰሰ ነበር፡፡ በርግጥ እኔም አንብቻለሁ፡፡ ያነባሁት ግን ሀዘን ገብቶኝ እንጂ በሌላ ምክንያት አይደለም፡፡ ታስታውስ እንደሆነ፣ 'አባቴ በህይወቱ ሻይ ጠጥቶ ያውቅ ይሆን?' ብዬህ ነበር፡፡ እውነቴን ነው፡፡ አባቴ ሻይ ለመጠጣት ቢያንስ የሁለት ሰዓት መንገድ ተጉዞ ወደ ከተማ መቀላቀል ይጠበቅበታል"

ቤተክርስቲያን እስኪደርሱ ድህነትና የአዕምሮ ሕመም ስለተጫናቸው አባቱ ብዙ ተረከለት፡፡

— 2 —

"የት ሄድክ?" አሉት፣ ሥራ አስኪያጁ፡፡

"እ?" አለ፣ ሞገስ፡፡

"በሃሳብ ጭልጥ ብለህ ሄደሃል"

"ገርሞኝ ነው!"

"ምኑ?"

"ተወዳድሬ ማለፌ አስደስቶኛል፡፡ ያለምንም የሥራ ልምድ መቀጠሬ ገርሞኛል፡፡ እንኳንም ሆነልኝ፡፡ ብዙ የቤት ሥራዎች ይጠብቁኛል፡፡ የዘራሁትን የማጭድበት ቀን ይናፍቀኝ ነበር፡፡ በሕይወቴ ብዙ ፈተናዎችን አልፌያለሁ፡፡ አራት ዓመት ሙሉ አንገቴን ደፍቼ ትምህርት ላይ ያተኮርኩት በወላጆቼ ቤት ውስጥ ተንደላቅቆ የተቀመጠውን ድህነት አሽመድምጄ ለመጣል ጉልበት ለማግኘት ነበር"

"ደስ ይላል!" አሉት፣ ሥራ አስኪያጁ:: ደስ ይበላቸው አይበላቸው ግን ፊታቸው አይናገርም:: ለእንደዚህ ዓይነቱ ሰው ከጥቂት ምልልስ ውጭ እንዲህ ያለውን አላስፈላጊ ማብራሪያ መደንጐር ምን ይሉታል? ብሎ አሰበ::

ግራ ገብቷቸው አዩት::

ግራ መጋባታቸው ግራ አጋብቶት ሳይጨርስ፣ "ለምኑ ነው ይቅርታ?" ብለው ጠየቁት::

"እዚህ ደረጃ ላይ የደረስኩት በህይወቴ ብዙ ቀይ መብራቶች ተደቅነውብኝ ነው:: እዚህ ደረጃ ላይ ከመድረሴ በፊት ብዙ ተፈትኛለሁ:: በየሄድኩበት የሚያቆመኝ ቀይ መብራት እፊቴ ይታየኝ ነበር ለማለት ነው፣ ያ ሁሉ ያወራሁት!" አላቸው::

"አላወራህምኮ! ማውራት የጀመርከው አሁን ነው:: ለብዙ ደቂቃ ፀጥ ብለህ ነበር..."

"እሺ ይቅርታ! ይቅርታ የጠየቅኩት ብዙ ያወራሁ መስሎኝ ነው..." አለ፣ ተለሳለሰ::

ሞገስ ከተመረቀ ወር አልሞላውም:: እሱ ግን ስድስት ዓመት ያህል የቆየ ነበር የመሰለው:: ትላንት ግን፣ 'አረንጓዴ መብራት ታየኝ!' አለ:: 'እንደ ልቤ መጓዝ እችላለሁ' አለ:: ሲቦርቅ አመሸ:: ነፍሳት ሲርርታ ሲያሰሙ፣ ዛፎች ሲንሾካሾኩ ስለ እሱ ዕድለኛ መሆን፣ ስለሱ ባለሥራ መሆን መረጃ የሚለዋወጡ እስኪመስለው ድረስ::

በጥንቃቄ የተገኘች የሥራ ዕድል ናት:: ዕድሏን ላለማበላሸት ብዙ ተደክሟል:: ከኤልያስ ኮትና ሱሪ ተውሷል:: ምባይሉን ጭምር ተውሶታል:: ምባይሏ መኖር አለመኖሯን ለማረጋገጥ እጁን ወደ ኪሱ ሲሰድ እንደ አጋጣሚ ጮኸች::

"ይቅርታ!"

"ችግር የለም፤ ስልኩን አናግረህ መመለስ ትችላለህ!" አሉት ሥራ አስኪያጁ::

ስልኩ ላይ የተጻፈውን ስም አነበበ:: ጋሽ ደረጀ ናቸው:: መምህሩ:: የእኚህ ሰው ዕርዳታ ባይታከልበት ኖሮ ዛሬ ከተመራቂዎች መሀል አንዱ የመሆን ዕድሉ የጠበበ ይሆን ነበር:: በምን ይበልጥ እንደተግባቡ ፈጽሞ አይረሳውም:: ገጠር ሄዶ ሲመለስ አንድ ፈተና አመለጠው:: የፈተናው ውጤት ከሰላሳ ነበር የሚታረመው:: ሄዶ አነጋገራቸው:: ‹ካልተፈተንክ

እንዴት ልረዳህ እችላለሁ?› አሉት:: ለመናቸው:: እሳቸው ግን፣ ‹ለብዙዎች የከለከልኩትን፣ አንተ ምን የተለየ ነገር ስላለህ ነው እንደገና የመፈተን ዕድል የምንሰጥህ? ተው እንጂ!› አሉት:: ‹የሚያሳዝን ነገር ባይደርስብኝ ኖሮ በፈተና ቀን አባቴን ጥየቃ ብዬ ተሳፍሬ አልሄድም ነበር› አላቸው:: ዝም አሉት - የማይሰማ መስለው እየሰሙ:: ‹አባቴን አይቼ የመጣሁት በተለያዩ ውድድሮች ተሳትፌ በማሸነፌ የተሸለምኳቸውን መጻሕፍት ሸጬ ነው!› አላቸው:: አመኑት:: ዕንባው መጣ:: 'በቃ! ትፈተናለህ!' አሉት:: ‹አባቴ ራሱን ሊሰቅል ሲል ነው፣ አንድ መንገደኛ ደርሶ የገላገለው!› ብሎ ማልቀስ ጀመረ፣ ሞገስ:: 'በቃ አታልቅስ፤ ትፈተናለህ አልኩህ እኮ!' አሉት፣ጋሽ ደረጀ:: 'እኔ ዕብድ አባት ነው ያለኝ:: በደንባራ በቅሎ ቃጭል ተጨምሮ:: የኛ ቤተሰብ አባላት ሦስት ብቻ ነን:: እኔ፣ አባቴ እና አንዲት ጊደር:: በቃ!'

ጋሽ ደረጀ፣ በሞገስ መረበሽ ተረብሸው፣ 'በቃ! አልኩህ'ኮ! ትፈተናለህ፤ ታልፋለህ፤ እናም ትመረቃለህ፤ሥራ ትይዛለህ፤ አባትህን ታሳክማለህ፤ አንተም ሀገርህን የምትወድ ኢትዮጵያዊ ዜጋ ይወጣሃል:: አይዞህ ሁሉም ያልፋል...' አሉት፣ *ሶፍት* እያቀበሉት::

አልሰማቸውም፤ *ሶፍቱንም* አልተቀበለ...

'በቃ አታልቅስ!'

'ማልቀስ ስፈልግስ?' ኮስተር አለ::

'እንዴ? ለምን?'

'ስለ አባቴ ሳወራ ዝም ማለት አልችልም'

'ራስህን ለምን ትጎዳዋለህ?'

'ይኼ ራስን መጉዳት አይደለም፤ ራስን ማከም ነው:: የእኔ ፀበል ዕንባዬ ነው:: ካላነባሁ እደርቃለሁ:: ካላነባሁ ርኩስ መንፈስ ይቀርበኛል:: ከፈለጉ የማወራውን አለመስማት ይችላሉ:: እንዳልናገር ከሚከለክሉኝ ይልቅ ቢሮዎን ቆልፈውብኝ ቢወጡ ይሻለኛል› አላቸው::

ጋሽ ደረጀ ተደናገጡ:: ይህን ጭምት ተማሪ እንዲህ ሲሆን አይተውት አያውቁም:: በርግጥ ስለ እሱ በሰሙ ቁጥር የሚገርማቸው አንድ ነገር አለ:: ተባባሪ ነው:: በበጎ አድራጎት *ሥራዎች* ላይ ራሱን ሲያሳትፍ ያገኙታል:: ያዝኑለታል:: 'ሁል ጊዜ ቀብር ላይ እንዳለ ሰው ነው' ይላሉ፣ ብቻቸውን ሲያስቡት:: የዩኒቨርስቲው መውጫ በር ደጅ ላይ አያጡትም:: አንድ ከአዲስ

አበባ ውጪ የሆነ ተማሪ ከዚህ ዓለም በሞት ከተለየ፣ አስከሬኑ የሚሸኝበት ገንዘብ ካስፈለገ ጊዜውን ያላንዳች ማመንታት ነው የሚገብረው:: ትንሽ ካርቶን እግሩ ስር አድርጎ፣ የሟቹን ፎቶ እደተደገፈው ግድግዳ ላይ ለጥፎ፣ ምፅዋት ይጠይቃል- ለሚያውቁትም ለማያውቁትም::

ቀና ሲሉ፣'እዩ ጋሽ ደረጀ! ድህነትና ዕብደት አባቴን አስረጁት' አላቸው::

'አባትህ ምን ሆነው ነው?'

'ዕብደቱ ማለትም የአዕምሮው ሕመም የጀመረው ያኔ ርሃብ በነገሰበት ጊዜ ነው:: እናቴ በዕርዳታ የተሰጠንን እህል ስትበላ - ለካስ እህሉ አልተስማማት ኖሯል - ጤንነቷ ታወከና ወዲያውኑ ሞተች:: ርሃቧን ለማስታገስ የበላችው እህል እናቴን ይዟት ሄደ:: ያኔ የስድስት ዓመት ልጅ ነበርኩ:: እኔም ሆንኩ የተቀረው ቤተሰብ እናቴን አርቆ የሚቀብር፣ ሬሳዋን ወደ ምትወደው ቂርቆስ ቤተክርስቲያን የሚያደርስ አቅም አልነበረንም:: እና ጓሮ ተቀበረች - እንደ አብዛኛው የአካባቢው ነዋሪ:: በተከለቻቸው ጐመኖች መሃል ራሷን ደበቀች:: የእሷ ገላ ለም አፈር ሆኖ የምንበላውን እህል ያበቅልልን ይመስል:: በህይወት ሳለች የኖረችልን ሳያንሳት ከሞተች በኋላም እኛን ልታኖር ጓሯችን ውስጥ ተቀበረች:: ርሃቡ ከፍቶ የትውልድ መንደራችንን ትተንወጣን:: ሁኔታው ረገብ ብሎ ከሄድንበት ከተመለስን ከጥቂት ቀናት በኋላ አባታችን ወደ ጓሮ ሄዶ ሲቆፍር የእናቴን እጅ አገኘ:: ለሰባት ዓመታት ያህል ከእጇ ያላወለቀችውን አምባር እንዳጠለቀች:: በዚህ ጊዜ ጮኸ:: ስቅስቅ ብሎ አለቀሰ:: ጩኸቱን የሰማ ጐረቤትና መንደርተኛ ተሰበሰበ:: ሀዘናቸው ዳግም አንሰራራ:: አፅሟን ሰብስበው ቀበሯት:: ያኔ በመጽሔትና በጋዜጣ የመነጋገሪያ ርዕስ ሆነ:: አባቴ የዕብደትን ፀበል የተጐነጨው ከዚያን ጊዜ ጀምሮ ነው'

ይህን ታሪክ ጠንቅቀው ያውቁታል - ጋሽ ደረጀ:: ምስጢሩን ነግሯቸው እሳቸውን ያልጠላበት ምክንያት፣ ከነገራቸው በኋላ፣ 'አባትህ እንዴት ሆነ?' ብለው ስላልጠየቁትና ባዩት ቁጥር ከንፈር ስላልመጠጡለት ሳይሆን አይቀርም::

ይኸው አሁን ደግሞ ደውሉለት::

"ጋሽ ደረጀ፣ ይቅርታ ቆይቼ እደውልልሃለሁ!"

## — 3—

“ግባ...” አሉት፣ ሥራ አስኪያጁ:: ሥራ አስኪያጁ ምንም የማመንታት ነገር አይታይባቸውም:: ሞገስ ስልክ አነጋጋሮ እስኪመለስ ድረስ ሌላ ሰው ገብቶ ጠብቆታል::

ገባ:: ባለ ጉዳይ እያለ ‘ግባ’ ማለታቸው ገርሞታል::

ተቀመጠ:: ከተቀመጠበት ወንበር ትይዩ ሌላ ሰው ተቀምጧል:: ሰውየው ጐልማሳ የሚባል ዓይነት ሰው ነው:: ፊቱ ላይ ሀዘን ተጋግሮበታል:: የዕንባ መስመሮች ይታዩበታል:: ሰውየው ሥራ አስኪያጁን በተፀፀቱ ዐይኖች ሲያያቸው ቆይቶ፣ “እባክዎትን! ለአንድ ወር ብቻ ይታገሱኝ፤ ለአንድ ወር ብቻ!” አላቸው::

ሞገስ በጐልማሣው ባለጉዳይ ሁኔታ ማዘን ጀመረ:: አንዴ ማዘን ከጀመረ መመለሻ የለውም::

“ለአንድ ወር አልከኝኮ! በአንድ ወር ውስጥ ባንተ የተነሳ ስንትና ስንት ደንበኛ ነው የሚጉላላው? የድርጅቱን ስምኮ ነው ያስደብከው!”

“እሺ፤ አንድ ነገር ልለምንዎት?”

“ምንድነው?”

“ባለቤቴ ለአንዲት ቀን እንኳን ለብሼው በሞትኩ የምትለውና ልቧ እስኪጠፋ ድረስ የምትወደው የጨርቅ ዓይነት ነበር:: ከዛሬ ነገ ስለቴ ሰምሮ፣ ዕድሌ ተቃንቶ፣ ምኞቷን አሟላለሁ ብዬ ስንደፋደፍ ሞት ቀደመኝ”

ዕንባ ተናነቀው:: “አሁን ደግሞ አንድም ቀን ልጄን ሳላስጌጥ - እናቷ በወደደችው ጨርቅ ሳላሳምራት ሞት እኔን እንዳይነጥቀኝ እፈራለሁ - የአንድ ወር ጊዜ ብቻ ይስጡኝ!”

ሞገስ በምስኪኑ ሠራተኛ አነጋገር ልቡ ተያዘ::

ወደ ኋላ ሄደ:: ወደ ራሱ ታሪክ ተመለሰ::

የአስራ ሁለተኛ ክፍል ተማሪ እያለ በትጋት ነበር የሚያጠናው:: ትምህርት ቤቱ ካስፈተናቸው ጥቂት ተማሪዎች መሀከል አንዱ ሆኖ ነበር:: በከፍተኛ ነጥብ ብልጫ ነበር ያለፈው:: ውጤቱ ለዲግሪ መርሐግብር የሚሆን ነበር::

እሱ ግን ምርጫው የዲኘሎማ ውጤት መጥቶለት ቶሎ ሥራ ይዞ አባቱን መርዳት ነበር:: እና ምኞቱ ስላልሰመረ አለቀሰ:: አራት ዓመት ሙሉ የሚፈጅ ትምህርት እስኪማር አባቱ አንድ ነገር ቢሆኑበትስ? አንድ ነገር ቢሆንብኝስ? አለ:: አራት ዓመት ሙሉ በትምህርት ምድጃ ላይ መጣድ ከበደው:: ዲፕሎማ ግን ሁለት ዓመት ናት:: እሱ የሚፈልገው ትንሽ ዓመት የሚወስድ ትምህርት ተምሮ፣ ደረጃውን የሚመጥን ደሞዝ ተቀብሎ፣ ለአባቱ ፈጥኖ መድረስ እንጂ መቸ ተደላድሎ ለመማር ሆነና? የናፈቀው ከነገ ወዲያ ከሚያገኘው ኬክ ይልቅ ነገ በእጁ የሚገባ ዳቦ ነበር::

በየዋህነቱ ሀገር ሳቀበት::

ይሄ ተማጻኝ የጥበቃ ሠራተኛ ነው፣ ወደ ራሱ ህልም ጐትቶና ጐንትሎ የወሰደው:: እና ልቡ ተነካ::

ዝም ማለት አቃተው::

"ክቡር ሥራ አስኪያጅ!" አላቸው፣ የአማላጅነቱን ሚና በራሱ ፍቃድ ለመውሰድ ልቡን አነሳስቶ::

"አቤት!" አሉት፣ ለማለት የፈለገው የገባቸው ይመስል መቆጣት ጀምረዋል::

"ባለቤቱ እየወደደችው ሳትለብሰው ያረፈችውን ቀሚስ ለገዛ ልጁ እስኪያለብሳት ድረስ ጥቂት የጊዜ ገደብ ቢሰጠውና..."

መጨረስ አልቻለም::

"ምን?"

"የአንድ ወር የጊዜ ገደብ ቢሰጠው..."

ሥራ አስኪያጁ ወደ ተማጻኙ ጥበቃ ዞረው፣ "አምጣው እሱን ወረቀት!" አሉት፣ ባለጉዳዩን:: ወረቀቱ ከሥራ መሠናበቱን የሚገልጽ ደብዳቤ ነበር:: በደብዳቤውም ላይ አንዳች ነገር ጻፉበት:: ጸሐፊዋንም ጠርተው ሰጧት::

ሁለቱም - አዲሱ ሊቀጠር የመጣው ሞገስም፣ ሊሰናበት የነበረው ጎልማሳም- ሥራ አስኪያጁን አመሰገኗቸው::

ፀጥታ ሆነ::

ሞገስ፣"ጌታዬ! መቼ ነው ሥራ የምጀምረው?" አላቸው::

“ጥቂት የጊዜ ገደብ ቢሰጠው እኮ ነው ያልከው? የሥነ ምግባር ጉድለት ይታይብሃል ልበል?” አሉት፡፡ “በማይመለከተው ጉዳይ ከሚዘባርቅ ሰው ጋር መቼም ኮከቤ አይገጥምም”

“አልገባኝም !”

“ጥበቃውን ወደ ቀድሞ ሥራው መልሸዋለሁ፤አንተን ደግሞ ሳልቀጥርህ አሰናብቼሃለሁ!

.....

# የመኝታ ቤት ምስጢሮች

**(ዱላው)***

ቅንዝንዝ ነው፤ ቅብጥብጥ:: ሴት አቅፎ ካላደረ ሰውነቱ አለቅጥ የሚፈታተነው፤ እንደ ብረት ምጣድ እየጋለ የሚያስቸግረው:: እና ሰብለ ውል አለችበት:: ሰብለ የጓደኛው ሚስት ናት:: ጓደኛውና ሰብለ ከተጋቡ ሰባት ዓመት ሊሞላቸው ነው:: ሰብለን አባብሎ ለመተኛት ብዙ ቀናት አልፈጀበትም:: ያሸነፋት አተኩሮ በማየት ብቻ፤ መልሶ መላልሶ በማየት ብቻ ነው:: በዐይኑ አጥር ሠራባት፤ አጠራት:: ውብ ገላዋን የሚያሞካሹ ቃላት ተጠቅሞ ለራሷ የነበራትን ፍቅር በእጥፍ አሳደገው:: የማታውቀውን የብልግና ዓለም አሳያት...

እና ያ ቀን ከእሷ ጋር መሆን ነበር ያሰኘው:: እሷም የጠበቀችው በደስታ ነበር:: እንደ አጋጣሚ ሆኖ ወሲባዊ ፊልም እያየች ነበር:: ስታየው የቆየችውን

---

** ይህች አጭር ትረካ መነሻ ሃሳቧ እውነት ናት:: መጠኑንና ጭብጡን አብዝቼ እንዲህ የጋገርኩት እርሾዋን ይዤ ነው:: እውነተኛ ታሪክ ነው ተብሎ ይነገረኝ እንጂ መቼ፣ በማን፣ የት እንደተፈፀመ እርግጠኛ ሆኖ የሚተርክልኝ አልገጠመኝም:: ድርጊቱ የተፈጸመው በስልሳዎቹ ዓመታት ውስጥ ነው፤በደብረ ዘይት ከተማ ይላሉ:: አሉ ነው እንግዲህ:: እርግጥ የተነገረኝን እንዳለ አልገለበጥኩትም:: ባለታሪኳ በስተመጨረሻ አበደች ያለኝ አለ፤ ራሷን ሰቀለች ያለኝ አለ፤ ገዳም ገብታ መነኮሰች ያለኝ አለ፤ እኔ ግን እንዲሆን በምፈልገው መንገድ ነው የቋጨሁት:: እርሾዋን ይዤ ነው፣ መጠኑንና ጭብጡን አብዝቼ እንዲህ የጋገርኳት:: እውነተኛ ታሪክ ናት ተብሎ ይነገረኝ እንጂ መቼ፣ በማን፣ የት እንደተፈፀመ እርግጠኛ ሆኖ የሚተርክልኝ አልገጠመኝም:: ድርጊቱ የተፈጸመው በስልሳዎቹ ዓመታት ውስጥ ነው ይባላል፤ በደብረ ዘይት/ ቢሾፍቱ ከተማ:: እርግጥ የተነገረኝን ወሬ እንዳለ አልገለበጥኩትም:: ተለዋውጦአል:: ባለታሪኳ በስተመጨረሻ አበደች ያለኝ አለ፤ ራሷን ሰቀለች ያለኝ አለ፤ ገዳም ገብታ መነኮሰች ያለኝ አለ፤ እኔ ግን እንዲሆን በምፈልገው መንገድ ነው የቋጨሁት::*

ሕይወት እንዲኖሩት እና እንዲሠሩት ገፋፉት:: በምታየው ፊልም ሰውነቷ ፍም ሆኖ ነበር:: እናም ሆነ::

ግና እጅግ ከመጣደፋቸው የተነሳ ለካስ በሩን አልዘጉትም ኖሯል! በዚያ ደስታ ውስጥ ሆነው ባለቤቷ በድንገት መጥቶ እፊታቸው ሲደቀን አቤት የተሰማቸው ድንጋጤ!

ወዲያውኑ ገላቸው ቀዘቀዘ:: ፈገግታቸው ደበዘዘ::

አባወራው መጀመርያ በፀጥታ - በከባድ ፀጥታ ተውጦ - ነው ያያቸው:: ጓደኛውና ሚስቱ ተቃቅፈው ከተኙበት አልጋ ጥቂት ርምጃ ፈንጠር ብሎ ተቀመጠ - አደገኛ መሳይ ዐይኖቹን ከዐይናቸው ላይ ሳይነቅል:: ከጥቂት ደቂቃ ዝምታ በኋላ፣ እዚያና እዚህ የተበታተኑ ልብሶቻቸውን ሰብስቦ፣ አፍንጫቸው ላይ ወረወረው::

"ልበሱ!"

ለበሱ::

አባወራው ሽጉጡን ከሳጥኑ ውስጥ አውጥቶ በፍቅር ይዳብሰው ጀመር:: የሰብለ ልቅሶ ይሰማዋል:: የአባወራው ጓደኛ ሰብለን አይዞሽ ብሎ ሊያባብላት ቀርቶ ዐይኗን ለማየት እንኳን ብርታት ጐድሎታል:: ደግሞም እርግጠኛ ሆኗል:: ዛሬ የመሞቻ ቀኑ ነው:: ምን ማድረግ እንዳለበት ግራ ሲገባው ቆየና፣ በከባድ ፍጥነት ከአልጋው ላይ ወርዶ እግሩ ስር ተደፋ::

"ምንድነው?" አለ፣ አባወራው::

"ይቅርታ አድርግልኝ...ሁለተኛ አይለመደኝም...ሁለተኛ አይለመደኝም!"

"ዝም በል! ሽጉጤን ያወጣሁት እንዲህ ዓይነቱን ዝብዝብ ለመስማት አይደለም!"

የአባወራው ጓደኛ አንገቱን እንደደፋ ዝም አለ::

"ሁለተኛ አይለመደኝም፤ እኔ ነኝ ጥፋተኛ! እኔ ነኝ ..."

"ይህን አንተ አትነግረኝም፤ነገረኝ ብዬም አልጠየቅሁም:: አውቅሃለሁኮ! አውቅሃለሁ:: ቀበቶህን ባገኘህበት የምትፈታ ወንድ መሆንህን አውቃለሁ:: የምትተኛቸውን ሴቶች ቁጥር በማብዛት፣ ግዳይ እንደጣለ ጀግና ለራስህ የምታጨበጭብ ሰው መሆንህንም አውቃለሁ:: የማላውቀው ነገር ቢኖር ሚስቴንና የልጆቼን እናት..."

አባወራው ጥርሱን ማፏጨት ጀመረ:: በዚህን ጊዜ ሰብለ ቤቱን በልቅሶ ሞላችው::

"ዝም በይ!"

ዝም አላለችም::

"ሴትዮ ዝም በይ! እኔ በዕንባና በልቅሶ ብዛት የሚሸነፍ ልብ የለኝም"

ዞረ:: ወደ ጓደኛው ፊት ተመለከተ:: ቀረበው:: አንገቱንም በሽጉጡ ቀና አደረገ::

"አንተንም ሚስቴንም በዚህ ሽጉጥ መድፋት እችል ነበር፤ በተቃቀፋችሁበት አልጋ ላይ ሬሳችሁን ማጋደም እችል ነበር" አለና የዕብደት ሳቁን አመጣው:: "ፍቅር እስከ መቃብር! ድንቄም ጓደኝነት! ድንቄም ሚስትነት:: ያለሽ መስሎሻል ተበልተሽ አልቀሻል አለ ሰውየው!"

ተወቃሾቹ ዝም ከማለት ውጭ የሚመልሱለት ነገር አልነበረም::

"ስማ!"

"አቤት!"

"አልገድልህም! እሺ? ሁለታችሁንንም አልገድላችሁም:: አልገድላችሁም ስል ግን በነፃ አሰናብታችኋለሁ ማለቴ አይደለም:: በተለይ አንተ! አሁን አንድ ነገር እንድታደርግልኝ እፈልጋለሁ:: አድርግ የምልህን ነገር ማድረግ የማትፈልግ ከሆነ ግን ዛሬ ሬሣህ ከዚህ ቤት ይወጣል..."

"ምን ላድርግ?" ተለሳልሶ ሊለምነው ሞከረ::

"መቸም ወደሷ የመጣኸው ብቻዋን የምትሆንበትን ሰዓት ስለምታውቅ ነው:: የወሲብ ፍላጐትህን ለማርካት ብለህ እንጂ ለሌላ እንዳልሆነ እገምታለሁ!"

የአባወራው ጓደኛ ዝም አለ:: እሱ ግን ቀጠለ::

"ስለዚህ የተገለገልከበትን ከፍለህ ከመኝታ ቤቴ እንድትወጣ እፈልጋለሁ"

"አልገባኝም!"

"ምኑ ነው ያልገባህ?"

"የተገለገልከበትን ስትል?"

"ቡና ቤት ሄደህ ከአንዷት ሸርሙጣ ጋር ብትተኛ ስንት የምትከፍል ይመስልሃል?"

ፀጥ! ሚስት በድንጋጤ ቀጥ!!

አባወራው የሁለቱም ዐይኖች እንደፈጠጡ ታውቆታል፡፡

"በል እንጂ?!"

"ለምንድነው እንደዚህ የምታደርገው? ምን እየሠራህ እንደሆነ በጭራሽ አልገባኝም"

"እንዴት አይገባህም? ሥጋዊ ፍላጐትህን ለማርካት መጣህ፡፡ የልብህን አደረስከ፡፡ እና ከሴተኛ አዳሪ ጋር ብትተኛ ኖሮ የምትከፍለውን ከፍለህ ውጣ ነው የምልህ፡፡ አሁንስ ገባህ?"

"እኔ ከቡና ቤት ሴት ጋር ወጥቼ አላውቅም!"

"ዋናው በነጻ አለመሆኑ ነው፡፡ በል ይበቃታል ብለህ የምታስበውን፣ ማለትም የቡና ቤት ሴት ብትሆን ኖሮ ትጠይቀኛለች ብለህ የምትገምተውን ያህል ብር ስጣትና ውጣ! መቼም በነጻ አይሆንም"

አሁንም ፀጥ! ከባድ ዝምታ!

"በል እንጂ..."

ኪሱን ፈተሸ፡፡ ከድፍን ሃምሳ ብር ሌላ አልነበረውም፡፡ እሱን አዘጋጀ፡፡

አባወራው የብሩን መጠን አይቶ፣ "ሃምሳ ብር? የሚስቴን ዋጋ በሃምሳ ብር? እንዴት ነው ሚስቴን ያረከስካት? ሃምሳ ብር በፍፁም አያዋጣትም፤ አይመጥናትም፡፡ ተጨማሪ ካልያዝክ ግን አምጣው፡፡ አምጣው ሃምሳ ብሩን ...ማለቴ ሃምሳ ብሩን ለሷ ስጣት፡፡ ዋጋዋ ነው !"

ተወቃሹ ዝም አለ፡፡ ሰብለ ምን እያሰበች ይሆን ብሎ እያሰበ፡፡ በህይወቱ ራሱን እንዲህ በተዋረደ አጋጣሚ አግኝቶት አያውቅም፡፡ የራሱ ዋጋ ቀለለበት፡፡ ጨሀ ጨሀ አሰኘው፡፡

"ምን ያፈዝሃል፤ ስጣት እንጂ..."

"ምኑን?"

"ሃምሳ ብሯን ነዋ! የአገልግሎቷን ዋጋ!"

የአባወራው ጓደኛ፣ ብሩን ሊሰጣት እጁን ወደ እሷ ሲዘረጋ ጮኸች:: ጮኸች ስብሰ:: ራሷን መቆጣጠር ሁሉ አቃታት:: ፊቱን አንገፈገፈችው፤ ሰውነቷን አንዘፈዘፈችው:: ተሰቀቀች:: ለሃምሳ ብሩ ጀርባዋን አቀበለችው:: ባሏ ግን አስገደዳት:: እናም በላብ በራስ እጇ ተቀበለችው::

ባልየው ደግሞ መልሶ ብሩን ተቀበላት:: "እኔ የተሻለ ቦታ አስቀምጥልሻለሁ!" አላት::

ጓደኛውን አሰናበተው:: "ትልቁ ነገር በህይወት መትረፍህ አይደለም:: ይኸ ቀን በአሮጌው ማንነትህ ላይ ተኩስ ከፍተህ፣ ባለጌ ማንነትህን አንቀህ የምትገድልበት ቀን ይሁን:: የምልህ ይገባሃል?"

እሱ እንደወጣ፣ ባልየው ሃምሳ ብሩን ይዞ ሚስቱን አስከትሎ ወደ ሳሎን ሄደ:: ሳሎን አንድ ቄንጠኛ የምግብ ጠረጴዛ አለ:: የጠረጴዛው የላይኛው ክፍል በመስታወት የተሸፈነ ነው:: መስታወቱ ስር ሰፊ ጣውላ ተጋድሟል:: የጠረጴዛውን መስታወት በጥንቃቄ አነሳውና ጠረጴዛው እምብርት ላይ ብሩን አስቀመጠው::

ሃምሳ ብሩ ላይ መስታወቱን ጫነበት::

"ነይ!"

አጠገቡ ቀረበች::

"አሁን የምልሽን በጥንቃቄ ስሚኝ፤ እሺ?"

"እሺ" አለች፣ በትንፋሸዋ::

"ይህን ብር ከዚህ ቦታ ያነሳሽው ቀን እገድልሻለሁ!"

አንገቷን ሰብራ ዝም አለች::

"እስኪ አሁን የሰጠሁሽን ትዕዛዝ ድገሚልኝ!"

"ይህን ብር ከዚህ ቦታ ያነሳሽው ቀን እገድልሻለሁ! ነው አይደል ያልከኝ?"

"አዎ! ሃምሳ ብሩ ቦታውን የለቀቀ ቀን ወይም ብሩ የተቀየረ ለታ አይማረኝ ብምርሽ!"

ልጆቿ ስለዚህ ብር በጠየቋት ጊዜ - ዘመድ ጓደኛ ቤታቸውን ለመጎብኘት መጥተው የብሩን ነገር አንስተው በጠየቋት ጊዜ - ይኼ ብር 'ምንድነው?' ብለው ባስጨነቋት ጊዜ እምትመልሰው ግራ ይገባት ቀጠለ::

'ይሄ ብር ምንድነው?' ይላል፣ የመጣ እንግዳ::

'እኔ ምኑን አውቄ! እስኪ የልጆቼን እናት ጠይቋት!' ይሆናል፣ የአባወራው ምላሽ:: አንድም ቀን ስለፈፀመችው ስህተት ለሰው አላወራባትም:: ሰድቦ ለሰዳቢ አሳልፎ አልሰጣትም:: አልነዛነዛትም:: ከጓደኛው ጋር የነበረውን የጓደኝነት ክር ግን ወዲያውኑ በጠሰ::

የሰብለ መሳቀቅ እየበዛ መጣ:: ዝምተኛ ሆነች:: ብቸኛ ሆነች:: ከሰውነት ተራ ወጣች:: መነመነች:: የመለወጧና የመቀዝቀዟ ምስጢር ብዙዎቹን ያስደነገጠ ሆነ::

አንድ ቀን - እኩለሌት ላይ - ከእንቅልፉ ቀሰቀሰችው::

"ፍታኝ!"

"ፍታኝ?"

"ፍታኝ ወይም ግደለኝ!"

"ግደለኝ?"

"ፍታኝ ወይም ግደለኝ!"

ገብቶታል:: ለምን እንደዚህ ልትለው እንደቻለች ያውቃል:: የእስካሁኑ ቅጣት በቂ እንደሆነ ገባው:: ከአልጋው ወርዶ፣ ወደ ሳሎን ሄዶ፣ ያንን ብር አነሳው:: አንስቶም ኪሱ ውስጥ ጨመረው::

ሰብለ ወደ ቀደመ ሰውነቷ የተመለሰችው ከዚህ በኋላ ነው::

----

# ወደ ታች

መዳፏን ወደ ልጅዋ ግምባር ላከችው:: አመድ በለበሰ ፍም ላይ መዳፏን የማኖር ያህል ትኩሳቱ ፈጃት:: ባለቤቷ የምትሆነውን ሁሉ እየተከታተለ ስለነበር መረጋጋት እንዲሰፍንበት ብላ መረበሽዋን ደበቀችው:: እሱ ግን ሲያተኩርባት ቆየና፣ "እስኪ ለዛሬ እንኳን እረፍት ውሰጂ፤ ቤት ሄደሽ እደሪ" አላት::

"አቢቲስ?" አለችው፣ ሳምባውን ብርድ ነክቶታል ወደተባለ ታካሚ ልጇ እያየች::

"እኔ አለኋ...እየተጐዳሺ ብኝ እኮ ነው:: እንቅልፍ ባይንሽ ላይ ከዞረ ምን ያህል ጊዜ ሆኖታል? ራስሽን መጠበቅ ረስተሻልኮ - የኔ ሆድ! ሆስፒታል ከገባሽ ሃያ ቀናት አልፎሻል እኮ! አንድ ቀን እንኳ ከፎቅ ወርደሽ ፀሐይ መትቶሽ መች ያውቅና?"

ያቀረበላትን ሃሳብ አጣጣለችበት::

ከፍሉም የሃዘን ድባብ አረበበበት::

አመሻሽ ላይ፣ 'ደህና እደሪ' ብሏት ሆስፒታሉን ለቆ ሊወጣ ሲል፤ የአቢቲን ግምባር ሲስም ትኩሳቱ ጫን እያለ መምጣቱ ገባው:: ዓመት ያላስቆጠረ ልጃቸውን ለማሳከም ነው ከገጠር የመጡት::

በማግስቱ ዐይኗ አባብጦ ፊቷ በዕንባ ታጥቦ ደረሰና መላ ሰውነቱ ራደ:: "ሆነ?" አላት፣ ዐይኑን ወደ ታማሚ ልጁ መላክ ከብዶት::

ዕንባዋ ከጉንጭዋ ላይ ተንሸራትቶ ወደ አፏ እየገባ... አንገቷን በአዎንታ ነቀነቀችው::

መንሰቅሰቅ ከፍሉን ገዛው፡፡

የሕጻኑን ደህንነት በቅርብ ትከታተል የነበረችው ነርስ ባልና ሚስቶቹን ስታባብላቸው ቆየችና እሷ ራሷ ራሷን መቆጣጠር አቅቷት ተወቻቸው፡፡ "ያልቅሱ! በእንባ ቢወጣላቸው ይሻላል" ብላ፡፡

ከጥቂት ደቂቃ በኋላ ባለቤቷ ከተቀመጠበት ሲነሳ እጁን ያዘችው፡፡ "የት ለመሄድ?"

"ጓደኞቼን ላስቸግራቸው፡፡ ገንዘብ ያስፈልገናል"

"ቁጭ በል!" ድምጿ ጠነከረ፡፡ "እንደባለፈው ልታደርግ ነው? አይደል?"

እንዳልገባው ለመምሰል ሞከረ፡፡ "ምን? ባለፈው ምን አደረግሁ?"

"ደምህን ለበሽተኛ ሸጠህ አይደል ለአቢቲ መድኃኒት የገዛህለት? ሐኪሞቹ የምታደርገውን ካወቁና እጅ ከፍንጅ ከደረሱብህ ያሳስሩሃል፡፡ እስር ቤት አውለው ካሳደሩህ ደግሞ ለአቢቲ ቀብር አትደርስም፤ የምልህ ይገባሃል?" እንባ ተናነቃት፡፡

በርግጥም፣ 'ለአቢቲ ቀብር አትደርስም' ባትለው ኖሮ አታድርግ ያለችውን ከማድረግ አይመለስም ነበር፡፡

ቀስ በቀስ አቢቲ ተኝቶበት የነበረው ክፍል በጠያቂዎች ተሞላ፡፡ በታላቅ ድንጋጤ የተዋጡ ጐስቋላ ዘመዶች፡፡ የመከራ ቤቶች፡፡ አባት ግራ ገብቶታል፡፡ 'የውርደት ቀን!' ይላል በልቡ፡፡ ባዶ ኪስ፡፡ የማያልፉት ፈተና፡፡ ሬሳ በምን ይወሰዳል? መኪናዎች ደግሞ አስከሬን ለመጫን ውድ ነው የሚጠይቁት፡፡ ገንዘብ ከየት ይመጣል? ከማን ይበደሩታል?

ጭንቀቱ ገብቷታል፡፡ ሌቱን በሙሉ ስታብሰለስል ስላነጋችበት ጉዳይ አጫወተችው፡፡ "እኔ ምንም ያልተፈጠረ መስዬ፣ በነጠላ ሸፋፍኜ፣ ወሊሶ እስከንደርስ ስሜቴን ደብቄ እይዘዋለሁ፡፡ ማንም አይጠረጥረኝም ... እናንተ ደግሞ በሌላ መኪና ትከተሉኛላችሁ፡፡ ፊትና ኋላ ሆነን እንደርሳለን"

አንዲት ጠያቂ ሀሳቧን ተቃወሙት፡፡ "ከፍለ ሀገር እስከትደርሺ ብቻሽን ልትሆኚ? ይሄማ ወጋችንም አይፈቅድ! እግዜሩስ ምን ይለን?" አሏት፤

ተመላልሰው ይጠይቋቸው የነበሩ አሮጊት አከሰቷ:: ከንፈራቸውን ባዳፋ ነጠላቸው ሸፍነው ያጉተመትሙ ገቡ::

"ምንም አልሆንም እትዬ! እኔ በምገኝበት መኪና እናንተም ተሳፍራችሁ ከሆነ ስሜታችንን መቆጣጠር ስለሚያቅተን እንጠረጠራለን..." አሁንም እንባዋን ለማሸነፍ ትጣጣር ጀመር::

ከጥቂት ደቂቃ በኋላ ታክሲ ይዛ ወደ አውቶብስ ተራ ሄደች::በጎያዋን መሐል፣ ሟች ልጇን ታቅፋ ጉዞ ወደ ከፍለ ሀገር::

—

# ያልተኖረው ሕልም

ከናፈቀችኝ መታገስ አልችልም:: ልቤ አሁኑኑ አግኛት! አግኛት ይለኛል:: ስሜቴን እምቢ ልለው አልደፍርም:: የኔይቱ ቢራቢሮ ይህን ጊዜ አልጋዋ ላይ ሆና ልጥፍ ብላ ተኝታ ሙዚቃዋን እየኮመኮመች ይሆናል ብዬ አስባለሁ::

እናም እደውልላታለሁ::

"ሲገርም! በጣም እያሰብኩህ ነበር" ትለኛለች:: እኔም ይገባኛል:: በጣም ሳስባት እያሰበችኝ ይሆናል ብዬ አስባለሁ:: ወይም እንድታስበኝ እያደረግሁ ነው ብዬ አስባለሁ:: እንተሳሰባለን:: "ክረምት ትወድ የለ፤ ይኸው ሰማዩ ጨፍግጐልሃል፤ደስ ይበልህ" ትለኛለች:: ላግኝሽ አልላትም:: ፀሃይዋ ብቅ ብላ ሰማዩ ካልፈገገ የሚኖራት ፊት የደበተው ነው::ብርሃን ይጐድላታል::

መነን!

ስሟን ስጠራ በፈገግታ እበራለሁ፤ በሙቀት እገዛለሁ:: እኔ ለሷ ያለኝ ስሜት 'ፍቅር' የሚለው ቃል ከሚገልፀው በላይ ነው::

መነን ለኔ ብዙ ናት:: ሳወራት ውዬ ባድር አታልቅብኝም:: ፍቅረኛ እንዳላት እያወቅሁ አይደል በቁጥጥሯ ስር የዋልኩት::

መነን...

'እንዴት ነው የምታየኝ?' አለችኝ፣ አንድ ቀን::

'ረዥም ጊዜ የሆነን ይመስለኛል፣ ረዥም ጊዜ'

'ምን?' አለችኝ::

'አንቺን ማፍቀር ከጀመርኩ:: ከተዋወቅን ጥቂት ወራት ብቻ ብናሳልፍም ከድሮ ጀምሮ ስጠብቅሽ የኖርኩ ይመስለኛል'

'ነግሬሃለሁ! ከእኔ ጋር ፍቅር እንዳይይዝህ፤ኋላ የለሁበትም ብዬ አስጠንቅቄሃለሁ፤ ስቃይ ነው የሚተርፍህ...'

'እንኳን እኔ አንቺ ራስሽ ከኔ ጋር ፍቅር ይዞሻል:: ከፋቱ ግን በፍቅር መውደቅሽን ከልብሽ ማመን አትፈልጊም:: ስሜትሽን መካድ ነው የተያያዝሽው፤ ታፈቅሪኛለሽ' አልኳት፣ ኮራ ብዬ::

'እንዴ ሲሳይስ?' ደንገጥ ብላ ጠየቀችኝ፤ ትላልቅ ዐይኖቿ እየፈጠጡ፣ ልስልስና ስስ ከናፍሮቿ እየተርበተበቱ፣ ጠይም ፊቷ እየደነገጠ...

'እኔ የማውቀው አንቺን ማፍቀር ማቆም እንደማልችልና አንቺን ከማፍቀር የሚያግደኝ ምንም ሃይል እንደሌለ ብቻ ነው ...' አልኳት::

ሁለታችንም በአንድ የግል ማሰልጠኛ ተቋም ውስጥ *የሲኒማቶግራፊ* ተማሪዎች ነን:: በሳምንት ቢያንስ ለአምስት ቀናት አብረን እንሆናለን:: በቀን ለሁለት ሰዓት ያህል ስንማር እንቆይና 11:30 ሲሆን፣ ተቋሙን ለቅቀን እንወጣለን:: ከዚያ ወደ ካፌ:: ከምሽቱ 2:30 እስኪሆን ድረስ የባጥ የቆጡን ስናወጋ ሰዓቱን እንገፋዋለን::

አንድ ቀን፣ ራሽያ ተምሮ በመምጣቱ ኩራት የሚያበዛው፣ ኩራትም የሚያምርበት የፊልም ድርሰት አጻጻፍ መምህራችን፣ አንድ ቀጭን ትዕዛዝ ሰጠን...ጥንድ ጥንድ ሆነን አጭር ጭውውት ሥርተን እንድናሳየው::

ሁለት ሰው ብቻ ሊሳተፍበት የሚችል የአስር ደቂቃ ድርሰት ጽፌ ለመነን አሣየኋት::

ባነበበችው ነገር ተደሰተች::

ሠራነው....

ፊልሙን ኤዲት ልናደርገውና ከወሰድነው ኮርስ አንፃር ሲገመገም ምን እንደጐደለው ለማየት ተቀጣጠርን::

በሰዐቱ አላገኘኋትም:: አርፍዳ መጣች:: "ያረፈድኩት ፋዘር ታሞ ሐኪም ቤት ወስጄው ስለ ነበር ነው..." አለችኝ፣ ተኩል ሰዓት በመዘግየቷ ያንዣበበብኝን የቅሬታ ደመና በፈገግታዋ ፀሃይ ለመግፈፍ ቸኩላ::

"አልተሻላቸውም?" አልኳት:: አባቷ ይገርሙኛል:: መነን እንደነገረችኝ ከሆነ በቀን ከሃያ ገጽ በላይ ካልጻፉ ቀኑን እንደኖሩበት አይቆጥሩትም:: ይተጋሉ፤ ተዋጊ መሆን ይሻሉ፤ ልቤ ውስጥ ሰርገው አልገቡም እንጂ የተወሰኑ ሥራዎቻቸውን አንብቤያቸዋለሁ::

የአባቷ መጣጥፎች እንደማይመስጡኝ ታውቃለች::

"ምን ይሻለዋል ብለህ ነው? ለሊቱን እንዲችው ነው ያነጋው:: ያስለዋል:: ያስመልሰዋል:: እንዲያም ሆኖ ስለእኔ መጨነቅ ነው የሚያስበው::አጠገቡ ሆኜ 'ትሪት' እንዳደርገው እንኳን አይፈቅድልኝም:: ሂጂ ተኚ፤ እንቅልፍሽን አጥተሽ ምንም የምትፈይጂው ነገር አይኖርም ይለኛል:: እሱ ባቃሰተ ቁጥር እኔ እንዳልረበሽበት ብሎ ላለማቃሰት ሲሳቀቅ ይነጋል" አለችኝና ተከዘች::

ስትተከዝ፣ ጠይም ፊቷ ብርሃን መስጠት እንዳቃተውና ላለመጨለም እንደሚፍጨረጨር ኩራዝ ይሆናል::

እናቷን ያጣችው ሦስተኛ ዓመቷን ሳታከብር ነው::

አባቷ መነን እንጂ ሌላ ልጅ የላቸውም::

"ለምን ወደታወቀ ሆስፒታል አትወስጂያቸውም?"

"ኧይ አንተ! አባቴ የአልጋ ቁራኛ ከሆነ መንፈቅ አልፎታል:: ባይገርምህ በሱ ሕመም የተነሳ ያልጐበኘሁት ሆስፒታልና ያልተዋወቅሁት ስመ ጥር ዶክተር የለም"

"በሽታቸው ግን ምንድነው ተባለ? ምንድነው እንዲህ ሰቅዞ እና ቀስፎ የያዛቸው?"

"ምን የማይሉት አለ ብለህ ነው? አንዱ የጨጓራ *አልሰር* አለባቸው ይላል፤ አንዱ ይመጣና የምን የጨጓራ *አልሰር* የልብ ድካም ነው ይላል:: ሌላው ብድግ ብሎ የኩላሊት *ኢንፌክሽን* ነው ይላል:: ኧረ ተወኝ:: አብዛኞቹ የሚስማሙበትና እኛም የምናምነው ሕመም ደም ብዛት እንዳለበት ነው:: አንድ ዶክተር ደግሞ በጣም ጠቃሚ መድኀኒት ነው አለና ስሙ የረዘመ ሃያ ስድስቱንም የእንግሊዘኛ ፊደል ያካተተ የሚመስል ከኒን አዘዘለት"

"ጥሩ ነዋ ታዲያ፤ከኒኑን አገኛችሁት?" አልኳት፣ መጓጓቷን አይቼ::

"ዕድሜ ለሲሳይ! ዱባይ የሚመላለሱ *ኮንትሮባንዲስት* ጓደኞች አሉት:: እንዴት እንዳሳሰበኝ ነግሯቸው ይዘውልኝ መጡ:: ደግሞ ውድነቱ?" ሲሳይ እጮኛዋ ነው::

ስለ አባቷ በሽታና ስለ ሲሳይ ውለታ ማውራት አቆምንና ስለሠራነው ፊልም ተነሳ:: ልናየው ተቻኩለናል:: ካሴታችንን ይዘን ወደ አንዲት ክፍል ገባን:: የሠራናቸውን *ሥራዎች* መልሰን መላልሰን ማየት ስንፈልግ የምንጠቀምበት ክፍል ነው::

የሠራንበትን ካሴት ለዴኩ አጐረስነው:: ዋጠው:: ጥቂት ደቂቃ ጠብቆ የሁለታችን ምስል *እስክሪኑ* ላይ ብቅ አለ:: ወደደችው:: የሠራነውን መውደዷን ለመግለፅ ተቸገረች:: አንዲት ሴት የሚተርክ አጭር ፊልም ነበር::

ቀስ በቀስ የውይይታችን ርዕስ ተቀየረ:: አሁንም ብቻችን ነን:: ማንኛውም ተማሪ *ሥራውን* በሚገመገምበትና *ኤዲት* በሚያደርግበት ጊዜ ክፍሉን ቆልፎ የመቀመጥ ግዴታ ስላለበት እኛም ለመመሪያው ተገዢ ሆነናል:: የሁለታችንም ልብ *ሥራው* ላይ እንዳልሆነ አውቃለሁ፤ ታውቃለች::

አተኩራ ስታየኝ፣ እኔም ዐይኔን ካይኗ ሳልነቅል ወደ ፊቷ ተጠጋሁ:: የሚገዳደረኝም ሆነ የሚያግደረድረኝ መንፈስ ፊቷ ላይ አላነበብኩምና ፊቴን ወደፊቷ ይበልጥ አስጠጋሁት እንጂ ወደ ኋላ አላፈገፈግሁም:: እናም ከንፈሬ ከንፈሯን አወቀው::

ሆነም::

"ስለአሳሳትኩሽ ይቅርታ!" አልኳት፣ በመሳሳሙ ብዙ ከሄድንበት በኋላ:: ስህተት ያልኩትን ነገር እንደስህተት እንዳልቆጠርኩትና እንዳልቆጠረችው ገብቶኛል::

መንገድ ስንሄድ የብዙዎች ዐይን መነን ላይ ያርፋል:: የት ነበር ያየናት በሚል ስሜት:: "ካንቺ ጋር መታየት ከጀመርኩ በኋላ ዝነኛ አርገሽኛል" እላታለሁ::

"ዕድሜ ቲቪ ላይ ለተላለፈልኝ የሳሙና ማስታወቂያ! ሲሳይ ግን ተቆጥቶኛል"

"ምነው?"

"ቀንቶ ነዋ! እኔን ሳታስፈቅጂ እንዴት ሠራሽ አይለኝ መሰለህ? ድርጅቱ ማስታወቂያ እንድትሠሪለት የመረጠሽ አንቺን የት አግኝቶሽ ነው? እያለ እየጨቀጨቀ አስጨነቀኝኮ!" አለችኝ፤ ጭቅጭቁም ጭንቀቱም ፊቷ ላይ እየታየ::

"የት እንዳገኙሽና እንዴት እንደመረጡሽ አትነግሪውም ነበር?"

"መች ያምነኛል? ደግሞ ሲቀና እንዴት እንደሚያምርበት ባየህ? ላለማልቀስ ራሱን የሚያስገድድ ሕጻንን ልብ ብለህ ታውቃለህ? ቁልጭ እነሱን!" አለች፣ ሣቋ እየመጣ::

የሁለታችን ነገር...

በሌለችበት ጥፋተኝነት ይሰማኛል:: የጀመርነው የፍቅር መንገድ በአጭሩ መቋጨት እንዳለበት ይሰማኝና አቋሜን ለራሴ አውጃለሁ:: ከእሷ ጋር ስሆን ግን ይብስብኛል:: ታምረኝና 'እሳሳታለሁ':: ራሴን የታዘብኩት? ስንት ጊዜ ነው

አንድ ቀን ቤቴ ቀጠርኳት:: ሳታወላውል ታዘዘችኝ:: መጣች:: መስተንግዶዬን ወደደችው:: አልጋዬን ተላፋንበት::

"ለምንድነው ካንተ ጋር ስሆን መቅበጥ የሚያምረኝ? ለምንድነው አዲስ ሰው የምሆነው?" ብላ ጠየቀችኝ፣ አንድ ቀን::

የምላት ጠፋኝ::

አቤት ዕርቃኗን ስትሆን!

ብዕር አውጥታ ጣቶቼ መሃል አኖረችና ጡቷ ላይ ስሜን እንድጽፍላት አዘዘችኝ::

“ሲሳይ ቢያየውስ? ቢያይብሽስ?” አልኳት፣ ስሜታዊ መሆኗን እንዲገባት እና ከትዕዛዟ እንድትታቀብ ብዬ::

ለምቦጯን እንደመጣል አድርጋ፣ “እሱ ጡቴን ሊያይ አይችልም:: ጡት መደባበስ ስሜት አይሰጠውም:: ጡት ሥጋ የለበሰ ጉንጭ እንጂ ሌላ ምንም ማለት አይደለም ብሎ ጡቶቼን አጣጥሎብኛል:: አንተ ነህ - እሱ የጣላቸውንና ያጣጣላቸውን ጡቶቼን ሞራል ሰጥተህ ያነሣሣኻቸው... አይገርምህም ግን፣ ከሲሳይ ጋር መውጣት ከጀመርን ዓመት አልፎናል:: ግን አንድም ቀን፣ መብራት ጠፍቶ ያለንበት ክፍል ካልጨለመ በቀር፣ አቅፎኝ አያውቅም:: አንተ ግን...” በአድናቆት አየችኝ::

ሌላ ቀን ደግሞ....

“አንድ ነገር ላስቸግርህ ነው?”

“አንድ አይደለም አንድ ሺህ አንድ ቢሆኑ እንኳ እተባበርሽ  ዘንድ ልቤ ግድ ይለኛል”

አገላላጼ  ሣቋን አመጣው::

“እኛ ቤት ልወስድህ ነው:: እወስድህና ካባቴ ጋር አስተዋውቅሃለሁ:: ትላንት ማታ ስላንተ ብዙ አውርቼዋለሁ”

“ምን ብለሽ? ማን ነው ብለሽ?”

“አለ አይደል፣ስለአንዳንድ ነገሮችህ:: በእውነቱ አባቴ እንዲያገባኝ የሚመኘው ዓይነት ወንድ ስለሆንክ ልትደሰት ይገባሃል...” አለች፣ ሣቋን እያንደላቀቀችው::

“መነን!”

“አቤት!”

“እየቀለድሽብኝ ነው ልበል?”

“አባቴ ይሙት! ‘በህይወት እያለሁ ባል እንዲሆንሽ የምትመርጪው ሰው ማወቅ እፈልጋለሁ፤ እባክሽን አምጪውና እጆቹን ልዳብሳቸው፤ ድምጹንም ልስማው’ ብሎኛል”

“እና ልታገቢኝ ነዋ?”

“የማገባው ሲሳይን ነው” አለች፣ ቁርጥ ብላ ውሣኔ፡፡

“ታዲያ ከአባትሽ ጋር ማስተዋወቅ ሲሳይን ነዋ፡፡ እኔ ምን ቤት ነኝ?” የቀና ልብ ይጠቀምበታል ብዬ በምገምተውና መጠቃት በሚስተዋልበት ድምጽ መልስ ሰጠኋት፡፡

“አባዬ ሲሳይን በተደጋጋሚ በመንግስት ቲቪ ያየዋል፡፡ በመንግሥት ቲቪ መታየት የሚያበዛ ሰው ደግሞ ከገዢው *ፓርቲ* ጋር የተለየ ግንኙነት አለው ብሎ ይገምታል...”

በዝምታ መስማቴን ቀጠልኩ፡፡

“እና አንድ ውለታ እንድትውልልኝ ነው፡፡ ለአባዬ ስላንተ ያወራሁት ያልሆንከውን ነው፡፡ አንተ ከምትለው እና እኔ ከነገርኩት ታሪክ ጋር ልዩነት እንዳይፈጠር! ልትዋሸው ቃል ትገባልኛለህ?” ብላ ያስገረመኝን ሃሳብ አመጣች፡፡

መገረሜን ፊቴ ላይ አይታዋለች፡፡

“ይከብድሃል?”

“ያልሆንከውን ስትይ አልገባኝም”

“እንዴት ብዬ ልንገርህ? አለ አይደል መንግሥትን የሚተናኮል ድርሰት በመጻፍህ በደህንነቶች ክትትል እንደሚደረግብህ...እና በዚሁ ሰበብ በየጊዜው እስር ቤት እንደምትመላለስ ...እና የገዥው *ፓርቲ* አባል እንድትሆን የቀረበልህን ጥያቄ ባለመቀበልህ የደህንነት አባላት ከማስፈራራት አልፈው ማንነታቸው ያልታወቁ አፋኞች ጉዳት እንዳደረሱብህ...ሌላም ሌላ!”

“አሁን ያወራሽውን ሁሉ የኖርኩት አስመስለሽ ተርከሽላቸዋል?”

“ከቅዱሳን ውሸቶች መሐል እንደ አንዱ ትቆጥርልኝ ዘንድ በትህትና እማፀንሃለሁ...” አለች፣ እየሣቀች::

“መዋሸቱ ለምን አስፈለገ?”

“አባቴ እኔን እንዴት ላለ ወንድ መዳር እንደሚፈልግ አውቃለሁ:: አንድ ነገር ብነግርህ ግን አትታዘበኝም?”

“ሳልሰማው መወሰን ይከብደኛል፤ንገሪኝ” አልኳት:: የምትመርጣቸው ቃላትና የፊቷ እንቅስቃሴ ትኩረቴን ሰርቀውታል::

“አባቴን እንድታስፈራራልኝ እለምንሃለሁ”

ጆሮዬን አላመንኩትም::

“ይህን ስልህ እንደሚገርምህ አውቃለሁ:: ግን አባቴን እንዲያስፈራሩልኝ ከመረጥኳቸው ወንዶች መሃል ሌሎች ያንተን ያህል ሊሳካላቸው እንደማይችል ስለገመትኩ ነው ሌሎቹን የተውኳቸው:: አባቴን እወደዋለሁ:: የሚወደውን ነገር ደግሞ እንዲያጣ አልፈልግም:: አባቴ የሚያስፈራራው ሰው ይፈልጋል”

እንዲህ ስታወራኝ ጤንነቷን ተጠራጠርኩ::

“መነን ነገር እያወሳሰብሽብኝ ነው?”

“ምንም የሚያስፈራ ነገር የለውምኮ”

“ቆይ እስኪ አባትሽን ማስፈራራት ለምን አስፈለገ?”

“ፍርሃቱን ይፈልገዋል”

“አልገባኝም!”

“አባዬ ከዚህ መንግሥት ጋር የሚጋጭና የሚተናነቅ የፖለቲካ ሰው ይወዳል:: እሱም የተቃውሞ ግጥሞቹን የሚጽፈው አምኖባቸው ብቻ ሳይሆን

የተሰማውን ስሜት ለመግለፅ ምንም የማይፈራው ነገር እንደሌለ ለማሣየትም ጭምር ነው።"

እንዴት የሚገርሙ አባት ናቸው?

"ይከብድሃል?"

"ምኑ?"

"አባዬን ማስፈራራቱ?"

"ምን ብዬ ማን ነኝ ብዬ? ዝም ብሎ ከምድር ተነስቶ ማስፈራራት አለ እንዴ?"

"ያልሆንከውንና ያልኖርከውን የፖለቲካ ህይወት ስትተርከለት ይደሰታል:: እሱም የጻፋቸውን ያነብልሃል:: አንተም እስከዛሬ ከተፈጠሩት የፖለቲካ ተንታኞች በስንት እጥፍ እንደሚልቅ አስረግጠህ ንገርልኝ:: ከዚህም በላይ ብስለት የተሞላባቸውና በጥልቅ ፍልስፍና የተሞሉ ጽሑፎቹ በደህንነት ሰዎች እጅ ቢገቡ ኖሮ በህይወቱ ላይ አደጋ ሊያንዣብብ እንደሚችል ተርከለት"

"ይህ ሁሉ የተቀነባበረ ሴራ የት ለመድረስ ነው?"

"የተረዳሽኝ መስሎኝ ነበር"

"ከአባትሽ ጋር የምናደርገው የሌባና ፖሊስ ጨዋታ ጥቅም በቅጡ እንዲገባኝ አላደርግሽም እኮ ነው የምልሽ"

አኮረፈችኝ:: ኩርፊያ እንኳን ያምርባታል::

"እስከሁን ካወራሁልህ ውጪ ዛሬ ጨምሬ የምነግርህ የለኝም! ሐሙስ አመሻሽ ላይ ቤትህ እመጣለሁ፤ ግንኮ ያ ቀን ክላስ አለን:: ክላስ ባንገባ ቅር ይልሃል?"

"አንቺ ትበልጪብኛለሽ" አልኳት፣ ዐይኖቿን እየሣምኩ::

አዝናብኛለች ልበል? ጨልማለች::

ሐሙስ:: አመሻሽ ላይ...

“ምን አባቴ እንደሚሻለኝ...አባዬ ህመም ፀንቶበት ስጋት አድሮብኛል:: ደም ብዛቱ እየተነሣበት ስንጨነቅ ስንሣቀቅ ነው የምናነጋው!” እንደተገናኘን ነው ይህን ያለችኝ::

“አይዞን ይሻላቸዋል” አልኳት::

ቦርሣዋን ከፍታ ጋዜጣ አወጣች:: ገጾቹን ገላለጠቻቸው::

“ምንድ ናቸው?”

“አነብልሃለሁ”

አንድ የጋዜጣው ቋሚ አንባቢ፣ ‘የኢትዮጵያ ሥነ ጽሑፍ ውድቀት መነሻዎች’ በሚል ርዕስ የሀገሪቱን መንግሥታት ተጠያቂ አድርጐ የጻፈው መጣጥፍ ነው:: ‘ዮፍታሄ ንጉሴ፣ ዮሐንስ አድማሱ፣ አቤ ጉበኛና በዓሉ ግርማ በመሪዎቻችን ሰበብ አጥተናቸዋል:: በዘውዱ ሥርዐትም በደርግ መንግሥትም እምር የሆኑ የብዕር ሰዎችን አጥተናል:: አሁን ደግሞ ማንን እናጣ ይሆን?’ ይልና ጽሑፉን ሲቋጭ፣ ‘አቶ ቢልልኝ ምንገዶት ያሰጋቸዋል’ ብሎ ስጋቱን ይጠቁማል::

አንብቤ ስጨርስ ቀና ብዬ አየኋት::

“ማነው እንዲህ የሚጽፉባቸው? እንዴት ያለ ቀላማጅ ብዕረኛ ነው እንዲህ አባትሽ ላይ የሚያሟርተው?” አልኳት::

“ኧይ አንተ! ቀላማጅ ብዕርተኛ አልከው?” ሣቀች... ከት ብላ:: ዐይኗ ውስጥ ያለው የጨለመ ነገር ግን በሣቋ ብርሃን ጨርሶ ሊጠፋ አልቻለም፤ እና በሣቋ መሃል፣ “አባቴኮ ነው የጻፈው” አለችኝ::

ተደንቄ ሰማኋት::

እኚህ አባት ልክ እንደ መነን ናቸው:: የሆኑ ተአማኒነት የጐደለው ገፀባህርይ የሚመስሉ::

“እኔ የምልሽ መነን፣ አባትሽ አቶ ቢልልኝ እንዲህ በመጻፋቸው ምንድነው የሚያገኙት ጥቅም?”

"አባዬ ከልጅነት አብሮ አደጎቹ ጋር ሲገናኝ ሃፍረት ነፍሱን ትጫወትበታለች:: በዚያን ዘመን ከነበሩት ወጣቶች ጉን ተሰልፎ የሚጠበቅበትን ሃላፊነት ስላልተወጣ ሁሌም ይቆጨዋል:: ጓደኞቹ ነፍሳቸውንም ቢሆን እንኳን አሳልፈው ሊሰጡ የተዘጋጁበት የፖለቲካ አላማ ነበራቸው:: እሱ ያልኖረውን ሕይወት አንቆለጳጵሰው ሲተርኩለት የበታችነት ስሜት ይሰማዋል:: ያኔ ያጣውን የጀብደኝነት ስሜት በአሁኑ ዘመን ሊያገኘው ይሞክራል:: አልኮሆል በተጎነጨ ቁጥር መንግሥትን ማንኳሰስ፣ማብጠልጠል ይይዛል:: ያኔ ታዲያ በሰማኸው ነገር ተደናግጠህ አፉን እንዲይዝ ስትገስፀው እንጂ በቸልታ ስታልፈው አይወድህም:: ለሃቅ ሟች ነው መባልን ይፈልጋል"

ግራ ይገባኝ ጀምሯል:: ሰው ሣይኖረው ባለፈው ህይወት ይህን ያህል ይቆጫል እንዴ?

አባቷን በአካል እስካውቃቸው ቸኩልኩ::

በዚያው ሰሞን መነን ደውላ በአስቸኳይ ልታገኘኝ እንደምትፈልግ ነገረችኝ:: ትምህርቷን መከታተል እያቆመች ነው:: አብዛኛው ጊዜዋን የምታውለው አባቷን በማስታመም ሆኗል::

ከቀጠረችኝ ሰዐት ቀደም ብዬ ተገኘሁ። ዘግይታ መጣች::

ሰላምታዋን በወጉ ሳትጨርስ፣ "ሲሳይን አይተኸው ታውቃለህ? ተጣላንኮ!" አለችኝ፣ በሚያሣዝን ድምጽ::

ተናደድኩበት:: ቀንቼ ሣይሆን አይቀርም:: እንዲህ ራሷን ጣል አድርጋ ፊቷ ፈገግታ ተርቦ እፊቴ ስትቀርብ እንደምን አልናደድ፣እንደምን አልቀና:: እንዲህ ራሷን ጣል ማድረጓ በአባቷ ሃሣብ ስለተወጠረች ነው ብዬ አሰብኩ እንጂ ሲሳይን ስለተጣላችው ነው ብዬ መች ጠርጥሬ?

የአባቷ ጉዳይ ግን አስገራሚ ሆኖብኛል:: ካስተዋወቀችኝ ጊዜ ጀምሮ እንድርቃቸው አይፈልጉም:: ያላንዳች ጥርጥር እንደ ልጃቸው 'ባል' ቆጥረውኛል።

"‹ሀገሬ ተራምዳ ካልረገጠች ርካብ፤ ነገራችን ሁሉ የእንቧይ ካብ የእንቧይ ካብ!› ብሎ የገጠመውን ባለቅኔ አታደንቀውም?" ይሉኛል አንዳንዴ፣ መረጋጋት ሲሰፍንባቸውና ጤናቸው መለስ ሲል::

"ቀኝ ጌታ ዮፍታሄ ንጉሴ ትልቅ ሰው ነበር" እላቸዋለሁ::

"ትልቅ ሰው ብቻ? የትልቅም ትልቅ፤ ሊቀ ሊቃውንት የቅኔ አለቃም ጭምር ነበር እንጂ! ምን ዋጋ አለው፣ እዚህ ሀገር መች ሀቀኛ ይወደድና! ዮፍታሄን ለምን እንደማደንቀው፣ ለምን እንደምወደው ለሱ መታሰቢያነት የሚውሉ አስራ ሦስት ግጥሞችንስ ለምን እንደጻፍኩ ታውቃለህ?"

"አላውቅም"

"ማወቅ አለብህ"

"እሺ..."

የያዙትን ጋዜጣ እያጠፉ፣ "ባለቅኔው - ብዙ መሥራት ሲችል በአጭሩ የተቀጨው፣ በሀገር ፍቅር ስሜት ልቡ የነደደው ገጣሚና የኢትዮጵያ ዘመናዊ ቴአትር አባት ዮፍታሄ ንጉሴ - ነገረ ሥራው ከማን ጋር እንደሚገናኝ ልብ ብለሃል?"

"ልብ አላልኩም፤ ከማን ጋር ነው የሚገናኘው? እንደሱ ዓይነት ተወርዋሪ ኮከብ ከስንት ዓመት አንዴ ነው፣ ብልጭ ብሎ ጥፍት የሚለው..." አልኳቸው፣ ሞቅ አድርጌ:: እሳቸው ግን እንዲህ ባለ ሁኔታ ተተኪ የለሽነቱን፣ አምሳያ አልባነቱን በመመስከሬ ቅር ብሏቸዋል::

"ምነው?"

"ዐይንና ቅንድብ ቢቀራረቡም አይተያዩም የሚባለው ብሂል ትዝ አስባልከኝ"

"እንዴት?"

"እንዴ አታየኝማ - አላይኸኝማ! በመንግሥት ከርን የተደቆስክ፤ በመንግሥት ምላስ የተሸነቆጥክ፣ አምባገነናዊ አገዛዝን በብዕርህ መጋዝ ገዝግዘህ ለመጣል የተነሣህ አንተ እንዴት እኔን ከዮፍታሄ ንጉሴ ጋር ማመሳሰል ይሣንሃል?"

ሣቄ መጣ:: ልውጣ፣ ልውጣና ልፈንዳባቸው የሚለኝን ሣቄን ተቆጣሁት::

"ለምን መሰለህ? በፋሽስት ወረራ ጊዜ ወጣት ብሆን ኖሮ ላስባቸው የምችላቸውን ሃሣቦች ዮፍታሄ አስቧቸው አልፏል፤ ከትቧቸው አርፏል፤ ያኔ

ብኖን ኖሮ ልቀኝባቸው በምችላቸው ጉዳዮች ሁሉ ባለቅኔው ዮፍታሄ ንጉሤ ገጥሞባቸዋል:: ኧረ ስንቱ!"

ፖለቲካዊ ጭብጥ ያዘሉ ጽሑፎች ለመጻፍ በመታደሌ ያደንቁኛል:: ጹሑፎቼም መዘዛቸው ከፍቶ ለእስር እንድዳረግ ምክንያት ስለሆኑ ሊቀናብኝ እንደሚገባ ይነግሩኛል::

እኔም ለማስተባበል ጉንጬን አላለፋም:: ይልቁንስ በምጽፋቸው ጹሑፎች የተነሣ የደህንነት ሰዎች ስለሚያደርሱብኝ በደል - ባለስልጣናት ለህይወትህ አታስብላትም ወይ፤ ለምን አርፈህ አትቀመጥም እንደሚሉኝ - እኔ ደግሞ በእምቢታዬና በአቋሜ በመፅናቴ ድሮ ቀበሌ ለወላጆቼ የሰጣቸውና እኔ የወረስኩትን ቤት ለመንጠቅ እንደሚያስቡ...ሌሎችም የሚያሣዝኑ ዜናዎች::

አቤት! እንዴት ነው በምፈፅማቸው ጀብዱዎች የሚደሰቱብኝ (ለነገሩ እኔም ራሴ በምፈጥረው ታሪክ መመሰጥ ጀምሬያለሁ)

ሁሌም እተኙበት አልጋ ጐን እንድቀመጥ በምልከት ያዙኛል:: አንድ ቀን ግንባሬን ስመው፣ እጄንም በፍቅር እየዳበሱ፣ "ልጄ! የሞቴን ቀን አላውቀውም፤ ግና መልዐከ ሞት አፍንጫዬ ስር ተገትሮ የቆመ ነፍሴን ሊነጥቅ እየተጣደፈ እንደሆነ ይገባኛል:: ያም ሆኖ የሚያስፈራኝ አንዳችም ነገር የለም:: በፊት የልጄ ጉዳይ ያሳስብኝ ነበር፤ አሁን ግን ይኸው! አባቷ መሆን የሚፈልገውን ዓይነት ሰው ለጋብቻ ትመርጥ ዘንድ የአምላክ ፍቃድ ሆነ..." አሉኝ::

የተባልኩትን ምንም ሳልቀንስና ሳልጨምር ለመነን ነገርኳት::

ምንም አልመሰላትም::

ከፋኝ:: ምንም ስላልመሰላት ብቻ ሳይሆን፣ ለእኔ ያላት ስሜት እየቀዘቀዘ የመጣ መስሎ ስለታየኝም ጭምር ነው የተከፋሁት:: ድራማውን በጥሩ መንገድ እየተጫወትኩላት እንደሆነ ለምን ልብ እንዳላለች ሊገባኝ አልቻለም:: ዐይኖቿን ሳያቸው፣ "ነገ ከነገወዲያ ልተውህ ስለምችል ካሁኑ ራስህን አዘጋጅ" እንደሚሉኝ ተሰማኝ::

አንድ ቀን ከአባቷ ጋር ስናወጋ አመሸንና፣ "ቢቃ ተነስ ሰዐቱ ሄዶብሃል፤ ተባረክ ልጄ! መነን ተነሽ፤ሸኚው" አሏት:: ስትሸኘኝ፣"አባትሽ ሲሳይን አያውቁትም::

ቢያውቁትም የሚወዱት ዓይነት ሰው አይደለም። ባለፈው እንደነገርሽኝ ከሆነ ደግሞ አንቺ ለትዳር መርጠሽዋል:: እንዴት ነው፣ አሁንም በሀሣብሽ እንደፀናሽ ነሽ ወይስ?"

"ምትጠይቀኝ ምናይነት ጥያቄ ነው?" አለችኝ፣ ግልፍ ብሏት::

"አባትሽ የሚጠሉትንና እንደ አጥፊያቸው ከሚቆጥሩት መሐል አንዱን ለራስሽ ስታደርጊ ምን ይሰማሻል እያልኩሽ ነው?"

"አሁን እንዲህ ላለው ጥያቄ መልስ የምሰጥበት ጊዜ አይደለሁም ያለሁት..." አለች፣ በተበሳጨ ድምጽ::

ፀጥ ተባባልን::

በጥያቄዬ አፈርኩ:: ዶሮ ብታልም ጥሬዋን ብዬም በራሴ ላይ ተረትኩ::

ይኸው ዛሬ ደውላ መጣላታቸውን ‹አበሰረችኝ::› የዜናው የምስራችነት ለኔ ነው:: እናም፣ "እንዳስታርቃችሁ ነው የምትነግሪኝ፤ አማላጅ ሆኜ ራሴን እንስገባ?" አልኳት፣ ሃሳቧ ይሄ ከሆነ እንድትሰርዝ እና ተባባሪ እንዳታደርገኝ በሚጠቁም ቅላጼ::

"ሲሳይን ካጣሁት ምክንያቱ አንተ እንጂ ሌላ ማንም ሊሆን እንደማይችል ልትዘነጋው አይገባም"

ዝም አልኳት::

እሷ ግን ቀጠለች:: "በተደጋጋሚ ጊዜ ካንተ ጋር ስላለኝ ወዳጅነት በተለያዩ ሰዎች አፍ ሰምቷል:: ከመጠን በላይም ታግሶኛል:: አየህ ከአባቴ ጋር መተዋወቅ እየፈለገ መንገዱን ዘግቼበታለሁ፤ ደግሞ ታውቃለህ፤ ቢገናኙ አባቴ ጥላቻውን የሚያሳውቀው መነጋገር ከመጀመራቸው በፊት ነው:: ሲሳይ እንዴት እንደሚሳቀቅ አስበው እስኪ! እሱ ደግሞ በአባቴ ዘንድ የመወደድና የመፈለግ ከፍተኛ ረሃብ አለበት"

ማንን አብልጣ ይሆን የምትወደው? ከሁለታችን ማንን ማስቀደም እንዳለባት ግራ ሳትጋባ አትቀርም::

"መታረቅ አለብኝ" አለች መነን፤ ሰማይ ላይ ወደተበተኑት ከዋክብት ዐይኖቿን ልካ፣ "መታረቅ ነው የሚያዋጣኝ..."

እንዲህ ስትለኝ ንድድ አልኩ:: ይህንን ውሳኔ በአንደበቷ ስሰማ ቅናቴ...

"አድርጊዋ! ታረቂዋ! ታረቅሽው ተጣላሽው ምን እንዳይጎድልብኝ፤ የሚያዋጣሽን የምታውቂው አንቺ ነሽ"

እንዳልሰማች ሆና ቀጠለች::

"ሲሳይን ፊት ካልሰጠሁት አባቴ የሚያስፈልገውን መድኃኒት በእጄ ማስገባት አይሆንልኝም:: ሲሳይ ተሯሩጦና ጓደኞቹን አስቸግሮ ከውጭ ሀገር ይዘውለት እንዲመጡ ካልተማፀናቸው በቀር፣ አባቴ የታዘዘለትን መድኃኒት ማግኘት አስቸጋሪ ይሆንብኛል..."

እውነቷን ነው::

"ትላንት ቤቱ ደውዬ መልዕክት አስቀመጥኩ:: ሲሳይ ሊያገኘኝ እንደሚፈልግ አውቃለሁ:: እንዴት ላያውቅ ይችላል? ደግሞ ካንተ ጋር የሆንኩትን ሁሉ ያውቃል፤ በየቤቱ ስንት አቃጣሪ አለ መሰለህ፤ ምን አውርቼ ልደር ባይ! እና ስለእኔና ስለአንተ ተነግሮታል፤ነግረውታል፤ አምኗቸዋልም..."

ትንሽ ቆየችናም፣ "ልትቸገርልኝ ፈቃደኛ ከሆንክ ግን አንድ ነገር ከልቤ ልለምንህ፤ ላልተወሰነ የጊዜ ገደብ እኔና አንተ እንለያይ፤ አንተያይ:: አባቴ እንዲድን ከፈለግህ አንዱ መንገድ አንተን አርቆ ሲሳይን ማቅረብ ነው"

ዐይኗ ውስጥ ዕንባ አየሁ:: እውነቷን ይሆን? ወይስ እንዳምናት ፈልጋ ነው ዕንባዋን የምታሣየኝ? ወይስ ብቸኛው መፍትሔ ይኼ ሆኖ?

"እስከ መቼ?" አልኳት፣ መደንገጤን እንዳታየው ተጠንቅቄ:: ልብ ብሎ ላጤናት፣ የተበደረችውን እንድትከፍል አስጨንቀው ሲይዟት፣ የመክፈያ ጊዜ እንዲራዘምላት እንደምትማፀን እናት ትመስል ነበር::

"እስከ መቼ መነን?" ጥያቄውን ደገምኩት።

"እኔ እንጃ!"

"እንዴት አኔንጃ?"

"ስታስፈልገኝ አደውልልሃለሁ" አለችኝ፣ ዝግ ባለ ድምጽ::

ፊቷ ፀፀት አርግዟል::

"መነን!"

አየችኝ:: ጥያቄዬ ገብቷታል:: ቢገባትም ከአንደበቴ እንድትሰማው ብዬ ጠየቅኋት፤ "ልትተይኝ እያሰብሽ ነው አይደል?"

አልመለሰችልኝም:: ዐይኗ ሰሌዳ ላይ ግን አራት ፊደላት ያነበብኩ መስሎኛል:: "በ-ፍ-ፀ-ም!"

ከሦስት ቀናት በኋላ ድምጽዋን በስልክ ስሰማው በመፍነክነክ ተሞልቶ ነበር::

"ምን አዲስ ነገር አግኝተሽ ነው?" አልኳት::

"አባዬ ሊድንልኝ ነው!" ለዓመት በዓል አዲስ ልብስ ተስፋ እንደሰጡት ደሃ ብላቴና ፍንድቅድቅ ብላለች::

"ሲሳይን አግኝተሽው ነበር ማለት ነው?" አልኳት፣ መድኃኒቷን ሊያገኝለት የሚችል ብቸኛ ሰው መሆኑን ደጋግማ የነገረችኝን አስታውሼ::

ደስ ስላላት ደስ ብሎኛል:: ልትደሰት የቻለችው በሲሳይ አማካይነት እንደሆነ ሳስብ የመበለጥ ስሜት ተሰማኝ:: በውለታ አስሮ እንዳያሸንፈኝና እንዳያሸነፋት ብዬ ሰጋሁ::

"ፋዘር እንዴት ናቸው? ደም ብዛቱ እየተስተካከለላቸው አይደለም?" "ካንተ ሃሣብና ናፍቆት በስተቀር..." አለችኝ ስቃ:: ስትስቅ ከሰማኋት ብዙ ጊዜዬ ስለሆነ ነው መሰል፣ ነፍሴ የሃሴትን ወይን ተጎንጭታ ለስካር ራስዋን ስታዘጋጅ ታወቀኝ:: "በጣም ወዶሃል- በጣም!"

"እኔን አይደለም የወደዱት፤ አንቺ በፈጠርሽውና ባዘጋጀሽው ድራማ ውስጥ እኔ ወክዬ የምጫወተውን ገፀባህርይ እንጂ..."

ሣቋን ስታሰማኝ ቆየችና "አይገርምም ግን? ስላንተ ሲያስብ በወኔ ይሞላል፡፡...ማታ ደግሞ አንድ ጽሑፍ ሲያስጽፈኝ ነበር፡፡ በሽታውን ለመርሣት ምክንያት በማግኘቱ እኔ ያንተዋ ደስ እያለኝ ነበር፣ ስቸከችከ ሌቱን ያነጋሁት..."

ያንተዋ! የሚለውን ቃል በድምጿ ውስጥ አገኘሁትና ደስ አለኝ፡፡ ያንተዋ! ያንተዋ!

*ብራቮ!*

የአባቷ የጤንነት ሁኔታ አሁንም አስተማማኝ ደረጃ ላይ አልደረሰም፡፡ በሲሳይ አማካኝነት ይገኛል የተባለው መድኃኒትም የውሃ ሽታ ሆኖ ቀርቷል፡፡

ልጠይቃቸው ወደ ግቢያቸው ስዘልቅ፣ቤቱ ሕመምተኛውን ለመጠየቅ በመጡ ጐረቤቶች፣ ወዳጆችና ዘመዶች ተሞልቶ ነበር፡፡ የተለመደው አሰልቺ ጥያቄ ከየአቅጣጫው ይወረወራል፡፡

- መቼ ነው የጀመራቸው? ዶክተሮች በሽታቸው ምንድን ነው አሉ? ለምን የኡራኤል ወይም የኪዳነምህረት ፀበል አታስጠምቂያቸውም? ለምን ወደ ባሕላዊ መድኃኒት አዋቂዎች ዘንድ አትወስጂያቸውም..."

መነን ለእያንዳንዱ ጥያቄ ያለመታከት መልስ ትሰጣለች፡፡

አባቷ እንቅልፍ ላይ ናቸው፡፡

"እንዴት ናቸው አሁን?" አልኳት፡፡

"ደህና ነው፡፡ ግን ሰሞኑን ፊቱ ላይ ያልተለመደ ስሜት አይበታለሁ፡፡ እያንዳንዱን ነገር በስስትና በናፍቆት ነው የሚያየው፡፡ ለአንዴና ለመጨረሻ ጊዜ በሚመስል ሁኔታ..." አለኝ ተረብሻ፡፡ ድምጽዋ ብቻ ሳይሆን ሁለንተናዋ ተረብሿል፡፡ አለባበሷ...አነጋገሯ... አረማመዷ...

"ማታ ስለምንድነው ያስጻፉሽ?" አልኳት፣ ርዕስ ለማስለወጥ፡፡

ላለመረበሽ ወደ በረንዳ ወጣን፡፡

"ያው መንግሥትን ወቀሣ ነው"

አሳዘኑኝ::

ምናለ መንግሥት ላንድ ሁለት ቀን ቢያስራቸው? አስሮ አስፈራርቶ ቢለቃቸው? መንግሥት ግን ረስቷቸዋል:: እንኳንስ ሊያስራቸው፣ እንኳንስ የጻፉትን ጽሑፍ እንደ መረጃ ጠቅሶ ሊሟገታቸው፣ ስማቸውንም ሰምቶ የሚያውቅ አይመስልም::

"ትላንት እነዚያ በባለፈው ስርአት ስለፈፀሙት ጀብድ መተረክ የማይታክታቸው አብሮ አደጎቹ እዚህ ነው ያመሹት:: ከነሱ ጋር በተገናኘ ቁጥር የሚሰማውን የበታችነት ስሜት ለማጥፋት ብሎ ከመንግሥት ጋር ታግሎ የማሸነፍ ሞራሉ ይነሣሣል..." አለችኝ::

"ከመንግሥት ጋር ታግሎ የመሸነፍ ሞራል..."

ይህች መነን በትክክል አባቷን መግለፅ ትችላለች:: ወደ መኝታ ቤታቸው ደርሳ ስትመለስ ከእንቅልፍ መንቃታቸውን ነገረችኝ::

አገኘኋቸው::

የዘረጉልኝን እጅ ስጨብጥ፣ "ከትላንት ወዲያ ምን የመሰለ ሸጋ ጽሑፍ ጻፍኩ መሰለህ? ለእነዚህ መሪዎቻችን ልክ ልካቸውን ነገርኳቸው! ሰሞኑን እንቅልፍ አሣጥቼ ነው የማከርማቸው!" አሉኝ በደስታ:: ልብ ብዬ አይቻቸዋለሁ:: ሲሳይ ይዞላቸው ከሚመጣው መድኃኒት ይልቅ በእኔ አንደበት የሚያደምጧቸው የማስፈራሪያ ቃላት ሲያበረታቸው አይቻለሁ::

እና፣ ባገኙኝ ቁጥር፣'አደራህን ልጄ፤ ጥለኸኝ አትሂድ በጥንቃቄ ጠብቀኝ› ይሉኛል:: ሕመሙ እየጠናባቸው መጥቷል:: ወደ መንግሥት ሆስፒታል ገብቶ መታከም ደግሞ ፈርተዋል:: ሐኪሞች በመንግሥት የደህንነት ሰዎች ታዘው የተሳሳተና መርዝ ከኒን አስገድደው ቢያስውጧቸውስ? ደህንነቶች በጠያቂ ዘመድ ተመስለው መጥተው በትራስ አፍነው ቢገድሏቸውስ? ለዚህ ነው የግል በሆነ ከፍተኛ ክሊኒክ ካልሆነ አልታከምም የሚሉት::

"የመነን አባት! እርስዎ በህይወት ቢቆዩልንኮ ስለኢትዮጵያችን የሚናገሩትና የሚያስነብቡን ብዙ እውነት አለ" አልኳቸው፤ እንደተለመደው ብርታት ቢሆናቸው ብዬ::

"ሙች ያሠሩኛል ብለህ ነው፤ እየነው እኮ! ሆስፒታል ብገባ የራሳቸው የሆነ ሰው ልከው ዕድሜዬን በአጭሩ ይቀጩታል፤ለመሆኑ ዛሬ በወጣው ጋዜጣ ላይ የማስታወቂያ ሚኒስቴር ቢሮ እኔን አስመልክቶ ያወጣው የዛቻ ወይም የቁጣ መግለጫ አለ?" አሉ፣ አንድ የጋዜጣ ስም ጠቅሰው።

የመንግሥት ልሳን እንደሆነ የሚነገርለት ጋዜጣ ነው። ጊዜ አግኝቼ እንዳላነበብኩት ነገርኳቸው።

"አደራህን ጠብቀኝ። በደህንነቶች ጥርስ ከገባሁ ዘመን የለኝም! እንከተው እንዳይበሉኝ ከጐኔ አትራቅ"

"አይዞዎት!"

"መነንህ የት ሄደች?" አሉ፣ ድካም ባደቀቀው ድምጽ።

ቶሎ መልስ አልሰጠኋቸውም። ስሟ መጨረሻ 'ህ'ን አስከትለዋል ልበል፣ ወይስ ጆሮዬ ነው?

መነንህ... መነን.... ህ .... መነንህ!

"ዕቃ ልትገዛ ሱቅ ሄዳ ነው አሁኑኑ ትመለሳለች" አልኳቸው።

ከጥቂት ደቂቃ ቆይታ በኋላ ዘመዳቸው የሆነ ነርስ ሊጐበኛቸው መጣ። "አንተ እንጂ ማንም ሰውነቴን እንዲነካ አልፈቅድለትም" ይሉታል፣ በየጊዜው።

መርፌ ወጋቸው። ነርሱም፣ "እረፍት ያስፈልጋቸዋል" ብሎም ወጣ።

አፍታም ሳይቆይ እንቅልፍ ይዟቸው ሄደ።

ከሩብ ሰዓት ቆይታ በኋላ ይሆናል ብዬ ባልገመትኩት ሁኔታ፣ ሲሳይ ወደ ክሊኒኩ መጣ። አባቷ እዚህ እንደሆኑ ማን እንደጠቆመው አላውቅም። ዞር ዞር ብሎ ሰው ፈለገ። የሚፈልገውን አውቃለሁ። በዐይኑ አስሶ አጣት።

ከፍሉ ደጅ ቆሜያለሁ፤ እኔ ብቻ ነኝ ያለሁት።

ዐይኑ ውስጥ እንደገባሁ በንዴት አፈጠጠብኝ:: ይኼ ሰውዬ ዛሬ ሊተናኮለኝ እንዳሰበ ገብቶኛል:: ቅናት ዛሩን አስፍሮበታል::

"የታለች?" አለኝ፣ መነንን ማለቱ እንደሆነ አውቄያለሁ::

"ትመጣለች" አልኩት፣ ተረጋግቼ::

ተንኰራደደብኝ:: ከጥቂት መንኰራደዶች በኋላ ፊቱን በግልምጫ አመላግጦ፣ "ላንዳፍታ እንኳን ከጭኗ ለመውረድ ፍላጎትም ጊዜም ይኖርሃል ብዬ አልጠብቅኩም ነበር" አለኝ፣ በአሽሙረኛ አሮጊት ድምጽ::

"ሥነ ሥርዓት ይኑርህ!" አልኩት::

"ሥነ ሥርዓት የሌለኝ እንደሆነስ?" አለ፣ ጮኽ ብሎ:: "ሥነ ሥርዓት ይለኛል እንዴ? ሥነ ሥርዓት ባይኖረኝስ? አሁን ያልከውን ሂድና ለምታሸኮረምማት ሴት ንገራት..."

ዝም አልኩት::

ወደ ጠብ የሚያመሩ ቃላትን በመጠቀም ራሱን ያሰለጠነና ቅናት ቤቱን የሠራበት መስሎ ታየኝ::

"የት ነው የተኙት?" ቁጣው አልበረደም:: ከዚህ በፊት አቶ ቢልልኝን በአካል አግኝቷቸው እንደማያውቅ አውቃለሁ::

"ተኝተዋል:: ማንንም ባያነጋግሩ ምርጫቸው ነው:: መነን ካገኘሃት በኋላ እሳቸውን ብታገኝ ይሻልሃል"

ለራሷ እንደሚያወራ ሆኖ፣ "እሷ በጭራሽ አባቷን እንዳውቃቸው አትፈልግም:: እኔ ደግሞ የአባቷን ሕይወት ለማዳን ያልፈነቀልኩት ድንጋይ ያልፈረከስኩት ቋጥኝ እንደሌለ ላሳውቃቸው ቆርጬ ተነስቻለሁ" አለ::

"ጠብቃት፤ትመጣለች"

"አንተ ማን ሆንክና ነው፤ የእጮዬን አባት እንዳልጠይቅ ልትከለክለኝ የምትሞክር?"

"እረፍት ላይ ናቸው..." አልኩት፡፡

"ማን እንደሆንኩና ከማን ጋር እያወራህ እንደሆነ ያለማወቅ ከፍተኛ ጥጋብ አለብህ ልበል? አስፈላጊ በሆነ ጊዜና ቦታ አስተነፍስልሃለሁ..." አለኝ፣ አፍንጫዬ ሥር እየተንጐማለለ፡፡ ቀበቶውንም እየነካካ፡፡

ይሄ ሰውዬ ምን እየሆነ ነው?

ጭቅጭቃችንን ሰምተው ነው መሰል አባቷ ነቅተዋል፡፡ "ምንድነው?" አሉኝ በጮከታ፣ ፈራ ተባ ብለው፡፡

"ምንም አይደል" አልኳቸው፣ ምን እንደምል ግራ ገብቶኝ፡፡

በዚህ ጊዜ የአቶ ቢልልኝ የመርበትበት ድምጽ ጎላ ብሎ በቤቱ ተሰራጨ፡፡ "እንዳታስገባው! እንዳታስገባው! እነዚህ አድርባዮችና ዘመናዊ አገዛዝን ናቂዎች ምን አባታቸው እንድፈጥርላቸው ነው የሚረብሹኝ? እንዳታስገባው! ለምንድነው የማትተወኝ፣ ለምንድነው?" አሉ፣ ጮከ ብለው፡፡

"አደራህን ልጄ! አደራህን! ይህን ሰውዬ እንዳታስገባው"

ሲሳይ፣ "መድኃኒት አምጥቼልዎታለሁኮ ነው ያልኩት፤ ገብቶኛል አላወቁኝም!"አላቸው፡፡

እየሰማው ባለው ነገር ተደነጋግጧል፡፡ አባትየው ከውስጥ፣ "ለምንድነው የማትተዉኝ? ድሮም ሀቅ ጽፌው ሲያስነብቡአችሁ አትወዱም፤ በመድኃኒት ልትገድሉኝ እንደምትፈልጉ ሁሉ አውቃለሁ!" ይላሉ፡፡

ሲሳይ ወደእኔ ዞሮ ጮኸብኝ፡፡ "ያልሆነ መረጃ ሰጥተሃቸዋል!"

"ምንድነው ምትለኝ?"

"የመንግሥት ሰላይ ነው ካላልካቸው በቀር እንዴት እንዲህ ድምጼን ሲሰሙ ይርበደበዳሉ?"

"እየረበሸከ ነው!"

"ለጠየቅኩህ ጥያቄ መልስ እንድትሰጠኝ እፈልጋለሁ"

የሽሚዙን እጅጌ ሰብስቧል:: እንድንቦቃቀስ ፈልጓል:: የስድብ መዐት ያዘንብብኝ ጀምሯል:: "የሰው ፍቅረኛን ማማገጥ ምን ማለት እንደሆነ እንዲገባህ አደርጋለሁ" አለኝ፣ በሹክሹክታ::

ምናለ መነን በመጣች? ከመጣች ግን ፀቡን ታበርደዋለች ወይስ ታባብሰው ይሆን?

ከውስጥ ድምጽ ሰማሁ:: አባቷ የሆነ ነገር ሳይሆኑ አይቀርም :: የዕቃ መገጫጨት ይሰማኛል:: መድኃኒቱ ከኪሱ አውጥቶ በጁ ይዞታል:: ወደ ከፍላቸው ለመግባት ይታገለኝ ጀመር:: በአንድ ቦክስ አናቴን አዞረው:: ያሉበትን በር በርግዶት ገባ:: ተከተልኩት::

አቶ ቢልልኝ ከአልጋቸው ወድቀዋል:: ግልኮሱ ተነቅሏል:: ዐይኖቻቸው ፈጧል:: እጄን ወደልባቸው ሰደድኩት::

----

# ማደሪያ

ጫኔ፣ 'የቴአትር ኤክስፐርት' ተብሎ ወሊሶ በተመደበ በዓመቱ፣ ከተሾመ ጋር ድንገት በመንገድ ተገናኙ:: ብቻውን ነበር:: አብሮ አደግ ወዳጁ ብቻውን ሲያዘግም ያገኘው ከምሽቱ የቅዝቃዜ አየር እየተካፈለ ሳለ ነው::

ሁለቱም የሰበታ ልጆች ናቸው:: ዩኒቨርስቲ ገብተው የሁለተኛ ዓመት ተማሪ እስኪሆኑ ድረስ መለያየት በሁለቱ መሃል አልነበረም ነበር::

"ተሼ! ምን እግር ጣለህ?" ብሎ ናፍቆት በተሞላበት ሁኔታ ሠላምታ ሰጠው::

አብሮ አደግ ቢሆኑም ለብዙ ዓመታት ያህል ሳይገናኙ ቆይተው ነበር::

"ጅማ እየሄድኩ ነው፣ *ሥራ ፍለጋ!* እዚህ ከተማ የመጣሁት ዛሬ ነው:: አንተ የምትኖረው እዚህ ነው እንዴ?" አለ ባልተረጋጋ ድምጽ:: አሁንም እንደ ያኔው ንፁህ የአዕምሮ ታማሚ ነው:: ሌላውን ሰው አይተናኰልም:: በሰው ላይ ክፉ ማሰብ የሚችል አዕምሮ ያለው አይመስልም::

ከስንትና ስንት ዓመታት በኋላ ለመተያየት የበቁ ዐይኖች::

ተሾመ ከዓመታት በፊት ብዙ ምዕመናን ማፍራት የቻለ ሰባኪ ሆኖ ነበር:: ከዕለታት ባንዱ ቀን በሕዝቡ ፊት፣ 'ከእንግዲህ እኔና እናንተ አንተዋወቅም፤ ለምትጠይቁኝ የሚመልስ አዕምሮ የለኝም!' ብሎ ራሱን አገለለ:: 'ለምን?' ብለው የሚያውቁት ሲጠይቁት፣ 'ይህች ሃይማኖት ኖሮ የሚያሳይላት እንጂ አውርቶ የሚያሳምንላት ሰው አላጣችም!' ብሎ መለሰ:: መስበኩ አቆመ::

በመሐሉ *የማትሪክ* ውጤት መጣለት:: መጣለትና አዲስ አበባ ዩኒቨርስቲ ገብቶ የፍልስፍና ጥናቱን ይከታተል ገባ:: በሁለተኛው ዓመት አቋርጦ ወጣ:: ምነው ሲሉት ከሴቶች ጋር የማሳልፍበትን ውብ ጊዜ እየተሻማ አስቸገረኝ! አለ:: አለ ተባለ:: ዘግይቶ ግን ከውብ ሴቶች ጋር ፈገግታ መለዋወጥም

አቆመ:: 'የማስላስልበትን ጊዜ ተሻሙኝ' አለ:: 'ተሾመ ለየለት!' ተባለ:: 'ተሳከረበት!' ተባለ:: የሚዘባበትበትም በዛ:: ብቻውን ሆነ:: ቤተሰብ ፀበል ቤት ወሰደው:: ባሕላዊ ሐኪም ቤት ወሰደው:: ለተወሰኑ ወራት ያህል አማኑኤል ሆስፒታልን እንዲያውቅ ተደረገ::

ጥቂት ለውጥ አመጣ:: የማይተናኮል 'ፅዱ ዕብድ' ወጣው::

ጫኔ፣ ተሾመን ትክ ብሎ አየው:: ተጎሳቁሏል:: በአለባበሱ አይደለም:: አለባበሱ እንደማንኛውም ጨዋ ሰው ነው:: "ከትላንት ወዲያ ወዲያ የሚጋብዘኝ አግኝቼ ቁርሴን በልቼ ነበር! ከትላንት ወዲያም በነበረችኝ ሳንቲም ዳቦ ገዝቼ ምሳዬን በልቼ ነበር:: ትላንትም ራቴን ሆቴል ተመግቤ የሚከፍልልኝ አላጣሁም" አለ ተሾመ:: "ዛሬ ከነጋ ጀምሮ ምንም አልበላሁም:: አሁን ከአንተ ጋር ነው ያለሁት!"

ጫኔ፣ በተሾመ ዐይን ውስጥ ያገኘው የመሰደድ ስሜት ልቡን ነክቶታል:: በተሾመ ድምጽ ውስጥ ያገኘው የአለመረጋጋት ስሜት ረብሾታል:: በተሾመ ፊት ላይ የሚያነበው መጎሳቆል አንጀቱን በልቶታል:: ግን መንፈሰ ፅዱ ነው:: ንፁህ ነው:: ሰላማዊ ነው::

ፍንጥር ብሎ ተነሳ:: በድንግዝግዝ ብርሃን ተውጠው ወደአያቸው አሮጊት ተጠጋ:: በትህትና እያናገራቸው እንደሆነ ያስታውቃል::

"ተሾመ!" አለው ጫኔ፣ ከአሮጊቷ እጅ ብዙ ኮተቶችን እንደያዘ የሚያስታውቅ ትልቅ ዘንቢል ሲቀበላቸው ጐንበስ ሲል አይቶ::

"ጠራኸኝ?"

"ና እስኪ!"

መጣ:: ጨለማውን ሰንጥቆት ወጣ:: ጫኔ አጠገብ ቆመ:: ቅር እያለው አሮጊቷን አሻግሮ አያቸው:: አንድ ወጣት ዘንቢሉን ተቀብሏቸው አስፋልቱን አሻገራቸው:: ይህን አየ ተሾመ:: እናም ከፋው::

ፊቱን ወደጫኔ መልሶ፣ "ለምንድነው የጠራኸኝ? ስትጠራኝ ላልመጣልህ ነበር"

"የእሳቸውን ዘምቢል ብትሸከም ኖሮ ሊሰጡህ የሚችሉትን ሳንቲም አስቤ እጥፉን እሰጥሃለሁ ብዬ ነዋ!"

"ለምን?" ብሎ ጠየቀው፣ ግራ እንደተጋባ ሰው ሆኖ:: "ብሸከምላቸው ምን እሆናለሁ - ጨው አይደለሁ አልሟሟ!"

"ደከሞሃል ብዬ ነዋ! በዚያ ላይ ነገ መንገደኛ ስለሆንክ ጉልበት መቆጠብ ይኖርብሃል!" አለው፣ ጫኔ ፈገግ እያለ::

"አስከፋተኸኛል:: ይቅርታ አድርጌልሃለሁ እንጂ በጣም ነው ቅር ያሰኘኸኝ! እንዴ አሁን ቤታቸው ሲደርሱ ለልጃቸው ቢነግሩብኝስ? ዕቃዬን ተሸከም አስፋልት ማሻገር ሲገባው 'ዝም አለኝ!' ብለው ቅሬታቸውን ለአንድዬ ልጃቸው ቢነግሩብኝስ?"

ጫኔ ግራ ገብቶት፣ "ለከተማው አዲስ መሆንህን አውቃለሁ፤ ነግረኸኛልም! አሮጊቷን የት ታውቃቸዋለህ? ልጃቸውንስ?" ብሎ ጠየቀው::

የተቃውሞ ጩኸት በተቀላቀለበት ድምጽ፣ "አንተ! መንገድ ላይ የተቸገረች ሴት ባየህ ቁጥር የምታስበው እናትህን ብቻ ነው እንዴ? ምናይነቱ ነህ በማርያም? እመብርሃን በየዕለቱ በእናቶች ተመስላ የመራራት አቅምህንና ሌላውን የመርዳት ችሎታህን ትከታተላለችኮ! ኋላ ለልጇ ለአለም ቤዛ ልትነግረው! እንቶኔ የተባለ ሰው የሠራኝን ጉድ ሳልተርክልህ ወይም የሠራልኝን ውለታ ሳልነግርህ ትለዋለች" አለ::

ጫኔ ሣቁ መጣ:: ግን አልሣቀም:: ቢስቅ ተሾመን ሊያስቆጣው እንደሚችል ገመተ:: ወይም የሚከፋው!

ወደ ጫኔ ቤት ሄዱ:: ቤቱ አንድ ክፍል ቢሆንም ሰፊ ነው:: ተሾመ ወደ ክፍሏ ጐራ ብሎ ከተቀመጠ ከጥቂት ደቂቃ በኋላ ብድግ ብሎ ጫኔ እግር ስር ተደፋ::

"ምን ሆንክ?" አለው::

"ራት አብሬህ እንድበላ እንደፈቀድክልኝ ሁሉ ካንተ ጋር እንዳድር ደግሞ ፍቀድልኝ"

"ምንም ችግር የለም!" የሚለው ቃል ከጫኔ አፍ ሲወጣ ተሾመ ከተንበረከከበት ተነሳ:: የጉልበቱን አቧራ እያራገፈ፤ ሰማያዊ ጂንስ ሱሪውንና ሱፍ ሹራቡን እያስተካከለ::

ጫኔ ጓደኞቹን አግኝቶ ስለአብሮ አደግ ወዳጁ ቢነግራቸው፣ 'ያንተ ድፍረት ማለቂያ የለው - ብለህ ብለህ ደግሞ ቤትህ ውስጥ ዕብድ ታሳድር ጀመር!' ብለው ይገረሙበት ይሆናል:: ወይም፣ 'ቴአትር አድርገህ ከጻፍከው ካራክተሩን ወከዬ እንድጫወት አንተ ታዘጋጀኛለህ?' ይሉት ይሆናል::

ጫኔ ኒያላ ሲጋራ ከደረት ኪሱ አውጥቶ ለኮሰ:: ማቡነን ሲጀምር ተሾመ ትክ ብሎ የሲጋራውን የሚጨስ ክፍል በንቃት ይከታተል ያዘ:: አጭሶ ጨረሰው:: ይህ ሁሉ ሲሆን ተሾመ ዐይኑን ከጫኔ ሲጋራ አልነቀለም ነበር:: ሲጨርሰው፣ "ቶሎ በል፤ ሲጋራውን አጥፋው" አለው::

"የሲጋራውን ቁራጭ የጣልኩበት ቦታ ለእግርህ አይቀርብም?"

"እኔ ባጠፋው ሲጋራው የእኔን ህይወት ስለሚመስል - በከንቱ ላቃጠላቸው ዓመታት ተቆጭቶ፣ እንደ ጭስ ላቦነናቸው መልካም ዓላማዎቹ ተበሳጭቶ - 'ራሱን ገደለ' ብለው ያስወሩብኛል" ሲል-

"እነማን ናቸው የሚያስወሩብህ?" አለው፣ ጫኔ::

"በውድቀቴ ደስ የሚሰኙ ክፉ መናፍስት ናቸዋ! ይቅር ይበላቸው!"

ሣቀ ጫኔ:: ሣቀ:: ከት ብሎ ሣቀ::

ተሾመም ሣቀ::

"ምናሣቀህ?" አለው፣ ጫኔ::

"የሚሥቅ ሰው ያሥቀኛል"

"ለምን?"

"እንጃ! ለምን እንደሚያሥቀኝ አለማወቄ ደግሞ የበለጠ ያሥቀኛል" አለ፣ በትንሹ ብቻ የሚደመጥ ሣቁን እየለቀቀው...

እራት ቤት ያፈራውን ተመገቡ::

የመኝታ ሰዓትም ሆነ:: ጫኔ አልጋው ላይ፣ ተሾመ ወለል ላይ - በፍራሽ!

ጫኔ ተሾመን በንቃት መከታተሉን ቀጥሏል:: እያየው ያለው እንደ ለማዳ ድመት ነው:: አልፈራውም:: ባልተለመደ እንቅስቃሴው፣ ባልተለመደ ንግግሩ፣ ባልተለመደ አስተሳሰቡ መዝናናትን ገብይቷል እንጂ!

"የሌሊት ልብስ ልስጥህ? ቱታ ነገር..."

"ይቅርብኝ!" አለ፣ ተሾመ::

"ሱሪህንና ሹራብህንም ሳታወልቅ ብርድ ልብስ ተከናንበህ ስትተኛ አይወብቅህም?"

"አዎ!"

"ብታወልቀው ነው የሚሻልህ"

"አይሻለኝም!"

ጫኔ ዝም አለው:: ሊጫነው አልፈለገም:: ድንገት አንድ ነገር አይቶ ከትራሱ ቀና አለ:: የተሾመ እግር...የተሾመ ጫማ! "ተሼ! ጫማህን ሳታወልቅ ነው እንዴ የምትተኛው?"

"ጫማዬን ከፍራሹ እና ከብርድልብሱ ውጪ አድርጌዋለሁ!"

"ኧረ ባክህ ተው! ነውር አይደል እንዴ? ዘና ብለህ ተኛ እንጂ! ጫማህን አውልቀው!"

"አላወልቀውም!" አለ፣ ቁርጥ ባለ ውሳኔ::

"ለምን?"

"ሌሊት ተነስቼ ካንተ ቤት ሰው ጫማዬን በማድረግ ጊዜዬን ከማዝረከርከው አጥልቄው ባድር ይቀለኛል አልፈልግም!"

በዚያ እኩለሌት የጫኔ ሣቅ ተሰማ፣ የተሾመም!

"መልካም እንቅልፍ ይሁንልህ!" ተባባሉ::

ነጋ::

ጫኔ የገመተውን ያህል የረባ እንቅልፍ አልወሰደውም:: ይህን የአዕምሮ ሕመም ታማሚ በማሳደሩ አንድ ከባድ የሆነ ነገር ቢደርስበት ማን ይወቀሳል? ሰው በገዛ እጁ ጣቱን ድመት አፍ ውስጥ ይሰድዳል? ምንስ የለመደው ድመት ቢሆን!

ተሾመ ግን ምንም የሠራው 'ስህተት' ሳይኖር ነጋ::

ጫኔ ነቃ! እናም አብሮ አደጉን ያዋራው ጀመር! "ጫማዬን ሳላወልቅ የምተኛው ስለምቸኩልና ከእንቅልፌ እንደነቃሁ መውጣት ስለምፈልግ ነው ብለህ አልነበር?" አለው፣ ጫኔ ዐይኑን አሻሽቶ ብርድ ልብሱን ከገላው ላይ እየገፈፈ::

"ማታ ለሽንት የተነሳሁ አስመስዬ አተኛኘትህን ልብ ብዬ አየሁት:: ስትተኛ ሰፊ በሆነው አልጋህ ላይ ፊትህን ወደ ጣሪያ ታደርገውና፣ እጆችህን ደግሞ እንደ ንስር ክንፍ ዘርግተህ፣ እግርህን ቀጥ አድርገህ ነው:: ከዚያም ገባኝ!"

"ምንድነው የገባህ?"

"አንድ ጥያቄ ነበረኝ:: ራሴን እጠይቅ የነበረው ይሄ ልጅ ምን አግብቶት ነው እንደዚህ የሚያጫውተኝ? ማን ቢሆን ነው፣ እንደዚህ በፈገግታ ተሞልቶና የደግነት መንፈስ አርብቦበት - እንደዚህ በዕለተ ሐሙስ ራት የሚያበላኝ? ማን ቢሆን ነው፣ ቤቱ አምጥቶ የሚያሳድረኝ? ማን ቢሆን?" እል ነበር ለራሴ::

"ኧይ ተሾመ! አብሮ አደግ ወዳጄ ስለሆንክ ነዋ! በእህል ውሃ ምክንያት ለብዙ ጊዜ ተራርቀን ቆይተን የለ? ስለተገናኘን ደስ ብሎኝ ጋበዝኩህ እንጂ በሌላ መንገድማ አትተርጉመው!" አለ ጫኔ፣ ተሾመን ለማሳመን እየጣረ::

"ይሄ ይሄማ 'ሰሙ' ነው"

"ሰሙ?"

"አዎና! በአንድ ሰው ውስጥ ሁለት ማንነት ይኖራል:: ቀለል ባለ ቋንቋ ልንገርህ! ሰው ቅኔ ነው:: ቅኔ ደግሞ ሰምና ወርቅ ይኖረዋል:: እና፣ብዙውን

ጊዜ የሚሆነው፣ ብዙ ሰው የሚያውቅለት ወይም የሚያውቅበት ማንነቱ ስሙ ሲሆን - ሁለተኛው ደግሞ ለአንዳንድ ሰው ብቻ የሚገለጥ ወርቅ የሆነ ማንነቱ ነው:: አንዳንድ ጊዜ፣ አንዳንድ ሰው፣ በአንዳንድ ቦታ የሚፈጽማቸው ደጋግ ወይም ከፉ ድርጊቶች ከራሱ ከባለቤቱ ቁጥጥር ውጭ ስለሆነ ነው፣ ከቅኔው ከፍል የ'ወርቁ'ን ድርሻ ይይዛል ብዬ ነው የማምነው!"

ጫኔ በአብሮ አደግ ወዳጁ ተፈላሳፊ መሆን እየተደነቀ፣ መገረሙንም ጠይም ፊቱ ላይ እየታየ፣ "እና፣ ትላንት የኔ ወርቅ ማለትም ድብቅ ማንነት ተረዳኸው ማለት ነው?" ብሎ ጠየቀ::

"አዎ!"

"ማን ሆኜ ተገኘሁ?"

ተሾመ፣ ጥያቄውን ትቶ ላልተጠየቀው ይመልስ ጀመር:: "አንተ ከተኛህ በኋላ ለጸሎት ተነስቼ ነበር:: 'ጌታ ሆይ!' አልኩት አምላኬን:: 'ጌታ ሆይ! አንከራተትከኝኮ! አንድ ሰው አንተ መድበህ ያኖርክለትን እውነተኛ እንጀራ ፍለጋ ይህን ያህል መንከራተት አለበት ወይ? ለምንድነው እንድጐሳቆል ብቻዬን የተውከኝ?' ብዬ ተማርሬ በጠየቅሁት ጊዜ አንድ ድምጽ ወደኔ መጣና እንዲህ አለኝ:: 'አይዞህ! አይዞህ! የትም ብትሄድ የት እኔን በንፁህ ልብህ ፈልገኝ እንጂ በጭራሽ አታጣኝም:: አይጐድልብህም! በሰው ልብ ውስጥ ሆኜ የምትሻውን እፈጽምልሃለሁ:: እኔና እናቴ በሰው ተመስለን የሌሎችን ህይወት ቀና ለማድረግ እንተጋለን:: አስፈላጊ ሆኖ ሲገኝም የሰው ልጅ ከመፈተን ከመፈታተን ቦዝነን አናውቅም' አለኝ የኔ ጌታ! ከዚያም ምን አለኝ መሰለህ? 'ተነስ! ተነስተህ አልጋው ላይ ያለውን ሰው እየው!' አለኝ:: የአምላኬን ድምጽ ሰምቼ አልታዘዝም የምል እኔ ማን ነኝ?

"ተነሳሁ:: አየሁህ:: አተኛኘትህ እንደተሰቀለው ጌታዬ ነው፤ እንደተሰቀለ! ሕማም ፊትህ ላይ እየተነበበ:: ሁለቱን እጆችህ እንደ ከንፍ ዘርግተህ:: እና ፊትህን ሳየው በድምጽ ያልመጣልኝ መልዕከት ፊትህ ላይ አነበብኩ:: 'ተሾመ ሆይ! በቂውን ያህል እንደምወድህ ለምን አይሰማህም? ስላንተ ይገደኛል:: ለምን አብዝተህ ትማረራለህ? ከዚህ በላይ ምን ልሁንልህ? ተሰቃየሁልኮ! ነፍሴን አሳልፌ ከመስጠት በላይ ምን ላድርግልህ' ያልከኝ ያልከኝ መሰለኝ!"

"ኧረ አንተ! በጣም የምታስቅ ሰው ነህ!" አለው ጫኔ፣ በፍልስፍናው ተገርሞ!

"ላንተ አይገባህ ይሆናል፡፡ ለእኔ ግን ትላንት መድኃኔአለም አንተ ውስጥ አድሮ ብዙ ውለታ እንደዋለልኝ - ጉድለቴን እንደሞላልኝ አምኜ ነው ያነጋሁት፡፡ አዎ! እንደዚያ ነው ነገሩ! በቃ! ቻዎ! ልሂድ!"

"የት?"

"ለመሄድ ወደተነሳሁበት ቦታ!"

"እሺ ዛሬ ከእኔ ጋር አትውልም? አመሻሽተህ ትሄዳለህ"

"ይቅርብኝ!"

"ለምን!"

"መድኃኔአለም አንተ ውስጥ አድሮ በቂውን ያህል ውለታ ውሎልኛል፡፡ የእስካሁኑ ደግነትህ ይበቃኛል፡፡ ወደ ትክክለኛው አመለካከትህ ማለትም 'ሰም' ወደሆነው ሰውነትህ ስትመለስ ትጠላኛለህ፡፡ ትጣላኛለህ! 'ውጣልኝ፤ አንተን መሸከም የሚችል ጫንቃ የለኝም ብለህ ብታባርረኝስ! የአንተን ጐተራ ሆድ ሞልቶ የማሳደር የዜግነት ግዴታ የለብኝም ብትለኝስ?" አለ ተሾመ፣ "ብሰነባበትህ ነው የሚሻለው!"

ከተቀመጠበት ተነስቶ፣ በአክብሮት ተሞልቶ ሊወጣ ሲል ጫኔ ተከተለውና እጁ ላይ ድፍን መቶ ብር አኖረለት፡፡

የዚህን የ'ሰላማዊ ዕብድ' ታሪክ ለጓደኞቹ እስኪነግራቸው ድረስ ተቻኩሎ ይለባብስ ጀመር፡፡

---

# የሟቹ ጥላ

ከኑሮው ባህርይ የተነሳ፣ በረሃ ቆይቶ ወደ ቤቱ መድረሱ ነውና ለብዙ ጊዜ የተለያትን ሚስቱን ለማግኘትና ናፍቆቱን ለመወጣት እጅጉን ጓጉቷል:: አቀዬው ሲደርስ እንደጠበቀው ሚስቱ በደስታ አልተቀበለችውም:: የጠበቀው ነገር ሌላ ነው:: እጎጆው በር ላይ የተሰበሰቡ ጥቂት የአካባቢ ሰዎች እንደህውልት ቆመዋል:: ማንም እንኳን ደህና መጣህ አላለውም:: አንዳች ክፉ ነገር እንደተፈጠረ ገባው::

ምን ተፈጠረ? ሚስቴ የታለች አለ፤ ወደ ጎጆው በር እየተመለከተ፣ከቆሙት ሰዎች በእድሜ ጠና ያለችው ሴት ጉሮሮዋን ሞረደችና ሚስትህ ሞታለች አለችው:: ደነገጠ፤ በከባድ ነገር እራሱን የተመታ ያህልም ተሰማው:: የመውደቅ ያህል እንዘጭ ብሎ መሬት ላይ ተቀመጠ:: አቀርቅሮ ሲተክዝ ቆየና ድንገት ብድግ ብሎ እንደተቆጣ አውሬ ቀያይ ዐይኖቹን በዙሪያው ባሉት ሰዎች ላይ አጉረጠረጠ::

በባህሉ መሰረት ምርር ብሎ ማልቀስና ሀዘንን ለመግለፅ ራስን መጉዳት እንግዳ ነገር ነው::

"ሞታለች? ባለቤቴ ሞታለች? የት እንደቀበራቿት ንገሩኝ" አለ፣ በሲቃ በታፈነ ድምጽ:: ጐረቤቶቹ በቀዘቀዘ ስሜት ተመለከቱት::

ግራ ገብቶታል:: ለከብቶቹ ግጦሽ ፍለጋ ከተሰማራበት እሩቅ ስፍራ ከጓደኞቹ ተለይቶ ሲመጣ፣ ይገጥመኛል ብሎ ያሰበው እንዲህ ያለው አሳዛኝ ነገር አልነበረም:: እንበሳዋን ለመጥባት እንደተጣደፈች ላም በጉጉት እና በከፍተኛ ናፍቆት ተሞልቶ ነበር የገሰገሰው::

"አልቀበርናትም፤ እሷን ለመቅበር አንተን መጠበቅ ግድ ነበር:: አስከሬኗ ጓዳ ውስጥ ነሰልህ" አለ፣ አንድ ልጅ እግር ሰውዬ ሚስቱ የሠራችውን ሳር ቤት እያየ:: እንደ አካባቢው ልማዳዊ አኗኗር ሳር ቤት የምትቀልሰው ሴት ናት:: ሴቷ በሠራችው ቤት ውስጥ ነው ተመቻችቶ በተነጠፈለት መኝታ ላይ ወንዱ ጎኑን የሚያሳርፈው::

ወደ ጎጆው ገባ:: የሚስቱ አስከሬን ፊቷ ላይ ብጣሽ ጨርቅ ጣል ተደረገበት በጀርባው ተንጋሏል:: ጨርቁን ገለጠው: ትልልቅ ዐይኖቿ ተደብቀዋል:: ችምችም ያሉት ነጫጭ ጥርሶቿም አይታዩም፤ አትንቀሳቀስም:: ህይወቷ ካለፈ ሁለት ቀኖች አልፈዋል::

ዘመዶቹና የአካባቢው ሰዎች ለሟች ሚስቱ ብቻ ሳይሆን ለእሱም ከፍ ያለና ልኩ የበዛ ንቀት እንዳላቸው ያውቃል...አፈንጋጭነቱን አይቀበሉትም:: ሞገደኛነቱ ያናድዳቸዋል:: በርግጥ ብዙ መንገድ ያውቃል:: እነሱ በማይውሉባቸው ቦታዎች ተገኝቶ ያውቃል:: በነጋዴነት ሰበብ ከሌሎች ብሔር ተወላጆች ጋር እየተገናኘ የአኗኗር ልማዳቸውን ሰምቷል፤ አይቷልም::

በየሄደበት እምቢ ባይ ጀግኖች አይቶ እኔስ? እኛስ? በማለት መቆርቆር ጀምሮ ነበር:: ይሄው ምክንያት ሆኖት በንግዱ እያመካኘ ከአካባቢው ርቆ ነበር፤ ከአርባ ምንጭ ጂንካ፣ ከጂንካ ዲመካ፣ ከዲመካ ቱርሚ:: ብዙ ቦታዎች ረግጧል:: የነበረው ሀብት እየጎደለበት፣ ጤናውም እየተናጋበት አልስማማ ሲለው ጊዜ ወደ ጠላው የአኗኗር ልማድ ፊቱን መለሰ...

የሚንቃቸው ይመስላቸዋል:: ይበጀዋል ብለው ያሰቡትን ነገር ሲያመላክቱት እንኳን በሚያሳዩት መንገድ ለመመላለስ ፍቃደኛ አይደለም:: ዥንጉርጉር ይሆንባቸዋል:: እንደነሱ አንድ ወጥ የሆነ ቀለም የለውም:: አንዳንድ ነገሮቹ ብቻ ናቸው የእነሱን የሚመስሉ...

በርግጥ፤ ይህችን ሴት መርጦና ፈቅዶ ሊያገባ ሲወስን አበጀህ የኛ ልጅ ብለውታል:: በሀገሬው ልማድ መሰረት ሽማግሌ ልኮ፣ ለወላጆቿ ጥሎሽ ከፍሎ ነው ይህችን ሴት የግሉ ያደረጋት::

አባቷ፣ "ሃያ አምስት የቀንድ ከብት እፈልጋለሁ!" አለ:: "ለመጀመሪያ ልጄ ስድስት የቀንድ ከብት አዘጋጅ፤ በፈለገ ጊዜ ስጠው:: ለሁለተኛው ወንድ ልጄ ደግሞ አራት ከብት ቆጥረህና አስቆጥረህ በፈለገ ጊዜ አስረክበው:: የተቀሩትን ከወዲሁ፣ ልጄን ወደ ቤትህ ከማስገባትህ በፊት እንድትልክልኝ ይሁን..."

እንደተጠየቀው አደረገ:: ዘጠኝ የቀንድ ከብት ሰጥቶ አገባት::

ሚስቱ ከወላጆቹ ጋር ተቀላቅላ የአባቱን ሚስቶች ተጎራብታ ኑሮዋን ቀጠለች::

በዳሰነች ባህል (ደቡብ ኦሞ) ሴት ልጅ ካገባች በኋላ ባሏ አሷንና ልጆቿን የማስተዳደር አቅም ካነሰው ወይም ተለይቷት የሚኖር ከሆነ ለአባቱ ሚስቶች ነው፣ 'ያዙልኝ፣ ጠብቁልኝ፣ ሙያ አሰልጥኑልኝ፣ ደግሞም ኢጋዥ ትሁናችሁ፤ የፈሰሰ ውሃ ታቅናላችሁ!' ብሎ መስጠት ያለበት:: እሱ ግን አላደረገውም:: "ለጥቂት ጊዜ ነው ተለይቼሽ የምኖረው፣ ላንቺም ለእኔም ለምንወልዳቸው ልጆች የሚበጀን የከተማ ሕይወት ነው እንጂ ይሄ የተለመደ የባላገር እና ኋላ የቀረ አኗኗር አይደለም" ብሏታል::

ወደ ጂንካ ሄደ ...

አባቱ ሦስት ሚስቶች አሏቸው:: ሚስቱ ለሦስቱም ታዛዥና ታዳጊ ሆና ሸክማቸውን አቀለለችላቸው:: እረፍት አልባ ሆነች:: የአንዳቸውም ጓዳ እንዳይጎድል ላብዋ ጠብ እስኪል ትዳክራለች:: ጠዋት ተነስታ የመጀመሪያዋ ተብላ ክብር ወደተሰጣት የበኩር 'ሚስት' ቤት ትሄዳለች:: ይህንን ቤት አፀዳድታ፣ የቆሻሸሹ ዕቃዎችን አጣጥባ፣ ቁርስ አዘገጃጅታ፣ ተልካ፣ ተላልካ ታረፍዳለች:: ነገሮች ቦታ ቦታቸውን የያዙ ሲመስላት ወደ ሌላኛዋ ቤት ትሄዳለች:: በሥራ ተጠምዳ ትውላለች:: አመሻሽ ላይ ደግሞ ወደ ሦስተኛ ሚስት...

የእንቅልፍ ሰዓት ሲቃረብ፣ "ሂጂ ሌሊቱ እየገሰገሰ ነው" ስትባል ወደ ቤቷ ትሄዳለች:: ቀሪ ጉልበት የላትም:: የቀራትን እንጥፍጣፊ አቅም እንደምንም ብላ ትቆጥብና ወደ መከዳዋ ታመራች፣ ወደ መኝታዋ...

ትላንት እንደዚሁ፤ ነገም እንደዛሬ፤ ከነገ ወዲያም ....

ምድጃዋ በጭስ እና እሳት አምሮት ተንገብግቦ ያመሻል:: የገዛ ጎጆ ቤቷ የመቃብር ቤት ይመስል ረጭ ብሎ፣ ቅዝቃዜ ለብሶ ይጠብቃታል::

እንዲህ ባለው የተለመደ አኗኗር እየቀጠለች ሳለ ባሏ ያከናውን የነበረው የንግድ ሥራ አቋርጦ መጣ:: የማይነግደው ነገር የለም:: ማገር፣ ቀለሃ፣ የቡና ሸፈሮ...

ወደ ባህሉ ባህር እንደገና ሲቀላቀል፣ የሆነውን አወቀ፡፡

ለመጀመሪያ ጊዜ ሚስቱን ተቆጣት፣ አክብሮትና ትህትና ያንበሸብሻት የነበረው ባሏ የፈረጠመ ክንዱን ወደ ዕርቃን ጫንቃዋ ሰዶ፣ ያለውዴታዋ አስቀምጦ፣ "አርፈሽ ተቀመጪ! ያለኔ ፍቃድ ወደ የትኛዋም የአባቴ ሚስት ደጅ ደርሰሽ ስትንጎዳጎጂ እንዳላገኝሽ" አላት፣ ምላሱ ቅል የላሰ ይመስል ተንገሸገሾ፡፡

ግራ ገባት፡፡ "ማንን ልታዘዝ?" ብላ ራሷን መጠየቅ ጀመረች፡፡ ባለቤቴን ወይስ የማኅበረሰቡን ደንብ?

ማኅበረሰቡ፣ የባለቤቷን ወላጆች እንድትንከባከብ ኑሮአቸው እንዳይቆመጥጥ፣ እህል ውሃቸው እንዳይሻግት፣ ጎህ ቀዶ ጀንበር እስኪጠልቅ ድረስ ከሥራቸው መራቅ እንደሌለባትና ሴትነቷን፣ ባለሙያነቷን እንድታስመሰክር ያዝዛል፡፡ የባለቤቷ አባት ሚስቶች ሁለትም ይሁኑ ሰባት ወደ ቤታቸው እየተመላለሰች፣ 'ሲጠሯት አቤት፤ ሲልኳት ወዴት?' ማለት አለባት፡፡ ቤታቸው ከተዝረከረከ፣ ማጀታቸው ከጎደለ ተወቃሽዋ እሷ ናት፡፡ ይኼ ደግሞ መብት አይደለም፤ ግዴታ ነው፡፡

ባሏን የሚያስቆጣው ይሄ ነው፡፡ "ያገባሁሽ የእኔ፤ የብቻዬ እንድትሆኚ እንጂ ከአባቴ ሚስቶች ጋር እንድሻማሽ አይደለም፡፡ ጊዜሽን ለቤትሽ ብቻ አድርጊው" አላት፣ ተቆጥቶ፡፡

"ማንን ልታዘዝ?" ትላለች፣ አሁንም አሁንም፡፡ ባለቤቴን ወይስ የማኅበረሰቡን ደንብ?

ማኅበረሰቡ ሰው መርጦ፣ ጥሎሽ ተቀብሎ፣ 'ሚስት ትሆኚው ዘንድ ፈቅደናል!' ካለ በኋላ፣ የባሏ ተገዥ ናት፡፡ የሰውነቷ ጌታ ባሏ ነው፤ ከትእዛዙ ፈቀቅ ማለት አትችልም፡፡

"ሚስትነትሽ ለእኔ ብቻ ነው፣ ትእዛዜ ደግሞ መከበር አለበት፡፡ እንኳንስ ለነሱ ለእኔም አሽከር እንድትሆኚ አልፈቅድም..."

የሞት ሞቷን አንድ ጥያቄ ጠየቀችው፡፡

ያፈላችውን ሽፈሮ ቡና እያቀበለችው፣ ግራ መጋባቷን በፊቷ እንቅስቃሴ እያሳየችው፣ "እኔ ነኝ የምጎዳው፡፡ በጉልበቴ ብታዘዛቸው ምናለበት?" ብላ ጠየቀችው፡፡

"ሚስቴ እንጂ አሽከራቸው አይደለሽም፤ ለእናቴም ቢሆን አሽከር አይደለሽም"

የእሱ ሃሳቦች አሸነፏት፡፡ አንድ ቀን እናትና አባቱ ወደ ቤታቸው አስጠሩት፡፡ በእርምጃውና እርምጃዋ ሊገስፁት መስሎት ነበር፡፡ ግን አልሆነም፡፡

"ልጄ!" አሉት፣ አባትና እናት ብርኩታቸውን አመቻችተው፣ አፊቱ እየተቀመጡ፡፡ አፍንጫቸው ስር ቀርቦ ድምጻቸውን እስኪያሰማቸው ድረስ ደጅ ላይ ተቀምጠው ሲያብሰለስሉ እና ሲብሰከሰኩ ነበር፡፡ "ልጄ!"

"አቤት..."

"እንዴት ነው?"

"ምኑ!"

"ሰሞኑን፣ ማለትም ማታ ማታ በነበሩ ጭፈራዎች ዐይንህ ያረፈባት ልጃገረድ የለችም ወይ?"

ደንገጥ አለ፤ ግንባሩን ሽብሽብ፣ ዐይኖቹን ኮስተርተር፣ "ምን ለማለት ፈልገህ ነው?" አለው፣ አባቱን፡፡

"የለችም? አንተ የመረጥካት ከሌለች እኛ ልናጭልህ ነው"

ፈገግ አሉ፡፡

"ሚስቴስ?"

"አሷማ አለች፤ ማንም አይወስድብህም" አሉት፣ የዋህነቱ እንደግንባር ቁስል ፈጦ ያገኙት ይመስል፡፡

"እና እንዳንተና እንደሌሎች ሚስት እንዲበዛልኝ ብለህ ነው?"

አባቱ እንዲህ ያለውን መገንፈል፣ እንዲህ ያለውን ነቃፊ እንደበት ለምደውታል፡፡ በፊትም እንደዚህ ነው፡፡ በአንደበቱም በድርጊቱም እንዴት እንደሚበልጣቸው ለማሳየት እንደሚጥር ሰው ይቆጥሩታል፡፡

"አባት መሆን አትፈልግም ልጄ?"

የሳቸው ቤት ሕጻን አልባ ነው:: በሾህ የታጠረ ግቢያቸው የህፃን ጉልበት ከዳኸበት ብዙ ጊዜ ሆኖታል::

ሲፈራውና ሲሸሸው የነበረ ጥያቄ:: አባት መሆን...

"እንዲት ሚስት ትበቃኛለች..."

መልስ አሰጣጡ አላስደሰታቸውም:: አኳኋኑ እንደ ዳሰነች አባወራ አልሆነም:: ገንዘብ ሳያንሰው፣ የከብቶቹ ቁጥር ሳይመናመኑ እንዴት አንድ ሰው የሚስቶቹን ቁጥር ለማብዛት መጣር ሲገባው አርፎ ይቀመጣል?

ወጣ ገባ እያሉ፣ ሸፈሮ ቡና እያቀራረቡ፣ የአባት እና የልጅን ምልልስ ሲያዳምጡ የቆዩት አሮጊት እናቱ ደግሞ ለእረኛው አልታገድ እንደሚል ከፉና አስቸጋሪ ፍየል ቆጥረው፣ በተቆናጠረ ድምጽ ይገስፁት ያዙ::

"አንተኮ ማስቸገር የጀመረከው አሁን አይደለም፤ አሁን አይደለም! በፊት ነው፣ ታላቅ ወንድምህ ሲሞት፣ በወንድምህ የሚጠራ ዘር አስቀምጥ ስንልህ ምንድን ነበር ያልከን እ? ልጄ አዋረድከኝኮ! መጠሪያ የሚሆን ዘር ተውለት ብልህ፣ ወንድሜ በምን እንደሞተ የት እውቅና ነው፣ እሷን በሚስትነት የማስቀምጠው ብለኸኝ ነበርኮ! አዋረድከኝ..."

ከሞተ ሰባት ወር ያለፈው ታላቅ ወንድሙ የአርባ ምንጭ ከተማ ነዋሪ ነበር:: በከተማው ውስጥ ከሚታወቁት ታላላቅ ሆቴሎች የአንዱ አስተዳዳሪ ነበር:: ሳምባዬን አሞኛል ብሎ፣ ከሰውነት ተራ ወጥቶ ወደ ዳሰነቾች ቀዬ ሲመጣ፣ ‹ዘር ሳይተው፣ ስሙን ሳይተከል ሊሞትብን ነው› አሉና፣ የዳሰነች ቆንጆ ልጃገረድ አጨሉት:: ሚስቱም ወንድ ልጅ ወለደችለት:: የተወለደው ሕጻን ግን ብዙ ሳይቆይ ሞተ::

"ከወንድምህ ሚስት ጋር ተኛ:: ማታ ዝግጁ ሆና እንድትጠብቅህ እንነግራታለን" አሉት::

መገረም ዐይኑን አስፈጥጦት፣ መዳፉን በአፉ እየሸፈነ፣ "ይሄ ነገር አልቀረም እንዴ?" አለ::

"ግባና በታላቅ ወንድምህ ስም የሚጠሩ ልጆች ውለድ" አሉት፤ የምንልህን የማታደርግ ከሆነ የምንወስድብህን ጥብቅ እርምጃ እኛ እናውቃለን ዓይነት አነጋገር::

ጥቁር እና አትንኩኝ ባይ ፊቱን ጨመደደው፡፡

"እኔ አልፈልግም፡፡ እኔ እንዲህ ያለ ነገር አልወድም፡፡ እንዲህ ባለ አጉል ልማድ እራሴን አላሰለጥንም፡፡ ማንን ማግባት እንዳለበት የምትወስነው እሷ እንጂ እናንተ አይደላችሁም፡፡

"ተወዋ! ተወው፤ ማን ይለምንሃል? ከብሩ ላንተ ነበር፡፡ የሟች ወንድምህን መንፈስ ለማስቆጣት ባትፈጥን ምን ነበረበት?" ለቁጣቸው ግድ አልነበረውም፡፡

በሳምንቱ የሟቹ የታናሽ ታናሽ የወንድሙን ሚስት ደርቦ ለመያዝ ፍቃደኛ መሆኑን ተናገረና የወላጆቹን ልብ በደስታ፣ የእሱን ልብ ግን በቅሬታ ሞላው፡፡

አባትና እናትም የተደላደለ ትዳር ይግጠምህ ብለው መረቁት፡፡

ታላቁ ግን፣ "በምን እንደሞተ የት ታውቅና ነው፤ እንዲህ ዓይነቱን እርምጃ የምትወስደው? ምንድነው ሳሩን አይቶ ገደሉን እንዳላጤነ ነሆለል በሬ መሆን?" ነው ያለው፡፡

እንዲህ ያለው አባባል እንዲህ ያለው ተግሳፅ ከታናሹ መረዳት በላይ ነው፡፡ ፈጣሪ እንዴት ባልጠፋ ቦታ፣ ሞትን የሚያህል ነገር፣ ጭን ፈልቅቆ፣ ብልት ውስጥ ይቀብራል? ለጥሎሽ የከፈልነውን እንድንከስር ነው እንዴ የሚመከረኝ? አለና በልቡ የመካሪ ወንድሙን ሀሳብ አጣጣለው፡፡

ያጣጣለው ሀሳብ ይዞ ወደ ወላጆቹ ፊት ቀረበ፡፡ ወላጆቹም፣ አግቢው ልጃቸው የዳሰነችን ስርዓትና ደንብ ላለማፍረስ የሚያደርገውን ተጋድሎና ሰልጥኛለሁ ብሎ በራሱ፣ በቤተሰቦቹና በወገኖቹ ላይ ሙዋርት ይዞ ከመጣው ወንድሙ ጋር የሚያደረገውን ትንቅንቅ አስተዋሉ፡፡

ይኼ ከገዛ ቤተሰቦቹ ጋር ያደረገው አንድ ጦርነት ነው፡፡ ጦርነቱ የአስተሳሰብ ሻሙላዎች ናቸው የተማዘዙበት፡፡ የሚጥልም የሚጣልም ሳይኖር ኑሮአቸውን የቀጠሉበት፡፡

የአካባቢው ተወላጆች ስም አበጅተውለታል - 'ልጅ አልባው ባል፣ አባት ለመሆን ያልታገለው ያልታደለው አባወራ!'

በቃ!

ሚስቱም፣ "ለምን ሌላ ልጃገረድ አታገባም? ለምን የወላድ ዘር የሆነች ሴት አላጭልህም?" አለችው አንድ ቀን፣ ያገነፋችለትን ገንፎ እያቀረበች::

"ገና እኮ ሁለት ዓመታችን ነው፤ ከሁለት ዓመት በኋላ አንቺም እናት፣ እኔም አባት የመሆን ፀጋ እንጎናፀፍ ይሆናል..."

"የታደለችው በመጀመሪያ ዓመቷ አይደል ልጅዋን የምትታቀፈው!"

"ትንሽ እንቆይ"

"ይህን ጊዜ ሁለት ልጆች ይኖሩን ነበር:: እባከህን እሺ በለኝና..." አልቅሳ ለመነችው::

መጀመሪያ ቀልድ ቀጥሎ ደግሞ የምር መሆኑን ያረጋገጠችውን ነገር ነገራት::

ችግሩ ከእኔ እንደሆነስ? እኔ እንደሆንኩ ዘር ማፍራት የማልችለው?

ብድግ ብላ ከአጠገቡ ራቀች:: እንዲህ ዓይነቱን ነገር መስማት ያስቀስፋል:: ስንት ቀንና ሌሊት፣ የምትተኛበት ቆዳ በእንባ ርሶ እንደሚያድር ማን በነገረው? ውሃ ቀጅዎችና እንጨት ለቃሚዎች በመሃንነቷ እንደሚዘባበቱባት ማን በነገረው?

የእሱ ወላጆች፣ 'አባት ለመሆን ባልታደለው' ልጃቸው ጉዳይ መፍትሄ በማበጀት አዋቂ ቤት ሄዱ:: አዋቂው የአካባቢውን ችግሮች ለመፍታት ሲዳከሩ የሚያነጉት በእሾህ በታጠረ እና ሦስት ትናንሽ ጎጆዎች በተሰሩበት ግቢ ውስጥ ተቀምጠው ነው:: አዋቂ ነው፤ ታዋቂም ጭምር:: ማኅበራዊ ጉዳዮች ጎርፍ ሆነው ወደ ግቢው ይፈስሳሉ:: አስደማሚ መልሶች በአዋቂ ጭንቅላት ምንጭ ሆነው ይፈልቃሉ:: እሳቸው እንዲሆን ብቻ ሳይሆን ወደፊት ሊሆን የሚችለውን ይተነብያሉ:: ነገ ለእነሱ ሩቅ አይደለም፤ ዛሬ ላይ ሆነው ያዩታል:: ጫማ ጥለው ነው፣ ትላንት ያለፈውን ነገ የሚመጣውን የሚገመግሙት::

አባት ጓደኛቸውን አስከትለው ሄዱ:: በርግጥ ልጃቸው የዳሰነችን ደንብና ስርዓት ካላፈረሰኩ የሚል ተሟጋች ነው:: እያት ቅድመ አያቶቹ አይተውትም አውርተውትም በማያውቁት የሙያ ዘርፍ ራሱን አሰማርቶ፣ ነጋዴ ተሰኝቶ ነበር:: ግን የዘር ማንዘሮቹን የሙት መንፈስ ተቆጥተው፣ ለከስረት እንዲደረግ ፈርደው ቀጥተውታል ብለው ደምድመዋል::

እንደ ደንቡና እንደ ስርዐቱ ባለጉዳዩ እሱ ነው:: እሱ ነበር፣ 'ሂዱልኝ፣ አዋቂ ጠይቁልኝ፣ ጫማ አስጥሉልኝ' ማለት የነበረበት:: እሱ ነበር፣ 'መሀን ሚስት የገጠመችኝ በራሴ በቤተሰቤ እና በዳሰነች ሰዎች ላይ ምን የሠራሁት በደል ቢኖር ነው?' ብሎ ጥፋቱንም ስርየቱንም መቀበል የነበረበት:: ግን አላደረገውም::

የአዋቂው መልስ አጭር ነበር:: አረጋዊ ገፃቸው ላይ አርምሞ እየተደመመበት የአባትየውን በረባሶ ጫማ አስወለቁ:: አንዳች ነገር አነበነቡ፤ የተመሰጡ መሰሉ:: ሁለቱን ጫማዎች ወደላይ ወረወሩ:: አተኮሩባቸው:: ከእናታቸው ብዙም ራቅ ሳይሉ በረባሶዎቹ ወደ መሬት ተመለሱ:: የአባትና የሌሎች ሽማግሌዎች ልብ ተሰቀለ::

አዋቂው፣ "እህ..." ጉሮሮአቸውን አጠሩ:: "የሟች ወንድሙ መንፈስ ጥላ በቤታቸው አጥልቷል:: ሟቹ አጥልቶባቸዋል:: በሁለቱም ጭን ላይ ሟቹ ጥላውን አሳርፏል:: ባልየው የወንድሙን ሚስት ለመውረስ ምነው ልቡን አደነደነ? እሷስ ብትሆን ምን ነካት? ምን የሚሉት ከፉ መንፈስ ቢፀናወታት ነው? ለምን ገፋፍታ ደካማ ሀሳቡን አላስጣለችውም?"

ይኸ ነበር የተፈለገው፣ ለጥያቄው መልስ:: ለመልሱ ደግሞ ሌላ ጥያቄ ...

"ምን ቢያደርጉ ነው፣ አያትነቴን በእነሱ በኩል የምቀበለው? የሚል ጥያቄ አመጡ"

"ጥቁር ፍየል እረዱና በፈርሱ ይተጣጠቡ፤ሟቹንም ይቅርታ ይጠይቁ"

"እሺ!"

"ከዚያ በኋላ፤ ያልኩትን ከፈፀሙ በኋላ መጪ እድሜያቸውን አምላክ እንዲባርከው እመርቃቸዋለሁ..."

አባትየው በአሮጌ ከረጢት የተጠቀለለ ሽፈሮ ቡናቸውንና በጨርቅ የተሸፈነ አረቄያቸውን በስጦታ መልክ አቅርበው ወጡ:: አዋቂው የተሰጠውን በረከት በፍቅር ይዞ መርቆ ተቀበለ::

እንደወጡ ጉዞ ጀመሩ:: ወደ ልጅ አልባው አባወራ ቤት ደረሱ:: ይዘውት የሄዱትን ጥያቄና ለጥያቄያቸው ያገኙትን መልሰ ነገሩት::

"አስብበታለሁ!" አለ አስብበታለሁ ማለቱ አባቱን መጫን ያበዛ መስሎት ነው እንጂ ነፍሱ የወደደው እውነተኛ ምላሽ አልነበረም::

"ምን ማሰብ ያስፈልገዋል፣ ህመምተኛ ሰው ለህመሙ መድኃኒት ሲገኝለት ከዛሬ ነገ እያለ የመሰቃያ ጊዜውን ያስረዝማል?"

ባለቤቱ ብቸኝነቷ እየበዛ መጥቷል:: ሆዷ አይገፋም:: የገመድ ቋጠሮዋን ይዛ፣ የጨረቃን አወጣጥና አገባብ ተከታትላ፤ የሚረገዝበትን ቀን ጠብቃ ብቻ አይደለም የፍቅር ግብዣዋን የምታቀርብበት:: ሁሌም ዝግጁ ሆና፣ ሁሌም ፀዐዳ ሆና ወደ መኝታ ትጋብዘዋለች:: ግን የወር አበባዋ አይቀርም:: ደግሞ በየቀኑ የሚያሰቅቃት ነገር መብዛቱ!

ባለፈው ክረምት የዳሰነች ተራራ በጉም ተሸፍኖ ሰማዩ በመብረቅ በሚታረስበት እና ጭቃማ ቀኖች በሚበዙበት ጊዜ ወንድሟ መጣ::

"ባንቺ መናደዴን ልነግርሽ ነው የመጣሁት" አላት፣ ድምጹን ነጎድጓድ አልብሶ::

ደንግጣ፣ "ምን በድዬህ?" አለችው::

"ለምንድነው አዋቂው ያዘዛችሁን የማታደርጉት?"

አንገቷን ደፋችው:: ስታቀረቅር ስትኳትን የዋለችበት እግሯ የተላቆጠ ጭቃ ጎርሶ አየችው::

"ለኔ ስንት የቀንድ ከብት ሊከፈለኝ እንደሚገባ ታውቂያለሽ አይደል? ሰባት የቀንድ ከብት ነው ባል ከሚከፈለው ጥሎሽ የሚደርሰኝ፣ ይኼ የሚሆነው ደግሞ አንቺ ስትወልጂ ነው ..."

"ምን ላድርግ ወድጄና ፈቅጄ አይደለም የማህፀኔን በር የዘጋሁት፤ ወድጄ አይደለም"

ባለቤቷ በመጀመሪያው ዙር መስጠት ያለበት የቀንድ ከብት ከሰጠ ሁለት ዓመት ሊሞላው ነው:: ቀሪው ከብት መሰጠት ያለበት ልጅ ስትወልድ ነው:: እናም የቤተሰቦቿን ተስፋም ጭምር ማጨለሟ የታወቃት አሁን አይደለም:: የቤታቸውን ቋሚና ማገር ይዛ የጠፋች ይመስል በሕይወታቸው ውስጥ ላጋጠሟቸው ጎዶሎ ነገሮች ሁሉ ተጠያቂ አድርገዋታል::

ወንድሟ ለራሱ የሚያወራ በሚመስል ድምጽ አጉተምትሞ ተሰናበታት:: "ማግባት ፈልጌ ነበር:: የምወዳትን ልጅ መርጬ አጭቼ ነበር:: ከዓመት በኋላ ነበር እሺ ያሰኘኋት ግን ከብት ከየት ላምጣ? ከየት? አዋቂው ይሁን ያለው ብታደርጉና ሚቹን ይቅርታ ብትጠይቁ አንቺም ልጅ በልጅ ትሆኚ ነበር:: እኛም ድርሻችንን እናጣም ነበር"

ከዝምታ በቀር መልስ የላትም:: ምን ትበለው? የምትለው ነገር ቢኖር እንኳን ወንድሟ መስማት የሚችል ጆሮ ይዞ ከቤቱ አልወጣም::

ከወር በኋላ ...

የባለቤቷ ወላጆች ከሽማግሌ ጋር ተማክረው ወደ ወላጆችዋ ቤት የመሄዳቸውን ነገር የሰማችው ከእናቷ አንደበት ነው::

አሮጊት እናቷ እና አረጋዊው አባቷ ሲንቀረፈፍ የዋለውን ቀን በቻልተኛ መንፈስ ሸኝተው፣ ተነጥፎ ወደሚጠብቃቸው ቁርበት በማምራት ላይ ሳሉ አራት እንግዶች መጡባቸው::

የሰላምታው ዕድሜ አጭር ነበር::

"ልጃችሁን እንድትወስዱልን ነው አመጣጣችን" አሉ እንግዶቹ::

አንድ ቀን እንዲህ ሊባሉ እንደሚችሉ ወላጆቿ ይገምቱ ነበር:: ዘር የማይሰጥ መሬት ማን ይፈልገዋል?

የዳሰነች ስርዓትና ደንብ እስከፈቀደ ድረስ:: ግን ለአፍ አመል ያህል ምክንያት ይጠየቃል::

"ባሏን አልታዘዝ፣ ቤት አልሠራና ምግብ አሳሰናዳ ስላለች ነው ልጃችንን ወደ ወጣችበት ቤት የምትመልሷት?" ይላሉ፣ አባቷ::

"እረ! በጭራሽ!"

"የባሏን ቤተሰቦች አንጓጣና መልካም ባህርይ አላሳይ ስላለች ነው ወደ ወጣችበት ቤት የምትመልሷት?" ይላሉ፣ አባቷ::

"እረ በጭራሽ!"

"ታዲያ በልጃችን ላይ ምናይነት ነውር አገኛችሁባት?"

"መሃን ናት"

"ናት?"

"አዎ!"

"እንግዲያውስ እውነት አላችሁ:: ራሳችንን ስናውቅ የወላድ ዘር ነበርን:: ነን ብለንም ነበር ልጃችንን የዳርንላችሁ:: ግን አለመታደል ሆኖ፣ የመረገም ጉዳይ ሆኖ ለመዛመድ ያደረግነው ጥረት አልተሳካም..." ድምጻቸው ንፋስ እንደሚያባብለው የላስቲክ ቁራጭ አቅሙን አጠንክሮ መቆም አቃተው::

"አዎን፤ልጃችሁን ውሰዱ ማለታችንም ለዚህ ነው"

"እንወስዳታለን:: ማሽላ በበዛበት ጊዜ እንክርዳድ ዝሩ ማለት አንችልም መቼስ..."

"አስቀድመን ለጥሎሽ የሰጠናችሁን የቀንድ ከብት እንድትመልሱ!"

"እንዴት እንዴት ነው ነገሩ!" አሉ፣ አባቷ ቆጣ ብለው፤ "የዳሰነች ስርዓትና ደንብ የሚያዘው እንዲህ ነው? ባለቤቷ ነው ስለጥሎሹ ሲጠይቀን የሚገባው፣ ይምጣ፣ ይምጣና ቆጥረን እናስረክብ፣ ያዋረደችን ልጃችንንም እንቀበል ..."

በሁለቱም ቤተሰቦች መካከል ያለመተማመን አምራ አንዣበበ:: ከንፋን አላርቅ አለ::

አባወራው ከእኩዮቹ ጋር ከብቶቹን ይዞ የአሞ ወንዝን ተከትሎ ርቆ በሄበት ጊዜ ታመመች:: መሃን ሚስቱ ታመመች:: በርግጥ አልፎ አልፎ የሚያገረሽ የንዳድ በሽታ ነበረባት::

ዘመዶቹ በቂውን ያህል ትኩረት አልሰጧትም:: ህመሟም የመረገም ውጤት ነው፤ ተባለ:: አንዲት ሴት እንዴት ለሁለት ቤተሰብ ውርደትና ከስረት ተጠያቂ ትሆናለች?

የሟች ጥላ ያረፈባት፣ የሟች መንፈስ የተቆጣትና ርኩሰት የተፀናወታትን ሕመምተኛ ተጠግቶ፣ ባህላዊ መድሃኒት አቀብሎ ወደ መዳን የሚመልስ እሱ ማነው?

መሃኗ ሞተች::

በዳሰነች ልማድ ሚስት ስትሞት ባል ነው ወደ ጎጇቸው አቅራቢያ ሄዶ፣ የቀብር ጉድጉድ የሚቆፍረው:: እሱ የመጀመሪያውን መቆፈሪያ አፈሩ ላይ እንዳሳረፈበት በኋላ ወዳጅ ዘመድ ይረዳዋል:: ከዚያ በፊት ግን ከሟቹ፣ አናቱ አካባቢ ካለው ፀጉር ይላጩና፣ ለቀብር ወዳዘጋጀው ቦታ ወስደው፣ ከብት አርደው /የሚገድሉት በቀስት ወግተው ነው:: ደሙ ተንዠቅዥቆ ሲያልቅ በሬው ይሞታል/ በደሙ ፀጉሩን አርሰው፣ ከሟቹ ጋር ይቀብሩታል::

ባል ሲሞት ልጅ የቀብር ከዋኔውን ያስኬዳል:: የመጀመሪያው መቆፈሪያ ቀብር ጉድጓድ ላይ አኑሮ ...ልጅ ሲሞት ደግሞ አባትየው...

መሃኗ ስትሞትስ?

የአሞ ወንዝ ሞልቶ ነበር:: ወንዙ ሞልቶ ብዙ ንብረቶቻቸውን እንዳልነበረ አድርጓል:: ሰዎቻቸውንና ከብቶቻቸውን እንዳልነበረ አድርጓል:: ሰዎቻቸውና ከብቶቻቸውን በገዛ ወንዞቻቸው ተዘርፈዋል:: የወንዙ አካሄድ አደገኝነት የበዛው ነበርና ጉዞው ተገታ:: ባለቤቱ መታመሟን ያላወቀው ባሏ፣ መሞቷን ሲሰማ ደነገጠ:: ታመመ:: ለአንዴና ለመጨረሻ ጊዜ ከማኅበረሰቡ ተለይቶ ሊኖር ይዟት ሊሄድ ነበር ያሰበው:: የብቻዬ ያላትና እራሱን የሰጣት ሚስቱ ግን ትታው ወደማትመለስበት ዓለም ሄደች::

"ማናችሁንም አልፈልግም፤ ወደ የሥራችሁ ሂዱ" አላቸው::

ሚስቱን ሊቀብር ከጎጆው ጀርባ ጉድጓድ ይቆፍር ጀመር:: ኃዘኑ ወደ ቁጣና እልህ ተለውጦ ጡንቻዎቹን አፈረጠማቸው:: ዶማውን በሰነዘረ ቁጥር እሱ ብቻ የሚሰማቸው ቃላት ይናገር ነበር:: ይበቃል ብሎ የገመተውን ጥልቀት ከቆፈረ በኋላ ወደ ጎጆው ሄዶ፤ የባለቤቱን አስከሬን አመጣው፤ በዝግታ እየተራመደ፣ እየተንገዳገደ የሞት ጥልመት የጋረደውን ፊቷን እያየ፤ ወደ ውስጡ እያነባና ጥርሶቹን እያፋጨ...

የባለቤቱን ግብዓተ ምድር ካጠናቀቀ በኋላ ወገቡን በሁለት እጆቹ ይዞ በመቆም መቃብሩን ላንድ አፍታ ተመለከተው:: ቀና ብሎ ደግሞ ዙሪያ ገባውን ቃኘ፤ ደኑን፣ ኮረብታዎችን፣ በሩቅ የሚታዩ ተራሮችን ...ሁሉም ፀጥ እረጭ ብለዋል:: አዕዋፍ እንኳን ድምጻቸው አይሰማም:: ፍፁም ባይተዋርነት ተሰማው:: ጦሩን ሚስቱ መቃብር እራስጌ ሰካውና መለስ ብሎ በዝግታ ያስብ ጀመር፣ ከራሱ ጋር እያወራ፣ ጠያቂም መልስ ሰጪም እየሆነ...

.....

# የመኝታ ቤት ምስጢሮች

## (እናትና ሚስት)

ከወንድ ጋር አግኝቷት፣ እጅ ከፍንጅ ደርሶባት ሳይሆን፣ ራሷ ናት ፈተና ላይ መውደቋን የነገረችው:: 'ሃጥያት ፈጽሜያለሁ' ያለችው:: ከወንድ ጋር:: በገላዋና በትዳራቸው ላይ የፈፀመችውን በደል ስትናዘዝለት፣ ራሱን መቆጣጠር ተስኖት፣ 'መጀመርያ ለምን አጥፍቼያት አልጠፋም?' አለ:: ቀጥሎ ደግሞ፣ ትንሽ አደብ መግዛት ሲጀምር፣ ለምን እሷን ወደማላይበት ጥቃቴን ወደማላስታውስበት ጦር ሜዳ አልሄድም አለ- ወዶ ዘማች ለመሆን:: ለምን ከደርግ ወገን ተሰልፌ ወያኔንና ሻዕቢያን እየወጋሁ በአንድ ድንጋይ ሁለት ወፍ አልገድልም አለ:: ሚስቱ ያደረሰችበትን በደል ለመርሳትና በውትድርና ደሞዝ ህይወቱን ለመምራት:: በዚህ ሃሣብ ተስማምቶ እና ተፅናንቶ በፈቃደኝነት ራሱን ለውትድርና ከመለመለ በኋላ ግን አንድ ነገር ትዝ አለው:: እናቴስ? አለ:: ደግሞ ሌላ ሃሣብ መጣለት:: 'በሴት ሰበብ እራሴን ከማጠፋ ወይም ደግሞ ምርጫዬ ወዳልሆነው የውትድርና ዓለም ከምገባ፣እናቴንም ያለመከታ ከማስቀር ብፈታት አይሻልም?' አለ::

ይህ ከመሆኑ በፊት ግን ፊቱን እንዳጨፈገገ ጠየቃት::

"እንዴት በእኔ ላይ ወንድ ትደርቢያለሽ?"

"በናትህ ተረዳኝ፤ አንተ ያልተረዳኸኝ ማን ሊረዳኝ ነው? አንተንም ሆነ ራሴን ለመበደል ብዬ አይደለም እንደዚያ ዓይነት ስህተት ውስጥ ገባሁት!" አለችው፣ ዕንባዋን እየዘራች፣ "ይቅርታ!"

አብዝታ ለመነችው::

"እና፣ ምክንያትሽ ምንድነው?"

"ለምኑ?"

"ከሌላ ወንድ ጋር የተኛሽው ምን አጉድዬብሽ ነው?"

"እ?"

"ምን አጉድዬብሽ ነው?" አላት:: አሁን ደግሞ ፈራ ተባ እያለ ጠየቃት:: ካንተ ጋር አልጋ ላይ አልተጣጣምንም እንዳትለው እየሰጋ::

"ባታውቀው ይሻላል"

"ለምን?" ይበልጥ ደነገጠ:: ለምንድነው ባላውቀው የሚሻለኝ? ለመወስለት ያበቃትን ሰበብ እንዳላውቀው የምታደርግበት ምክንያት ምንድነው?

"ከነገርኩህ ልዋሽህ አልፈልግም፤ እውነቱን ከነገርኩህ ደግሞ ትጎዳለህ!"

"ንገሪኝ" ልቡ የሆነ ነገር መርጨት ጀመረ:: መሬት የለቀቀ፣እየተንሳፈፈ ያለ መሰለው:: መቀመጥ ፈለገ:: እየተሰማው ያለውን ስሜት ሊያሳያት ስላልፈለገ - ራሴን ስቼ ከመውደቄ በፊት ብሎ - ግድግዳውን ተደገፈ::

"ንገሪኝ!"

"ገንዘብ ቸግሮኝ ነው... "

"ቸግሮኝ ነው?"

"ያ! ብር አስፈላጊዬ ነበር"

አሁን አመመው::

"የከፈለሽ ስንት ነው?"

"ትንሽ ብር ነው፤ ሃምሳ ብር!"

ሊያጥወለውለው ሆነ፡፡ "ሃምሳ ብር?"

"አዎ!" አለችው በደቀቀ ድምጽ፣ በተሰበረ ልብ ሆና፡፡ "ከማን ጋር ነበር? ሰውየው ማነው?"

"ከድሮ ደንበኞቼ አንዱ!"

"ደንበኞቼ?"

"ካንተ፣ ከባለቤቴ ውጪ ከሌላ ወንድ በመሄዴ ራሴን አጥፊ አጥፊ የሚል ስሜት ተሰምቶኝ ነበር"

"ጐድተሸኛል..."

አለቀሰ፤ እሷም አለቀሰች፤ አባበለችው፡፡ "አይለመደኝም!" አለችው፡፡

"የት ተገናኛችሁ ነው?" ዓረፍተ ነገሩን የመጨረስ አቅም አጥቷል፡፡

"በናትህ አትጠይቀኝ..."

"ንገሪኝ"

"ምን ይጠቅምሃል?"

"ንገሪኝ!"

"ይቅርታ ጠየቅኩህ አይደል፤አይለመደኝም አልኩህ አይደል፤ ለምን እርስ በራሳችን እንጐዳዳለን?"

"ማወቅ እፈልጋለሁ..."

"ከነገርኩህ እውነቱን ነው የምነግርህ፤ እውነትን ማወቅ ደግሞ አንዳንድ ጊዜ ይጐዳል"

"የት አገኘሽ?" ድምጹን አጠነከረባት፡፡

"እኔ ነኝ ያገኘሁት"

"የት?" ይንዘርዘር ያዘ፤ጥርሶቹ መንቀጫቀጭ፣ ከንፈሮቹም መንቀጥቀጥ ጀመሩ::

"ቤቱ ሄጄ..."

"ሄጄ?"

ጭንቅላቱን ከግራ ወደ ቀኝ፣ ከቀኝ ወደ ግራ፣ ከላይ ወደታች፣ ከታች ወደላይ ሲንጥ ቆየና ከግድግዳው ጋር አጋጨው::

ደነገጠች:: ያሳበደችው መሰላት:: "በእናትህ እንደዚህ አትሁን፤ባፈቅርህ አይደል ሳትጠይቀኝ የተናዘዝኩት? በናትህ እንደዚህ አትሁን! በናትህ!"

"ዞር በይልኝ! ዞር በይ! ጥፊ! ከፊቴ ጥፊ! ሴትዮ! አንቺን እኮ ነው:: ሂጂልኝ! ውጪልኝ!!!!!!!!!!!!!!!!!!!!!!!!!!!!!!!!!!!!!!!!!!!!!!!!!!!!!"

"የት?"

"ወደ ምትሸረሙጪበት...ወደ ምትሸረሙጪበት...."

ቆጣ ማለት ጀመረች::"ሸርሙጣ እንደነበርኩ አስታዋሽ አያስፈልገኝም:: ይህንን ነበር የፈራሁት"

"እንደነበርሽ አይደለም፤ ነሽ እንጂ! ነሽ፤ ሸርሙጣ ነሽ!"

በረዶ ሆነች:: "ይህንን ነበር የፈራሁት፤ የትላንት ህይወትሽን እያነሳሁ አልነተርክሽም ብለህ የገባህልኝ ቃል ምን ዋጠው?"

"አንቺስ ብትሆኚ ምን እያደረግሽ ነው?"

"እንዴት?"

"ለሃምሳ ብር ብለሽ ገላሽን ስትሸቅይ ምንም ያልተሰማሽ"

"ስርዓት ያዝ እሺ! ምንም ያልተሰማሽ አትበለኝ፤ ቢሰማኝ አይደል ለሦስት ቀናት ያህል እንቅልፍ አጥቼ ያደርኩት? ቢሰማኝ አይደል ሳትጠይቀኝ በገዛ ፍቃዴ የተናዘዝኩት? ቢሰማኝ አይደል..."

“ጅራፍ ራሱ ገርፎ ራሱ ይጮሃል አሉ:: አሁን ምንሽ ተነከቶ ነው፣ እንዲህ እምጺር እምጺር የምትይው? “ምንም ያልተሰማሽ አትበለኝ፤እኔ ነኝ ምን እንደተሰማኝ የማውቀው!”

“ለሃምሳ ብር ብለሽ አመንዝረሻል!”

“ሃምሳ ብሩን ምን እንዳደርግኩበት ለምን አትጠይቀኝም? እናትህ በጠና ታመው፣ ፀበል አድርሱኝ፤ ከመሞቴ በፊትም ደብረ ሊባኖስን አሳልሙኝ ብለው ሲማፀኑኝ፣ ምኞታቸውን ለመሙላትና አንተንም የማስደሰት መስሎ ስለታየኝ እንጂ...” ዕንባ ተናነቃት::

“ድፍረትሽ!”

“እናትህን ለማስደሰት ብዬ ነው:: ጅልነቴ ነው ያዋረደኝ:: እሳቸውን ደብረ ሊባኖስ ለማድረስ መባለጌ ሳያንስ በሠራሁት ሥራ ተፀፅቼ ስህተቴን ላንተ መናዘዜ...”

“ሸርሙጣ ነሽ...”

“ነኝ!”

“የድፍረትሽ ብዛት ጣትሽን ወደ እናቴ መቀሰርሽ!”

“እንኳን!”

“ምን?”

“እንኳን! ምን ታመጣለህ? ሸርሙጣ ነኝ፤ በሃምሳ ብር ገላዬን የምሸጥ ሰው ነኝ፤ ለምሠራው ስህተት እናትህን ተጠያቂ የማደርግ ነኝ፤ነኝ! ሁሉንም ነኝ፤ እስካሁን ያልከውን፣ አሁንም የምትለውንና ወደፊትም ልትለኝ የምትችለውን ሁሉ ነኝ!” አለችው፣ ጥርሷን ነከሳ::

ፊት ለፊት ተፋጠጡ:: ፀጥ!

“የእኔ ስህተት ከማያዋጣኝ እውነት ጋር ለመፋጠጥ መሞከሬ ነው!”

“ሸርሙጣ!”

"ነኝ! ነኝ! ነኝ!"

ከማታሸንፈው ዕንባዋ ጋር መታገል ጀመረች::

"ሁለተኛ የእናቴን ስም አትጥሪ:: የሃጥያትሽ ተባባሪ አድርገሽ አትከሰሻት..."

"መች ከሰስኳቸው? መች ወቀስኳቸው?"

ወጣ:: ተመልሶ ገባ:: አሁንም ወጣ:: አሁንም ተመልሶ ገባ:: ኮቱን ለብሶ ወጣ:: ከዚህ በኋላ አልተመለሰም:: ይሄ ሁሉ ሲሆን እሷ ቆማ ነበር:: የሆነው ነገር ሁሉ ረበሻት:: የካበችው ሲናድ ታወቃት:: ስቅስቅ ብላ አለቀሰች::

ሁለት ዓመት:: በሁለት ዓመት የትዳር ቆይታ ውስጥ ከፉ ተመላልሰው አያውቁም ነበር:: ከሦስት ቀናት በፊት ግን አንድ ስህተት ተፈፀመ:: የፈፀመችውን ስህተት አለመናገር ከበዳት:: እናም ነገረችው:: ከሁለት ሦስት ዐረፍተ ነገሮች በኋላ አሁን የሆነው ነገር ሆነ:: "ተሳስቻለሁ" አለች፤ "ዝሙት ባልፈፅም ጥሩ ነበር፤ በዚያ ሰዓት ግን ጨንቆኝ ስለነበር አደረግኩት:: ትልቁ የእኔ ስህተት የሠራሁትን መንገሬ ነው..."

እናቱ፣ የወለዱት ከትዳር ውጭ ነው:: በደርግ ጊዜ የነበረ አንድ ባለስልጣን፣ 'ባልሽን ከምገድለው፣ በምስጢር ከምትተኚልኝ?' አላት::

ባሏን ትወደዋለች:: ገላዋ የእሱ ነው:: ይሄ ባለስልጣን የመግደልም የማስገደልም መብት በእጁ አለ:: ባሏ እንዲሞት አትፈልግም...

ከራሷ ጋር ስትሟገት ቆየችና በምስጢር ተኛችለት:: አረገዘች፤ የተረገዘው ልጅ አባቱን መሰለ፤ ባል አጥብቆ ጠየቃት፤ በንሰሃ አባታቸው በኩል እውነቱን ተናዘዘች:: ባል ሚስቱን ካልገደልኳት ብሎ ፎከረ::

ከነልጇ ከቤቷ እንድትባረር 'ተፈረደባት::'

ስደተኞቹ እናትና ልጅ ኑሮአቸውን አሸንፈው መኖር ከጀመሩ ከሠላሳ ዓመታት በኋላ፣ ልጅየው አንድ ድካም ወደ ተጫጫናት ቡና ቤት ገብቶ አንዲት ሴት አየ::

በዕለቱ 'ሃብታም' ሆኖ ነበር:: ስልሳ ብር ነበረው:: ለአንድ የጉልበት ሠራተኛ ስልሳ ብር ብዙ ነው:: አንድ ሁለት ቢራ ጋበዛት...

እንዴት እንደጀመረው ሳያውቅ ስለ እናቱ ሲተርከላት ራሱን አገኘ::

አዘነችላቸው፤ ለእናቱም ለእሱም!

'እናቴ፣ እውነቱን ተናግሬ በመሸበት አድራለሁ ብላ ይኸው ማደርያ አጥታ ስትንከራተት ሠላሳ ዓመት ሞላት...' አላት::

ሳታስበው ከተቀመጠችበት ተነስታ አቅፍ አድርጋ ሳመችው- በጠጪዎች መሐል:: 'አይዞህ እሺ?'

'እሺ'

ተከዘች::

በሁኔታዋ ሲገረም ቆየና፣ 'እኔ ከተሰማኝ በላይ አዝነሻል፤ ልብሽ ተነክቶ ነው?' ብሎ ጠየቀ::

'እውነተኞች ያሳዝኑኛል...' አለችው::

ተለያዩ:: ሌላ ቀን መጣ:: ድንገት በጨወታ መሃል፣ 'እናትህን አስተዋውቀኝ? አስተዋውቀኝ አልኩህ እንዴ' በራሷ ሳቀች:: 'ከርቀት ያቺ ናት ብለህ ታሳየኛለህ:: አታሳየኝም?'

አንድ ቀን ሰፈሯ ወደሚገኝ ሱቅ ደጅ ደርሳ፣ ስልክ ደውላ፤ አባካችሁን ከጐረቤት ጥሩልኝ አለቻቸው - ይህንን ሰው::

መጣ::

'ሄለው!'

'አቤት...'

'እንዴት አደርክ?'

'እየቀለድሽ ነው?' አላት፣ ለመሣቅ እየሞከረ::

'ምነው?'

'ከሰላሳ ደቂቃ በፊት ደውለሽ እንዴት አደርክ ብለሽኝ ነበርኮ!'

'ነበር?' ደንገጥ አለች::

'ብለሽኝ ነበር'

'አይገርምም? ልደውል መፈለጌን እንጂ እንደደወልኩልህ ረስቼ ነበር:: እየወደድኩህ ነው መሠለኝ፣ ቶሎ ቶሎ አግኘው አግኘው ይለኛል'

ከዚህች ቀን በኋላ በሁለቱ መካከል አዲስ ምዕራፍ ተጀመረ:: ተፈቃቀዱ::

ልቧን እንደሞላው እርግጠኛ ስትሆን የቡና ቤት ህይወቷን እርግፍ አድርጋ ተወችው:: ከምንም ነገር በላይ ደግሞ ጋብቻቸውም በእሱ እናት ዘንድ ሞገስ ያገኘ መሆኑን ማመኗ እና ማወቋ ልቧን አረጋጋው::

ለሁለት ዓመታት ቆዩ - ፍቅራቸውና ትዳራቸው የሚያንገጫግጭ ነገር ሳያጋጥመው::

አዲስ የተለየ ምዕራፍ የተከፈተው ዛሬ ነው:: ይሄ መንገድ ወዴት እንደሚያደርሳት አታውቅም::

ረበሻት:: የት ሄዶብኝ ይሆን?

የእሱም ህሊና ተረብሾ ነበር:: ባዶነት...ከንቱነት...ዝብርቅርቅ ያለ ስሜት...አጥፍቶ የመጥፋት...ሦስት ወር ሙሉ ቤት ሳይገባ በየጐዳናው ሲንከራተት...በየጓዳ ጉድጓዳው ሲንጐዳጐድ...ሲባትል ቆየ::

አንድ ቀን...

ጠጅ ቤት ተቀምጦ ትካዜውን በሰካራሞች ጫጫታ እያስታመመ ሳለ፣ አጠገቡ የተቀመጡ አንድ ምራቅ የዋጡ የሚመስሉ ጠጪ፣ 'የሆነ ነገር ሆነሃል፤ የሆነ ውድቀትም ደርሶብሃል፤ የሆንከውን ካልነገርከኝ ሞቼ እገኛለሁ፤ ግድ የለም፤ እንማከር' አሉት:: ከብዙ ደጅ ጥናት በኋላ፣ የደረሰበትን በደል ይተርክላቸው ያዘ:: ሞቅ ብሎት:: እሳቸውም ከዚህ ሃሳብ ውጣ፤ ከዚህ ሃሳብ ውረድ ሳይሉት ከሆነው ነገር ጋር የሚተካከል ታሪክ ነገሩት::

.

.

.

*ፊታውራሪ ሀብተጊዮርጊስን አታውቅም? እሳቸውን የማያውቅ ኢትዮጵያዊ ካለ እንዳልተወለደ ይቁጠረው:: ፊታውራሪ ሀብተጊዮርጊስ ዲነግዴ አባመላ ነው ሌላኛው ስማቸው:: በአጼ ምኒልክ ዘመን በሕይወት የቆዩ የፍትህ አባት:: ከዕለታት አንድ ቀን አገር አማን ብለው፣ ቤት ያፈራውን ለመቅመስ ወደቤታቸው ሲገቡ፣ አንድ ያልተለመደ ነገር አዩ:: ያዩትን ነገር ማመን አቃታቸው:: ባለቤታቸው የፊጥኝ ታስራለች:: 'ምን ሆነሽ ነው ሆዴዋ?' አሉ፣ ተደናግጠው::*

*የአባ መላ ባለቤት ዝም:: አንገቷን ደፍታ ፀጥ::*

*'እናንተ ሰዎች ማን አባቱ ደፋር ነው ሚስቴን፣ መልካም ዘውዴን የፊጥኝ እንዲህ ያሰራት?'*

*'እኛ ነን አባ መላ!' አሉ፣ ታማኝ አሽከሮች::*

*'ምን ተፈጥሮ?'*

*'ስትወሰልት፣ ዝሙት ስትፈፅም፣ ስትሴስን፣ መኝታዎን ሲታስደፍርና ርስዎ ብቻ የሚያውቁት በሚመስሎት ገላ ላይ ሃጥያት ስትፈፅም ይዘናት...'*

*'እኮ የኔን ሚስት?' አሉ፣ አባ መላ::*

*'እጅ ከፍንጅ ይዘናታል፣ ምላሳችን እርስዎን ለመዋሸት የሰለጠነ አይደለም!' ይሏቸዋል::*

*'ሚስቴን ከማን ጋር ነው የያዛችኋት?'*

*'አባ መላ፣ የሰውዬውን ማንነት መናገር የርስዎን ክብር ማዋረድ ይሆንብናልና ...' ብለው ሊቀጥል ሲሉ፣*

*'ሰውየው ማን ነው?' አሉ፣ በቁጣ::*

'ከአሽከሮችዎ መሃል አንዱ ጥጋበኛ ሴሰኛ ነዋ:: ሰውየውን ይዘነዋል፤ ሁለቱንም መኝታ ላይ ደርሰንባቸው ነው ያሰርናቸው:: እሱን አንድ ከፍል ውስጥ ቆልፈንበታል!' አሉ፣ አሽከሮች በቁጣ እየተንተገተጉ::

አባ መላ ያሰላስሉ ጀመር::

አሽከሮችም፣ 'ከፈለጉ ሁለቱንም በጐራዴ ይቅሏቸው፣ ወይም ስቅላት ይፍረዱባቸው:: ሕጉ ለአመንዝራዎች የሚራራ አንጀት የለውም!' አሏቸው::

'ሁለቱንም አምጡአቸው!'

መጡ::

'የታሰሩበትን ሰንሰለት ከእጃቸው አላቁልኝ!'

አላቀቁላቸው::

'አሁን ሁለቱን አስረኞች እንጂ ሌሎቻችሁ አታስፈልጉኝም! አሉና ታማኝ አሽከሮቻቸውን አሰናበቷቸው::

ሚስታቸውንና አሽከራቸውን ደግሞ ለብቻ ብቻ ጠየቋቸው::

ሀሰት ያልተቀላቀለበት ወሬ ለማውራትም ተስማሙ::

'ድንገት ተገናኝታችሁና ጊዜያዊ ስሜት አሸንፏችሁ ነው፣ በአልጋዬ የማገጣችሁት?'

'መቸስ...እውነት እውነቱን ብቻ ልናወራ ተስማምተን የለ? ድንገትም አይደል የተገናኘነው:: ጊዜያዊ ስሜትም ጥሎን አይደለም:: እውነት እውነቱን እናውራ ካልን ሁለታችንም አስበንበት ነው' መለሰች ሚስት:: 'ቀን ቆርጠን ቦታ መርጠን ነው እንጂ ድንገት አይደለም ተገናኝተን የወሰለትነው'

'ከልብ ተዋድዳችሁ፣ ተፈቃቅዳችሁ?' አሉ፣ ጥያቄያቸውን ረግጠው::

'አዎን አባ መላ!'

'በድብቅ ስትገናኙ ምን ያህል ጊዜ ሆናችኋል?'

'ኧረ ዘመንም የለን፤ ሰንበተናል'

ነው?' አሉ፣ አባ መላ::

'እንዋሽ ከተባለ የሆነውን ነገር እንዲህ ነው' አለች ሚስት::

አባ መላ አሰረኞቹን ለቀቋቸው:: ወዲያውኑ ለሰላሳ ሰው በቂ የሚሆን እራት እንዲዘጋጅና የተከበሩ መሳፍንትና መኳንንት ጥሪ እንዲደረግላቸው ትዕዛዝ እንዲተላለፍ አደረጉ:: ሰዓቱ ሲደርስ ጥሪ የተደረገላቸው እንግዶች ቦታ ቦታቸውን ሲይዙ፣ አባ መላ የመክፈቻ ንግግር ቢጤ አሰሙ::

'ስለመጣችሁ አመሰግናለሁ:: ይህ በይፋ ያልወጣ ትዳር ነበር:: አሁን ግን ጋብቻውን በይፋ እንዲያከብሩ ፈቅጃለሁ!' ይሉና ሁለቱን ሙሽሮች ማስተዋወቅ::

ባል- ቢታማኝ አሽከሮቻቸው መሐከል አንዱ::

ሚስት - ሀገር ያወቃት፣ ፀሐይ የሞቃት ባለቤታቸው::

ያለ አጃቢ ያለሚዜ ሠርጉ ተጠናቀቀ:: አባመላ፣ ለቀድሞ ባለቤታቸውና ለታማኝ አሽከራቸው ከመሬታቸው ቆርሰው፣ ከከብቶቻቸው ቆጥረው ከገንዘባቸው ቀንሰው ሰጧቸው::

በዚያን ሰሞን፣ አጼ ምኒልክ ይህን ሰምተው ኖሮ፣ 'እውነት ነወይ?' ብለው አባ መላን አስጠርተው መጠየቅ:: 'ሚስትህን ለአሽከርህ ድረሃታል የተባለው ነገር ... ›

‹አዎን አድርጌዋለሁ!'

'አባ መላ!'

'አቤት ጃንሆይ...'

‹እንዲያ መወሰንህ ምን ዓይነት ሃሳብ በልቦናህ ቢያድር ነው?'

'ጃንሆይ!'

'አቤት አባ መላ ...'

‹እኔ በሃብት የደረጀሁ፣ ብልፅግናዬ የበዛ ሰው አይደለሁም?'

‹ነህና!'

*'የርስዎ የቅርብ አማካሪ፣ የጦር ሚኒስትር አይደለሁም?'*

*'ምን ይጠራጠሯል!'*

*'ታዲያ ይሄ ሆኖ ሳለ ከብልፅግናም ከስልጣንም እዚህ ግባ ከማይባል ሰው ጋር ሚስቴ መልሳ መላልሣ አልጋ ላይ መውደቋ ከአሽከሬ ጋር ፍቅር ብትሆን አይደለም ወይ? ታዲያ ለምን እከለከላታለሁ' አሏቸው አሉ::*

.

.

.

ሚስቴ ዝሙት ፈፀመችብኝ ብሎ በደሉን ሲናዘዝ የነበረው አባወራ ወጉን ያዳመጠው በፀጥታ ነበር:: የሽማግሌው አካሄድ ገብቶታል:: የእጅ አዙሩ ምክር ገብቶታል:: ጉዳዩን ያቀለሉበት እንደሆን ገብቶታል:: አልተዋጠለትም:: ይልቁንስ አንድ ሃሣብ መጣለት:: ተቃራኒ:: ለምን አልበቀላትም? አለ:: እንዳነደደችኝ አነዳታለሁ ብሎ አሰበ:: ሊቀጣት መዘባበቻ ሊያደርጋት ወሰነ::

አንዲት የሚያውቃት ሴት ነበረች:: ልጅቱ ከወንድ ጋር ተኝታ ሳለ እጮኛዋ ደረሰባት አሉ:: እጮኛዋ የሆነውን ነገር መኝታ ቤት ገብቶ አየ እንጂ ሰው አልነገረውም አልጋ ላይ ደረሰባቸው:: አልጋው ፊት ለፊት ወንበር አለ:: ሄዶ ተቀመጠ:: ልብሳቸውን ሲያጠልቁ፣ በደንጋጤ አመዳቸው ቡን ሲል፣ እሱ ግን በርካታ የቤት መክፈቻ ቁልፎች በእጁ ይዞ ነበርና ከቀኝ እጁ ወደ ግራ እጁ እያቀባበለ ያንን ዝምታ ይሰብረው ጀመር...

ቃል አልተነፈሰም:: ከልጅቱ ጋር የተያዘው ወንድ ተደናግጦ ወጣ:: ከመደንገጡ ብዛት የተነሣ የውስጥ ሱሪውን ማድረጉን ሁሉ ረስቶ ነበር:: እሷ ግን አለቀሰች:: እግሩ ስር ተደፍታ አለቀሰች:: እሱ ግን - በወጣ በገባ ቁጥር - የገዛ ቁልፉን ከማቅጨልጨል ውጭ አንዳችም ያደረገው ነገር አልነበረም:: ይሄ የበቀል ርምጃ በየሄደችበት ይከተላት ጀመር:: የቤት ወይም የመኪና ቁልፍ ባየች ቁጥር፣ የቁልፍ ድምጽ በሰማች ቁጥር መበርገግ ሆነ ሥራዋ!

ወንዱ ከእሷ ጋር የነበረውን ህይወት አልሰረዘም:: እሷ ግን ፀፀት ከምትችለው በላይ ሆነባትና በቃኝ! ብላ ወጣች::

'ከተበቀሉ አይቀር እንዲህ ነው!' ብሎ፣ ወደ ቤቱ ተመለሰ፡፡

ከሚስቱ ጋር እንደተገናኙ ተቃቅፈው ተላቀሱ፡፡

"ይቅርታ ሆዴ! ጐዳሁህ አይደል!"

"እኔንም ሆነ ራስሽን ለመበደል ብለሽ አይደለም ያደረግሽው"

"ጐድቼሃለሁ..."

"ታማሚ እናቴን ደብረ ሊባኖስ መውሰድ መቻልሽን ብቻ ነበር ያሰብሽው"

"ሁለተኛ እንደዚያ አላደርግም፤ በፍፁም አልሞክረውም!"
መሸ፡፡

ተቃቅፈውና ተሳስመው ሊተኙ ሲሉ ብድግ አለችና አንዲት ወረቀት ይዛ መጣችና ሰጠችው፡፡

"ምንድነው?"

"ተመረመርኩ..."

"መቼ?"

"የተጣላኸኝ ቀን"

"ራስሽን ተጠራጥረሽ ነበር?"

"በጭራሽ!"

"እና..."

"የተኛሁለት በኮንዶም ነበር፡፡ ቢሆንም..."

"ደግ አደረግሽ!" አላት፡፡

"ጭር አላልኩብህም?"

"ብለሺብኛል"

"ምን አዲስ ነገር አየህብኝ?"

"ተጸጽተሻል"

"ሌላስ? የጐደለ ነገር አላገኘህብኝም?" አንገቷን ወዘወዘችለት::

አልገባውም::

"የጀሮ ጌጥሽ የት ሄደ አትለኝም?"

"ተሰርቀሽ ነው?"

ለመጋባት የወሰኑ ቀን የሰጣት ስጦታ::

"የተበደርኩት የጆሮ ጌጤን አስይዤ ነው"

"መዋያ አጥተሽ ነው?"

"ለምን? ልመረመርበት ብዬ እንጂ:: አወድህ የለ? በህይወት እንድትቆይልኝ እፈልጋለሁ"

"አመሰግናለሁ!"

ደስ የሚል ማታ ሆነላት::

ነጋ:: ጠዋት እንቅልፍ ጥሏት ነበርና ቀሰቀሳት:: መንቃቷን እርግጠኛ ሲሆን እጁን ወደ ኪሱ ሰዶ ሃምሳ ብር አውጥቶ ሰጣት::
"ምንድነው? የቤት ወጪ?" አለችው፣ ከትራሷ ቀና ብላ::

"የቤት ወጪ አይደለም"

"እና?"

"ከእንግዲህ በነጻ አልተኛሽም"

ብድግ አለች::

"ምን?"

"ለእስከዛሬው ይቅርታ! ከእንግዲህ በኋላ ግን በነጻ አልተኛሽም!"

አማተበች::

"ምን እያልከኝ ነው?"

"ከእንግዲህ በተኛሁሽ ቁጥር ሃምሳ ብር እከፍልሻለሁ"

"እከፍልሻለሁ?"

"ከፈለግሽ በእናቴ ስም ቃል እገባልሻለሁ"

የእሷ ባልሆነ ድምጽ፣ "ሚስትህ እኮ ነኝ" አለችው::

"ብትሆኝስ! ከእንግዲህ ለቤት ወጪ የሚሆን ብር መስጠቴን እቀጥላለሁ:: ይሄ ሃምሳ ብር ግን ለቤት ጉዳይ እንዳታውይው:: ልትኳኳይበት እና ልትጊያጊያጭበት ነው እንጂ ብሩ ከሌላ ጋር እንዳይደባለቅ..." ቀጭን ትዕዛዝ ሰጣት::

"ለአንድ አዳር ሃምሳ ብር:: ሸርሙጣ ስለሆንኩ ነው አይደል?" አለችው፣ የመረረ ሣቅ ሥቃ::

"አሁንም ‹አይደለሁም!› ብለሽ ነው የምታምኝው?"

ወጣ:: ሥራ ሄደ::

ማታ ተመለሰ፡፡

የሚስቱ መረበሽ አድጓል፡፡ ተረጋግታ አልጠበቀችውም፡፡ ታማ መተኛቷን ሲያይ ደስ አለው፡፡ ይኼ ነገር እየተደጋገመ መጣ፡፡ መንፈሷ ተሰቃየ፡፡ እራሷን መቆጣጠር እስኪያቅታት ድረስ መልመድ አቃታት፡፡ ሁኔታውን መልመድ ቢቸግራትም የስሜቷን መረበሽ ልታዋየው አልፈቀደችም፡፡

ቀስ በቀስ ግን ሁሉም ነገር የተዋሃዳት መሰለ፡፡ ኑሯቸው እንደነበረ ቀጠለ፡፡ እንደ ድሮው መሣሣቅ - እንደድሮው መቀላለድ - ሁሉም ነገር እንደነበረው ሆነ፡፡ የነበረ አዲስ ነገር ቢኖር በሣምንት ሁለት ወይም ሦስት ጊዜ ይተኛታል፡፡ በተኛት ቁጥር ይከፍላታል፡፡ ሳይጨምር፤ ሳይቀንስ፡፡

ኑሯቸው ግን እንደነበረ ነው፡፡

ወጪዎቹ ከመብዛታቸው የተነሳ የገቢ ማግኛ መንገዶቹን በማብዛት የእንቅልፍ ሰዓቱን ያሳንስ ጀመር፡፡ በርግጥ በእሷ ላይ ለውጥ ማየት ፈልጐ ነበር፡፡ የሚሰጣት ገንዘብ አንኰል ሲያደርጋት ሲያሳብዳት ... ከሰውነት ተራ ሲያስወጣት...ሲያስቀበዥራት...ይህን ነበር ለማየት የናፈቀው፡፡ እሷ ላይ ግን ለውጥ አልነበረም፡፡

"ይሄ ሥጋ ከየት መጥቶ ነው?" አለ አንድ ቀን፣ ከጐመን ጋር የተቀቀለ ሥጋ ለራት ሲቀርብለት፡፡

"ገዝቼ ነዋ! ድሮስ ከየት ላመጣ ነው?" አለችው፣ በጥያቄው ግራ የተጋባች መስላ፡፡

"ገንዘብ ከየት አመጣሽ?"

"አንተ የምትሰጠኝ የቤት ወጪ የት ሄዶ?"

ዝም!

"የዚያን ከዚህ እየቀላቀልሽ አይደለም አይደል?" አላት፣ ሌባ ጣቱን ወደ መሸጊያዋ እየጠነቆለ፡፡

"አታድርጊው ብለህ አዘኸኝ የለ?"

"እናቴ ትሙት በይኝ እስኪ..."

"እኔ እዋሻለሁ? ብዋሽስ አንተን እዋሽሀለሁ?"

"ግራ እያጋባሽኝ ነው:: ለመሆኑ የምሰጥሽን ገንዘብ ምን እያደረግሽበት ነው? ለገላሽ መከፈል ከጀመርኩ አንስቶ ሰውነትሽ ላይ አዲስ ነገር አላየሁም:: የምልሽ ገብቶሻል አይደል? ቅባት ወይም ጌጣጌጥ ወይም አዲስ ልብስ በቅርቡ አልገዛሽም፤ ለምንድነው?"

"እንዴ አሁን መግዛት - መዋብ - መሽቀርቀርና ወንዶችን በሚያማልል አለባበስ መሽሞንሞን ያላማረኝ እንደሆንስ?"

"እንደዚህ የሚያስኘሽ መቼ መቼ ነው?"

"ሲደርስ ታየዋለህ"

በልቡ፣ 'ሽርሙጣ!' ብሎ ሰደባት:: 'ድመት መንኩሳ አመሏን አትረሳ'

ቀን ሄደ:: ወር መጣ:: ሁሉም ነገር እንደነበር ቀጥሏል::

ባልም ለአንድ አዳር በተኛት ቁጥር ሃምሳ ብር መክፈሉን...ሚስትም ቁጥሩ መቀበሏን...በሰጣት ቁጥር ይበሳጫል:: ምን ዓይነት ድንጋይ ልብ ቢኖራት ነው ድርጊቴ የማያሳብዳት? ፀፀት የሚሉት ነገር አልፈጠረበትም ወይስ ምንድነው? ግራ ይገባዋል:: ቀኑን ሙሉ ሲያስበው ይውላል::

ሁለት ወር ሆነው::

አንድ ቀን - እንደተለመደው ተኝቷት ሲነሳ - ሃምሳ ብር ሲሰጣት አንድ ነገር ሆነ:: አምስት የአስር ብር ኖቶች:: አንዷ ቀራጣ ነች:: ለብዙ ጊዜያት ኪሱ ውስጥ ስትንከራተት ቆይታለች:: የሚቀበላት አጥታ:: 'ቀሪውን ሌላ ቀን እከፍልሻለሁ' ማለት ድህነቱን በይፋ ማወጅ መሆኑን ገመተ:: ስለዚህ ቀራጣውን ብር ልብ ብሎ ያላየ መስሎ ሰጣት::

ሁል ጊዜ እንደምታደርገው የብር ኖቶቹን ተቀብላ ወደ ተኛችበት ፍራሽ ስር...

ይህ በሆነ በሁለተኛው ቀን፣ ደብረሊባኖስ ሄደ - እናቱን ለማየት፡፡

"ባለቤትህስ?" አሉት፣ በስስትና በናፍቆት፡፡

"ደህና ናት..."

"እንደው ስወዳት!"

"አንቺ እንዴት ነሽ?"

"ማርያም ጥላዋን ብታጠላብኝ አይደል፣ በሷ በኩል ጠባቂ ጧሪ የላከችልኝ! ለእኔ ለናትህ እንዲህ የምትጨነቅ ላንተስ እንዴት ትሆንልህ ይሆን?"

በሚስቱ ዙርያ የውይይት መድረክ መከፈቱን አልፈለገውም፡፡ "እንዴት ነሽ አንቺ?" አለ፣ ርዕስ ለማስቀየር፡፡

"አንተ ኑርልኝ፤ ሚስትህ ትከበርልኝ እንጂ እኔማ ምን እሆናለሁ?"

"አያምሽም አይደል?"

"ምን ጐሎብኝ? ይሄን ሁለት ወር ምን ጐድሎብኝ? ሚስትህ አይደለች እንዴ፣ ለናቴ ላኪልኝ ብለህ በሳምንት ሁለት ቀን ሃምሳ ሃምሳ ብር ስትሰጣት እሷ ደግሞ ወዲህ በሚመጡ ሾፌሮች የምትልክልኝ? ሰሞኑን ግን ምንነው? ከላከልኝ ብር አንዱ ድፍን አስር ብር ላይ ቁጥሩ ተቆርጧል እያሉ ማን ይቀበለኝ? ባንክ ቤት ይለውጣሉ አሉ፡፡ ታስለውጥልኛለህ" አሉና፣ መቀነታቸውን ፈትተው ብሩን ሰጡት፡፡

ደነገጠ፡፡ ጨለመበት፡፡ ጭልም!

"ምን ሆንክ ልጄ!" እጃቸውን ግንባሩ ላይ፣ ዐይናቸውን ዐይኑ ላይ እየተከሉ፡፡

"ምንም!"

"ፊትህ ተለውጧል፤ አምሀል መሰለኝ"

"ተሰምቶኝ ነው!" አለ አንገቱን ሰብሮ፣ የሰጡትን ቆራጣ አስር ብር ጭርምትምት እያደረገ፣ በጫጫቆም እየቀደደ፡፡ "ተሰምቶኝ ነው!"

....

# የእንጀራ እናት ነገር

ክፍሌ ሳራን ካገባት በኋላ ቤቱ በአዳዲስ ነገሮች ተሞላ:: ቤቱም ቀለም ተቀባ::

ሳራ የግድግዳው ቀለም ሲደርቅላት ግድግዳ ላይ ጌጣጌጦችን መሰቃቀል ይዛ ነበር:: ድካሟ በዝቶ ጉልበቷ ሲዝልባት እመኝታ ቤቷ ገብታ ተኛች:: የሁለቱ ሴት ሕጻናት መንጫጫት ግን እንቅልፍ አላስወስድ አላትና መነጫነጭ ጀመረች:: "ምንድነው የሚያንጫጫችሁ?" አለች፣ ከተኛችበት አልጋ ተነስታ::

"ሳላውቅ ወድቄባት ነው" አለች ታላቅ፣ ጥፋቷን ማመኗ ፊቷ እያሳበቀባት::

"ወድቄባት?"

"ከበርጩማ ላይ ወደቀችብኝ" ልቅሶዋን አባሰችው፣ ታናሽ::

"ምንድነው የምትሉት?"

"ጥቅስ ስሰቅል ወድቄባት ነው" አለች ታላቅ፣ ድርጊቱ ወደተፈፀመበት ግድግዳ ጥግ በእጇ እና በአገጯ እያመላከተች::

ሳራ ግድግዳውን አየችው:: ሌኦስ የጠገቡና ለብዙ ዓመታት የነበሩ ጥቅሶች ናቸው:: ከቆሻሻ ወረቀቶች ጋር ልታቃጥላቸው ደጅ ላይ አኑራቸው ነበር::

"ከደጅ አንስቶ ያመጣቸው ማን ነው?"

"እኔ!" አለች ታላቋ፣ የሚመጣባትን ቅጣት ለመቀበል እንደተዘጋጀች ሆና::

ሳራ ጓደኛዋ ከመሞቷ፣ ከፍሌን ደግሞ ከማግባቱ በፊት የምታውቃቸው ጥቅሶች እንደ አዲስ ዐይኖቿን ጣለችባቸው::

*እናት ለምን ትሙት ትኑር አጐንብሳ*
*ታሳድግ የለም ወይ በችጋር ተጠብሳ ...*
*....*
*እናቴ አትሙቺ ልሙትልሽ እኔ*
*ከአጠገቤ ሳጣሽ ይባክናል ዓይኔ ...*

ይህ ከሆነ ጥቂት ወራት አልፎታል::

ሳራ፣ ወልቂጤ መኖር ከጀመረች ጊዜ አንስቶ እንደ ዘንድሮ በውሃ ችግር ተፈትና አታውቅም:: ከተማዋ የፀሃይዋን ግለት በእጥፍ ለመጨመር እንጂ የነዋሪዎቿን የደረቀ ከንፈር በጠብታ ውሃ ለማርጠብ አልሆንልሽ ብሏታል::

ከወልቂጤ ሰማይ በታች የሚመሹ እንጂ የማይነጉ ቀናት እየተወለዱ ሲመጡ ስጋት ቤቱን ሠራባት:: በሹፍርና ሙያ የሚተዳደረው ባለቤቷ ከፍሌ ሰሞኑን አውቶብሱን ይዞ ወደ ከፍለ ሀገር አቅንቷል:: የልጆቹን ጤንነት እንደተጠበቀ ለማቆየት የምትችለውን ያህል ስትዳከር ቆይታለች:: አሁን ግን ከምትችለው በላይ ተፈትና ከእንቅልፍ መጣላት ልማዷ ሆኗል::

የከፍሌ የመጨረሻና ሁለተኛ ልጅ ወባ ነድፏት አልጋ ይዛለች:: ስሟ መሳይ ነው:: እናቷን መስላ ስለተወለደች ነው መሳይ መባሏ:: ሦስት ዓመት አልሆናትም:: ታላቋ አስቴር የምታንሳት በሁለት ዓመት ነው::

እናታቸው ካረፈች ዓመት ከመንፈቅ ይሆናል:: ቢጫ ወባ እናቷ ላይ ወጥቶ ሆስፒታል በገባች በሦስተኛው ቀን ዘመኗን ፈፀመችው::

ሕጻናቱ፣ ሳራ ቀደም ሲል የእናታቸው የልብ ጓደኛ በነበረች ጊዜ 'አክስቴ' ብለው ያቆላምጧት እንዳልነበር ሁሉ፣ ዛሬ የአባታቸው አዲስ ሚስት ስትሆን ቀዝቅዘውባታል:: የምትሠራውን ምግብ የመብላት ፍላጎታቸው የሞተ ነው::

አጣፍጣ የምትሠራላቸውን እህል የምታጎርሳቸው ለምና፣ አባብላ፣ ሳንቲም መጽውታ ነው::

በሠፈርተኛው ዘንድ ትዳሯ ተቀባይነት አላገኘም:: ጎረቤት እንዴት ያለችዋ ደፋር ናት? ብሎ ቡና በተጠራራ ቁጥር አፋቸውን የሚያሟሹባት ሆናለች:: የሚች ጓደኛዋን ባል ከንድ ስትንተራስ ትንሽ እንኳን አይቀፋትም? እያሉ::

ባለቤቷ ከፍሌ ግን ውሎ ባደረ ቁጥር ለልጆቹ በምታደርገው ከልብ የመነጨ እንክብካቤ ይደነቅ ያዘ:: በሁለቱ ዙርያ የሚሰሙ ጉርምርምታዎች ምንም ማለት እንዳልሆነ ከመናገርና ስሜቷ የማይጎዳበት መላ ከመዘየድ ሰንፎ አያውቅም::

በእርግጥ ባለቤቱ ካረፈች በኋላ ቤቱን ቀጥ አድርጋ ይዛ የነበረው ውሃ አጣጩ የመሆን ሀሳብ አድሮባት አልነበረም:: ሚችዋን ትወዳት ስለነበር...አብሮ አደግና ምስጢር የማይደባበቁ ስለነበር...ልጆቿን እንደ እራሷ ልጆች ቆጥራ ሰው እንደምታደርጋቸው ቃል ገብታ ስለነበር ...የሚቿ ቤት ከድባቴ ተላቆ ነፍስ እንዲዘራ ስታደርግ ...ከከፍሌ ጋር ተላመዱ::

መላመዳቸው መዋደድን ወለደ:: ስሜታቸውን መግታት አልሆንላቸው አለና የሦስት ጉልቻ ጥያቄ ከፍሌ ይዞ መጣ:: ሳራ ያለአንዳች ቅሬታ፣ ተቃውሞና ማመንታት ጥያቄውን ተቀበለችው::

ሚስት ከሆነችለት በኋላ፣ ሕጻናቱን ያዩ ሁሉ በእንጀራ እናት እጅ ያደጉ አይመስሉም ተብላ የምትሞካሸበት ቀን ይናፍቃት ጀመር:: ታላቅየዋን ከማስጠናትና ፊደል ከማስቆጠር ወደኋላ አላለችም::

ርግጥ ነው፣ ትንሿ ቀስስተኛ ናት:: ዝምተኛ እና አኩራፊ ናት:: እህል የምትጎርሰው ተለምና ነው:: በሳምንት ለሁለት ሦስት ቀናት ራሴን ያዞረኛል ብላ ወደ አልጋዋ ታዘግማለች:: ህመሙ በከበዳት ቁጥር አዩዩዋን ታስነካዋለች:: ሲያባብሏትም ዝም አትልም:: በዚህ ጊዜ ሳራ ትረበሻለች:: የመሳይ ጤና አለመሆን ራሷን ያሳምማታል:: ሰሞኑን ሲሆን የሰነበተውም ይኸው ነው::

ሐኪም ቤት ልትወስዳት ተዘጋጅታ ሳለች አንድ ነገር ታውሷት ነው የመሄዱን ነገር ያዘገየችው:: ትዝ ሲላት የመሳይ ገላ ውሃ ከነካው ሰንብቷል:: ይህ ያዩ

ጐረቤቶች ግድ የለሽ መስዬ እታያቸዋለሁ ብላ አሰበች እንጂ የውሃ ችግር የእያንዳንዱን ቤት የፈተነ መሆኑን ልብ ይላሉ ብላ አልገመተችም::

ከፍሌ ደግሞ ከፍለ ሀገር ከሄደ ሳምንት አልፎታል:: ሥራው ከተለያዩ አውራጃዎች አስተዋውቆታል:: ከሦስት ቀን በኋላ ሊመለስ እንደሚችል ደውሎ ነግሯታል:: 'ልጆች ደህና ናቸው?' ሲላት የመሳይን መታመም አልነገረችውም:: ከተማዋ በውሃ ማጣት እየተሰቃየች መሆኗን ግን ሳትነግረው ነው ያነሳባት:: በየመገናኛ ብዙሃን የሚነገር ርዕሰ ጉዳይ ሆኗል::

ሳራ አምስት ሊትር ውሃ ለማግኘት ያልኳተነችበት መንገድ አልነበረም:: የሌሊት ቁር ሳይበግራት በማታውቃቸው መንገዶች ብትመላለስም አልሆነላትም:: በጠራራ ፀሃይ ተንከራትታ፤ ልፋቷ መና በመቅረቱ ተቆጭታ ወደቤቷ ልትገባ ስትል፣ ጐረቤቷ ደጅ ላይ ሁለት ትናንሽ እንስራዎችን አየች::

አ - የ - ች:: እንስራዎቹ ባዶ አልነበሩም:: አ - የ - ች:: ልቧ የአንዱን እንስራ ውሃ ከጀለው:: ልቧ ይመታ ጀመር:: ብትለምናቸው እንደማይሰጧት ታውቃች:: እንዳቸውም ሊቀርቧት እንደማይፈቅዱ ስለምታውቅ አትወዳቸውም:: ከአንገት በላይ የሆነ ሰላምታ ነው የምትለዋወጠው - በአንድ ግቢ ከሚኖሩት ሦስቱ ጐረቤቶቿ ጋር::

የአካባቢው ሰዎች - ሁሌም ዝናብ ሲጠፋ እንደሚያደርጉት - ተሰባስበው አንድ ጥግ መርጠው - ነጠላቸውን ለባብሰው በተርታ ተሰልፈው፣ አንገታቸውን ዘንበል አድርገው ዐይኖቻቸውን ወደ ሰማዩ ሆድ ልከው፣ የ'እግዚአ አ መሀረነ ክርስቶስ' ጸሎት ሲያደርሱ፣ ሳራ ግን ያንን ውሃ የሞላውን እንስራ በመስረቅና ባለመስረቅ መሃል እያመነታች ነበር::

ወሰነች:: አዎ መሳይን አጥባ ሐኪም ቤት መውሰድ አለባት::

አዎን መሳይ ሻወር መውሰድ አለባት:: ከፍሌ ታናሿን ከታላቋ አብልጦ እንደሚንከባከባት ታውቃለች:: እናቷን ስለምታስታውሰው ይሆን ብላ ትገምታለች::

ዙሪያዋን ገልመጥ አደረገችው:: ግቢው ቀፎ ሆኗል:: በዝምታ የተሞላ ቀፎ:: መንቀሳቀስ ጀመረች:: ተጠጋችው እንስራውን:: ዘወር - ዘወር - ወር - ግቢው አሁንም ዝም ብሏል:: የምታደርገውን የሚከታተል ዐይን መኖር

አለመኖሩን ለማረጋገጥ ዐይኖቿን ከወዲያ ወዲህ አሯሯጠቻቸው:: ምንም:: ማንም:: ልቧ አሁንም ፍጥነቱን ጨምሮ መታ::

መስረቅ እንዴት ያስፈራል?

ጠላቶቿን ያሸነፈች መሰላት:: የእጅ አመል ኖሮባት ሳይሆን የሚች ጓደኛዋን ልጅ ለማዳን ብላ እየከፈለች ስላለችው መስዋዕትነት ስታስብ ልቧ በሃሴት ተሞላ...ፈገግ አለች::

ጠጋ ብላ እንስራውን አነሳችው::

ተጣድፋም ወደቤት አስገባችው::

ውሃውን ይዛ የጓዳውን በር ስትከፍት ትልቅየዋ እንስራውን አይታ ፊቷን በፈገግታ አበራችው::

"ዝም በይ! ለማንም አትንገሪ እሺ? ለናንተ ብዬ ነው!" አለች ሣራ::

"የናቴ አጥንት እሾህ ሆኖ ይውጋኝ ለማንም አልነግርም" አለች ታላቅ::

"እንደዚህ ብለሽ አትማይ አላልኩሽም?"

"ለማንም አልነግርብሽም ማለቴ እኮ ነው..."

አልጋ ላይ ሆና፣ 'ውሃ ጠማኝ' ብላ፣ ዕንባዋን ትዘራ የነበረችው መሳይ በዝግታ ከአልጋ ወረደች::

ሳራ እንስራውን አስቀምጣ ወደ ገባችበት በር አመራች ደጇን ቆለፈችውና ወደታማሚዋ መሳይ ተጠጋች:: "ገላሽን እጥብ አድርጌ ሃኪም ቤት እወስድሻለሁ እሺ? እሺ?"

"እኔ መጠጣት ነው የምፈልገው" አለች የምትፈልገውን ነገር እንዳትከለከል፣ በዐይኖቿም በእጆቿም እየተማፀነች::

"አሁኑኑ አፍልቼ አጠጣሻለሁ፤ አለበለዚያ ያምሻል"

ትልቋ ጣደፍ ብላ፣ "ትጠጣው፤ ስጪያት! የእናትና የውሃ መጥፎ የለውም ይባል የለ?" አለች፣ ኮስተር ብላ:: መሳይም አሁኑኑ ውሃ ሊሰጣት እንደማይችል ገምታ መነጫነጭ ጀመረች:: "እምቢዮ - እ- ም - ቢ - ዮ የተፈላ ውሃ አይጣፍጠኝም!" አፍንጫዋን ነፍታ ፊቷን አሳበጠችው:: የእንስራውን አንገት አንቃ ይዛ፣"የምጠጣው ጢንጥ ነው:: አላሳልቅብሽም - ጢኒጥ ብቻ - ከስኒ የማይበልጥ..." ብላ መለመኗን ቀጠለች::

ሳራ ከፋት:: "ከልቤ እንደምወዳቸው የሚገባቸው መች ይሆን? ለምንድነው እንደ ከፉ የሚቆጥሩኝ?"

መሳይ አኩርፋ እንስራው ስር ተቀምጣለች:: "ደሞ እንደባለፈው ያልታጠበ ልብስ የምታለብሽኝ ከሆነ አቢ ሲመጣ እነግርብሻለሁ" አለች፣ለንቦጭዋ እንደተንጠለጠለ:: ክፍሌን ነው 'አቢ' የሚሉት::

"መሳይ ውሃ ስለጠፋ እኮ ነው፣ ከልብሶችሽ መሃል በደንብ ያልቆሸሹትን መርጬ ያለብስኩሽ! ቧንቧችን ሲመጣ፣ ወይም ዝናብ ከዘነበ አጥብልሻለሁ፤ እሺ የኔ ቆንጆ?"

ገላዋን ለማጠብ የሚያስፈልጓትን ቁሳቁሶች አመቻችታ፣ የመሳይን ልብሶች እያወላለቀች ሳለ ወደ ቤቷ አፍንጫ ስር እየቀረበ የሚመጣ የእግር ኮቴ ሰማች:: ኮቴው እየቀረበ ሲመጣ ...የሳሎን በር ተንኳኳ...

ሳራ ብድግ አለችና የመንኳኳት ድምጽ ወደሰማችበት በር አመራች:: "ደህና አመሸሽ?" አለቻት፣ ቤቷ ደጅ ላይ ለቆመችዋ ወይዘሮ::

"ጉድ ነው፤ከጉድም ጉድ፤ ታፍረን በተከበርንበት መንደር እንዲህ እንደፈር? ደግሞ እንዲህም ተጀመረ? በስንት ልፋት ያገኘሁትንና ጉልበቴን ያሟሟሁበትን ውሃ ትወስጂብኝ ትሰርቂብኝ ጀመር?" ወይዘሮዋ ወገቧን ይዛ ተውረገረገች::

ሳራ ደነገጠችና፣ "ምን እያልሽ ነው?" አለቻት ደግማ፣ ከወይዘሮዋ ባልተናነሰ ቁጣ::

"ኧረ ባክሽ! አስመስለሽ ሞተሻል ሂጂና ለማያውቅሽ ታጠኚ..."

"ሳደርገው አይተሻል? ትልቅ ሰው አይደለሽም እንዴ እንዴት እኔን በዚህ ተራ ነገር ትጠረጥሪኛለሽ?"

"አንቺ ካልሆንሽ ታዲያ ማን ነው?"

"እኔ ምን አውቅልሻለሁ፤ እኔ የውሃሽ ጠባቂ ነኝ? ቀድሞ ነገር አንቺ ባልጠፋ ቦታ ደጅ ላይ ማስቀመጥሽ እንቁልልጮ ለማለት ይሆን?"

"የማን ናት ሙጢ?" አለች፣ ባለውሃዋ::

"ሙጢ? እንኳን እኔ አንቺም አልተባልሽ" ሳራ ትበግን ጀመር::

"እንዲህ ሲያዩሽ ደህና ትመስያለሽ:: ከፉ - የሰው ከፉ - የጓደኛሽን ባል መውረስሽ ሳያንስ ልጇን ለማሳከም የሰነፍሽው ከፉ ብትሆኚም አይደል? ንገሩኝ ባይ!"
ሳራ ፊቷ ቀላ:: ሁለቱን ተፋላሚዎች ዝም ለማሰኘት ጥረት ያደርጉ የነበሩ ጎረቤቶቿ ከንፈራቸውን ሲመጥጡ ሰማች፤ በንቀት አይን ሲያይዋትም::

ሳራ አፏ ላይ የመጡትን ቃላት በብስጭት ትንጣጣባቸው ጀመር:: "ቅናት ነው እንዲህ የሚያስለፈልፍሽ - ቅናት ነው - ዕድሜ ልክሽን ስትንጨረጨሪ ትቆያታለሽ እንጂ ባለቤቴን እንደሆነ አታገኚውም"

ሳራ ንዴት ናላዋን አዞሮታል:: ተሰዳቢዋንና ጎረቤቶቿን ትታ ገባች:: እንደገባች፣ ቤቱ በውሃ መጥለቅለቁን፣ እንስራው መሰበሩን አየች::

ቀና ስትል ትልቋ ግድግዳ ጥግ ተለጥፋ፣ ሊመጣ ከሚችለው አደጋ ለመከላከል የምታስብ ስትመስል፣ ትንሽዋ መሳይ ግን የእንስራው ስባሪ ገል ላይ ያለውን ውሃ ወደ አፍዋ ለማስጠጋት ትስገበገብ ነበር::

ሳራ ህጻኗ የያዘችውን ገል አመናጭቃ ነጠቀቻትና ወዲያ ስትገፈትራት፣ ቀሰስተኛዋ ህጻን ከንብል ብላ በአፍጢሟ ተደፋች::

የመሳይ ግምባር ከሲሚንቶው ወለል ጋር ሲጋጭ ደም ታየ:: ዐይኗ ይገለባበጥ ጀመር:: የታናሽ እህቷን መድማት የሳራን መደናገጥ - ልብ ብላ ያየችው ታላቅም ተፈትልካ ወጣችና እዬዬ ትል ገባች:: "ወይኔ እህቴን! ወ - ይ - ኔ - እማምዬ ድረሺልኝ - እ - ህ - ቴ - ን ገደለችብኝ - ወይኔ - ወይኔ!!!" ደጅ ላይ ቆማ እናቷን ይዛ ሰፈሩን በጩኸት ደበላለቀችው::

ሦስት በድንጋጤ የተሞሉ እናቶች፣ ለሹከሹከታ የሾለ አፋቸውን እያንሸራመሙ፣ ሁለት ሦስት አባወራዎች ለተግሳፅ የፈጠነ ምላሳቸውን እያነቃነቁ፣ በሩን በርግደው ሲገቡ፣ የደነገጠችዋንና ግራ የተጋባችዋን ሳራን ሳይሆን ወለሉን የሞላውን ነገር ነው- መጀመሪያ ልብ ያሉት::

ው - ሃ - ! ውሃና ደም!

....

## ተራኪው

ከደሴ ወደ ኮምቦልቻ በሚወስደው መንገድ ላይ ሃያ ኪሎ ሜትር ርቃ የምትገኝ ናት - ገታ:: ወደዚህች ገጠር የመጡት የሐጅ ሰይድ ቡሽራ ከብረ በዓል ላይ ለመሳተፍ ነው::

ሐጂ ሰይድ የተቀመጡት እፊት ነው:: ታዳሚዎች እግሮቻቸውን አቆላልፈው ግማሽ ክብ ሠርተዋል:: አንድ በኑሮው የጐሰቆለ መሆኑ የሚያስታውቅ፣ 'ተወልዲያ ነው የመጣሁት' ያለ ሰው ይዞ የገባውን ጫት አቀረበላቸው:: ስጦታ አበርካቹ ጫቱ ላይ እጆቹን አሳርፎ፣ "ጫት ጀባ - ከፍታ ጀባ - ለምለም ጀባ! " ብሎ ሰጣቸው::

መራቂውም፣ "አማን ጀባ - በረካ ጀባ - ከፍታ ጀባ - ብለሃልና ከፍ ያርግህ፤ ለምለም ጀባ እንዳልከ ለምለም ያርግህ፤ የማይበጅህ ይንጫጫ፤ በቀልብህ ያንጐራጐርከው ሀጃህ ይሙላ:: ጌቶቹ መጀን:: ኡምርህን ሳብ አርጐ የልጅ ልጅ ስመህ የምትበላ ያርግህ!" አለ::

ጫት አበርካቹም፣ ጐንበስ ብሎ፤ሁለት እጆቹን ዘርግቶ፣ "አሜን ...አሜን!" አለ:: ምርቃቱ ሲጠናቀቅ፣ የመራቂውን እጅ ስሞ ወደነበረበት ቦታ ተመልሶ ተቀመጠ::

ጫቱን ለዕድምተኛው የሚያድሉት እሳቸው ናቸው:: ዱአው ተጀምሮ አበቃ:: ሁለት ዜማዎች በቅብብል አዜሙ:: ሐጂ፣ "አብሻቂም - በሻቂም - በዳይም ተበዳይም ለአላህ ብላችሁ አውፍ በሉ!" ሲሉ፣ ሁሉም ራሱን ይፈተሽ የተቃቃረውም ይታረቅ ጀመረ::
ጫት እየተቃመ ነው - በዝምታ:: ሁሉም ምዕመን በፀጥታ ውስጥ ስለ ፈጣሪው ማሰላሰል ጀምሯል::

"አብሽር!" ይላል አንዱ፣ በየመሃሉ::

ሐጅ ሰይድ፣በእምነታቸው ፅናት የተነሳ ልዩ ልዩ ፈተናዎችን አልፈው ለድል ስለበቁ አማኞች ሲተርኩ መስማት ደስ ይላል:: እንደበታቸው የጣፈጠ ነው:: አዕምሮአቸው ስለ አላህ መልዕክተኞች፣ ስለቅዱሳን ሰዎች፣ ስለ ከሊፋዎችና ወልዮች ተዐምራት በማሰላሰል የተሞላ ነው:: ቅዱስ ቁርአንን ቀርተዋል፣ ምስጢራቱን መርምረዋል:: መካ መዲናን ተሳልመው ለሐጅነት በቅተዋል::

ታዳሚዎቹ፣ሐጅ ሰይድ ገና እግራቸውን ከማስገባታቸው ዐይናቸው በራ፤ ጆሮአቸው ተከፈተ፤ ልባቸው ተነቃቃ::

እጣኑ መትጐልጐል ጀምሮ፣ በጭሱ አየር ላይ ሥዕሉን ያሳይ ጀምሯል:: የመነቃቃትና ትረካውን የማድመጫ ጊዜ አሁን ነው::

"እንግዲህ የጌቶቻችንን ከራማ አላህ ያስረዳንና..."

"መርሃባ!" አሉ ታዳሚዎች፣ በኅብረት::

"ኢብን ኡመር /አላህ ሥራቸውን ይቀበላቸውና/ እንደተናገሩት፣ ነብዩ መሐመድ /ሰላምና ደህንነት በሳቸው ላይ ይውረድ/ በአንድ ወቅት ለተከታዮቻቸው እንዲህ ብለው ነበር አሉ:: ይኼ የምነግራችሁ ታሪክ በሀዲስ ላይ ተከትቧል:: እኔ ግን መጣፉን አላገኘሁትምና የሰማሁትን ነው የምነግራችሁ:: የነገረኝ ሰው ደግሞ ከሰማው ወይም ካነበበው የቀጠለው የቀጣጠለው ነገር ካለ - ለሸር ታልሆነ በቀር - አላህ አፉ ይበለው:: የሆነው ሆኖ በአንድ ወቅት ሦስት መንገደኞች ረዥም መንገድ ጀመሩ አሉ:: እግራቸው ውሃ እስኪቋጥር፣ ጉሮሮአቸውም በውሃ ጥም እስኪደርቅ በብዙ ተጓዙ:: አመድ የመሰለው ሰማይ፣ ዝናቡን ድንገት ቢለቅባቸው ጊዜና አንገታቸውን የሚያስገቡበት፣ ለጐናቸው መገለበጫ ለዐይናቸው ማረፊያ ቤት አጡ..."

"አጃባ ሆዬ..." ከእድምተኞች መካከል አንዱ ትረካውን የሚያሟሙቁ ቃላት መጠቀም ጀመረ::

"ብዙም ሳይቆዩ አንድ ተራራ ስር የተወተፈች ዋሻ አገኙና አንገታቸውን ሰደዱባት"

"መርሃባ!"

"ታፍታ ቆይታ በኋላ፣ ዝናቡ ሿ እያለ ሲወርድ፣ በመሀሉ መብረቅ ወረደና ድንጋጤ ወደቀባቸው:: እንዲያ ከባድ መኪና ሰማዩ አጉረምርሞ ጆሮአቸውን አደንቁሮ ልባቸውንም በፍርሃት የሚገዛ ነገር ተከሰተ:: አንድ ዲንጋይ መጣና - ዝሆን የሚያክል ዲንጋይ - ዋሻውን ዘጋው"

"ጉድ እኮ ነው አቦ!"

"በዚያች የጨለማ ዋሻ ውስጥ ብዙ ተተቀመጡ በኋላ - ያንን ድንጋይ ቢሉት ቢሰሩት - መቼ እሺ ብሎ? አራቅነው ባሉ ቁጥር ወደ ዋሻው እየገባ መቆሚያ መላወሻ አሳጣቸው:: ቢጣሩ የሚደርስላቸው የለ? ማን ለበይክ ብሎ ይጠጋቸው? ዱኣ ቢያደርጉ፣ አላህን ቢለምኑ አልሆን አላቸው... መላ ይመቱ ገቡ:: ከእውነት በስተቀር ምንም ሊያድነን አይችልም:: ስለዚህ ከልባችን አስበን፣የአላህን ደስታ ለማግኘት ብለን ያሰብነውን ተግባር በመጥቀስ እያንዳንዳችን የአላህን ዕርዳታ መጠየቅ አለብን" ትረካቸውን ገታ ቆም አደረጉ::

"አቤት የጌቶቻችን ያለህ!" አለ፣ አንዱ ታዳሚ::

ተራኪው ቀጠሉ:: "ቆየና፤ አንድ መንገደኛ እስኪ እንዲህ እናድርግ:: የአላህ ፍቅር አድሮብን፣ የነቢያችንን ስም ፈርተን፣ የፈፀምነውን አስታውሰን፣ ተራ በተራ እናውጋ፤ እንዲህም በማድረጋችን አላህ ይምረን ይሆናል! አላቸው::"

"እንዲያ ነው እንጂ መሰጠት!" አለ፣ አሁንም ከታዳሚዎች አንዱ::

"አዎ! አንደኛው ተነሳና ድሮ ያደረገውን ይተርከ ጀመረ:: 'አላህ ሆይ! እኔ ሀብቴ ቁጥር ስፍር ያልነበረው፣ ብዙ እረኞችና ባርያዎች የነበሩኝ ሰው በነበርኩበት ጊዜ፣ አንድ ልግመኛ ነበረኝና ታንተ ጋር ያለኝ ጉዳይ አከትሟል ብዬ አባረርኩት:: ያባረርኩት ለሌሎች ሰነፍ አራሾቼ ማስተማርያ እንዲሆነው ብዬ እንጂ መች ልጨክንበት ሆኖ? ለካስ እሱ በቁጣዬ ደንግጦ ኖሮ የላቡን ዋጋ ሳልከፍለው አብስ ብሎ ታይኔ ስር ጠፉ:: ተብዙ ከረምት በኋላ፣ያልወሰደውን የላቡን ዋጋ ሊቀበለኝ እደጄ ከተፍ አለ:: ሦስት ወር ነበረ፤ አንተጋ የከረምኩት፤ የሦስት ወር ከፍያዬ ሦስት ጊደር ነውና በጄ በለኝ!

አለ:: አላህ ምስከሬ ነው፤ ወደ ከብቶቼ በረት ወሰድኩትና የሚገባውን ብሰጠው ጊዜ፣ እንዴት ይሄ ሁሉ ይደርሰኛል? እርስዎ ዘንድ የከረምኩባቸውን ጊዜያት ዘነጉት ልበል? በኔ ስም ለሚጠራ ለሌላ አሽከር የተሰናዳች እንዳይሆን ነገሩ!' አለኝ:: እኔም፣ 'ግድ የለም ሀቆችህ ናቸው፤ ድርሻህ ነውና ሳታመነታ ውሰዳቸው:: አንተ የሚገባኝ ሁለት ጊደር ነው ትላለህ:: ሁለት ብቻማ እንዴት ሆኖ? ተዛሬ ነገ ትመጣና ድርሻህን ዋጋህን ትወስዳለህ ብዬ ስጠባበቅ ብዙ ዓመት አለፈ:: ጊደሮችህም ተዋለዱ:: ወተታቸው ጊደሮችህን ለጠበቁልኝ አሽከሮችህ ሰጠሁ:: በቃ የሆነው ይኼ ነው:: መግደርደርህን ተውና አራት ጊደሮችህን እየነዳህ ሂድ!" ብዬ ሸኘሁት፤ አላህ ታየኛለህ ብዬ ለሰው ያደረኩት በጐ ነገር ይሄው ነው! አለ የመጀመርያው ሰው!"

"ይኼ የተባረከ ሰው ነው:: አለኮ አንዳንዱ ተሠራተኛው ደሞዝ የሚሰርቅ..." አለ፣ አንዱ አድምተኛ::

"እህና!"

"እንዲህ ያለውን በሰው ላብ የሚቀልድ ደህን የሚያሳዝን አላህ እጁን ይቁመጠው!"

"አሜን!"
"አሁን ወቅት መጀን፣ ከላይ ታቦቱ ከታች ረከቦቱ ቁምጥምጥ ያድርገው!"
"አሜን!"
"እንደ ጉም ያብንነው፤ የወሰደው ገንዘብ የከፈን መግዣ ይሁነው!"
"አሜን!"
"የአፋፍ ላይ አመድ፣ የቁልቁለት ቅምብቻ፣ የውሃ ላይ ኩበት ያድርገው!"
"አሜን!"
"በኖ ተኖ ይለቅ፤ ድውይ ይሁን!"
"አሜን!"
"የጉልበት ደሃ ያድርገው!"
"ዕድሜ ልኩን በጥፊ እንደተረገመ ይኑር!"
"አሜን!"
"የቁም ቅል፣ የተላጠ ግራር ያድርገው!"
"አሜን! አሜን! አሜን! አሜን! አሜን!"

ተራኪው ካቆሙበት ቀጠሉ:: "ያ አሽከር ጊደሮቹን እየነዳ ተመሄዱ በፊት የድሮ አሳዳሪውን አብዝቶ መመረቁን አላህንም ማመስገኑን በነገራቸው ጊዜ፣ ያቺ ጭልማ የዋጣት ጐጆ በትንሹ ተከፍታ እርስ በርስ ታተያያቸው ጀመር:: ከጉልበት ይልቅ የብልሃት ዘዴያቸው በመሥራቱ ተደሰቱ:: እንዲህ እንዲህ እያልን ስለ መልካም ሥራዎቻችን ስናነሳ፣ አሁን ብርሃን እንደመጣ ሁሉ ቀስ በቀስ ከገባንባት ያልታሰበች እስር ቤት ያለ እንግልት ነፃ እንወጣ ይሆናል ተባባሉና ሁለተኛውን ሰው፣ እህሳ አንተስ ምንድነው የምትነግረን በጐ ሥራህ? አሉት"

"ምን ብሏቸው ይሆን?"

"እኔ እንኳን በቅርብ የሆንኩትን ነው የማወራው አለ ሁለተኛው ጐልማሳ:: ርሃብ የሚሉት ከፉ አውሬ፣ የቤተሰቦቼን ሥጋ ቆርሶ ለመጉረስ ባደባበት ጊዜ የፈፀምኩት ታሪክ ነው የማወጋችሁ:: ዳቦ መግዣ ፍለጋ ያልረገጥኩት የዘመድ ወዳጅ ደጅ አልነበረም:: በመጨረሻም ተሳካልኝ:: የገዛሁትን ዳቦ ይዤ ወደቤቴ አመራሁ:: ልጆቼ በሩጫ ተቀበሉኝ:: በደስታ ብዛትም አለቀሱ:: ይህን ሁሉ ደስታ ግን ወላጆቼ አላዩም፤ ተኝተው ነበር:: እንዳልቀሰቅሳቸው ሁለቱም ከእንቅልፍ የሚያነቃቸውን መቸ በጀ ይሉና? ዳቦአቸውን ይዤ እስኪነቁ ጠበቅሁ:: ወላጆቼ እህል ከጉሮሮአቸው ሳይወርድ ልጆቼን አላስቀድምም ብዬ የአብራኮቼ ከፋይ ቢለምኑኝ አልሰማ ብዬ ወላጆቼን አስደሰትኩ ...ብሎ ተረከላቸው"

"እንዴት ቀልብ የሚነካ ነገር ነው አቦ!" አለ፣ አንዱ ታዳሚ!

"አቦ እንዲህ ያለው ሰው ጀባታው ብዙ ይሁን!"
"አሜን!"
"የገዛው ይርባ!"
"አሜን!"
"ያረደው ይሰባ!"
"አሜን!"
"እጁ አይጣ!"
"አሜን!"
"ስር ይስደድ!"

"አሜን!"
"ጫፉ ብቅ ይበል!"
"አሜን!"
"አይበጀው ይጠመድ!"
"አሜን!"
"እንደ ሻኛ ቆለል!"
"አሜን!"
"እንደ ቅቤ ጠለል ይደላደል፤ ይሞናደል፤ ሁሉም የሱ ይሁን!"
"ይሁን!"

ተራኪው ቀጠሉ::

"ይህን ብሎ ሲያበቃ፣ ዋሻውን አፍኖ ዘግቶት የነበረው ድንጋይ በትንሹ ተከፈተ:: የከፍተቱ መጠን ግን እናትን እሾልኮ የማስገባት አቅም ነበረው እንጂ ድንጋዩ ገለል ብለ ሙሉ ለሙሉ ሰውነትን የሚያሾልከ አልነበረውም አላለላቸውም:: ተረኛው ሰው ለጠቀ..."

"መርሃባ!"

"እኔ ብሎ ጀመረ ተረኛው፣ እኔ ሴት አልፋ ተራምዳኝ ባለፈች ቁጥር ይህቺን አሁን የምተርከላችሁን ሴት አስባታለሁ፤ አላህ ምስከሬ ነው የምወዳትን ያህል ነበር የምትጠላኝ:: በድህነቴ ተሳለቀችበት:: ተጓደኞቿ ጋር ሆና ተዘባበተቺብኝ:: ከፉም አልተናገርኳት፤ ተንኮልም አልሰራሁባት:: ሃጃው ለሞላለት፣ አዱኒያ ለበዛለት ሰው እጅዋን ለጋብቻ ሰጠች ባሉኝ ጊዜ እንኳ እንዴት ችዬ ተውስጤ ላውጣት? ሥራ ሆነችብኝ:: የኛ ሀገር ሴትና የጣት ቀለበት፣ ሲያጠብቁት አይወድም ልከ እንደ ዘበት እያልኩ ባስጠናችኝ ዜማ ሳንጐራጉርላት ቆይቼ፣ ቅናቴን ንቄ ለቀቅ ባደርጋት ጊዜ መሰስ ብላ እንደ ዘበት ሄዳብኝ ባለ ቀለበት ሆነች...አላቸው ሦስተኛው ሰው!"

"ያረቢ! ብቻውን ነበራ ሲንገበገብላት የቆየው!" አለ፣ አንድ ታዳሚ::

"ኋላሳ! በህልሜ እየመጣች ሁሉ አተኛት ነበረ! አላቸው:: ቆየና ይህች ተፈቅራ የነበረችዋ ሴት ልትዘይረኝ መጣች:: ያ አማላይ ገላዋ ሟሽሾ፣ አርጅና አብሯት የሚውል መስሎ፣ ቁመናዋም ፍሬ እንደከበደው ማሽላ አጐንብሶ እቤቴ መጣች:: የተዘራ የተዋለደን ተፍሬ የሚያደርስ አንከላፋ ይያዝልንና፣ ለካስ

ባሏ አዘንተኛ አድርጓታልና! አዱንያውን ሁሉ በቁማር ጨርሶት ባዶ እጅ በቀረ ጊዜ ነው - እንድረዳት የመጣቹብኝ:: ቤቷ በዕዳ ተይዞባታል፡ አመጣጧ ልትበደረኝ ነው:: እሷ ደሃ ብላ ባትሰድበኝ መቸ ተድህነት እላቀቅ ነበር? ስንፍናዬን የገደልኩት፤ የሷ ስድብ ጦር  ሆኖ ቢወጋኝ አልነበረም ወይ? የፈለግሽውን ያህል እሰጥሻለሁ፤ ብድር ለምን ተብሎ? ግና የምትፈልጊውን እምሰጥሽ ልቦናሽ ፈቅዶኝ አልጋ ላይ አብረሽኝ ወድቀሽ የተነሳሽ እንደሆነ ነው:: ፀጉርሽን ለመልበስ የብዙ ጊዜ ምኞቴ ነበረ:: ጡቶችሽ ስር ለመደበቅ ያመታት ዱአዬ ነበረ:: አሁን ላድርገውና እምትፈልጊኝ ውሰጅ አልኳት"

"አጀባ ሆዬ!"

"በዚህ ጊዜ፣ መቸም ተመራብ፣ ተመሞት፣ ለአንድ ቀን ቢባልጉ ምናለ አለችና - እንዲያው ቅር እያላትም ቢሆን - ልብሶቿን አወለቀች:: እኔም ቤቴን ቆልፌ፣ ሻማዬን ለኩሼ፣ መለመላዬን ሆኜ፣ ገላዋን ተገላዬ ጋር ላዋድድ ስል ድንገት እመር ብላ ተነሳችና የሀቅ ወልይ ያላህ ባርያ ተሆንክ በድህነት ጉዳይ ገላዬን እንድሸጠው አታስገድደኝ አለችና እመር ብላ ተመኝታዬ ተነሳች:: እኔም የአላህን ስም ጠርታብኝ ልበድላት አልቻኩልኩም:: ልሰጣት የነየትኩትንም እንዴት ብዬ ልከልክላት? አላህንም እሷንም አስደስቼ አጣኋቸው:: አላህ ለእውነት ብዬ የሰራሁት ርዝቅ ይኼ ነው፤ ብሎ ሦስተኛው ሰው በተረከላቸው ጊዜ፣ በከፊል ተከፍቶ የነበረው ዋሻ ሙሉ ለሙሉ ተበርግዶ ተጉድጓድ እስር ቤት ነፃ ወጡ..." አሉና ተራኪው ትረካቸውን ደመደሙ::

መራቂውም፣ "የመከራ ዳርቻ ይሁን!" ብሎ ቀጠለ::
"አሜን!"
"የሲሳይ ቤት፣ ሰደቃው የሰመረለት ይሁን"

"አሜን!"
"አገራችንን አማን አርገው፤ ተተዛመድነው ተተዋለድነው ጋር አፊያ አርገው!"
"አሜን"
"አስብቶ አራጅን ለሳንጃው፣ አዛ ሸረኛን ለአሽከላው እርጎ አላህ ይያዝልን!"
"አሜን!"
"አገር አማን፤ ገበያ ጥጋብ ይሁን!"
"አሜን!"
"ተሚወራው ተሚፈራው በልአ ጠብቆ አላህ ያገናኘን!"

"አሜን!"
"አላሁ ሙሰሌ!"
"ወሰላ መሃላ ሰይድና ሙሐመድ ወላአላ ሰይድና መላውና ሙሐመድ!"

.....

# ብርሃን ፍለጋ

ወይንሸት የመጀመርያ ልጅ ነች:: ዕድሜዋ አስር ሆኗል:: እኩዮቿ ከከፍል ወደ ከፍል በተዘዋወሩ ቁጥር እሷ ግን ታናናሾቿን በመሸከም ነው፣ ከዓመት ወደ ዓመት የምትሸጋገረው::

ወላጆቿ ሞግዚት የመቅጠር አቅም የላቸውም፤ ለዚህም ነው ወይንሸትን ወደ ፊደል ገበታ ያልሰደዷት:: አባቷ 'ስርቆ በይ!' የሚል ድምጽ ወደሰማበት የሚሮጥ፣ ቤተሰቡን ፆም ላለማሳደር የሚተጋ አባወራ ነው:: እናቷ የምትሸጠውን እንጀራ በመጋገር የምታሳልፍ፣ ነፍሰጡር አለመሆን የሚከፋው ሆዷን እየገፋች፣ ለአራት ልጆቿ ሆድ ስትኳትን የምታድር ናት!

እና፣ ወይንሸት ቀርቶባት ተማሪ ቤት የተላከው ታናሿ ነው:: በዓመቱ የታናሸዋ ታናሽ! ዘንድሮም፣ 'እሹሩሩ ማሙሽ ውረድ ከጀርባዬ' ነው ቅኝቷ::

ዛሬ ደግሞ ከጥዋት ጀምሮ ከፍቷታል:: እናቷ ምጥ ይዟት ወደ ከፍተኛ ክሊኒክ ከወሰዷት በኋላ መረጋጋት ርቋታል:: 'ስድስተኛ ወር አልፎኛል' ስትል እንጂ 'ዘጠነኛ ወሬን ሞልቻለሁ!' ስትል አልሰማቻትም ነበር፣እናቷን::

እናቷ ፈርታለች! 'እንጃልኝ ዘንድሮ' ባይ ሆናለች፣ የሐኪም ቤት ደጅ ረግጣ በተመለሰች ቁጥር:: ድንገት አንድ ሐሳብ መጣላትና ፈገግ አለች...ፈገግ...

የጥዋት ፈረቃ ተማሪዎች ከትምህርት ቤት የሚመለሱበት ሰዓት ነው::

ወይንሸት፣ "የማደርገውን ኣውቃለሁ!" በሚል ስሜት ውስጥ ሆና፣ የምታዝላትን ሕጻን 'እሹሩሩ' ብላ አስተኝታ፣ ‹ሽንት ቤት ሄጄ ልምጣ› የሚል ምክንያት ፈጥራ...

ወደ ማርያም ቤተክርስቲያን ሄደች:: ከነፈች:: ተሳልማ ገባች:: ከዚህ በፊት ጸልያ አታውቅም:: እንዴት ነበር የሚጸለየው? እንዴት ነበር? እንዴት እንደሚጸለይ ትዝ አልልሽ አላት::

ተንበረከከች:: ተንበርክካ ስለደረሰባት በደል ታሰላስል ያዘች:: ጓደኞቿ ዛሬ ባለ ብዙ እውቀት ሆነዋል:: የሚያማምሩ ሥዕሎች የበዙባቸው መጻሕፍት አሏቸው:: ሊገቧት ባልቻሉ ርዕሰ ጉዳዮች ዙርያ እንኪያ ስላንቲያ ይገጥማሉ:: ይጽፋሉ፤ ያነብባሉ::

አራተኛ ክፍል ደርሰዋል:: አራተኛ! እያንዳንዱ ቀን ለነሱ ንጋት ነው:: አዳዲስ ተረት... አዳዲስ ሃሳብ...አዳዲስ ሰው!

ተረስታለች ወይንሸት:: በ'ሀ'ና በ'በ'፣ በ'ሠ'ና በ'ጠ' ፊደል መሃከል ስላለው ልዩነት የማወቅ ዕድል ተነፍጓታል:: ጨዋታ ጎድሏታል:: ሳታድግ አሳዳጊ ሆናለች::

በህጻን ልቧ ውስጥ ፊደል አልተዘራም፤ ቁጥር አልበቀለም፤ ቀለም አልፀደቀም:: እንደጓደኞቿ አያበበች አይደለም:: አረም ተብላ ከእኩዮቿ ተነጥላ፣ ተነቅላ እንዳትጣል ነው ስጋቷ!

ዕንባ ዕንባ ሲላት ቆየና፣ "ማርያም!" አለች በሹክሹክታ፣ "ዛሬ እናቴን ሐኪም ቤት ወስደዋታል፤ ልትወልድ ነው ብለው እናቶች ወስደዋታል!" አለች፣ ወይንሸት፣ ግራ ቀኝዋን ገልመጥ አድርጋ:: "ማርያም በናትሽ እናቴ እንዳትወልድ አድርጊ! እናቴ ከወለደች ከረምቱ ሲያልቅ ትምህርት ቤት ላያስመዘግቡኝ እኮ ነው:: በናትሽ! እናቴን አታስወልጂያት! ምንም ሳልማር ትልቅ ሰው ልሆን እኮ ነው፤ አላሳዝንሽም?"

ዕንባዋ...
"ሠራተኛ እስኪቀጠርልን ድረስ አታስወልጂያት:: ማርያምዬ....ጓደኞቼ አራተኛ ክፍል ናቸው:: እኔ ግን ዜሮ ክፍል የሚያስገባኝ አጣሁ፤ አላሳዝንሽም? በናትሽ....እ?"

ጸሎቷን ጨርሳ፣ ቤተክርስቲያኗን ተሳልማ ወደ ቤቷ ተመለሰች:: የምታዝለው ሕጻንም ከእንቅልፉ አልነቃም ነበር:: ጡጦ እንደጐረሰ አገኘችው::

ሳሎን ውስጥ ያገኘቻቸው ሰዎች ግን ቀደም ሲል የነበሩ ጎረቤትና ዘመዶች ብቻ አይደሉም:: እናቷም ከሐኪም ቤት መጥተዋል:: ፀጥ፤ ረጭ ብሏል - ቤቱ! ዕንባ ዘንቦበት፣ ልቅሶ ተሰምቶበት የቆዘመ ጎጆ!

ቀዝቅዟል:: ፊታቸው ደምኗል:: በተለይ እናቷ! እናም ደነገጠች:: ወዲያው አንድ የጎረቤት እናት፣ "ነይ! ነይ ሚጡ! አይዞሽ እሺ? ዋናው እናትሽ በሰላም መትረፏ ነው!" አሏት፣ በሚያፅናና ዜማ፣ ድምጻቸውን ቀንሰው::

አልገባትም:: ከዚህ በፊት፣ 'ወንድም ቢወለድልሽ ይሻላል ወይስ እህት ቢወለድልሽ?' እያሉ ያስጨንቋት የነበሩ አሮጊት ናቸው::

አሁን ግን፣ "እናትሽ መትረፏ ነው ዋናው ነገር! ጊዜው ሳይደርስ ነበር ምጡ ያጣደፋት!" አሉ፣ ዕንባ ባጀበው ሻከራ ድምጽ፣ "ሕጻኑ ያረፈው ለዚያ ነው!" አሏት::

የወይንሸት ፊት ላይ ሀዘን አልነበረም፤ ልቅሶ አልነበረም፤ ድንጋጤም፤ መታወከም አልነበረውም....

ፈገግ ብላለች:: የትምህርቷ ነገር....

"ምን እያሰብሽ ነው ልጄ?" ብለው ጠየቋት፣ አሮጊቷ::

"ቤተክርስቲያን ነበርኩ"

"ምን ልትሠሪ ሄደሽ?" ቀጠሉ፣ ጥያቄያቸውን::

"ልጸልይ!"

"የምን ጸሎት?"

"እናቴን እንዳታሳምምሚብኝ ብዬ ለማርያም ነግሬያት ቶሎ መጣሁ" አለች ወይንሸት::

"ሰምታሻለች!" አሉ፣ አሮጊቷ ደስ ብሏቸው፣ "ማርያም! የነገሯትን የማትረሳ፣ የለመኗትን የማትነሳ!"

ወይንሸት፣ ጎረቤት ወዳሉት እኩዮቿ ሄዳ በጥያቄ ታጣድፋቸው ጀመር::

-የአንደኛ ክፍል ምዝገባ መቼ ነው? ተጽፎበት ያላለቀ ደብተር ሲኖራችሁ አትሰጡኝም? እስኪቢርቶ ካቆራረጣባችሁ አትጣሉት፤ እኔ አስጽፌ አጠቀምበታለሁ:: በናታችሁ! እሺ?

የማትለው ነገር አልነበራትም:: እጅግ ብዙ ነገር..

"አንቺ የምትማሪ ከሆነ እናትሽ ብትወልድስ? ብቻዋን አትሆንም? ልጅ ማን ይይዝላታል?" ይሏታል፣ ጓደኞቿ::

"ዘንድሮ አትወልድም" ይሆናል መልሷ::

"ለምን ወይንሸት?" ሲሏት ደግሞ....

"ለማርያም እናቴን አታስወልጂያት ብዬ ነግሬያት የለ!" ትላቸውና፣ ስንጥር ቢጤ ፈላልጋ ትቀመጣለች:: ቀሚሷን በትንሹ ገለብ አድርጋ እግሮቿ ላይ ትጽፋለች:: ስም ያልወጣላቸው 'ፊደሎች'...የተንሻፈፉ መስመሮች...የተወለጋገዱ ክቦች!

ፊቷን ማየት ነው በዚህ ጊዜ:: በብርሃን የተሞላ ፊቷን፤ ፊደልና ቁጥር መለየት የናፈቀው ዐይኗን...

....

# አዲስ ስም

'ፍጠን ባለታከሲው! ፍጠን!' በልቡ ሾፌሩን ያዝዘው ጀምሯል:: ጥድፍ ብሏል:: የተሳፈረበት ሚኒባስ እሚፈልግበት ቦታ እስኪያደርሰው ጨንቆታል:: የታከሲው ረዳት አንገቱን ከመስኮት አሾልኮ፣ "ፍሬንድ የት ነሽ?" ብሎ ጠይቆ፣ ሾፌሩም ፍሬን አስይዞ፣ አዲስ ተሳፋሪ ባስገባ ቁጥር ይነጫነጫል::

አምን ተጣድፏል:: ዛሬ፣ ዐይኑ የንስር እንደሆነ የሚያስመሰክርበት ቀን ነው:: አሁን ዐይን ብቻ አይደለም፣ ክንፍም ይፈልጋል:: ወደ አለቃው ቢሮ የሚያደርሰው ክንፍ:: 'ገንዘብ ሊገዛው የሚችል ዜና በጄ እንዳለ ከዚህ ሁሉ ሕዝብ መሀል ማን ያውቃል? ማንም!' አለ፣አሁንም እየተጣደፈ፣ ዙርያ ገባውን ቃኘ::

ከጥቂት ደቂቃ በፊት የሰማውን የዓመቱን 'አቧራ የሚያስነሳ' ዜና እስኪነግረው ጭንቅ ይዞታል - 'ወሬ ኮማሪው' ስምዖን::

'ፍጠን! ፍጠን ባለታከሲው! ፍጠን!'

'ምናብ' በተሰኘች ሳምንታዊ ጋዜጣ ላይ በሪፖርተርነት ለመቀጠር የሙከራ ሥራዎቹን ማቅረብ ከጀመረ ሰነባብቷል:: *'ፍሪ ላንሰር'* ነው:: 'ፖለቲካን በሩቁ' በምትል የጥበብና የመዝናኛ ጋዜጣ ላይ...

ግና አንድም ቀን ዋና አዘጋጁን አስደስቶት አያውቅም::

'ዛሬ ግን ትልቅ ዜና በእጄ ገብቷል' አለ ስምዖን:: 'ከዚህ ቀደም በማንም ያልተዘገበ ምርጥ ያገራችን ዜና በእጄ ገብቷል!'

የፊልሞን ገዳይ ተገኘ! ፊልሞን የአህጉራችን ምርጥ የስነሰብዕ ምሁር ያነበበውንና የተማረውን በተግባር ለመተርጎም በመቻሉ በበርካታ ተቋማት ለመሸለም የበቃ...

የፊልሞን ገዳይ ተገኘ! ፊልሞንን የገደለው ወይም ያስገደለው የቀድሞው የሀገሪቱ መንግሥት እንዳልሆነ የሚቹ የቅርብ ጓደኛ የሆነው አንትሮፖሎጂስቱ አርዮን አስታወቀ!

'ፍጠን - ባለታክሲው ፍጠን - ፍጠን!'

ቀይ መብራት ታክሲው ላይ አፈጠጠበት::

ታክሲው ቆመ::

ምጥ እንዳስጨነቃት ሴት መረበሹን ያስተዋሉ አንድ አረጋዊ፣ "ረጋ በል እንጂ ጉበዝ! መሆን የሚገባው ሁሉ መሆኑ ላይቀር ይሄ ሁሉ መዋከብ ምን አመጣው?" አሉት::

"ጋዜጠኛ ነኝ!" አላቸው:: ለማለት የፈለገው ይህን አልነበረም:: ግን አላቸው:: ካላቸው በኋላ ነው፣ በጋዜጠኝነቱ ኩራት ይሰማው እንደጀመረ የገባው::

ፊልሞን! ፊልሞን! ፊልሞን!

- እኔ ጋዜጠኛ ነኝ፤ ወሬ እሸጣለሁ፤ ወሬ እገዛለሁ፤ ነገር እኮምራለሁ:: ፈላጊዎቼን በነገር አሰክራለሁ:: የማይከስር፣ ግብር የማይከፈልበት፣ ኪራይ የማይጠየቅበት፣ የወሬ ሱቅ አዕምሮዬ ውስጥ አለ:: በየትኛውም ሰዓት ሱቄ ክፍት ነው...

ነገ የጋዜጣው መውጫ ዕለት ነው:: ጋዜጣቸው ላይ ሊወጡ የሚገባቸው አበይት ዜናዎች አስራ ምናምን ይደርሱ ይሆናል:: የጋዜጣው ዋና አዘጋጅ ግን ለፊልሞን ባለው - ለአምልኮት በቀረበ ፍቅር የተነሳ - ጋዜጣው ላይ የፊልሞንን ምስል አጉልቶ በትልቁ ደግሞ፣ "የፊልሞን ገዳይ ተገኝቷል!" የሚል ዜና አስከትሎ ያትመው ይሆናል:: አንባብያንም ከነገ ጥዋት ጀምሮ እስከ አልተወሰነ የጊዜ ገደብ ምናልባትም እስከ ዕለተ ሞታቸው አጀብ ነው የሚሉበት ዜና ይሆን ይሆናል::

ከታከሲው ወረደ::

በመዋከብ ላይ ከነበሩት የሥራ ባልደረቦቹ መሃል አንዱ፣"ምን ሆነሃል?" አለው፣ ካቀረቀረበት በመጠኑ ቀና ብሎ::

"ምን ሆንኩ?"

"ከጥይት አምልጦ የመጣ ሰው መስለሃል:: አንድ ያልበሰለ ዜና ስታገኝ ነው እንዲህ የሚያደርግህ መቼም!" አለው፣ ቀዝቀዝ ብሎ:: ስምዖን ወደ ዋና አዘጋጁ ቢሮ አዘገመ:: ዋና አዘጋጁን አግኝቶ የሆነውን ሁሉ ነገረው:: የሰማውን ሁሉ...

ስምዖን በተስፋዬ ስሜት ተገርሟል:: ደንግጧል ልበል ወይስ የደነገጠ መስሎኛል እንጂ ስሜቱ ሌላ ነው? ብሎ ራሱን ጠየቀ::

"ማነው የነገረህ?" አለው፣ ከምቹ መቀመጫው እየተነሳ፣ የቢሮውንም በር በፍጥነት እየዘጋ:: አንገቱን ከመስኮት አሾልኮ አውጥቶ ዘወርወር ብሎ ዙርያ ገባውን እየቃኘ:: እንደ ሽረሪት ጥጉን ይዞ፣ ግድግዳ ተለጥፎ፣ የሁለቱን 'ዝግ ችሎት' የሚከታተል አልነበረም:: መስኮቱን ዘጋው::ጨለማውን ለበሰው:: ከፍሉ ውስጥ ነግሦ የነበረው ብርሃን አሁን ተባርሯል::

- ምን እየሠራ ነው? ምን እየሠራ?

ቋ! ሲል ሰማ::

መብራቱ ነው::

ተያዩ:: ዋና አዘጋጁ፣ የሪፖርተሩን እጅ ይዞ፣ "ማነው የነገረህ?" አለው በሹክሹክታ፤ "ማነው ፊልሞን የሞተው - በመንግሥት እጅ ሳይሆን በሚቀርበው ወዳጁ እጅ - ያውም በሴት ሰበብ ነው ብሎ የነገረህ?"

ፊልሞን፣ ከአስራ ሁለት ዓመት በፊት ነው የተገደለው:: አድናቂዎቹና ቤተሰቦቹ፣ 'ሞተ ብለን አናዝንም' አሉ:: 'የእሱ የህይወት መርሆዎች፣ የልምድ ተሞክሮዎች በልቦቻችን ውስጥ ቀርፀናቸው እንኖራለን!' አሉ:: በስሙ አንድ ከፍተኛ የትምህርት ተቋም ተገንብቷል:: በየዓመቱ ሃታቲያን በምርምር ሥራዎቹ ላይ በላ ልበልሃ ይባባላሉ:: እሰጥ አገባ ይገጥማሉ::

'አፍቃሪው ነኝ' የሚል - 'ተማሪው ነበርኩ' የሚል - ከአሜሪካ የመጣ አንድ ሰው በፌልሞን ስም ቤተመጻሕፍት ከፍቷል:: በፌልሞን ፎቶዎች - በፌልሞን ጥናታዊ ሥራዎች የታጨቀ - በፌልሞን ሥራዎች ዙሪያ በተሰጡ ሂሶች የተሞላ:: 'በኢትዮጵያ ውስጥ በአያያዙም በአሰራሩም የተለየ መሆኑን ልብ ይሏል?' ተብሎ ማስታወቂያ የተነገረለት::

በፌልሞን ስም ምን ያልተሰየመ ነገር አለ? የአጋጣሚ ነገር ሆኖ፣ ዋና አዘጋጁ በለበሰው 'ቲሸርት' ላይ የፌልሞን ፊት በትልቁ ተስሎበታል:: ከምስሉ ስር፣'ባሳየኸን የእውነት መንገድ እኛም እንሄድበታለን!' ተብሎ ተጽፏል::

የፌልሞን ዐይኖች የቼ ጉቬራን ይመስላሉ:: እንደ ማህተማ ጋንዲ ፊቱ ላይ በመንፈሳዊነት የተሞላ ፀጥታ ይታይበታል:: እንደ ማዘር ቴሬዛ በእግዜር እጅ ያለ እርሳስ ይመስላል::

ፌልሞን እንደዘበት ወጥቶ የቀረው....

ባለቤቱ ነገሮች እንዴት በአጭር ጊዜ እንዴት እንደተቀየረ ትዝ ይላታል:: ቤት መዋል አዘወተረ::

አየችው፤ አይሄድም:: አየችው፤ ወደ ሥራው አይመለስም:: አየችው፤ ሥራውን በተመለከተ የቀድሞውን ያህል ስሜት ሰጥቶት አያወራትም::

'ምንነው?' አለችው::

ላለመናገር ሲያመነታ ቆየና፣ 'መንግሥት ጠረጠረኝ' አላት:: 'አቋሜ ለመንግሥት አስጊ ሆነ ታየ' አላት:: 'መንግሥት እንዳልተመቸሁት በግልፅ ቋንቋው አሳወቀኝ' አላት:: እንዲህ ሲላት ደነገጠች:: በዘመኑ ቋንቋ መንግሥት ጠረጠረኝ ማለት በህይወት እንድቆይ አይፈቅድም ማለት ነው:: 'ጠረጠረኝ' ማለት የሚወዱህንና የምትወዳቸውን ሰዎች ከምድረ ገፅ እናጠፋለን ማለት ነው:: በቃ! ይኸው ነው:: ከዚህ የተሻለ አማርኛ የለውም::

'አይዞሽ!' አላት፤ 'ለጊዜው ነው!'

ዝም አለች፤ ዝምታዋ የሚያስደነግጥ እንጂ መረጋጋት በልቡ እንዲሰፍን የሚያደርግ አልነበረም:: ዐይኑ ላይ ዐይኗን ተክላ ለብዙ ደቂቃ ቆየች::

'ሂድ!' አለችው፣ 'ሂድ! ከሀገር ጥፋ...ፊልሞንዬ...ጥፋ!'

ተንሰቅስቃ ስታለቅስ የበኩር ልጇ መጣች:: ታናሿ ተከተለች:: የታናሿ ታናሽም...

'አባዬ ምን ሆናችኋል? ምን ሆናችኋል?'

'መንግሥት አባትሽን ሊገድለው ነው...'

ቤቱ ሃዘን ገባበት:: ዋይታም ሞላው::

በአስገራሚ ሁኔታ የዘመድ ወዳጅ እግር ቀስ በቀስ ከደጃቸው ራቀ:: ሴት ልጆቹ በየሚሄዱበት ከኋላቸው የሚንሾካሾክ ድምጽ ይሸኛቸዋል::

የፊልሞን ድምጽ ከሬዲዮ ተወገደ:: ፊቱ ከቲቪ መስኮት ራቀ:: ስሙ ከጋዜጦች አምድ ጠፋ::

አድናቂዎቹ ደግሞ ስለሱ ማወቅ አጓጓቸው:: ደህንነቱ አሳሰባቸው::

ወሬው ከንፍ አበቀለ:: መንግሥት 'ስለዘለፍከኝ የጅህን ታገኛለህ!' አለው ተባለ:: 'ተዘባብተህብናል፤ በሕዝብ ዘንድ ተቀባይነት እንዳናገኝም ሴራ ስትሸርብብን ቆይተሃል› ብሎ ጥርሱን ያፏጭበት ነበር ተባለ::

ተባለ - ተባለ - ተባለ - ብዙ ብዙ ተባለ::

አምባገነን ነበር ተብሎ የሚነገርለት መንግሥት ወድቆ፣ ሀገሪቱ በሌላ ፓርቲ መተዳደር ስትጀምር፣ ሕዝቡ፣ 'ሌላ ሌላው ይቅርብን:: የበጐ አድራጐት አባታችንን፣ የፍቅር አድባራችንን፣ የመብታችንን ተሟጋች ደም ደመ ከልብ ሆኖ አይቀርምና ገዳዩን ግደሉልን!' ማለት ጀመረ:: ተማጸነ::

ከዛሬ ነገ - የመንግሥትን መቀየር ሰምቶ - አድብቶ ከተሰወረበት ይመጣ ይሆናል የሚሉ ናፋቂ ልቦች በረከቱ:: ሕዝቡ ሰላማዊ ሰልፍ ወጣ::

'አምባገነኑ መንግሥት እንደገደለው እናውቃለን:: ለምን እንደገደለው ማወቅም ለቀባሪው ማርዳት ነው:: የተቀበረበት ቦታ ግን ይነገረን:: እልፍ አዕላፍ የሆንን እኛ አድናቂዎቹ የአበባ ጉንጉን እናኖርለታለን!' አለ::

ፊልሞን ለእውነት ብሎ ህይወቱን የከፈለ ታላቅ ሰው ነውና ሐውልት ይቁምለት ሲባል አስተባባሪ ሆኖ የሠራው አሪዮን ነበር:: ሐውልቱ ደግሞ ግሩም ተደርጎ ተሠራ:: ፊልሞን በተመስጦ ሲያነብ የሚስተዋልበትን ምስል ይዟል ሐውልቱ::

የምረቃው ቀን ታላላቅ የሚባሉ ሰዎች ተጋበዙ::

ሐውልቱ ላይ እንዲህ የሚል ጽሑፍ ነበረበት - በወርቅ ቅብ የተጻፈ::

*ብዙዎቻችን የዚህ ሀገር ምሁራን እንደ በልግ ካፊያ ነን:: አንተ ግን ብቻህን የሐምሌ ወጀብ ሆንክና ለውጥ የተጠማ ልባችንን አራስከው!'*

ይልና ከስር-

*ኢድናቂህና የልብ ወዳጅህ አርዮን::*

ሆኖም አንድ ችግር ተፈጠረ::

የፊልሞን ልጆች ዘራፍ አሉ:: ወደ አርዮን ተጠግተው ስምህን አስሰርዝ አሉት:: የታወቀ ነው፤ አርዮንን አይወዱትም:: በጭራሽ አይወዱትም:: የአባታችን የሥራ ባልደረባ ነው እንጂ፣ የልብ ወዳጁ አይደለም ይላሉ:: ወዳጁ ተብሎ ሊጠራ እንደ ገና ቅዱስ ሆኖ መወለድ ይኖርበታል ይላሉ::

አርዮን ደግሞ ሐውልቱ ላይ ባስጻፈው ጽሑፍ ጭብጨባ ነበር የጠበቀው:: ከዚህ ቀደም አግኝቶት ከነበረው ክብርና ሙገሳ የሚልቅ ጭብጨባ!

ግና የፊልሞን የበኩር ልጅ አርዮንን ኩም አደረገችው:: በባለስልጣናት ፊት በባለሀብቶች ፊት - ኩም!

'ስማ! አንተ እኮ በዚህ በጥቂት ዓመታት ውስጥ ብቻ መንግሥት በተገለበጠ በተገለባበጠ ቁጥር፣ለመጣው ሁሉ ስታሸረግድና ስታሸበሽብ ነው የኖርከው! የሱ ምስል ባረፈበት ቦታ እንኳን ያንተ ስም ሊጻፍ ያንተን ስም ደፍሮ የሚጠራ የተረገመ ይሁን!' አለች::

ጥቂቶቹ ተሳላቂ ሣቁ:: ጥቂቶቹ በሰሙት ነገር ተደስተው አጨበጨቡ:: ጥቂቶቹ ልጅቱን ተቆጡ::

ኦርዮን ግን ሙትት ባለ ድምጽ፣ 'እሳት አመድ ወለደ:: አሁን አንቺ የአባትሽ ልጅ ነሽ? አሁን አንቺ ከፊልሞን አብራክ ተከፍለሻል?' ሲላት፣ ጫማዋን አውልቃ አፍንጫው ላይ ልትወረውርበት ስትል፣ በቅርብ ቀን የተወዳጀችው፣ 'ኢትዮጵያ ውስጥ ከሼሁ ቀጥሎ ሀብታም አባቴ ነው' የሚላት ጓደኛዋ፣ ጫማዋን ከእጇ ነጥቆ፣ 'አህያ ረገጠኝ ተብሎ መልሰው ይረግጡታል?' አለና አቀዘቀዛት::

ከብረ በዐሉ እንዳልሆነ ሆኖ አለፈ:: *አምባሳደሮች - ዲፕሎማቶች -* የፊልሞንን ምስል ያረፈበትን *ቲሸርት ተጫርተው* ገዙ:: ተሻምተው ለበሱ:: ለወዳጆቻቸውም አበረከቱ::

የተደበቁ ወንጀሎችን በማጋለጥ፣ስውር ደባዎችን ለእይታ በማብቃት የሚታወቅ አንድ የቲቪ ጋዜጠኛ በፊልሞን ዙርያ ለየት ያለ ፕሮግራም አቀረበ:: የዕለቱ ዕለት የክብር እንግዳዎች ሁለት ብቻ ነበሩ:: የፊልሞን የበኩር ልጅ የሆነችው ሶስና እና የረዥም ጊዜ ወዳጁ ነኝ የሚለው ኦርዮን::

ጋዜጠኛው ከጉዳዩ ጋር የሚያያዙለት አንዳንድ መረጃዎችን ከሶስና ተቀብሎ ሲያበቃ ወደ ኦርዮን ተመለሰ::

***ጠያቂ፦*** *የፊልሞን ልጅ፣ ወይዘሪት ሶስና 'አቶ ኦርዮን የፊልሞን ጓደኛ ነኝ በማለት የማያውቁትን ነገር በማስተጋባት እራሳቸውን ከፍ ከፍ እያደረጉ ነው' ትላለች:: እርሶ ምን ይላሉ?*

***መላሽ፦*** *ምንም!*

***ጠያቂ፦*** *እንዴት ምንም? እስኪ ለፕሮግራማችን ተከታታዮች ግልፅ ቢያደርጉላቸው...*

***መላሽ፦*** *እኔ የምትጮህብኝን ውሻ ፀጥ ለማሰኘት ብዬ ጊዜዬን የማባክን ሰው አይደለሁም:: ኢድናቂዎቼም አከባሪዎቼም ጠንቅቀው ያውቁኛል::*

***ጠያቂ፦*** *ከቡር አንትሮፖሎጂስት ኦርዮን፣ የፊልሞን ልጆች ለእርሶ የሚያሳዩትን ስሜት መሠረት የለሽ ጥላቻ ነው ብለው ነው የሚያምኑት?*

ቲቪው ላይ የሶስና ገጽ ብቅ አለና፣ 'በጭራሽ ጓደኛ አይደሉም:: አንድም ቀን ቤት መጥቶ አያውቅም::' ትላለች ሶስና፣ ዕንባዋ እየተዝረበረበ::

የአርዮን ስም ለብዙ ወራት በየመገናኛ ብዙኃኑ ተብጠለጠለ:: ብቸኛ ሆነ:: ወደ ባህር ማዶም ኮበለለ:: ይኼ አገር የሚያውቀው እውነት ነው::

ስምዖን ግን ዛሬ አዲስ እውነት አግኝቷል:: ያቺን እውነት ከሚያውቁ ጥቂት ሰዎች መሃል አንዱ እሱ ነው:: አሁን አንድ ሰው ተጨመረ:: 'የምናብ' ጋዜጣ ዋና አዘጋጅ...

ዋና አዘጋጁ ተስፋዬ፣ "ስምዖኔ!" ብሎ ጠራው፣ አቆላምጦ:: ከዚህ ቀደም አቆላምጦ ጠርቶት አያውቅም ነበር:: ከስምዖን አዲስ መረጃ ካገኘ በኋላ ሁለንተናው ተለውጧል:: ደንግጧል:: የፊልሞንን ስም እየጠራ ተንሰቅስቆ አልቅሷል::

"ይህንን ነገር አንተ እንዴት ልታውቅ ቻልክ? እንዴት ደረስክበት?" አለ፣ ድምጹን ቀንሶ:: "ይህን ምስጢር ማን ነገረህ?"

"አላመንከኝም? የፈጠርኩት ወሬ መስሎሃል አይደል?" አለ፣ ስምዖን በቅሬታ:: ከዋና አዘጋጁ የጠበቀው ይህን አልነበረም፤ ይህን አልነበረም፤ በአድናቆት እንዲጨብጠው ነበር የፈለገው::

"አምኜሃለሁ ግን..."

"ይኸውልህ...እንደአጋጣሚ የፊልሞን ቤተሰብ የንስሀ አባት ወላጅ አባቴ ነው:: በዚህ የተነሳ ብዙ ምስጢር አውቃለሁ:: አርዮን፣ ‹ከእንግዲህ ያለኝ ዕድሜ የንስሀ መግቢያ ጊዜ ብቻ ነው› ብሎ የሆነውን ሁሉ ለሰናይት ተናዝዟል:: ‹በህይወቴ ሲቆጨኝ የሚቆይ ስህተት ሳልናዘዝ ባልሞት ደስ ይለኛል› ለሰናይት ኢ-ሜይል አድርጎላታል!"

በርግጥም አርዮን በእግዜር እጅ ተይዟል:: ያለህ ዕድሜ አጭር ነው ብለው የህክምና ባለሙያዎች አስረድተውታል:: በዚህ ጊዜ ነው፣ ለፊልሞን ባለቤት ስለአርዮን ምስጢሩን ዘክዝኮ ጻፈላት::

የሰላምታውን አንቀፅ ዘለለችው::

'እንዳትደነግጪ!' የሚለው ቃል የአራት ነጥብን ያህል በየዐረፍተ ነገሩ መጨረሻ ላይ ማግኘቷ የበለጠ ረብሿት ነበር::

-ልቤ ሆይ ፅናልኝ:: ልቤ ፅና! ልቤ ፅና! እያለች ማንበቧን ቀጠለች::

*'አደራሽን! ላለመደንገጥ ራስሽን አዘጋጅተሽ ይህን መልዕክቴን አንብቢ:: ይኸውልሽ! ፊልሞን ካንቺ ውጪ የሚያውቃት ሴት ነበረች - ወንድ ልጅ የወለደችለት:: ባለቤትሽ የወለደው ደግሞ ከእኔ ሚስት ነው:: እንዳረገዘችለት ያውቅ ነበር እንጂ፣ የተፀነሰው ወንድ እንዲሆን ስለት ያበዛ ነበር እንጂ፣ የአብራኩን ክፋይ የመሳም ዕድል አልገጠመውም:: 'ባለቤትሽ ሚስቴን ከእኔ ነጥቆ የማግባት ፍላጐት ነበረው:: እኔን ለመወንጀል ባልተሳተፍኩበት የመንግሥት ተፃራሪ ቡድን ውስጥ እንዳለሁበት አያስወራ ስሜን በከለው:: በሀሰት ሊከስሰኝ ሲያደባም ደረስኩበት:: እናም ሚስቴን ለማግባት ፈልጓልና በጭራሽ አይተኛልኝም! ብዬ ቀደምኩት:: ሚስቴን እንዳስረገዛት ያወቅሁት በራሱ አንደበት ነው፣ ሰከሮ:: ‹እኔና አንተ ስልጡን ስለሆንን በሴት የተነሳ አንገዳደልም:: ሚስትህ የምትወልደው ሴት ከሆነ ሁለቱንም አልፈልጋቸውም:: ወንድ ከሆነ ግን ልጀንም የልጀን እናትም የግሌ የራሴ አድርጌ አንተን በክብር አሰናብትሀለሁ!› ብሎኝ ያውቃል ...ይህ ዛሬ የጻፍኩልሽ ምስጢር ያለኔ በቀር- ምንም - ማ - ን - ም አያውቅም::*

*እስከዛሬ ድረስ ለሱ አንዳንድ ተግባራት አከናውን የነበረው ሀጥያቴን ለመሸፈን ብዬ እንዳይመስልሽ እወደው ስለነበረም ጭምር ነው:: እመኚኝ፤ የፊልሞን ገዳይ እኔ ነኝ:: የወደቀው መንግሥት አይደለም:: እኔ ነኝ፤ እመኚኝ:: የፈተኛውን መንግሥት አለሀጥያቱ ስትኮንኑ ቆይታችኋል:: ግን ልክ አይደለም:: እኔ ነኝ ገዳዩ:: ግን ለሴት ብዬ አይደለም የማከብረውን ጓደኛዬን ያጣሁት:: ካላጠፋሁት ያጠፋኛል ብዬ እንጂ:: ሚስቴንና የልጁን እናት ለብቻው የራሱ ለማድረግ ብሎ ያጠፋኛል ብዬ:: ሬሳው ያልተገኘው፣ በገዛ ቤቴ ሽንት ቤት ውስጥ ስለጨመርኩት ነው:: ይገባኛል፤ ሰምተሽው የማታውቂውን ነገር ስዘረዝርልሽ ምን ያህል እንደምትሳቀቂ ይገባኛል! ግን እውነት ነውና ልታምኚኝ ይገባል:: ቢመርሽም ዋጪው፤ ቢተናነቅሽም ተቀበይው:: ይህን የምጽፍልሽ ለሞት እየቀረብኩ እንደሆነ ስለሚሰማኝ ነው...ሲፀፀተኝ የኖረ በደሌን ለምን አልናዘዝም ብዬ ነው:: እንደገናም ወንድ ልጁን የመሳም ፍላጐት ካለሽ ልንገርሽ ብዬ ነው...'*

ደነገጠች ሰናይት:: እየደረሳት ያለው መረጃ በህልም መስላት:: ልቦለድ መሰላት:: የቃላት ጨዋታ መሰላት::

ፊልሞን! ፊልሞን! ፊልሞን!

ሰናይት አድራሻዋን አጠፋችው:: sign out!

እንደ ማበድ አደረጋት:: ለረዥም ደቂቃ ፍዝዝ-ቅዝዝ ብላ ኮምፒዩተሩ ላይ አፈጠጠች:: ዐይኖቿ ከንፈሮቿ ተከፍተዋል:: ከአፍንጫዋ ደም! ያልነበረባት ነስር - ትኩስ ደም- ጠብ ጠብ- ጠብ-ጠብ!

ከዚያ በኋላ የሆነችውን አታውቀውም::

ከሦስት ቀናት በኋላ ስትነቃ፣ ራሷን በአንድ ስመ ጥር ሆስፒታል ውስጥ አገኘችው:: 'ምን ሆኛለሁ?' ዙሪያዋን ከብበው፣ በጭንቀት ተሞልተው ለሚያዩዋት ልጆቿ ጥያቄዋን አቀረበች::

'እኛ ራሳችን ምኑን አውቀነው? ራስሽን ስተሽ አፋፍሰው ያመጡሽ ከኢንተርኔት ቤት ነው፤ ከቦርሳሽ ውስጥ አድራሻሽን አግኝተው ደውለው የጠሩን...' አሏት::

ህመሟ አለመረጋጋትና ከፍተኛ ጭንቀት ነበር:: በአምስተኛው ቀን ድና ከሆስፒታል ወጣች::

ብዙ ጋዜጦችም፣ 'ለጊዜው ግልፅ ባልሆነ ሁኔታ ነፍሷን ስታ የመገኘቷን ነገር...' በሰፊው ጻፉና የጠያቂዎቿን ቁጥር አበዙት::

ሰናይት ከሆስፒታል ከወጣች በኋላ ፀጥተኛ ሆነች፤ ብቸኛም ጭምር:: ደግሞ ዝንጉ ሆነች:: የልጆቿን ስም እያምታታች እስከትጠራ ድረስ!

ፆም ጸሎት አበዛች:: - እባክህን አምላኬ ፊልሞንን እንዳልቀየመው አድርግ:: ምስጢረኛም ሆነች:: የምትናገረው የማይገባ፣ የምታደርገውም ለማንም የማይገለጥ!

አንድ ቀን፣ 'ዘመድ ጥየቃ ሄጃለሁ' ብላ ከቤቷ ወጣችና ከአርዮን በተቀበለችው አድራሻ መሰረት የጣውንቷን አድራሻ ማፈላለግ ያዘች:: ከብዙ እንግልት በኋላ አገኘችው::

'የተማሪ ቤት ጓደኛዋ ነበርኩ:: ከውጭ ሀገር መምጣቴ ነው' ብላ ራሷን አስተዋወቀች::

የተፈላጊዋ እናትም ከንፈራቸውን እየመጠጡ፣ 'እሷኮ ከሞተች ቆይታለች:: ቆይታለችኮ! አልሰማሽም ኖሯል:: አንድ የወደደችው ሰው ነበር:: መንግሥት ተቀናቃኜ ነው፤ ተቃዋሚዬ ነው ብሎ ሲገድልባት ጊዜ፣ በሀዘንና በብስጭት ብዛት ጨጓራዋ ተልጦ በጠና ታመመችብን:: መታከም አልፈልግም፤ መዳን አልፈልግም ብላ ነበር:: ተይ ብንላት፣ ታከሚ ብንላት፣ ብንሰራት፣ ብንለምናት እሱ ሞቶ እኔ በህይወት አልኖርም ስትል ቆይታ አንድ ጧት ሞታ አገኘናት' አሏት::

ሰናይት ፊቷን ጥልቅ ሀዘን የለበሰ አስመሰለችው:: ለውሸት ትካዜዋ በቂ መፅናናትን ከእናትየው ስትቀበል ቆየችና ራሷን አንድ ጥያቄ ጠየቀች:: - የልጆቼ አባት አርፏል ብዬ፣ እኔም ተከትዬው መሞት ነበረብኝ እንዴ?

እሷ ከምትወደው በላይ ባሏን የምትወድባት ሴት በመገኘቷ ቅናት ቢጤ ጠቅ አደረጋት:: ሸነቆጣት::

'መሞቷን አታውቂም ነበር?' ብለው ጠየቋት::

'አላውቅም እትዬ፤ በፍፁም አላውቅም:: ከሀገር ከወጣሁ ወደ አስራ አምስት ዓመት ይሆነኛል'

'አስራ አምስት ዓመት? ጊዜው ረዥም ነው:: ያኔ ነፍስ ጡር ነበረች:: ልጇኮ አሁን እዚህ ነበር'

'ላገኘው እችላለሁ?'

ወደሚገኝበት የእርሻ ቦታ ወሰዷት::

አገኘችው::

የባለቤቷን 'ልጅ' አየችው:: ወንድ ልጅ! የፊልሞን ልጅ - ትንሹ ፊልሞን - የአባቱ ልጅ - ከአርዮን ሚስት የተወለደው::

'በፍቅር የሞተችለት ወንድ ነበር:: እጇንም በእጇ የበላችው፣ እሱ በህይወት ከሌለ የኔ መኖር ትርጉም የለውም ብላ ነበር:: ይሄ ልጅ ከትዳር ውጪ ነው የተወለደው:: ባለቤቷ፣ 'ወስልታብኛለች' ብሎ ተጣልቷት ነበር አሉኝ' አሉ አሮጊቷ፣ ጨዋታው ሲደራ::

'ያውቃል?' ብላ ጠየቀች፣ ሰናይት::

'ማን?'

'ልጁ!'

'ምን?'

እየፈራች ጠየቀች:: 'የአባቱን ማንነት?'

'እስካሁን አያውቅም ነበር፡፡ አሁን ግን ጐርምሷል! አባቱ ምን እንደሆነ እነግረዋለሁ'

'እስከዛሬ አልነገሩትም?'

'ምን ብዬ እነግረዋለሁ? አባቱ ከመንግሥት ተጣልቶ አይደል ደሙ ደመ ከልብ ሆኖ የቀረው? ታዲያ ይህን እያወቅሁ፣ 'የፊልሞን ልጅ ነህ!' ብለው መንግሥት ተከታትሎ ቢገድልብኝስ? ብዬ ለማንም ለምንም ሳልተነፍስ - እኔ እናትሽ ፀጥ! ረጭ! ይኼው ቀልቤ ለወደደሽ ላንቺ የልጄንና የልቤን ምስጢር ስተነፍስ...'

የሰናይት ልብ መምታት ጀመረ፡፡ ታውቋታል - ሊነስራት ነው፡፡ ደግሞ ራሷን ከፉኛ ፈለጣት፡፡ ራስ ምታቷ ሊመጣ ነው፡፡

አሮጊቷ ቀጥለዋል፡፡ 'አሁንማ እነግረዋለሁ - አባቱ ብዙ ታሪክ ያለው ሰው ነው፡፡ ይወቀውና ይደሰት፡፡ ትምህርት ቤት ሁሉ የሚጠራው በእናቱ አባት ስም ነው፡፡ አሁንማ መንግሥት ተለውጦ የለ? ምን ያስፈራኛል?...' አሏት፡፡

ሰናይት ቁዘማ ውስጥ ነበረች፡፡የአሮጊቷን የመጨረሻዎቹን ዐረፍተ ነገሮች አላዳመጠችም፡፡

ተመለሰች- ያየችውን አይታ፣ተልዕኮዋን ፈፅማ፡፡ ሴት ልጆቿ አሁንም ቢሆን እናታቸውን አያምኗትም፡፡ 'የሆነ እኛ እንድናውቀው የማትፈልገው ከፉ ነገር አለ፤ ምንድነው፤ምን ሆነሻል?' እያሉ፡፡ ወተወቷት፡፡

'አታስጨንቁኝ፡፡ ምንም አዲስ ነገር የለም!' ነበር፣ የሁልጊዜ መልሷ፡፡

ቆየ ቆየና ታመመች፡፡ 'ልትድን አትችልም!' በሚያስብል ሁኔታ ተሰቃየች፡፡

'የንስሃ አባቴን ጥሩልኝ!' አለች፣ አንድ ቀን፡፡

የንሰሃ አባት ተጠሩ፡፡

'ሁላችሁም እኔ ካለሁበት ክፍል ውጭ ሁኑ!' ልጆቿን አዘዘቻቸው፡፡

እንደምትፈልገው ሆኑ፡፡

'አባኪዎን አባ፣ከይቅርታ ጋር በሩን ይዝጉት!' አለች፣ ከአልጋ አላነቃንቅ ያላት ህመሟን እየረገመች:: በሩ ተዘጋ::

'ንገሪኝ:: የሆንሽውን ንገሪኝ - ልጄ! ከንስሀ አባት ምንም አይደበቅም'

ስለፊልሞን ገዳይ ማንነትና እስከዛሬ ተደብቆ ስለቆየው ወንድ ልጁ አሳጥራ ተረከችላቸው:: የንስሃ አባቷ ቅዥት መስሎ እየታያቸው እየደነገጡም ቢሆን አዳመጧት:: ከወዲያ በኩል የልጆቹ የልቅሶ፣ የዋይታና የወይኔ እናቴን አጣሁ ድምጽ ይሰማል::

'ለመሆኑ ከማን የተወለደ ልጅ ነው?'

ዝም::

'ንገሪኛ ልጄ...'

እየቀፈፋት ተናገረች:: 'ከጓደኛው ባለቤት! አሁን በህይወት የለችም'

ፀጥ!

'አሁን ምን እንዳደርግልሽ?'

'ልጆቼ ወንድም እንዳላቸው ይወቁ:: ይንገሩልኝ:: እኔ ድፍረት አጣሁ'

'ልጁ አሁን የት ነው ያለው?'

ፀጥ!

'አድራሻው የት ነው?'

ዝም!

'ንገሪኝ ልጄ!'

ትከሻዋን ነካ ሲያደርጓት ከንብል! ሄደች፤ ዘግይታም ቢሆን ባለቤቷን ተከተለችው...

ይሄ ነው - የፊልሞን ያልተዳሰሰ ገፅ:: ይሄ ነው ፀሃይ ያልሞቀው - ዜና ያልጐበኘው የፊልሞን አስደናቂው የጀርባ ታሪክ:: ይህን ታሪክ በተመስጦ ለአለቃው ተረከለት:: ዋና አዘጋጁ ጀማሪ ሪፖርተሩን ሳያቋርጥ ሰማው:: በመደነቅ - በመተከዝ - በመመሰጥ...

ድብልቅልቅ ባለ ስሜት ሲከታተለው ቆይቶ፣ "ላንተ ግን ማን ነው ይህን የነገረህ?" አለ፣ ለራሱ የሚያንሾካሽክ በሚመስል ድምጽ::

"አባቴ የሰናይት የንስሃ አባት ነው!" እያለ በአንደበቱ፤ በልቡ ደግሞ - ምንድነው በዚህ የጐሰቆለ በሚመስል አለቃዬ ፊት ዐይኑ ላይ የማነብበው ስሜት? ብሎ አሰበ:: ምን ሊለምነኝ ነው? በዋና አዘጋጁ ላይ የማየው የተለማማጭነት፣ የመሸነፍ ስሜት ከየት ተከሰተ? ይሄ ሰውዬ ምን ሆኗል?ብሎ ማሰብ ቀጠለ::

በስምዖን ጭንቅላት ውስጥ ብዙ ጥያቄዎች ተመላለሱ:: "... ለምን እንደነገርኩህ ይገባሃል? ነገ በምናወጣው ጋዜጣ ላይ ሰፊ የዜና ሽፋን ሰጥተን እንድናትመውኮ ነው" አለ፣ የተስፋዬ መቀዝቀዝ ግራ ገብቶት:: የለም! ከመቀዝቀዝ በላይ ነው የቀዘቀዘው::

ዋና አዘጋጁ ከትካዜ ቅጥር ሳይወጣ፣ "ይቅርብን ወዳጄ! በናትህ ይቅርብን:: ይህንን ዜና እንኳንስ ሀገር ሰምቶት ሊገረምበት እኔና አንተ ጆሮም በመድረሱ ልንሰቀቅ ይገባናል" አለ፣ ፊቱን አኮምጭጮ::

"እንዴት?"

"ይቅርብን ፊልሞንን አንንካው፤በልባችን ውስጥ እንደገነነ ይኑርልን"

"በሴት የተነሳ ህይወትን ማጣት አዲስ ነገር ነውንዴ?"

"በጭራሽ!"

"የሩሲያው ድንቅ ባለቅኔ አሌክሳንደር ፑሽኪን በሴት የተነሳ ሻመላ ሲማዘዝ እንደሞተ አታውቅም?"

"አውቃለሁ!" አለ አዘጋጁ፣ በፍቅር እጁን ትከሻው ላይ አሳርፎ::

"ታዲያ ፊልሞን በሴት የተነሳ ስለመሞቱ አንድም ሰው ያላወራውን፣ አንድም ጋዜጣ ያልዘገበውን፣ አቧራ የሚያስነሳልንን ምርጥ ዜና ይዤልህ ስመጣ ለምን ቀዘቀዝከብኝ?"

"እንዳላወቅነውና እንዳልሰማነው መቁጠር ይሻላል - አሁን የነገርከኝን በሙሉ!"

"ካላመንከኝ ፋዘር እንዲነግርህ ላደርግ እችላለሁ:: ለኔ ያጫወተኝ ሆዱን ሲቆርጠውኮ ነው:: ምነው? ምን ሆነሃል?"

"እባከህን ዕድሜ ልከህን ስትኮራበት የምትቆየውን ውለታ ዋልልኝ:: የነገርከኝን ለማንም አትንገር! ለአባትህም ንገራቸው:: ፊልሞን እንቁ እንደሆነ ይቀጥል:: ስሙ እንዳይከፋ እንጠብቀው..."

"የምትለው አልገባኝም!" አለ ስምዖን፣ ግራ ተጋብቶ::

"የነገርከኝን ሁሉ እንደቅዥት ቆጥረን እንርሳው:: ይህን ማድረግ ትችላለህ:: አንተ በሳል ነህ" አለ አዘጋጁ በሚያባባል ድምጽ፣ "ፊልሞንን እንተወው:: ኩራታችን እኮ ነው:: ወደፊት - አሁንም ቢሆን - ልጆቻችን እኮ ሮል ሞዴል እንዲያደርጉት የሚፈልጉት ሰው እኮ ነው:: በስሙ ስንትና ስንት ቅዱሳት ተግባራት ተፈፅመዋል? ስንትና ስንት የውጭ ሀገር ምሁራን፣ 'ለካስ እሱ ከተወለደበት ሀገር ነው የመጣችሁት?' ብለው ክብር ቸረውናል"

"ይገባኛል..."

"እየህ! ይህንን ስምና ይህንን ስሜት ነው ዘላለማዊ ማድረግ ያለብን:: እንኳንስ ሽሽግ ነውሩን ገልጠን - አደባባይ ልናሰጣው ይቅርና ያልኖረውን ቅዱስ ህይወት ኖሮታል ብለን ነው እሱንና ሥራውን ማግዘፍ ያለብን..."

በብዙ ምሳሌዎች ፊልሞንን አተልቆ አሳየው:: 'አቤት ይሄ ሰውዬ!' እንዲህ ዓይነት ሰው መሆኑን አያውቅም ነበር:: ያን ትልቅ የመሰለውን ዜና ለሌሎች ጋዜጦች ቢነግራቸው እንዴት ተስገብግበው እንደሚያትሙት ያውቃል::

ይሄ ሰውዬ ግን...

ሪፖርተሩ ገረመው:: የጋዜጣው ዋና አዘጋጅ ሰብዕና የዋርካ ያህል ገዘፈበት:: “በቃ ይቅር! ትቼዋለሁ፤ ዜናው ባይዘገብ የሚያመጣው ጥቅም ገብቶኛል” አለ::

“ማልልኝ!” አለው አዘጋጁ፣ በሚለማመጥ ዐይን በሚለማመን ድምጽ::

“ምን ብዬ ልማል? ለምን ብዬ?”

“ዛሬ የነገርከኝን ለማንም እንደማትነግር ነዋ!”

“እመነኝ”

“አምንሃለሁ:: አ - ም - ን - ሃ - ለ - ሁ:: አንተን ላለማመን ምን ምክንያት አለኝ:: አንተን ማመን ያልቻልኩ ማንን ላምን ነው? ገብቶሃል አይደል፣ ለምን ሃሳብህን እንደሰረዝኩብህ? ሀገሬ ታሳዝነኛለች:: መሆን ትመስለኛለች:: የወላድ መካን! እርሟን አንድ ዕንቁ አምጣ ብትወልድ የሠራውን ሁሉ አፈር ድቤ የሚያስግጥ ዕልፍ አዕላፍ ጉዶች ተወለዱ:: ኧረ እንኳንም በአንተ አፍ ሰማሁት:: በሌላው ቢሆን ኖሮ...” አለ አዘጋጁ፣ ሊመጣ ነበር ብሎ የሰጋውን ክስረት በፊቱ እንቅስቃሴ እየገለፀ::

“በቃ ለማንም - ም - ን - ም የማወራው አይኖረኝም:: የፊልሞን ስም ቅዱስ ሆኖ እንዲቆይ የምችለውን ያህል እጥራለሁ!” አለ ስምዖን ተረጋግቶ:: አዲስ ሃይማኖት ውስጥ የገባ መሰለው::

“በጣም - በ - ጣ - ም አድርጌ ነው የማከብርህ... ቅድም በነገርከኝ ነገር ደንግጬ ጩህ ጩህ ብሎኝ ነበር:: አባትህን ደግሞ እፈልጋቸዋለሁ:: ቀጠሮ ትይዝልኛለህ:: የንስሀ አባት ማለት ምን ማለት እንደሆነ እንጠይቃቸዋለን:: የንስሀ አባቶች ሚና እና ምስጢር ስለመጠበቅ ችሎታቸው እናወያያቸዋለን”

"ችግር የለም..."

አመሰግኖት ወጣ:: አቤት! እንዴት ያለ የመባረክ - እንዴት ያለ ንፁህና ቅዱስ የመሆን ስሜት - እንዴት ያለ የትልቅነት ስሜት ነው የተሰማው?

አዘጋጁ ቅዱስ የመሆኛን ክብሪት የመሰለውን ሃሳብ ለጋዜጠኛው አቀበለው:: ጋዜጠኛውም እሱም ለኮሰው:: አሁን በፍቅር ሙቀት፣ በደግነት ብርሃን የሚመላለስ ጧፍ ሆኗል::

"ባይታወቅልህም፤ሀገር ባያውቅልህም ዛሬ ትልቅ ጀብዱ ፈፅመሃል" አለው፣ ራሱን፡፡

እናም ከራሱ ጋር ፍቅር የያዘው መሰለው፡፡ መሰለው፡፡

----

# ከዘመን ጀርባ

ስለሺ ከመንፈቅ በላይ እስር ቤት የከረመና፣ 'የመንግሥት ተቃዋሚ የሆነው ፓርቲ ባስነሳው ነውጥ እጅህ እንደሌለበት ተረጋግጧል!' ተብሎ፣ በአንድ ካድሬ አማካይነት ከእስር ነፃ ለመውጣት የበቃ፣ የሰላሳ ሦስት ዓመት መምህር ነው::

ለሞት ተሞሽረው ከነበሩት ጓደኞቹ መሃከል የተለየው ዛሬ ነው:: ዕድሜ ለዚህ ካድሬ ...

"ነፃ የወጣኸው ንፁህ ስለሆንክ አይደለም:: ከመሰሎችህ ነጥዬ፣ ከሞት መንጋጋ ፈልቅቄ ያወጣሁህ አምኜህ ነው፤ አምስት ሺህ ብር ልትሰጠኝ የገባኸውን ቃል እንደማታጥፍ ተስፋ በማድረግ!" አለው ወጣቱ ካድሬ፣ ጥርጣሬ በበዛበት ድምጽ፤ "በሁለታችን መሃከል ስለተደረገው ስምምነት ለአንድ ሰው ትንፍሽ ብትል ግን አይማረኝ ብምርህ፤ ሞት ይጠብቅሃል?" አለና በሹክሹክታ አስጠነቀቀው::

"እመነኝ! ስለዋልክልኝ ውለታ ዕድሜ ልኬን..." የጀመረውን ዐረፍተ ነገር አልጨረሰም:: ቃላት አጥሮት አይደለም:: ካድሬው ጣቱን ስለሺ ከንፈር ላይ በማሳረፍ ስለሺን ዝም አሰኘው::

በልቡ ግን፣ 'ለዋልኩልህ ውለታ እጅ መንሻ ይሆን ዘንድ የምትሰጠኝ ብር በእጄ ይግባ እንጂ ሳምንት ባልሞላ ጊዜ ውስጥ አዲስ አበባን ለቅቄ ወደ ከፍለሀገር እሄዳለሁ' እያለ ነበር::

ያስታውቃል፤ካድሬው የመሰደድ ስሜት እንደተሰማው እንዲሁ ያስታውቃል:: ከቅርብ ጊዜ ወዲህ የሥራ ባልደረቦቹ 'ተራ' በሆነ ምክንያት እየታሰሩና የደረሱበት ቦታም እየጠፋ ስለሆነ ሥጋት አድሮበታል:: ቀጥሎ የሚሰማው የጅራፍ ጩኸት ማንን ለመግረፍ እንደተዘጋጀ የሚታወቅ ነገር የለም:: መግደልም መገደልም ገለባን የማቡነን እና አቡዋራን የማራገፍ ያህል ቀላል የሆነበት ጊዜ ነው ብሎ ደምድሟል:: በፓርቲዬ እጅ ያለሁ በትር ነኝ፤ መንግሥት የሚያዘኝን ነው የምፈፅመው ብሎ ስህተቶቹን ለማስተባበል

ቢሞክርም፣ የሚያውቃቸው ወዳጅ ዘመዶች ሁሉ ከማኅበራቸው ለይተውታል::

ማታ:: ሁለት ተኩል አካባቢ:: ስለሺና ካድሬው ዘመም ወዳለች ወደ አንዲት ቤት አመሩ:: የቤቱ አሮጌ ጣሪያ ቆርቆሮ ወንፊት ሆኗል:: ቆርቆሮው በተቆራረጠ ትንፋሽ - ስልት አልባ በሆነ ዜማ - የሀዘን መዝሙሩን ያሰማል:: ግርግዳው ላይ ያረፈው ጭቃም ቦታውን ለቅቋል:: ስለሺ ይህች ቤት እየሞተች ነው ብሎ አሰበና ወዲያው ደግሞ የለም አትሞትም...ይህች ቤት እንደኢትዮጵያ ናት...ኢትዮጵያ በአዲስ፣ በንፅህናና በድንግልና መንፈስ የሚወዳትን ነው ያጣችው:: እኔና መሰሎቼ ያረገዝናት ኢትዮጵያ እንዳትጨነግፍብን የምንውተረተር ትጉሃን ነበርን:: ነበርን:: ነበርን! ብሎ አሰበ::

አንኳኳ:: ገርበብ ያለውን በር ገፋ አድርገውት ገቡ:: ምድጃው ዳር ቁጭ ብለው የነበሩት ወላጆቹ ሕልም እንጂ ዕውን አልመሰላቸውም ነበር:: ከሞጨሞጨ የዐይኖቻቸው መስኮት ብርሃን ሲወጣ ሲያይ - ያለራሱ በቀር ሌላ ልጅ የላቸውምና የሚሆኑለትን ሁሉ ሲያይ - አንጀቱ ተላውሶ የተጐሳቆለ ሰውነቱ ተብረከረከ::

እንደሚያነክስ እንዳይታወቅበት የሚንቀሳቀሰው በዝግታ ነው:: መላ ሰውነቱ በጅራፍ ተተልትሎ የቁስል ማደሪያ አካል ሆኗል::

ወላጆቹ ሞትን ድል አድርጎ እንደመጣ ቆጥረው ዐይናቸውን ከዐይኑ መንቀል አልሆነላቸውም:: የታሰረበትን ቦታ ለማወቅ ያልኳተኑበት ቦታ አልነበረም:: ግራ በገባቸው ጊዜ ነው - ነፍሱን ይዞ ሥጋውን ለብሶ እፊታቸው የቆመው::

- ስለሺ ልጄ! ስለሺ ብርሃኔ! ስለሺ...

ዕንባ! ዕንባ! ዕንባ!!!

ወጣቱ ካድሬ፣ "የማባክነው ጊዜ የለኝም!" ብሎ፣ የስለሺን ትከሻ ጐሸም አድርጎ ከእናትና ከአባቱ እቅፍ አላቀቀው:: ካድሬውን፣ "ወዳጄ ነው!" ብሎ ቢያስተዋውቃቸውም፣ ዐይነ ውሃውን ሲያዩ የደስታቸውን መጠን አሳንሶታል:: ወዳጅ እንደዚህ አይደለም - ይሄ መረቡን ባህር ላይ እንደጣለ ዓሣ አጥማጅ ነው:: አንዱ መዳፍ ሌላው ወፍ ይመስላል፣ የአንዱ ህይወት በሌላው እጅ ናት:: ማዳንም መግደልም ይችላል::

“ፍጥነት!” አለ፤ ካድሬው:: “ብዙ መሥራት የሚጠበቅብኝ ዓይነት ሰው ነኝ!”

ስለሺ የጓዳውን በር ከፍቶ ሲገባ ካድሬው ተከተለው:: እያንዳንዱ የካድሬው እንቅስቃሴ ጥንቃቄና ጥርጣሬ የተሞላበት ነበር:: ካድሬው "ቶሎ በል!" አለ፤ የጓዳውን በር እየዘጋ:: ስለሺ፣ አንዲት መለስተኛ የቆርቆሮ ሳጥን ከአልጋ ስር አወጣ:: ሳጥኑ ውስጥ የነበሩት የጥንት ጋዜጦች፤ ተማሪ ቤት የተሸለማቸው መጻሕፍት፤ የሚያስተምርባቸው የትምህርት መረጃዎች ... አንዳቸውም የሉም:: በምትኩ ልብሶቹ ተጣጥፈው ተቀምጠዋል:: እናም መዝሙረ ዳዊት መጽሐፍ፡

ገፆችን ገላለፃቸው - የመጽሐፍ ቅዱሱን ገፆች:: ምንም!!!

ልብሶቹን በታትኖ የእያንዳንዱን ኮትና ሱሪ ኪስ ፈታተሸ:: ፈትሾም ጨረሰ:: እንደገና ተረጋጋና በድጋሚ ኪሶቹን ፈታተሸ:: ዝሙት ሲፈፀም እጅ ከፍንጅ እንደተያዘ የሃይማኖት አባት፤ ሃፍረትና ፍርሃት ተፈራረቁበት::

በስለሺ ፊት ላይ ግራ መጋባት ሲያይ፣ “ኧረ ፍጥነት!” አለ ካድሬው:: ከአዲስ አበባ ርቆ የመሄድ ፍላጎቱ ጨምሯል:: መጠላት እያሰቀቀው ነው:: የሰው ዐይን አሰቃይቶታል:: በየዕለቱ፣ በየመንገዱ፣ በእያንዳንዱ ሰው ዐይን ውስጥ ወደሱ የተሰበቀ ጦር ይታየዋል:: ካልገደልኩህ ስቃዬ አይቀንስም፤ ዕረፍት አይኖረኝም የሚሉ የሚመስሉ ዐይኖች በየዕለቱ የቀን ብርሃኑን ይነጥቁታል::

.....

“አምስት ሺህ ብሩን በፖስታ አሽጌ፣ ከደብተሮቼና ከመጽሐፎቼ ጋር ያስቀመጥኩት እዚህ ሳጥን ውስጥ ነበር:: የት እንዳደረጉት ወላጆቼን ልጠይቅ?” አለ፣ ስለሺ ተለሳልሶ:: ስጋቱን የመቆጣጠር አቅም እያነሰው ነው...

“ፈጠን በል አልኩህኮ! የማባክነው ጊዜ የለኝም!” አለው ካድሬው፣ በዐይኑም በእግሩም እየተከተለው::

የስለሺ ወላጆች፣ የደስታ ሲቃ እየተናነቃቸው አንገታቸውን ቀና አድርገው ‘የአዛኟቷን’ ስም ያነሳሳሉ:: ‘ዕንባችንን አብሰሻልና፤ ስምሽንም ጠርተን አላፈርንብሽምና፤ በመከራ ጊዜም ታድገሽናልና ...ድንግል ሆይ በየወሩ እንዘክርሻለን’ እያሉ::

ስለሺ ላለማልቀስ ራሱን አስገደደ:: ማን ነበር፣ ‹ዕንባ የመከራን አቧራ ያጥባል ብላችሁ የምታምኑ ከሆነ ተንሰቅስቃችሁ አልቅሱ› ያለው? የትኛውስ ነቢይ ነበር፤ ‹እንደ ነጣቂና እንደሚጮህ አንበሳ በላዩ አፋቸውን ከፈቱ› ብሎ በአሳዳጆቹ የተማረረው?

"አንተ ሰውዬ ኧረ ፍጥነት!" አለ ካድሬው - በሃሳብ ጭልጥ ብሎ የሰመጠውን ስለሺን እያየ፤ "ገንዘቡን አስቀምጠውልህ ከሆነ ከእነሱ ተቀብለህ ቶሎ ሸኘኝ"...መሄድ ...መሄድ...መሰደድ...ነፍስን ለማትረፍ ብቻ ሳይሆን፣ ከተሰበቀበት የጥላቻ ጦር ለማምለጥ...መሄድ::

ስለሺ ብሩን ሳጥኑ ውስጥ የቆለፈበት ዕቁብ እንደደረሰው ምንም ሳይቀንስለት ነበር:: ለቤቷ ማሳደሻ እንዲውል! ይህች ቤት አሮጌ ነገር በዝቶባታል፤ ትዝታ በዝቶባታል፤ ለውጥ ናፋቂ የሚኖርባት አይመስልም:: የተስፈኞችን ሣቅ የሚያቀነቅን ልብ ያላት አይመስልም:: መታደስ አለባት:: አሁን ግን ይህንን ስሜት ለማቃናት እንዲውል የተቀመጠው ብር የለም:: የት ሄደ? ጠየቃቸው፤ ወላጆቹን ጠየቃቸው:: መልስ ለመስጠት ቋንቋ መቀየር ግድ ሆነባቸው፤ ካድሬው ጆሮውን ቢቆርጡት እንኳን አይሰማም ብለው በሚገምቱት ቋንቋ ማውራት...

“ሳጥኑ ውስጥ የነበሩት ንብረቶቼን የት አስቀመጣችኋቸው?”

“ከታሰርክብን በኋላኮ ጠንቃቃ ሆነንልሃል:: መቸም እናንተና መንግሥት አይጥና ድመት ሆናችኋል:: ሺህ ላም ቢታለብ ያው በገሌ ነው አለች አሉ ድመት፤ የነበረውም ያለውም እንዲመጣ የምትናፍቁት መንግሥትም ለድሃ መች ግድ ይኖረዋል? ምናለ ልጄ አርፈህ ብትቀመጥ...ምናለ? ምናለ? ምናለ?”

ስለሺ ለአባቱ ተግሳፅ ጆሮ አልነበረውም:: የጠረጠረው ነገር እንዳይሆን ጸለየ:: በራሱ ላይ ያሚረተ መሰለው:: አማተበ:: - አባት ሆይ ቢቻልህ ይህች ፅዋ ከኔ ትለፍ! “እማ፣ ሳጥኑ ውስጥ ያስቀመጥኩት...”

እስኪጨርስ አልጠበቁትም:: “ነገርንህ እኮ ልጄ! ከታሰርክብን በኋላ ጠንቃቃ ወላጅ ወጥቶናል:: ጉድጓድ ቆፍረን፣ እስኪጨልም ጠብቀን፣ ሳጥን ውስጥ ያሉትን የወረቀት ዘር አንዱንም ሳናስተርፍ እሳት ለቀቅንበት!" አሉ አባቱ በኩራት፣ “የፖለቲካ መጻሕፍት ለመሆናቸው አልተጠራጠርንም ነበር... እኔና እናትህ የዋዛ ሰው እንምሰልህ!" አሉት፣ ያሳለፉትን የጭንቅ ምሽት እያስታወሱ::

ስለሺ በድንጋጤ በድን ሆኗል፡፡

ከባድ ዝምታ!

ቆይቶ፣ ወደ ካድሬው ፊቱን መልሶ፣ "አምስት ሺህ ብሩን አመድ አደርግንብህ እኮ ነው የሚሉኝ!" አለ - በሚንቀጠቀጥ ድምጽ፡፡ ያልበው ጀምሯል፡፡ አራት - አምስት - ስድስት ጊዜ በተለያየ ስሜት ዐረፍተ ነገሩን ደጋገመው፡፡

ወላጆቹ ግራ በመጋባት - የምን አምስት ሺህ ብር ነው እያሉ - በካድሬው ጉልበት ስር ሆኖ ተንሰቅስቆ ወደ የሚያለቅሰው ልጃቸው አመሩ፡፡ "ሳጥንህን በርብረው መጽሐፎችህን ካገኙ ይገድሉሃል ብለን እኮ ነው ልጄ!" እያሉ፣ "ወይ የመሃይም ነገር!" ብለውም ተፀፁ፡፡

"ሂድና የምታምነውን አሙኝ!! ባንተ ቤት እኔ ላይ ቴአትር መሥራትህ ነው አይደል፤ ቀድሞውንም ያልነበረ አምስት ሺህ ብር ፈጥረህ ነበር ስታጃጅለኝ የቆየኸው!" አለና ወገቡን ነካካ፡፡

.....

ቤቷም ድንጋጤና ታላቅ መረበሽ ጠፍንጎ ያዛት፡፡

ቃላት ጠፉ፡፡ ድምጾች ጠፉ፡፡ ተስፋዎች ጨለሙ፡፡ ቤቷም የምትሞት መሰለች፡፡ ዕርጅናዋም በዝቶ ታየ፡፡

"እንዳችሁ ትንፋሽ ብትሉ እፈጃችኋለሁ!" አለ ካድሬው፣ "ት - ን - ፍ -ሽ ብትሉ!" በስለሺ ወላጆች ላይ ዛተ፤ እነሱም ለትዕዛዙ ተገዙ፡፡

በካድሬው ዐይኖች ውስጥ ሲንቀለቀል የቆየው የተስፋ ብርሃን በስለሺ ትንፋሽ ጨለመ፡፡ ፊቱን ወደ አሮጊቷ ቤት ወራሽ መለሰ፡፡ አተኮረበት፡፡ በጣም አተኮረበት፡፡

ሽጉጥ፡፡ በስለሺ ግንባር ላይ ሽጉጥ ተደገነ፡፡ ሞት በሁለቱ መሐከል በኩራት ይንጎራደድ ያዘ፡፡

ደም፡፡

....

# የተቆለፈበት

እየሄደ ነው:: አውቶብሱ እየሄደ ነው:: አፍቃሪ ልብን ተሸክሞ! ብዙ ትናንሽ ከተሞችን አቋርጧል:: ተራራዎችን አሳብሯል:: ገና ብዙ መቶ ኪሎ ሜትሮች ይጠብቁታል:: የማያልቅ የሚመስል መንገድ ነው እፊታቸው የተዘረጋው:: የአንድ ቀን መንገድ...

እሱ የመሄድ ፍላጐት እንጂ ሲሄድ ሊያጋጥመው ስለሚችለው ነገር በጥልቀት አላሰበበትም ነበር::

የመሄጃ ገንዘብ ለማግኘት ብዙ ደክሟል:: ከህሊናው ጋር ተሟግቷል:: ለመሄድ ስላነሳሳው ጉዳይም ለማንም ትንፍሽ አላለም:: ለእናቱና ለአብሮ አደግ ወዳጁ ብቻ!

እናቱ፣ 'ጡቴ ይከተልህ፤የተመኘኸውን አትጣ ልጄ!' ብለው መርቀውታል:: አብሮ አደጉ፣'አደራ ሊጐዳህ ከሚችል ነገር ራስህን ጠብቅ!' ብሎታል:: እሱ ግን ጓደኛውን ትክ ብሎ እያየ፣ 'ሰውነቴኮ የእሷ ነው፤ በምንም ነገር አላቆሽሸውም' ብሎ ቃል ገባለት::

ድምጹን አለስልሶ፣ ቃላቱን አለዝቦ ከአሰሪዎቹ የሦስት ቀን ፍቃድ የተቀበለው፣ 'እናቴ በጠና ታምማብኝ...' የሚል የውሸት ምክንያት አቅርቦ ነው:: በዕድሜም፣ በሙያም፣ በቀን ገቢም ወደሚመጣጠኑት ወዳጆቹ ዘንድ ቀርቦ፣ '...ቸግሮኛልና አበድሩኝ!' ነው ያላቸው:: እነዚህን ሰበብ አስባቦች በምክንያትነት ባያቀርብ ኖሮ፤ ማን ወደ ክልል ደርሶ የመመለሻ ገንዘብ ይሰጠው ነበር?

ወደ እሷ ነው የሚሄደው:: 'ና' ብላው አይደለም:: አንድ ቀን መጥቶ ያየኝ ይሆናል የሚል ግምትም ያላት አይመስለውም::

ኤልሳ:: ከእሷ በፊት ሌላ ጓደኛ አልነበረችውም:: እሷ ከሄደች በኋላም ሌላ ፍቅረኛ አልያዘም:: ሴት ፈራ፤ ሴት ሸሸ:: ብቻነቱን አጥብቆ ወደደው:: የነብርን ጭራ የመያዝን ያህል፣ 'አልለቅህም፤ አልተውህም!' አለው:: ወንድነቱን ብቻ ይዞ ቆመ::

ኤልሳ ነበረች - የብዙ ነገሮቹ ቁልፍ:: ቁልፉን ይዛበት ሄደች:: ይኸው እንደተቆለፈበት አለ፤ እንደተከረቸመበት:: ልቡ ተዘግቷል:: ኤልሳ ብቻ ናት በተዘጋው ልቡ ውስጥ ያለችበት:: ተቆልፏል:: የገባችዋ እንዳትወጣ:: አዲሷም እንዳትመጣ:: ተቆልፏል!

ወደ ልቡ ደጅ የቀረቡ ነበሩ:: ምላሳቸውን አለሳልሰው፣ መልካቸውን አሰማምረው፣ ድንግል ልቡን በፍቅር ማረሻ ለማረስ የሞከሩ:: አንኳኩ ግን አልከፈተላቸውም:: ጠሩት ግን አልሰማቸውም:: ዓይቶ እንዳላየ ሆኖ አለፋቸው::

ኤልሳ ገዛችው:: በየዕለቱ የሚያድግ፣ አድጐም የሚጐለምስ ፍቅር ልቡ ውስጥ ቤት ሠራበት:: ቤቱን ይዞ ይዞራል:: ከገዛ ፍቅሩ ጋር ፍቅር ያዘው::

ይህን ማድረጉ ደግሞ ለህመም ዳረገው:: መንፈሱ ተረበሸ:: አዕምሮው ተጠቃ!

ለሦስት ዓመት ያህል አብረው በፍቅር ቆይተዋል:: 'ሦስት ዓመት' ብላ ቀን ቆጥራ ዘመናቸውን የነገረችው እሷ ናት:: እሱ አያውቀውም:: 'ከመወለዴ በፊት ይመስለኛል አንቺን ማፍቀር የጀመርኩት!' ብሏታል::

ይመስለዋል:: ቆይቶ ግን ሄደችበት:: እንጀራ ፍለጋ:: የእህል ውሃ ጥያቄ በሁለቱ መሃከል የአለመገናኘትን መንገድ ዘረጋ:: መሄድዋ ስህተት አልነበረም:: ድህነት አንገዳግዷት ነው:: እሱ ኤልሳን የማቆም አቅም አልነበረውም:: 'ሳይንገዳገዱ ስለመቆም ጥበብ' ጓደኞቿ አስጐምጅተው ተረኩላት::

ሄደችበት:: በሄደችበት ቦታ ስሙን አንስታለት የማታውቀው 'ባል' ተዘጋጅቶ ጠበቃት:: ኤልሳ ሚስት ሆነችለት::

ኤልሳን ወንድ ወሰዳት:: ወሰዳት!

እንዴት አምኖ ይቀበል? ምናይነት ባል ነው ከመዳፊ ፈልቅቆ የወሰዳት? ባለ ጊዜ፣ 'ባለቤቷማ ባለ-ቤት ነው' አሉት፡፡ ተሸነፈ፡፡ በፍልሚያው ተረታ፡፡ እንደተማረከ ጄኔራል ሆነ፡፡ ሺህ የነፃነት - ሺህ የዕናት - ሺህ የእምነት ወታደሮችን ያስማረ መስሎት ነበር፡፡ ግን ወታደሮቹ...

መኖሩን የማያውቀው ባለጋራ፣መፈጠሩን የማያውቀው ባለ - ቤት ኤልሳን ወሰደበት፡፡ ሆነ፡፡ ይኸው አንድ ዓመት ሊሞላ ሦስት ወር ብቻ ቀረው፡፡ 'ተጋብተን የምንወልድበት፣ ዐይንህን በልጄ ዐይን የማይበት ጊዜ ናፍቆኛል' ትለው ነበር፡፡

ብዙ ነገር ብላው ነበር፤ ግን አንዱም አልተፈፀመም፡፡ ቃሏን አጠፈች ብሎ ማመን ለኤልሳ የነበረውን ፍቅርና ክብር ማሳነስ መስሎ ይታየዋል፡፡ ምክንያቶች ይኖሯታል ብሎም ያስባል፡፡ ምክንያቶቹ ምን ሊሆኑ እንደሚችሉ መገመት ራስን ማሰቃየት ነው፡፡ ብቻ ደህና ሆና በቆየችኝ ይላል፡፡

ኤልሳ እውነቱም ህይወቱም ነበረች፡፡ በመንገዷ ተመላለሰ፡፡ በተመላለሰበት መንገድ ፈለጋት፤ግን አልተገኘችም፡፡

ኤልሳ ውበቱም ፍቅሩም ነበረች፤ በቀደደችለት ቦይ ፈሰሰ፡፡ የፈሰሰበት ቦይ ግን፣ 'እነኳት ፍቅረኛህ!' አላለውም፡፡

ኤልሳ ትላንት፣ ዛሬውና ነገው ነበረች፡፡ በትላንቱ ውስጥ እናቱ ነበር ልቡ ውስጥ የሞሉት፡፡ በዛሬው ውስጥ እሷ ነበረች፤ ጊዜውን ገዝታ የነገሰችበት፡፡ በነገ ውስጥ ደግሞ ልጁ፡፡

ትናንትናው ንፁህና ሙሉ ሆኖ አልፏል፡፡ ዕድሜ ለእናቱ፡፡ ዛሬው ግን ባዶ ነው፡፡ ኤልሳ ጉደለችበት፡፡ ነገም እንደዛሬ መስሎ ይታየዋል፤ ባዶ፡፡ ባዶ ቤት፡፡ ጨለማ ቤት፡፡

እየሄደ ነው፡፡ አውቶብሱ እየሄደ ነው፡፡ አፍቃሪ ልብን ተሸክሞ!

የለበሰው ልብስ የእሱ አይደለም፡፡ የተሳፈረበት ገንዘብ የእሱ አይደለም፡፡ ስጦታውን የገዛበት ብር የእሱ አይደለም፡፡ ወደ እሷ ለመሄድ እያባከነ ያለው ጊዜ የእሱ አይደለም፡፡ የእሱ የሆነው ነገር ልቡ ብቻ ነው፡፡ ልቡ ውስጥ አንድ

ምስል አለ፤ አንድ ስም አለ፤ አንድ ማኅተም አለ:: ምስሉ የኤልሳ...ስሙም የኤልሳ...ማኅተሙም የኤልሳ...

ነገ ያገኛታል፤ ሲያገኛት ልቡን ከፍቶ ያሳያታል::

ይህች ቀን ከሌሎች ቀናት ትለይበታለች:: ኤልሳን ለማየት ሞላለት:: ከሄደችበት በኋላ ጨልሞበት ነበር:: ዐይኗ ውስጥ ነው ያለው - ዘመኑን የሚለኩስበት ኩብሪት:: ባልጠረጠረው ሁኔታ ጥላው ስትኮበልል ግራ ገባው:: እንቅፋት መታው:: ከሰው ጋር ተጋጨ:: መመታቱና መጋጨቱ ሲብስበት ከጥቂት መደናብሮች በኋላ ቆመ:: በቆመበት ቆዘመ:: ዐይኖቹን ከድኖ ወደ ውስጡ ገባ:: ወደ ውስጡ ሰመጠ:: ከሰመጠበት የትዝታ ባህር እንደ ዕድል ሆኖ አዲስ የሃሳብ ዓሣ ይዞ ወጣ:: ሂድ! ሂድ! ሂድ አለው:: ኤልሳን! ኤልሳን! ኤልሳን! አለው:: ሂድና ምክንያቷን ጠይቃት አለው:: ለእኔ የነበረሽ ፍቅር ምን ገደለው? በላት በላት አለው::

ይኸው ዛሬ ለመጀመርያ ጊዜ ከትውልድ አገሩ ወጣ:: ወደማያውቀው ክልል መጣ::

አውቶብሱ ቆመ:: ተሳፋሪዎች ጩኸታቸውንና ጭነታቸውን ተሸክመው ወረዱ:: ጨልሞ ነበር::

በሁለተኛው ቀን፣ እንግድነቱን ያወቁት የሀገሩ ዱርዬዎች የያዘውን ዘረፉት:: ለኤልሳ የወሰደላትን ስጦታ፤ ከተጻጻፏቸው ደብዳቤዎች ጋር:: ከተነሷቸው ፎቶግራፎች ጋር:: ወሰዷቸው:: ከወሰዱበት ነገር መሃከል ለነሱ የሚጠቅም ነገር በማጣታቸው፣ ላበከኑት ጊዜና ጉልበት መታሰቢያ ይሆን ዘንድ በዱላ ነረቱት:: ግንባሩ ቆሰለ::

በተሰጠው አድራሻ መሰረት ወደ ኤልሳ ቤት ሄደ:: መናኸርያ አካባቢ:: ልቡ መታ:: መታ:: መታ:: በሃይል መታ:: የሚንቀሳቀስ ሳጥን የሆነ መሰለው:: ሳጥኑ ተቆልፏል:: ቢቆለፍም እግር አለው:: ለዘጠኝ ወራት የቆመው እግር አሁን መሄድ ጀምሯል:: አምስት መቶ ምናምን ኪሎ ሜትሮችን አቋርጦ:: በሳጥን ውስጥ የተቆለፈን ልብ እንደያዘ::

ደጇ ላይ ቆመ:: ቆመ:: ደግሞም ተቀመጠ:: እንደተቀመጠ ግማሽ ሰዓት ሞላው:: ተነሳ:: አንኳኳ:: ከአርባ ደቂቃ ቁዘማ በኋላ ድንገት አንድ ሃሣብ አየሮጠ መጥቶበት አፍቃሪ ልቡ ውስጥ ገብቶ ተሸነቀረ::

- ምን መሆኔ ነው? ምን ፍጠሪ ለማለት ነው ጐጆ መስርታ ያለች የበፊት ፍቅረኛዬጋ የመጣሁት? እኔን በማግኘቷ ለአላስፈላጊ ስቃይ ብዳርጋትስ? ለሚያፈቅሩት ሰው ስቃይና ፀፀትን ከመስጠት የከፋ ሃጥያት አለ ወይ? ብሎ አሰበ:: ፍቅር ሆይ በስምህ ሳይታወቀኝ ስህተት ልሠራ ነበርና ይቅርታ! አለ:: ለማንኳኳት ፈራ:: ምን ነካኝ? አለ:: ፀፀት ገባው:: ያሳነሳት መሰለው:: ንፁህ ፍቅሩን ላለማቆሸሽ መጠንቀቅ እንዳለበት ተሰማው:: ለዳግም ማንኳኳት የተዘረጋ እጁን ሰበሰበ:: ቆመ::

እንደቆመ አንድ አውቶብስ መጣ:: መጣና እሱ የቆመበት ስፍራ ቆመ:: "አንድ ሰው! አንድ ሰው! አንድ ሰው!!!"

የተዘጋ ልቡ ሲከፈት ታወቀው:: እጁን አውለበለበ - ወደ አውቶብሱ:: ረዳቱ ፈገግ አለ:: አፍቃሪው ሰው ወደፈገግታው ተጠጋ:: ትኬት ቆረጠ:: ወደ አውቶብሱ ሆድ እግሩን ሰደደ::

ተደላድሎ ተቀመጠ:: ተቀመጠ:: ተቀምጦ ወደነኤልሳ ቤት ግቢ አተኮረ:: በዐይኖቹ አንኳኳ:: መልሶ መላልሶ:: ዐይኖቹ ሃይል አላቸው:: በንፁህ ፍቅር የተሞላ ዐይን ያለው ሰው፤ የተዘጋን ደጅ የማስከፈት አቅም ያለው ይመስለዋል:: ያምናል:: ያመነው ነገር ደግሞ እንደሚፈፀምለት ያምናል::

ይኸው! ተከፈተ:: የኤልሳ ደጅ ተከፈተ:: ራሷ ናት:: ኤልሳ ናት፣ የተንኳኳውን በር የከፈተችው::

ጮኸ:: አፍቃሪው ወጣት ጮኸ:: ኤልሳ!

"ይህችት - ይ-ህ-ች-ት!"

ተሳፋሪዎች ግራ ገባቸው:: በጣም! ወግ ሰላቂዎችም፣ ጫት አመንዣኪዎችም፣ የብቻ ቆዛሚዎችም::

ስሟን ሲጠራ አልሰማችውም:: የተጣራው እንዲሰማት ብሎም አልነበረም:: እሷም ወደ አውቶብሱ አላየችም:: ሲያያት ግን ፀሃይ ልቡ ውስጥ ስትበራ ታወቀው:: ጭለማው ሲረታ:: የተረገዘ ናፍቆቱ ሲወለድ::

ቆመች:: አያት:: በዐይኑ ጐረሳት:: መጥገብ አቃተው:: አንድ ነገር ልብ አለ:: *ቲሸርቱ*.... አንዲት የምታምር ሴት የማያምርባትን *ቲሸርት* ለብሳ::

ኤልሳ!

የለበሰችው *ቲሸርት* የእሱ ነበር:: እሷ ናት 'ስላንተ ሳስብ ሁልጊዜ ይህንን ልብስ ለብሰህ ነው የምትታየኝ' ያለችው:: ያዘወትራት ነበር:: አንድ ቀን አስወለቀችው:: ወሰደችበት:: 'ይህንን *ቲሸርት* ለብሼው ማደር እፈራለሁ' ነበር ያለችው:: 'አንተን አንተን ይለኛል' ትለው ነበር:: አደረገችውም::

አሁንም፣ እሱን ለብሳ የምትኖር መሰለው:: 'እኔን ለብሳኝ የምትኖር ከሆነ አይበርዳትም፤ ፈጽሞ!' አለ::
ኤልሳ!

እወድሻለሁ!!!!!!

እወድሻለሁ!!!!!!!!!

እወድሻለሁ!!!!!!!!!!!!!!!

እወድሻለሁ!!!!!!!!!!!!!!!!!!!!

እወድሻለሁ!!!!!!!!!!!!!!!!!!!!!!!!!!!!

እወድሻለሁ!!!!!!!!!!!!!!!!!!!!!!!!!!!!!!!!!!!!!!!!!!

እወድሻለሁ!!!!!!!!!!!!!!!!!!!!!!!!!!!!!!!!!!!!!!!!!!!!!!!!!!!!!!!!!!!!!!!!!!!!!!!!!!!!!!

'ፍቅር ሆይ! እንዲህ እንዳስብ አድርገህ ስለሠራኸኝ አመሰግንሃለሁ!'

ዕንባው መጣ::

አጠገቡ የተቀመጠው ሰው፣ "ከትናንት በስቲያ አንተን የሚመስል ሰው አጠገቤ ተቀምጦ ነበር፤ የታላቅህ ታላቅ መሆን አለበት!" አለው፡፡

"እኔው ነኝ!" አለ አፍቃሪው፤ "እኔው ነኝ፤ የፍቅረኛዬን ዐይኖች አይቼ ነው፣ የጠፉና የባከኑ ዘመኖቼን፣ ትልቅ ሰው አስመስለውኝ የነበሩትን ዓመቶቼን ያስመለስኩት!" አለ፣ በፈገግታ፡፡

አውቶብሱ...አውቶብሱ እየተመለሰ ነው፡፡ እየተመለሰ፡፡ ነው! አፍቃሪ ልብን ተሸክሞ....

...

# የተቆለፈበት

እየሄደ ነው:: አውቶብሱ እየሄደ ነው:: አፍቃሪ ልብን ተሸክሞ! ብዙ ትናንሽ ከተሞችን አቋርጧል:: ተራራዎችን አሳብሯል:: ገና ብዙ መቶ ኪሎ ሜትሮች ይጠብቁታል:: የማያልቅ የሚመስል መንገድ ነው እፊታቸው የተዘረጋው:: የአንድ ቀን መንገድ...

እሱ የመሄድ ፍላጐት እንጂ ሲሄድ ሊያጋጥመው ስለሚችለው ነገር በጥልቀት አላሰበበትም ነበር::

የመሄጃ ገንዘብ ለማግኘት ብዙ ደክሟል:: ከህሊናው ጋር ተሟግቷል:: ለመሄድ ስላነሳሳው ጉዳይም ለማንም ትንፍሽ አላለም:: ለእናቱና ለአብሮ አደግ ወዳጁ ብቻ!

እናቱ፣ 'ጡቴ ይከተልህ፤የተመኘኸውን አትጣ ልጄ!' ብለው መርቀውታል:: አብሮ አደጉ፣'አደራ ሊጐዳህ ከሚችል ነገር ራስህን ጠብቅ!' ብሎታል:: እሱ ግን ጓደኛውን ትክ ብሎ እያየ፣ 'ሰውነቴኮ የእሷ ነው፤ በምንም ነገር አላቆሸሸውም' ብሎ ቃል ገባለት::

ድምጹን አለስልሶ፣ ቃላቱን አለዝቦ ከአሰሪዎቹ የሦስት ቀን ፍቃድ የተቀበለው፣ 'እናቴ በጠና ታምማብኝ...' የሚል የውሸት ምክንያት አቅርቦ ነው:: በዕድሜም፣ በሙያም፣ በቀን ገቢም ወደሚመጣጠኑት ወዳጆቹ ዘንድ ቀርቦ፣ '...ቸግሮኛልና አበድሩኝ!' ነው ያላቸው:: እነዚህን ሰበብ አስባቦች በምክንያትነት ባያቀርብ ኖሮ፤ ማን ወደ ክልል ደርሶ የመመለሻ ገንዘብ ይሰጠው ነበር?

ወደ እሷ ነው የሚሄደው:: 'ና' ብላው አይደለም:: አንድ ቀን መጥቶ ያየኝ ይሆናል የሚል ግምትም ያላት አይመስለውም::

ኤልሳ:: ከእሷ በፊት ሌላ ጓደኛ አልነበረችውም:: እሷ ከሄደች በኋላም ሌላ ፍቅረኛ አልያዘም:: ሴት ፈራ፤ ሴት ሸሸ:: ብቻነቱን አጥብቆ ወደደው:: የነብርን ጭራ የመያዝን ያህል፣ 'አልለቅህም፤ አልተውህም!' አለው:: ወንድነቱን ብቻ ይዞ ቆመ::

ኤልሳ ነበረች - የብዙ ነገሮቹ ቁልፍ:: ቁልፉን ይዛበት ሄደች:: ይኸው እንደተቆለፈበት አለ፤ እንደተከረቸመበት:: ልቡ ተዘግቷል:: ኤልሳ ብቻ ናት በተዘጋው ልቡ ውስጥ ያለችበት:: ተቆልፏል:: የገባችዋ እንዳትወጣ:: አዲሷም እንዳትመጣ:: ተቆልፏል!

ወደ ልቡ ደጅ የቀረቡ ነበሩ:: ምላሳቸውን አለሳልሰው፣ መልካቸውን አስማምረው፣ ድንግል ልቡን በፍቅር ማረሻ ለማረስ የሞከሩ:: አንኳኩ ግን አልከፈተላቸውም:: ጠሩት ግን አልሰማቸውም:: ዓይቶ እንዳላየ ሆኖ አለፋቸው::

ኤልሳ ገዛችው:: በየዕለቱ የሚያድግ፣ አድጎም የሚጐለምስ ፍቅር ልቡ ውስጥ ቤት ሠራበት:: ቤቱን ይዞ ይዞራል:: ከገዛ ፍቅሩ ጋር ፍቅር ያዘው::

ይህን ማድረጉ ደግሞ ለህመም ዳረገው:: መንፈሱ ተረበሸ:: አዕምሮው ተጠቃ!

ለሦስት ዓመት ያህል አብረው በፍቅር ቆይተዋል:: 'ሦስት ዓመት' ብላ ቀን ቆጥራ ዘመናቸውን የነገረችው እሷ ናት:: እሱ አያውቀውም:: 'ከመወለዴ በፊት ይመስለኛል አንቺን ማፍቀር የጀመርኩት!' ብሏታል::

ይመስለዋል:: ቆይቶ ግን ሄደችበት:: እንጀራ ፍለጋ:: የእህል ውሃ ጥያቄ በሁለቱ መሃከል የአለመገናኘትን መንገድ ዘረጋ:: መሄድዋ ስህተት አልነበረም:: ድህነት አንገዳግዷት ነው:: እሱ ኤልሳን የማቆም አቅም አልነበረውም:: 'ሳይንገዳገዱ ስለመቆም ጥበብ' ጓደኞቿ አስጎምጅተው ተረኩላት::

ሄደችበት:: በሄደችበት ቦታ ስሙን እንስታለት የማታውቀው 'ባል' ተዘጋጅቶ ጠበቃት:: ኤልሳ ሚስት ሆነችለት::

ኤልሳን ወንድ ወሰዳት:: ወሰዳት!

እንዴት አምኖ ይቀበል? ምናይነት ባል ነው ከመዳፌ ፈልቅቆ የወሰዳት? ባለ ጊዜ፣ 'ባለቤቷማ ባለ-ቤት ነው' አሉት:: ተሸነፈ:: በፍልሚያው ተረታ:: እንደተማረከ ጄኔራል ሆነ:: ሺህ የነፃነት - ሺህ የፅናት - ሺህ የእምነት ወታደሮችን ያስማራ መስሎት ነበር:: ግን ወታደሮቹ...

መኖሩን የማያውቀው ባለጋራ፣መፈጠሩን የማያውቀው ባለ - ቤት ኤልሳን ወሰደበት:: ሆነ:: ይኸው አንድ ዓመት ሊሞላ ሦስት ወር ብቻ ቀረው:: 'ተጋብተን የምንወልድበት፤ ዐይንህን በልጄ ዐይን የማይበት ጊዜ ናፍቆኛል' ትለው ነበር::

ብዙ ነገር ብላው ነበር፤ ግን አንዱም አልተፈፀመም:: ቃሏን አጠፈች ብሎ ማመን ለኤልሳ የነበረውን ፍቅርና ክብር ማሳነስ መስሎ ይታየዋል:: ምክንያቶች ይኖሯታል ብሎም ያስባል:: ምክንያቶቹ ምን ሊሆኑ እንደሚችሉ መገመት ራስን ማሰቃየት ነው:: ብቻ ደህና ሆና በቆየችኝ ይላል::

ኤልሳ እውነቱም ህይወቱም ነበረች:: በመንገዷ ተመላለሰ:: በተመላለሰበት መንገድ ፈለጋት፤ግን አልተገኘችም::

ኤልሳ ውበቱም ፍቅሩም ነበረች፤ በቀደደችለት ቦይ ፈሰሰ:: የፈሰሰበት ቦይ ግን፣ 'እነኋት ፍቅረኛህ!' አላለውም::

ኤልሳ ትላንት፣ ዛሬውና ነገው ነበረች:: በትላንቱ ውስጥ እናቱ ነበር ልቡ ውስጥ የምሉት:: በዛሬው ውስጥ እሷ ነበረች፤ ጊዜውን ገዝታ የነገሰችበት:: በነገ ውስጥ ደግሞ ልጁ::

ትናንትናው ንፁህና ሙሉ ሆኖ አልፏል:: ዕድሜ ለእናቱ:: ዛሬው ግን ባዶ ነው:: ኤልሳ ጉደለችበት:: ነገም እንደዛሬ መስሎ ይታየዋል፤ ባዶ:: ባዶ ቤት:: ጨለማ ቤት::

እየሄደ ነው:: አውቶብሱ እየሄደ ነው:: አፍቃሪ ልብን ተሸክሞ!

የለበሰው ልብስ የእሱ አይደለም:: የተሳፈረበት ገንዘብ የእሱ አይደለም:: ስጦታውን የገዛበት ብር የእሱ አይደለም:: ወደ እሷ ለመሄድ እያባከነ ያለው ጊዜ የእሱ አይደለም:: የእሱ የሆነው ነገር ልቡ ብቻ ነው:: ልቡ ውስጥ አንድ

ምስል አለ፤ አንድ ስም አለ፤ አንድ ማኅተም አለ:: ምስሉ የኤልሳ...ስሙም የኤልሳ...ማኅተሙም የኤልሳ...

ነገ ያገኛታል፤ ሲያገኛት ልቡን ከፍቶ ያሳያታል::

ይህች ቀን ከሌሎች ቀናት ትለይበታለች:: ኤልሳን ለማየት ሞላለት:: ከሄደችበት በኋላ ጨልሞበት ነበር:: ዐይኗ ውስጥ ነው ያለው - ዘመኑን የሚለኩስበት ክብሪት:: ባልጠረጠረው ሁኔታ ጥላው ስትኮበልል ግራ ገባው:: እንቅፋት መታው:: ከሰው ጋር ተጋጨ:: መመታቱና መጋጨቱ ሲብስበት ከጥቂት መደናብሮች በኋላ ቆመ:: በቆመበት ቆዘመ:: ዐይኖቹን ከድኖ ወደ ውስጡ ገባ:: ወደ ውስጡ ሰመጠ:: ከሰመጠበት የትዝታ ባህር እንደ ዕድል ሆኖ አዲስ የሃሳብ ዓሣ ይዞ ወጣ:: ሂድ! ሂድ! ሂድ አለው:: ኤልሳን! ኤልሳን! ኤልሳን! አለው:: ሂድና ምክንያቷን ጠይቃት አለው:: ለእኔ የነበረሽ ፍቅር ምን ገደለው? በላት በላት አለው::

ይኸው ዛሬ ለመጀመርያ ጊዜ ከትውልድ አገሩ ወጣ:: ወደማያውቀው ክልል መጣ::

አውቶብሱ ቆመ:: ተሳፋሪዎች ጨኸታቸውንና ጭነታቸውን ተሸክመው ወረዱ:: ጨልሞ ነበር::

በሁለተኛው ቀን፣ እንግድነቱን ያወቁት የሀገሩ ዱርዬዎች የያዘውን ዘረፉት:: ለኤልሳ የወሰደላትን ስጦታ፤ ከተጻጻፏቸው ደብዳቤዎች ጋር:: ከተነሷቸው ፎቶግራፎች ጋር:: ወሰዷቸው:: ከወሰዱበት ነገር መሃከል ለነሱ የሚጠቅም ነገር በማጣታቸው፣ ላበከኑት ጊዜና ጉልበት መታሰቢያ ይሆን ዘንድ በዱላ ነረቱት:: ግንባሩ ቆሰለ::

በተሰጠው አድራሻ መሰረት ወደ ኤልሳ ቤት ሄደ:: መናኸርያ አካባቢ:: ልቡ መታ:: መታ:: መታ:: በሃይል መታ:: የሚንቀሳቀስ ሳጥን የሆነ መሰለው:: ሳጥኑ ተቆልፏል:: ቢቆለፍም እግር አለው:: ለዘጠኝ ወራት የቆመው እግር አሁን መሄድ ጀምሯል:: አምስት መቶ ምናምን ኪሎ ሜትሮችን አቋርጦ:: በሳጥን ውስጥ የተቆለፈን ልብ እንደያዘ::

ደጇ ላይ ቆመ:: ቆመ:: ደግሞም ተቀመጠ:: እንደተቀመጠ ግማሽ ሰዓት ሞላው:: ተነሳ:: አንኳኳ:: ከአርባ ደቂቃ ቆዘማ በኋላ ድንገት አንድ ሃሣብ እየሮጠ መጥቶበት አፍቃሪ ልቡ ውስጥ ገብቶ ተሸነቆረ::

- ምን መሆኔ ነው? ምን ፍጠሪ ለማለት ነው ጐጆ መስርታ ያለች የበፊት ፍቅረኛዬጋ የመጣሁት? እኔን በማግኘቷ ለአላስፈላጊ ስቃይ ብዳርጋትስ? ለሚያፈቅሩት ሰው ስቃይና ፀፀትን ከመስጠት የከፋ ሃጥያት አለ ወይ? ብሎ አሰበ:: ፍቅር ሆይ በስምህ ሳይታወቀኝ ስህተት ልሠራ ነበርና ይቅርታ! አለ:: ለማንኳኳት ፈራ:: ምን ነካኝ? አለ:: ፀፀት ገባው:: ያሳነሳት መሰለው:: ንፁህ ፍቅሩን ላለማቆሸሽ መጠንቀቅ እንዳለበት ተሰማው:: ለዳግም ማንኳኳት የተዘረጋ እጁን ሰበሰበ:: ቆመ::

እንደቆመ አንድ አውቶብስ መጣ:: መጣና እሱ የቆመበት ስፍራ ቆመ:: "አንድ ሰው! አንድ ሰው! አንድ ሰው!!!"

የተዘጋ ልቡ ሲከፈት ታወቀው:: እጁን አውለበለበ - ወደ አውቶብሱ:: ረዳቱ ፈገግ አለ:: አፍቃሪው ሰው ወደፈገግታው ተጠጋ:: ትኬት ቆረጠ:: ወደ አውቶብሱ ሆድ እግሩን ሰደደ::

ተደላድሎ ተቀመጠ:: ተቀመጠ:: ተቀምጦ ወደኔልሳ ቤት ግቢ አተኮረ:: በዐይኖቹ አንኳኳ:: መልሶ መላልሶ:: ዐይኖቹ ሃይል አላቸው:: በንፁህ ፍቅር የተሞላ ዐይን ያለው ሰው፤ የተዘጋን ደጅ የማስከፈት አቅም ያለው ይመስለዋል:: ያምናል:: ያመነው ነገር ደግሞ እንደሚፈፀምለት ያምናል::

ይኸው! ተከፈተ:: የኤልሳ ደጅ ተከፈተ:: ራሷ ናት:: ኤልሳ ናት፣ የተንኳኳውን በር የከፈተችው::

ጮኸ:: አፍቃሪው ወጣት ጮኸ:: ኤልሳ!

"ይህችት - ይ-ህ-ች-ት!"

ተሳፋሪዎች ግራ ገባቸው:: በጣም! ወግ ሰላቂዎችም፣ ጫት አመንዣኪዎችም፣ የብቻ ቆዛሚዎችም::

ስሟን ሲጠራ አልሰማችውም:: የተጣራው እንዲሰማት ብሎም አልነበረም:: እሷም ወደ አውቶብሱ አላየችም:: ሲያያት ግን ፀሃይ ልቡ ውስጥ ስትበራ ታወቀው:: ጭለማው ሲረታ:: የተረገዘ ናፍቆቱ ሲወለድ::

ቆመች:: አያት:: በዐይኑ ጐረሳት:: መጥገብ አቃተው:: አንድ ነገር ልብ አለ:: *ቲሸርቱ*.... አንዲት የምታምር ሴት የማያምርባትን *ቲሸርት* ለብሳ::

ኤልሳ!

የለበሰችው *ቲሸርት* የእሱ ነበር:: እሷ ናት 'ስላንተ ሳስብ ሁልጊዜ ይህንን ልብስ ለብሰህ ነው የምትታየኝ' ያለችው:: ያዘወትራት ነበር:: አንድ ቀን አስወለቀችው:: ወሰደችበት:: 'ይህንን *ቲሸርት* ለብሼው ማደር እፈ፦ ገለሁ' ነበር ያለችው:: 'አንተን አንተን ይለኛል' ትለው ነበር:: አደረገችውም:

አሁንም፣ እሱን ለብሳ የምትኖር መሰለው:: 'እኔን ለብሳኝ የምትኖር ከሆነ አይበርዳትም፤ ፈጽሞ!' አለ::
ኤልሳ!

እወድሻለሁ!!!!!!

እወድሻለሁ!!!!!!!!!

እወድሻለሁ!!!!!!!!!!!!!!

እወድሻለሁ!!!!!!!!!!!!!!!!!!

እወድሻለሁ!!!!!!!!!!!!!!!!!!!!!!!!!!

እወድሻለሁ!!!!!!!!!!!!!!!!!!!!!!!!!!!!!!!!!!!!!!!

እወድሻለሁ!!!!!!!!!!!!!!!!!!!!!!!!!!!!!!!!!!!!!!!!!!!!!!!!!!!!!!!!!!!!!!!!!!!!!!!!!!!!

'ፍቅር ሆይ! እንዲህ እንዳስብ አድርገህ ስለሠራኸኝ አመሰግንሃለሁ!'

ዕንባው መጣ::

አጠገቡ የተቀመጠው ሰው፣ "ከትናንት በስቲያ አንተን የሚመስል ሰው አጠገቤ ተቀምጦ ነበር፤ የታላቅህ ታላቅ መሆን አለበት!" አለው፡፡

"እኔው ነኝ!" አለ አፍቃሪው፤ "እኔው ነኝ፤ የፍቅረኛዬን ዐይኖች አይቼ ነው፣ የጠፉና የባከኑ ዘመኖቼን፣ ትልቅ ሰው አስመስለውኝ የነበሩትን ዓመቶቼን ያስመለስኩት!" አለ፣ በፈገግታ፡፡

አውቶብሱ...አውቶብሱ እየተመለሰ ነው፡፡ እየተመለሰ፡፡ ነው! አፍቃሪ ልብን ተሸከሞ....

...

የእኛ ክፍል ልጆች እኔን ያዩኛል፡፡ ሳሰበው በነነዌ ዘመን ያለሁ መሰለኝ፡፡ ትምህርት ቤቱ ባህር መስሎ ታየኝ፡፡ ክፍላችን ደግሞ ማዕበል የሚያንገላታው መርከብ፡፡ ከተማሪዎቹ አንዱ ማዕበሉ የተነሳው በእኔ ሰበብ እንደሆነ ሊነግረኝ ተዘጋጅቷል፡፡ የአብዛኛው ተማሪ ዐይን እየከሰሰኝ ያለ ይመስለኛል፡፡ የፍቅርን ህግ የጣሰ፣ የአምላኩን መንፈስ ያስቀየመ አንድ ሰው እነሆ በእዚህ ክፍል አለ! እየተባባሉ እንደሆነ እገምታለሁ፡፡ ለአንዳንዶቹ እኔ እንደ ነብዩ ነኝ፡፡ ነብዩ ዮናስ፡፡ ያለፈውን ሴሚስተር እንደጨረስን ጸሎት ላይ ነበር የሰነበቱት፡፡ ዛሬ ክፍል ውስጥ መግባት ብጀምር፣ዕጣ ተጣጥለው፣ወደ ባህሩ ሊወረውሩኝ ተሸቀዳደሙ፡፡

አዎን፤ ወደባህር ሊወረውሩኝ ነው፤ ባህሩ ከመናወጽ ፀጥ እንዲል፡፡ ዓሣ ነባሪ እንደሚውጠኝ አውቃለሁ፣ ቢሆንም ሞትን አልፈራም፡፡

ከመጽሐፉ የተወሰደ





ዋጋው ሰባ ብር ብቻ

እታፎዘር አታሚዎች 011 849 53 81